http://ethioliberty.wordpress.com/

# ሸበጥ



ከብርሃን ዳኜ

Ethiopian Bookstore

Brought to you by

Ethiopian Bookstore

https://t.me/etbookstore

http://ethioliberty.wordpress.com/

# ሸበጥ
## እና
# ሌሎች አጫጭር ታሪኮች

ከብርሃን ዳኛ

ኩራዝ አሳታሚ ድርጅት
[illegible]

ኩራዝ አሳታሚ ድርጅት
KURAZ PUBLISHING AGNECY

ስልክ / Tel 11 27 19

ፖ.ሣ.ቁ / P.O.Box 30933

አዲስ አበባ
ኢትዮጵያ

Addis Ababa
Ethiopia

መብቱ በሕግ የተጠበቀ ነው
ALL RIGHTS RESERVED

የሽፋን ሥዕል ሉቃስ አሞሬ

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት ታተመ

http://ethioliberty.wordpress.com/

# ማውጫ

1. ራሄል . . . . . 5
2. አርትእት . . . . . . 32
3. ጠየቃ . . . . . . . . . 54
4. አትሌቷ . . . . . . . 80
5. አምሮት . . . . . . . . 116
6. ቀዜማ . . . . . . . . . . . 128
7. ሽባጥ . . . . . . . . 147
8. ወይኔ ልጆቼ ! . . . . . 157
9. ምኞት . . . . . . 180
10. ሽበጥ . . . . . 190
11. ፈጣን ! . . . 211

http://ethioliberty.wordpress.com/

# ራ ሄ ል

ሌቼንቶቶቹ «አራት ኪሎ—የካ» የሚል ታፔላ ለጥፈ ለች ። ቁርና ሐሩር ከዝናብ ጋር ተራ ገብተው የታፔላ ውን ቀለም ዳርና ዳር ቀርፈውታል ።

የቀበና ድልድይ ጠባብ ከመሆኑ ሌላ ረባዳ ነው ። ሌቼንቶቶቹ ከላይ ወደ ቁልቁለቱ እንደ ተወረወረች መልሳ ፊቷን ወደ የካ አዞረች ። ስትንደረደር ሞተሯ ጠፍቶ በዜሮ ብትወርድም ፣ አቀበቱን ስትወጣ በሥቃይ ነው - ሞተሩ ተነ ያለው ። ቤንዚን ለመቆጠብ ሞተር ማጥፋት ፣ እንጂት አበር እንጦጦ መውጣት እንደሆን አይታወቃትም ። ማጠፊያው በስተግራ እንደ ተጣበቀ ቁም ማግን ወደኋላ የሚከፈቱት በሮች ጥርቅም ተደር ገው ቢዘጉም ንጭ . . . ንጭ . . . ይላሉ ። የሚረገጠው ሆዷ አልፎ አልፎ ዐይን በሚያክሉ ሽንቁሮች አስፋልቱን ያሳያል ።

የሳምንቱን መጨረሻ አሳበው መኪኖች ይፈትሻ ሉ ። ገጽታቸው በደስታ የፈካ ሰዎችን ጭነው ሲከ

ሰው ፣ ያቺን በእቅም የደከሙች—ከርካሳ ሴቸንቶ ያስቱ ዋሉ አይመስለም ።

«እምም!…ምምም … ምን የሞተሯን ድምፅ ታወጣለች ።

በኋላው መቀመጫ ሁለት ወጣቶች አሳፍራለች ። ወጣቶቹ እንደ መንገደኛ ግራና ቀኙን እያስተዋሉም ። በውስጣዊ ሐሳብ መመሰጣቸው ያስታውቃል ። ዐይናቸው ቅዠዝ ባለ ሁኔታ በሬት መስታወቱ ተሻግሮ አፍጧል ።

ራሄል በዚያ ባልተወለወለ መስታወት እንኳ የሚመለከታትን መንገደኛ ታፈዛለች ። ዐይን የሚጐትት የውበት ማግኔት አላት ። ክብ ፊቷ ተመጥኖ እንደ የረር ብርቱካን ግመጡኝ ይላል ። የሕፃን ልጅ ጣት የሚያክል ሰው አፍንጫዋ ፣ በዚያ በቢ ዐይኖች ባይታጀብ ኖሮ ቁርጥ ጃፓኖችን ነበረች ። ዘወትር የምትከመከመው ድብን ያለው «ቢቢ» አፍሮ ከፊቷ ቀለም ጋር ተቃርኖ ልዩ ድምቀት ሰጥቷታል ።

ኑን ለጉን ሲንኳኳኩ ፣ ሰው እንዳይሰማቸው ያደሱ ይመስላሉ ።

«ራሄል !…ምንው ዝም አልሽ !» አለ ድንበሩ በለሆሳስ ። እንደም ምላጭ ያልነካው ጢሙ አቀምቆ ጓል ። ቀጭን ፊቱ እህል በልቶ የሚያድር አይመስለውም ። የልጅነት ላህዩን ጋርዶታል ።



http://ethioliberty.wordpress.com/

«ምን ልበል ብለህ ነው !… ፈራሁ ። የምሞት ፣ የምሞት ይመስለኛል … እንዲህ የሚያደርጉት ሴቶች ብዙውን ጊዜ ይሞቱ የለ!…እግዜር ምን ትለኝ ይሆን!» ፊቷ ስትወዉቅ ፣ የከተ ቀን መሪበሽ እንኳ ውበቷን መደበቅ አልቻለም ።

ድንበሩ እንደ ዓመታዊ ተዝካር ጠብ እርግፍ እያለ የሚዘጋጅበት ያ የጀኛ ክፍል መልቀቂያ ፈተና ካንዴም ሁለቴ ጉድ ባያደርገው ፣ ችግሮች እንዲህ ይከተሉት ነበር ! «መልሱ አልተሰጠም» ብሎ መለሰታል ። ሥራ አላገኘም — እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ—ለዓመም ጊዚያዊ ። በቤተሰብ ጫንቃ ላይ ማኖር ከቀን ቀን ሲቀጠቀጠው ከርሟል— በኑሮው ምንም ባይጐልበትም ።

ድንበሩ ጉብረአግዚ እንደ መፋቂያ የረዘመ ጣቶቹን እያንቋቋ ፣

«አይዞሽ ራሄል !…በራስሽ ላይ እንዲህ ያለ ክፋት አታስቢ ። ሴቶቹዋን ራሴ አናግራለቸዋለሁ ። 'ነትሉ ያወጣቸል' ብለናል ። 'ምንም ሳታመነታ ጭልጥ አርጋ ትጠጣው' ነው የሚሉት» ይላታል ።

«ገሬ ገባኝ !… መመጫ ቀለል ያጣች ወፍ አታውቅም !… የሆስፒታል መድኃኒት እንኳ ክፉኛ ያለ ፈሪቸል ። ድንበሩ ! ደም ከፈሰሰኛማ የምተርፍ አይመስለኝም … ወፍ»

«ሊሰው ነኝ አይደለ—ለዚህ ያበቃሁሽ!…በጣም!»

«ሕሉንግ ተወው ፣ ቢቃ እርሳው !... እንዴ የሆነ ነገር ! ዕድሉ ካወጣኝ ያወጣኝ ...»

ድንበሩ ክንዱን በትከሻዋ ላይ አሳለፈና ግጥም አርጎ አቀፋት ። በጣቶቹ ጸረሯን ዳበሰው ። ጡቶቿን ነካ ነካ ... ግን ፣ አሁንም በሹክሹክታ « እይዞሽ ! ... ብሬ ይለይለታል ። ማንም ሳይሰማ ይፈተሰካል ! » አላት ። አንገቷ ሥር መሽጉጥ ከጀለው ። ከነንት አበቦች ይነ ግል ከሚባለው መዓዛ የሚወዳደረውን የራሄልን ጠረን ባፍና ባፍንጫው ሳበው ። እሷም ድንገት ብርድ ውርር ያረጋት ይመስል—ጥብቅ አለችበት ።

ሾፌሩ ፣ ተሽሩርሮ ፋብ ያህል በቀረው የጀርባ ማሳያ መስታወት እየተመለከታቸው ጸጉሩን አሸት ... አከክ አደረገው ።

ድንበሩ 'እስቲ አሁን ምን ይወራል— ይቺ ልጅ ጉድ ብትሆን !... የሰው ልጅ እንዴት አድርጌ ምን እላለሁ ?' —በእግረ—ሕሊናው ወደ ኋላ ተመለሰ ...

ድንበሩ አሁን ጥብብ ጭንቅ የሚልላትን—ራሄል— የተዋወቃት ከሁለት ዓመት በፊት አራት ኪሎ አካባቢ በሚገኝ አንድ የጽሕፈት መሣሪያዎች መደብር ውስጥ ነበር ።

ራሄል ማስታወሻ ደብተር ለመግዛት በዋጋው መወ ደድ የተነሣ ከነጋዴው ስትከራከር ፣ ሳታስበው ከጎ ኗዋ ተከትሏት ለሷ በማድላት ድንበሩ ተከራከረላት ።



http://ethioliberty.wordpress.com/

ይህ ሁኔታ [illegible] መግቢት ። ወዲያው ሲተዋወቁ ...

... የሕሊናው ማኅደር ትውስታውን አላኪታትል ቢለው ፣ ምንጊዜም ወደማይጠፋበት እውሬ ትዝታ አመራ ።

ከሦስት ወር በፊት መሆኑ ነው ።

ድንበሩ ገብረእግዚ ባንድ የግል ድርጅት ጊዜያዊ ሥራ ከተቀናጠጠ ብዙም አላሳለፈም ነበር ። የስታትስቲክስ መረጃዎች ማዘጋጀት ነው—ሥራው ። ጠረጴዛ ላይ ተደፍቶ መዋል ባህር ለመደ ። ጥሎት ቢወጣ እንኳ እስኪነቃ የሚሆረው ዙሪት ወስል ብሎ ታየው ። ስለ ዚህ በሚያገኘው አነስተኛ አበል እየተጽናና አደፈጠ ።

የደመወዝ ይሁን አበል አዲስ ለማጀች ምን ይሁን ምን—የሚቀበሉት ብዙ ይመስላቸዋል ። ቢመዘዝ ግለ ቁን ጭራሽ ይጠራጠራሉ ።

በዚያች የወዙ እንጥፍጣፊ—ገንዘቡ—እያሉ ነገር ሊፈጽምባት ተመኘ—ድንበሩ ። ራሄልን ለማስደሰት ፣ በፍቅር የጉብበተ አክብሮቱን ለመግለጽ ፣ እሷን ማዝ ናናት ቅድሚያ ሰጠው ። የከሰዓት በኋላ ፈረቃ ሴርባ ስትወጣ ዳግማዊ ምኒልክ ትምህርት ቤት በር ጠብቆ ይቀበላታል ። ስለ ፲፩ኛ ክፍል ትምህርቷ ይጠይቃታል ። የሱን ዕድል መጥመም እየረገመ ፣ በርትታ እንድትማር ይመክራታል ።

http://ethioliberty.wordpress.com/

«ወየልኽ! ... መንገደኛ ሆንኽ ትቀሪና!» ይላታል። እያሰለሰ ሲያገኛት ተጨዋውተው፣ ተቀሳልደው ይለያያሉ። እሱ ወደ አትቡስ መቆሚያ ያመራል፤ ወደ የካ የሚወስደውን ለመያዝ። እሷ በብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት በኩል አልፋ ወደ ቤቷ ታዘግማለች።

ልብ ለልብ ተሰማሙ። በመተሳሰብ ተቀራረቡ።

ድንበሩ «ኪስ እንዳበጠ ይከርማል!» የሚለውን ሐሳብ በዚያ ለሁለተኛ ጊዜ ደመወዝ በወሰደ ሰሞን አልተዘነጋውም። እጠብቅሻለሁ ባላት የቀጠሮ ቀን ከትምህርት ቤቷ በራፍ አገኛት። እጅ ለእጅ ተያይዘው ወደ «ዳሽን ምግብ ቤት» አዘቀዘቁ።

ተማሪዎች ሲለቀቁ በሚንጎፍለው ትርምስ መካከል ብዙው ጉረምሳ ዐይኑን በራሄል ላይ ይወረውራል። ብቻዋን ወይም ከሴቶች ጋር ስትሆን—በቀጥታ የሚጐነትላት አታጣም።

«ቀይ ኸንክርት ... ጉርስ ኩኽ ኩኽ ማረግ ነበር» ይሏታል፣ አዘውትረው የማይጠቁና ባይን የሚያውቋት። ይህ ጋብ የሚለው ድንበሩ እጅቧት፣ ከትከሻው እጉን ብሶ እያናገራት አብረው ሲሔዱ ነው። ቢሆንም ከማኀይራቸው የተጐለጐሉ ዐይኖች ከፍ ዝቅ አርገው ያስተውሏቸዋል።

«ዳሽን ምግብ ቤት» ውስጥ ሳይገቡ ከበረንዳው ወንበሮች ላይ ሰረፍ ብለው፣ ሻይ ወተት አዘው ተቀመጡ።



«ሊሑድ ምን ትመራያለሽ» ብሎ ጠየቃት። እሑድ ቀን ከሰንት እንደ ነው—ቀጠሮ የሚይዙት። የራሄል ጓንጉል ቤተሰቦች «በዕረፍት ቀን እንገርኽ ይጠም፣ አይብግር» ብለው ይማኗታል። ድንበሩ በፊናው እንደትጋለጥበት አይፈልግም። ስለዚህ ራት ራት አርጉ ነው— የሊሑድ ቀጠሮ የሚሰጣት። እሷም እንዳይላቀቅ «እሺ» ብላ ሰበብ ትሰጣለች— ለቤተሰቧ— መውጫ።

«ምንም አልሠራ ... ምነው?» መልሳ ጠየቀችው።

«እይ እንዲያው አብረን ብንቆይ ብዬ ነው። ከቤት መውጣት ከቻልሽ?» ይላታል። የተቀበለው ደሞዝ ትዝ ብሎት የልቡ ምት እየፈጠነ! ጋብዞ ሲያስደስታት ታይቶት ምራቁ በአፉ እንደ መሙላት እያለ።

«እማዬ 'ዘመድ ጥየቃ ተከተይኝ' ትል ይሆናል፤ ብቻ ምክንያት ስተቼ እወጣለሁ» ብላ፣ ፍጥረት የሚያደንቀው ዐይኗን በሰለታም ፊቱ ላይ ወረወረችበት።

የፊት ገጽታዋን እሱም በዐይኑ ሲዳስሰው፣ በሰውነቱ ሙቀት ተቀጣጠለ። ፈገግታዋ ቤሕር ዳርቻ እንደ ወጣች የጠዋት ፀሐይ ተሰማው። ያጕጠጕጠት ጡቶቿ ሸሚዟን ወጥረውታልና ከድንበሩ እጅ ነገር ያላቸው ይመስል ጣቶቹ ሲንቀጠቀጡ፣ ንዝረት ወረረው።

ድንበሩ የጊዜያዊ ሥራውን ጉዳይ እንደሚቀ ትንሽ አሜውቷት፣ በዳሽን ምግብ ቤት ደረጃዎች ወርደው ተለያዩ።

እሑድ ፣ የራዲዮው የዘፈን ምርጫ ፕሮግራም ሲጀ ምር በአሥመራ መንገድ «የኔነሽ ሆቴል » ነበሩ ።

ደብዛዛ ያለ ብርሃን ባለው የመመገቢያ አዳራሽ ፣ ለመከለያ ከቆመው የተሰበጸ ሴጦ ጐን ካሉ ሁለት ዱካ ዎች ላይ ተቀመጡ ። እመሐል ፣ ከድንበሩ ይሁን ከራሄል ጉልበቶች ከፍ ያላለው አጭር ጠረጴዛ አንጋጦ «እንኳን ደህና መጣችሁ!» አላቸው ።

አዳራሹ ጥንታዊውን ኢትዮጵያዊ ቤት ለመምሰል በወለሉ …ዱካዎች ፣ ምንጣፎች… ተሠልፈዋል ። በግር ግዳው … ሲፈድ ፣ የመሶብ ክዳን ፣ ጭራ ፣ ቀንድ … ተሰቅ ለዋል ። አሳላፊዎቹ በሀገር ልብስ ተውበዋል ።

ድንበሩ ገብረእግዜ— በድንብ የተጠበሰ ክትፎ ለሷ ፣ ጥሬውን ለሱ ከቢራ ጋር አዘዘ ። ቀረበላቸው ። ክትፎ የሚየጅበው ሚጥሚጣ የድንበሩን አፍ በምሬት ሞላው ። እንጀራ ከእጃቸው እየተትረፈረፈ ቢያስቸግራቸውም መጉ ራረስ ጀመሩ ።

«መቼስ ክትፎ ያለ ቢራ ፣ ዶሮ ወጥ ያለ ጠላ ፣ ለቅሶ ያለ መሐረብ … ከሆነ ፣ ነገር ያጉድፋል» እያለ ራሄ ልን አሣቃት ።

«ይቺን መጨረስ አለብሽ!» አለ ድንበሩ፣ላመል ራሄል ፉት ካለችው ብርጭቆ ላይ አመልካች ጣቱን ቀስሮ ፣

«እኔ ቢራ አያሆንልኝም . . . አሁንም ላንተ ብዬ ነው ። ሳሙኤል ነው እንዳንዴ ጠጪ የሚለኝ ፣ … መጀመ



ሬያ የቀመስኩ ቀን [illegible]
አለች ራሄል— ግርምታ ፈገግ አልብሷት ።

እልፎ እልፎ እኔ ራሄል ቤት ድግስ ቢጤ ሲኖር ታላቅ ወንድሟ ሳሙኤል ፣ «ይልቅ ቀስ እያልሽ ልመጂው ፣ ለበዓላ እየተጋትሽ ዐይንሽን ብታቁለጨልጪ ፣ በእፍሽ ብታንፈንፊ ፣ ደስታ አይሠርፅብሽም» የሚላት ታውሳት ።

«ምን ምን አለሽ ታዲያ ?» ስለታም ፉቱ ለጨዋታ እንዳቀበቀበ ፣ የቀረውን ቢራ እንዶቀዶቀው ድንበሩ ።

«በልዩ ቅመም የተፈላ ፣ ግን ስኳር የሌለው የቀዝቃዛ ሻይ ጣዕም ይሰማኝ ነበር … ደግሞ ይጉመዝዘኛል ።»

« ሲጀመር የማይጉመዝዝ ምን አለ ?» ብሎ ጣቀ ። እሷም ፈገግ አለች ።

ቀጥሎም «ቢራ አፍቃሪዎች እንዳይሰሙሽ !» አላት ። ራሄል ጓንጉል በተጉነጨች ቁጥር የተፈላ ወተት የምታባርድ ትመስላለች ። የቀረበላቸው ገበታ ተንጣ ። እጃ ቸውን እየደረቁ ሳለ ፣

«የጥናቱን ነገር የት አደረሺው ?» ሲል ጠየቃት ።

«እንደሚሆን እየተፍጨረጨርኩ ነው ። ካሁን ፊር ቼዋለሁ ባይገርምህ… እየሰፈራም?»

«እሱማ ማስፈራቱ መች ይቀራል ?… ግን ካሁኑ ብታ ውቂበት ይሻላል።እስዚያ—ዐሥራ ሁለት ሲደመር ጭጭ— ሆንሽ ታርፊዋለሽ»

http://ethioliberty.wordpress.com/

«ቢሆንም 'ሰቀላር' ማፈላለግ ነው እንጂ ፤ ዝም አይባል ። እማዬ 'በርትተሽ ካጠናሽ የማደርገውን አታውቂም' ብላኛለች ። »

«ጥሩ ! በጣም ጥሩ … ታዲያ ለምን አትጠጪም !» ሲል ድንበሩ ፣ ቀስ እያለች ጠጣች— ራሄል ።

ስለ ጊዜያዊ ሥራውና የቢሮ ጣጣዎች ፣ ዲስፕሊን … በትንሹ ዘገበላት ። «በይ ድገሚ ከቢራው !» ብሎ ተጨማሪ ሲያዝ ፣ ራሄል ተቃወመች ።

«አይው ! ባንድ ተለክፈሽ ራስ ምታት ከሚይዝሽ ድገሚውና ይስተካከላል !»

«ተው ድንበሩዬ !. . . ይብቃኝ ፤ እየው ሳቡ እንኳ» ንግግሯን ሳትጨርስ !

«ታዲያ የትድሙ ሚጥሚጣ ነዋ! ቢራው ምንም አያደርግሽም»

«እኔ 'ንጃ !» ብላ ፣ ቅር እያላት ደገመች ። እሱም እንደ ዚያው ።

የድንበሩ ሰውነት ተጋጋለ ። ሽንት ቤት ደርሶ ሲመለስ ባዲስ መንፈስ ጨመረበት ። ቢራዎች … የፋብሪካ ጠላዎች … ስብታ … ሞቅታ … ንቃታት …

ድንበሩ ፣ 'አጥብቀው ከሚያፈቅሩት ጋር እንዳንዴ ያለገደብ መዝናናት ይናፍቃል ፣ … እንደ ልጅም እንዳዋቂም መጨዋወት' በሚል ሐሳብ ልቡን አደንድኖ ፣ ማመንታቱን ወደ ጕን አረገው ።



«መፈር እንዴት ነው?» አለ ።

«ጥሩ ነው … ብቻ ለካፌው በየ ። አንድ ጥቁር ወፍራም ልጅ ፣ ከሰዒድ ሱቅ የሚያጠፋው ፣ አይተኸዋል አይደል ?. . . እያስፈራራ የሚናገረውን ብትሰማ— ያናድዳል !» ብላ እንደ ተኰነነች ።

በሞቅቅ ተነቃቅተው እንደ አደባባይ አምፑል የሚያበሩት የድንበሩ ዐይኖች ራሄል ላይ አፈጠጡ ።

«ምን ለመሆን ነው ? … 'ሁሉም ነገር በግድ ነው የሚሆነው' ማለት ነው ? ምናይነቱ ደደብ ነው ። እሺ !… አቤት ነገርኛቸው ?»

«እሱማ … ለማዬ ነግሬአት ነበር ፤ 'እቆጣጠርሻለሁ' ብላለች ።»

የድንበሩ ትንፋሽ ብሽቀት እየጨሰች ፣ የተቀሰቀሰበትን ስብታ አጋመችው ። ከብርጭቆው እየጠጣ !

«ይገርምሻል ! … ምን ቢደረግ ሴቶች እንደ ፈሰት እንደሚሆኑ አላውቅም ። ትምህርት ቤት ለከፋ ፣ ቢሳቸው ድብደባ ፣ ሠፈር ለከፋ ፣ ጉንተላ … ደሞ ማስፈራራት ! . . . አንድ የሴቶች ደሴት ያስፈልጋል ፤ ሴቶች ለብቻቸው የሚኖሩበት— ለከፋ የሌለበት !»

«እሺ !… እኔስ ወደ ደሴቱ ብሔድብህ ?» ራሄል ካኰነበሰችበት ዐይኗን ንቅላ ወረወረችበት ። ድንበሩ ካይኖቿ በሚወጣው ጨረር ተመታ ። በከዋክብቶች መንደር እንደሚንሳፈፍ መንኮራኩር መጠቀ ። ትንሽ እፍን

ጫፍን ፣ እንጆሪ ከንፈሯን ፣ ትንቡክ ጉንጮቿን ፣ ና ወደኔ የሚል ግንባሯን . . . በጥቅታ መነጽር አበሰው ፣ ዳበሰው ።

«እንደሱማ የት ይሆናል ! ... ለምን ትሔጂብኛለሽ» ሲል ትዝዝ ብሎ ፣ ራሄል ልቧ ጢ. እስኪል ማቀች ።

ሲኮንድ ደቂቃን እየወለደ ደቂቃም እንዲሁ ሲከንፍ ራሄልን ደካከማት ። ከፊል ብኽታ አፈዘዛት ።

ድንበሩ ተጨማሪ ቢራ አዘዘ ። ሐሳብ የመሰጠው መሰለ ። 'ሌላ ክፍል ብቻችንን ብንሆንስ ? የመጀመሪያ ቢሆንም ክፋት የለውም' የሚል ሐሳብ አደረበት ። ሌላ ከማምቱ ያገባው ጉዳይ አልነበረም ።

«ራሄል ... ደክመሽ አይደል ? ነይ እንሒድ ። አንዱ ክፍል ውስጥ ዐረፍ እንበልን ። ትንሽ ቆይተን እንሔዳለን ። እንዲህ ሆንሽ ለሚመለከት ሰው በቁም የምታንቀላፊ ይመስለዋል ። »

«ለምን ? » ስትል ድንጋጤዋ የፈቷን ቅላት አነጣው ። ስሚቷ ተዘበራረቀባት ። ስለሚመጣው አልተነበየችም ።

ቆም እጇን ሲሰጣት ተደነጋግጃት ተከተለችው ። በጓሮው በር ወጡ ። ድንበሩ ማረፊያ ክፍል መከራየት እንደሚሻ ጠየቀ ። ያልደረቀ ያሽዋ ግርፍ ከሚታይበት ቀርታ ክፍሎች ወደ ሁለት ቁጥር ተመሩ ። ራሄል መሬት መሬት እያየች ስትከተለው ፣ እሱም እግሩን ብድግ ጣል እያደረገ ሲራመድ ፣ ሕፃናት እርስ በእ



http://ethioliberty.wordpress.com/

ርስ ፣ አንዱ ፈረስ ሌላው መሬ ሆነው የሚጫወቱትን ይመስላሉ ።

መስኮት የሌለውን ክፍል ከውስጥ ዘጋው ። ጭልም አለ ። በበሩ ራስጌና ግርጌ ወጋግን እየታገዘ መብራቱን አበራው— ድንበሩ ። ራሄል ግድግዳውን ከተደገፈ ብቸኛ ወንበር ላይ ዘፍ አለች ።

ድንበሩ እንደቆመ ፣

«ምነው ራሄል ... አልጋው አይኛልሽም ?...ፈራሽ?»

«አይ አልፈራሁም ...» አለች ፣ ዝግ ብላ ። እጆቹን ይዞ ፣ ከአንድ ሰው በተጨማሪ በማይበዛው አልጋ ላይ አስቀመጣት ። የራሄል ልብ ስንቀቅ ... ትርትር አለ ። ባዕድ ድንጋጤ ወረራት ።

ድንበሩ ከጉኗ ሆነና አቀፋት ። ትንቀጠቀጣለች ። ጉንጮቿን ፣ ከንፈሯን ሲስማት በሥረጸባት ድንጋጤ ስሚቱ ቀዝቅዞ በድን ሆነች ። ሌላው ቀርቶ ሲጊጣ ቢትም ቢሆን ጭምቅ አርጉ ሲስማት ፣ ስሚትዋ መቀበል ብቻ ላይ ሆን መስጠትም ይችል ነበር ።

« ራሄል ራስሽን አታስጨንቂው ... አለዚያ ራስ ምታቱ አይለቅሽም ፤ እንዲያውም ጋደም በይበት ። » ትርሮው ስለት ባሳ ምት ሲመህ ፣ የተቀበረጠ ድምፅ አወጣ ።

ጉልበቷን እጥሽቶ እጆቹን ከቢጫው «ባጊ» ስሬ ሥር ወሻሴት ጫማዎቿ ስዶ ፣ አወለቃቸው ። እግሮቿን እን

ደያዘ ቁርጭምጭሚቷን ፣ ባቷን እያበሰ አልጋው ላይ ሲዘረጋት ሕፃን ልጅ ለማስተኛት የሚያባብል ይመስላል።

ልቡ ድው ድው እያለ ይደልቃል፤ እጆቹ ይንቀጠቀጣሉ፤ እግሮቹ ይብረከረካሉ '… በል በል አትረፍ! … በል በል አትረፍ!' አለው የሆነ ውስጣዊ ሞገድ።

ራሄል ዐይኗን ጨፍናለች። ጥቁር … ቢጫ … ቀይ … ወይን ጠጅ … ነጭ … ቀለሞች ማቢያውን እንደ ላተ ቁሉጪኝን ብኘ አለባት። ልቧ ቱር ብሎ ይወጣ ይመስል ተንደፋደፈ። አየር ስትስብና ስትተነፍስ የም ታንኮራፋ ትመስላለች።

ድንበሩ ከጉኗ ተጋደመ። የጉንጮቹ ቀና ብሎ ግን ባኗን ፣ ትንፋሿን ፣ ከንፈሯን ሳም . . . ምጥጥ ሲያደርገው ቆየ። ባንደኛው እጁ ከሸሚዚ ሥር ያደረገችውን ሁናይትን ሸሚዝ ለመክፈት አዝራሮቹን ፈታቻቸው። ደረቷን ፣ ጠብቋን ወርዶ ሆዷን አሸት . . . ጫን አረገው። የደም ዝውውሩ በመፍጠን እያስገመገመ በሥራ አካላቱ እንደ ፈንዳ ቧንቧ ፏ አለ።

አሁንም ራሄል ዐይኗን እንደ ጨፈነች ነው። ድንበሩ እጁን ከደረቷ አወጣና በጭኗ መሐል ላከው። አሸት … አሸት ፣ ጫን . . . ጣቶቹ ኤሌክትሪክ የነኩ ይመስል ነዘሩቸው።

ቢጫውን «ባጊ» ሱሪ ለመፍታት ትግል ያዘ።

«ድንበሩ! … ድንበሩዬ ተው አይሆንም። ድንበሩ ስቀበር! በኋላ ለሁለታችንም አይሆንም! ተው! ይቅር



http://ethioliberty.wordpress.com/

ብን» አለች ራሄል ፣ [illegible]
ጥራ ለመንጣት እየታገለች።

ድንበሩ መድፍ ቢተኩስ እንኳ አይሰማም። ጆሮው ተደፍኗል — ስሜት ዘግቶታል። ዐይኑ ተሸብቦ ጭልም ብሎበታል። ጫማውን መንጭቆ ወረወረው። አልጋው ላይ ወጣ። ራሄል ጎንጉል እንደዚያ የሚከበድ ሰውነት ወጥቆ መተንፈስ እስኪያዳውት ያስጨነቃት አንድም ጊዜ አይታወላትም።

«ድንበሩዬ! … በናትህ! አይሆንም! እምቢኮ አይደለም — የምልህ! እምቢ አላልኩም። ግን መቆየት አለብን። እማዬ ገና ብዙ ትቆጣኛለች፣ መቆየት አለብን። የኔ ቆንጆ . . . በወለዱህ!» ተማጠነችው። በርበሬ የመሰለት ጉንጮቿ ረጠቡ። ከድንበሩ የሚወጣው ትንፋሽ፣ በወናፍ እንደሚገፋ የብረት ማቅለጫ እሳት ገረፋት።

ድንበሩ ራሱ ወደ ሥጋው ገብቷል። ምድራቱን ለቆ በእጆቹ ራቀ። ሰማዩ ሰማያት እየሰነጠቀ ከነፈ። አናቱብ በሚነካው አውሉ ንፋስ ለሞቅትና ተከሉች አሸበሸበ። «እልል!» አሉ። ውቅያኖስና ባሕር ተናወጠ። የምድር ሥረት ፈጠነ። ብር እምባር — ተሰበረ!

ያኛ ሲኞንቱ ለትዳሚው ገበያ ከወደ ኮተቤ ተጭኖ የመጣውን እህያ ቅልጥሙን ልትሰው ምንም አልቀራ ትም። ለትንሽ ሲጠጥ እርጋ እቆመች። ሽፈሩ ራሱን ወደ መሰኩቱ እዙር እህያ ነጂውን በስድብ አከናነበው።

የሴቸንቶዋ ሞተር ተግ እስኪል ድረስ መኪኖች ከኋላ ተሰለፈው ! «ኢ.ድ...ኢ.ድድ» እያሉ ሲጮሁ ፣ ድንበሩ ወደ ኋላው ተንኳመጠ ።

«አቤት ማንም አይኖር ፣ አይደል ? » አለች ራሄል በጅክጅክታ ፣ ኩሉል ባለውና የተሸፈነውን ዐይኗን ጣል አርጋ ።

«ማንም የለ ... ሠራተኞችን ብቻ ናት » ሲል እንተመተመ ። አባቱ ለመስክ ሥራ ወጥተዋል ። እናቱም ከነሱ ዘንድ አይኖሩም — ከባለቤታቸው ስለ ተለያዩ ። ወንድሞቹ ለትምህርት ውጭ ሀገር ሔደዋል ። ትልቋ እህታቸው አግብታለች ።

የሁሉም ምስል በሕሊናው እየተፈራረቀ ሲታሰበው የምርተ «አክተሮች» ፎቶግራፍ አንድ ፣ ሁለት እያለ የሚቆጥር ይመስላል ።

ሴቸንቶዋ ሾላ ገቢያ ሳትደርስ «እዚህ ይበቃል ! » ብሎ ድንበሩ ሐሳብ ሲከፍል ፣ በገበያው የሚተራመሰውን ሕዝብ ከርቀት ገላመጠው ።

ለራሄል እጇን ሰጣትና ወረደች ። ሌሎቹም መኪኖች ሴቸንቶዋን ተከትለው አለፉ ። የባቡር መንገዱን ገራና ቀኝ አይተው ወደ ላይ አቋረጡ ። በኩረኩንቹ ዘለቀው ወደ መንደሩ ገቡ ። በቆርቆሮ የታጠረ አንድ ግቢ በሩፍ ሲደርሱ ፣ ድንበሩ ለቁመቱ የማያስቸግረውን ደወል ከርር !... ከርርር ! አረገው ።



http://ethioliberty.wordpress.com/

በሩ ተከፍቶላቸው ገቡ ። የግቢው ግዳ ስፊ አይባልም ። ፊያት ፩፪፩፪ መኪና አጥሩን ተጠግታ ቆማለች ።

«ብርጭቆና ቀዝቃዛ ውሃ በጠርሙስ ይዘሽ ነይ !» አለ ድንበሩ ፣ ወደ ቤት ሠራተኛው እየጮኸ — ገና ሳይገን ከመግባቱ ። ራሄል ፎቴው ወንበር ላይ ዐረፍ አለች ። እሱም ወደ መኝታ ክፍሉ ተንደረደረ ።

ራሄል ፣ ዘመናዊ የቤት ዕቃዎች ያሳመሩትን ሳሎን በዐይኗ ስትማትር ትቆይና ፣ ወዲያው ድግሞ ጉዳይዋ ጠቅ ! ጠቅ ! ሲያደርጋት ሰብሰብ ትላለች ።

እንደ ተመለሰ ድንበሩ ፣ የያዘውን ትንሽ ብልቃጥ ከፍቶ ቀለሙ ይህ ነው — የማይባል ፈሳሽ በብርጭቆ ቀዳ ።

«ይህቺን ጭልጥ አርገሽ ትጠጪና ... ደጅ ትሮጪበታለሽ » አለ ።

« ለምን ?... ሩጫ ?» አለች — ራሄል እፍንጫዋን እንደ ማኮስ አርጋ ።

«ሴትየዋ ያሉት ነዋ !... 'ትንፋሽን ሳትቆርጥ ትጠጣና ትሩጥበት ' — ነው ያሉት ፤ እንቅስቃሴ ሲኖር ፅንሱ ይወጣል ።» አለ ጣቶቹን እያንቋቋ — ድንበሩ ።

«አይመርም ?» ፈራ ተባ ማለቷ ያስታውቅባታል ።

«ዶሮ ማታ ! ዶሮ ማታ እሌሻለሁ ... ስትጨርሺ ስኳር ትቅሚበታለሽ »— ወደ ጓዳ ሔደ ፣ ስኳር ሊያመጣ ።

ራሄል — ሰውነቷ ብርድ የነካው ይመስል እተር የሚያካክሉ ድቡልቡል ነገሮች ቆዳዋን ወረሯት ።

http://ethioliberty.wordpress.com/

ድንበሩ ሲመልስ « ፈረሱም ይኸው ፣ ሚዳውም ይኸው !» ብሎ ብርጭቆውን ሲያቀብላት ፣ እፍ እፏን ያስተውል ነበር ። ከንፈሯ ይንቀሳቀሳል ፣ የምትለው አይሰማም ።

ራሄል ገና ብርጭቆውን ስትይዘው ከረፋት ። ዐይኗን ጨፈነች ። ነጭ ፣ ነጭ … ትንፋሿ ቁርጥ ! … ነጭ ፣ ነጭ . . . ትንፋሿ ቁርጥ ! እያለች የለ ፣ አለቀ ።

«አሁን ዕረፍት ነው ። » እሱም አብሮ የጠጣ ይመስል ዐሥሬ ምራቁን ይውጣል ።

«ግን ከምንድነው የሠሩት ? » አለች ።

«ሴትየዋ ‘ብዙ ነገር አለው ሲሉ’ ነበር ። »

«ታዲያ አልተጠራጠርከም ?. . . ዕውነት ይሠራል ! እኔ የምተርፍ አይመስለኝም ! እማዬ ምን ትለኝ ይሆን ?»

«አይዞሽ ! ይሠራል ። በስንት ድካም መሰለሽ ይኸውም የተገኘው ። ከኛ ጋር የሚሠራ ልጅ ነው ‘ከሰዎች ሰማሁ’ ብሎ ወደ ሴትየዋ የመራኝ … ‘ፍቱን ነው’ ብለዋል ! አይዞሽ !» ብሎ ፣ ራሄል ከተቀመጠችበት ፎቴ በስተጀርባ ቆሞ «ቤቢ» አፍሮዋን በዝግታ ነካካው ። በቀጭን ጣቶቹ አንገቷን ፣ ደረቷን አሻሸው ። ዐይኗን ጨፍና አንገቷን ወደኋላ ለጠጠችው ። ድንበሩ አጕንብሶ ግንባሯን ሳመው ።

«ራሄል ! . . . አሁን ሩጫ ነው » አለ በሹክሹክታ። ወደ ደጅ ተያይዘው ወጡ ።



ወዲያው ዱብ ! ዱብ ! አለች — ራሄል ። የለበሰችው የ«ጂንስ» ቀሚስ እግሯን እንደ ፈለገችው እንድትዘረጋ አላመቻትም ።

«በርቺ ! … ታዲያ ፈጠን ፣ ፈጠን በይበት ። ቶሎ ቶሎ እንዲሠራ ፍጥነት ያስፈልገዋል ። » አለ ድንበሩ ። ሲያመነታ አብሮ ሩጫውን ተያያዘው ።

ራሄል ባንጉል ትንፋሿ እየተቆራረጠ « አሁ … አሁ … አፍፍ » እያለች አለከለከች ።

«በይ ! ማቆም የለም ! … ሩጪ ! » — አለ ድንበሩ ግብረአግዚ ፣ ከጐኗ እያስመሰመ ።

«ደከመኝ ድንበሩዬ ! … ደከመኝ ፣ ቆይ ትንሽ ልረፍ»

«የለም! . . . እንደምንም በኃይል ሩጪበት »

የሞት ሞቷን ሮጠች … ሮጠች …

ራሄል ፣ እግሯጂ ሲተሳሰሩባት ቀጥ ብላ በኃይል መተንፈስ ያዘች ።

«ሽንት ቤት አለ ? » በተዳከመ ድምፅ ።

ድንበሩ ደስ አለው ። ‘ሥራውን ሲሠራ እያደለ ?’ በሚል ሐሳብ «እዎ ! . . . ነይ ! »

እየደገፋት ወደ ሳሎን አመሩ ። የካ ኮረብታ አናት ላይ የመሸገው ጠቋሬ ደመና ፣ ዐሕይዋን ጋርዶ ያስገመግማል ። «ዱ ዱ ዱ … ! » እያለ ሲሮጥ ፣ ሰማያት ቁልቁል እየተመለከቱ የሚያቀበት መስሎት ድንበሩን ፣ እንጋጦ ገላመጣቸው። እየሩ ስለሚያይንቀሳቀስ እንደሚያይዘንብ ርግጠኛ ነበር።

http://ethioliberty.wordpress.com/

ከራሄል ጋር ሳሎኑን አልፈው «እዚህ ነው—ሽንት ቤቱ» አሳት ። ለመግባት ቢከጅልም ፣ የምንተፍረቱን ተመለሰ ። ራሄል ወደ ውስጥ ገብታ በሩን ስትዘጋ ልጥፍ ብሎ እያጓመጠ 'ወዲያ ጠራርጉ ባወጣው ! ' አለ በሐሳቡ ። ልቡ ክበር እየደለቀ ፣ መንፈሱ ተወጠረ ።

ከውስጥ ጸጥታ ነገሠ ። ጭጭ ! ... እረጭ ! ትንሽ የጨርቅ መተሻሸት ሰማ ። ስታወልቅ ወይም ስትለብስ መሆን አለበት ። የውስጥ ሱሪዋ ተለጣጭ ላስቲክ ጧ ! . . . ጧ ! ሲል ጆሮው ጥልቅ አለ ።

ተከታትሎ የሚኽጉዶጉዶው ውኃ ፏ አለ ።

'ከምኔው ወጣ ? እንዲህ ፈጥኖ ? . . .' እያለ ደንበሩ ሲያስብ ራሄል በሩን ከፍታ ስትወጣ ፊት ለፊት ተጋጠሙ ።

«እህስ ? ... ወጣ ?»

«ደከመኝ !... ሌጭ ምን ይወጣል ? ... ሽንት ብቻ »

ደንበሩ ፣ ለከረሜላ የገባ ሕፃን ልጅ እንቁልልጭ እያሉ ማሪያ ላይ ሲወረውሩበት ወሽመጡ ብጥስ እንደ ሚለው ሆነ ።

ፏ... ፏህ የሚለው የውሃው ድምፅ ስይማናዊ ማስ ካሴት መስሎ በሕሊናው አስተጋባ ...

«ደንበሩ !... ወደላይ ወደላይ ይለኛል ፤ ሊያስታው ከኝ ነው !... ደንበሩ ! ደረቴን ደባፈኝ ... »

* * *



ከሁለት ሳምንት በኋላ ነው ።

እዚያው እነ ደንበሩ ቤት ሁለቱም አንድ ላይ ነበሩ ። ደንበሩ የራሱ መንፈስ ከብድ እያለው አንዳች ነገር በሐሳቡ ቸጥ ይልበታል ። ነገሩን በውል ለይቶ አልጨበጠውም ።

እንዲያው የአባቱ ወደ መስክ ሥራ ከወጡ ብዙ ጊዜ ማለፍና 'ይመለሱ ይሆን ? ' — የሚለው አስተሳሰብ ሽውታ ነው ። ባንዳንድ አስቸኳይ ሥራዎች ሳቢያ የሚመለሱበት አይተነበይም ። ይህንንም ያውቃል ።

ወዲህ . . . የፅንስ ጊዜ መርዘም ፣ ያለፈው መድኃኒት አለመሥራት . . . ያሁኑስ ? . . . ጭራሽን ልጅቷን ቢያጠፋትስ ? . . . በሐሳብ መዋዠቁን ቀጠለ ።

እንደ ምንም ሐሳቡን ሰበሰበና ፤

« ራሄል ! ያሁኑ የመጨረሻ መሆን አለበት ... በደንብ ተጠንቅቀው የሠሩት ነው ። ገንዘብም ብዙ አስከፍለውኛል ። »

« አሁንማ የሚያስጨንቀኝ ጊዜው ነው ። እኔ እንጃልኝ ዘንድሮ ፣ በጤናዬ አልከርምም ! እማዬ ያለወትሮዋ ትከታተለኛለች ፣ ወይኔ ደንበሩዬ! . . . » ትለዋለች ራሄል ።

« አይዞሽ ! እንደ ምንም እንወጣዋለን ። እስከሁንም የቆየው ሲትዮዋ በደንብ እንዲያዘጋጁት ነው ። ከተ

ሊያዩ ነገሮች ተሞመው ፤ እዋሀደው ነው — የሰጡኝ ። የታወቁ ናቸው ... አትፍሪ ! ... ላያስተማምን አይቀርም 'ዝላይ ከተጨመረበት ይፋጠናል' — ብለዋል።

« ዝላይ ! ... እኔ አልገባኝም ... ራሱ መድኃኒቱ ከሥራ ለምን ሥርስር እያወጣውም? ... ባለፈው ጊዜ ነፍሴ ልትወጣ ነበር — እንደዚያ ስርጥ ... »

« እይውነ... 'ሰውነት ሲንቀሳቀስና ሲናጥ ስመውጣት ይፈጥናል' ብለው ነው — የሚያምኑት ። ታዲያ እንዳሉት ማድረግ እንጂ ... ሌላ? »

ቀጥሎ ድንበሩ ከሲርጥ ጠርሙስ ውስጥ « እዋቂዋ» ሌትዮ የቀመሙትን ፈሳሽ በብርጭቆ ገለበጠው ። ራሄል ጥቀርሻ መሰሉ በታየው ፊቷን አጠቀረች ።

« ዶር ማታ ፤ ዶር ማታ ! » እያለ ሰጣት ።

ተቀብላ ገና ሳትቀምሰው መረራት ። ድንበሩ « ጠጪው ፤ ግጥም! ... ጥጥት! » ይላታል ። ራሄል በመንገሽገሽ 'እህህ' እያለች ፊቷን ቅጭም አርጋ ሠረገበችው ። ወዲያው እንደ ማቅለሽለሽ ሲላት ሽንት ቤት ሄደች ።

ግንባሯን ጭምር በውሃ አብሳ ስትመለስ ፤

« በይ ትንሽ ቆጭ በይ ... ደጅ እንወጣለን ። » ይላታል ። እንዲያ መቸገሯ ፤ እሱን እምና ሁሉን ማድረግ እንጀቱን በላው ።



http://ethioliberty.wordpress.com/

ወደ ደጅ ሲወጡ ፤ « ራሄል ! የምትዘይበት ወንበር ላምጣልሽ ? » ብሏት ፤ ከሳሎን ውስጥ ረዘም ብሎ የታየውን ወንበር በጀርባው ተሸክሞ ተከተላት ።

« መጀመሪያ ርጥ ! ርጥ ! በይ » — አለ ድንበሩ። እያት ። አላስቻል ብሎት እሱም ተጨመረበት ። በራሄል ላይ ድካም ሲያንዣብብ !

« በይ አሁን ዝላይ ነው ... ወንበሩ አጠሪ ! ቆይ በርጩማ ልጨምርበት » ብሎ ፤ በሩጫ ደዞ ተመለሰ ። ወንበሩ ላይ ደረበና አመቻቸው ።

« በይ ልደግፍሽና ውጭ ፤ ከዚያ መዝለል ነው ። »

ራሄል የድንበሩን ትከሻ በእጆዋ ተደግፋ ወጣች ። እንደ ፌብ አለች ። ተያዩ ። ምንም የለም ።

« ድገሚ ! »

ቁና እየተነፈሰች ወጥታ ዝርግፍ ብትለው ፤ ግሩ እንሸራቷት ባፍጢሟ ተደፋች ። ጉልበቷ ተጋጋጠ ። ድንጋጤ ቢደብትም ፤ እግሯን ወለም አላት ። ደረቷ መሬቱ ላይ እንደ ተጣበቀ ባፏ አቧራውን ቃመችው ። አፍንጫዋ ደም ይረጫል ። ይሄኔ ትውከቱ ሲመጣራት ማጓራት ነበር የቀራት ።

ድንበሩ እንዲህ ዓይነት አደጋ ያገኛታል ብሎ በፍጹም አልገመተም ነበር ።

« ድንበሩዬ ! ... ወይኔ ! በቃ መሞቴ ነው ። ሆዴን አቃጠለኝ ፤ አቅለሸለሸኝ ፤ ድንበሩ መሞቴ ... አቃጠለኝ ! » ስለምልም ባለ ድምፅ ።

http://ethioliberty.wordpress.com/

ድንበሩ የደራረበውን ወንበርና በርጩማ ወርውሮ ደግፎ አነሳት ።

« ወደ ቤት ውሰደኝ ! . . . እማዬ ? . . . »

ወገቧን ጠበቅ አርጎ በመያዝ ፣ ደገፋት ። እሷም እጆቿን በትከሻው ላይ ዘና አርጋ ተደገፈችው ። እንዲህ ሆነው የግቢውን በር ወጡ ። የቤት ሠራተኞቹ ማድቤት ሆና ይሆን ሁሉ ትዕይንት አልተከታተለችም ።

አንድ መኪና በኮረኮንቹ ላይ እየዘለለ ከላከስ ያደርጋል ። ድንበሩ በድንጋጤ ደንዝዞ መኪናውን ልብ አላለውም ።

መኪናው በድንገት እነ ራሄል አካባቢ ሲደርስ ቆመ ። ዘለው የወረዱት አቶ ገብረእግዚ ናቸው ። ድንበሩ አባቱን ሲያይ ፣ ፆረበት ።

« ምንው ደህና አይደለሁም? » አሉት ።

« ደህና ። አንድ የሠፈራችን ልጅ እሟት ፣ ወደ ሆስፒታል ላደርሳት ነው ።» እንዲያው የመጣለትን ተናገረ ። ድንጋጤ ፣ ድካም ፣ ወበቅ . . . አንድም ሳይቀር በፍረውበታል ።

« የምን የሠፈር ልጅ ነው የምታወራው? »

« ምንው አባዬ ፣ እየነገርኩህ !— አታያትም ! . . . »

« ጉድ ነው ! የሚገርመኝ ሰሞኑን ጤና ያጣሁት . . . ይህንኑ ሲያሳየኝ ኖሯል ለካ ! . . . ምን አርገሃት ነበር ? » — ከመንገድ ሲገቡ ያልጠበቁት ችግር ሲጠመዝባቸው — ሐሳባቸው ተመሳቀለ ።



'የምን ጣጣ ነው ! የምን ፍርጃ ነው ! ' አሉ በልባቸው ። ቢያንስ ባለቤታቸው ቢኖሩ ልጁን « ሀይ» እንደሚሉት በመገመት — ለቅጽበት ።

ራሄል ራሷን ስታለች ። ባፏ የሚወጣውን መቆጣጠር አቅቷታል ። ልብሷ ተዝረከረኳል ። ዐይኗን ከድና በድንበሩ ድጋፍ ነው ያለችው ። መንገደኞች ቆም ይሉና በሐዘኔታ ስሜት አየት አርገው ያልፋሉ ።

የድንበሩ አባት « ተመለስ! » ብለው ያዘዙትን « ቶሎታ ላንድ ከፉዘር » ተገላምጠው — ተከዙ ።

« ይሻት ላዝማም ፣ ታክሲ ይኖራል! » ከማለቱ ድንበሩ ፤

« ቆይ መጣሁ! . . . ጠብቁኝ ! » ብለው የድንበሩ አባት በቶሎታ ያመሩት ወደ ቤት ነበር ። ፈጥነው ፊያት መኪናቸውን አስነሥተው በኮረኮንቹ ተመለሱ ። ድንበሩና ራሄል ሦስት እርምጃ ያህል አልተራመዱም ።

« በል አስገባት . . . ወዴት? » — አቶ ገብረእግዚ ከማለታቸው ፤

« ዳግማዊ ምኒልክ ሆስፒታል » አለ ካባቱ አፍ ነጥቆ— መኪናው ውስጥ ከራሄል ለጥቆ እየገባ— ድንበሩ ።

አባትየው መኪናዋን አስጋለቧት ። ያጋጣሚው ምሥጢር ባይገባቸውም ፣ በደመነፍስ የሚሰማቸው እንዳች ነገር በሕሊናቸው ውስጥ ጠጥሯል ።

★ ★ ★

በናይኑት ቀለም የተቀባው በር አናት ላይ « ልዩ የግ ሕፃን ክፍል » የሚል ጽሑፍ ይነበባል ።

የራሄል እናት ድምፅ አልባ እንባ ያነባሉ ። የነባ ዘለላዎቹን በመሐረብ ሲጠርጉና አፍንጫቸውን ሲናፈጡ ብቻ ድምፅ ያሰማሉ ።

ይኸው ከሁለት ሰዓት በላይ ጠብቀዋል — ራሄልን ለማየት ። በልባቸው ያልተማፀኑት ታቦት የለም ። እያንዳንዱ ደቂቃ ጭንቀታቸውን የሚያባብስ እንጂ ፣ የሚቀንስ አልሆነላቸውም ።

ዐሥራ ሁለት ተኩል ላይ የድንበሩን የስልክ መልዕክት ሲሰሙ ነው — ሆስፒታል ለመድረስ የተቅበዘበዙት ። የራሄልን ማሕፀን ክፍል መግባት ሲገነዘቡ ፣ አፋቸውን ደም ደም አላቸው ። መንፈሳቸው ተናጋ። ዘረባቸው። ሞት የሚያንዣብብ መሰላቸው ። ከሲኦል ሠራዊት ከበባ የማምለጥ ትንቅንቅ ተሰማቸው ። ሞትን በምን ተአምር እንደሚያባርሩት ውሉ ጠፋባቸው ። ሰው በተባለ ቁጥር መርዶ የሚያረዳቸው እርገው በመገመት — ተሸማቀቁ ።

ድንበሩ በድንጋጤ ደርቋል ። እጁን አጥፎ የበሩን ጽሑፍ ይመለከታል ። ጭው ያለ ሐሳብ ወስዶታል ። እንዳሚው ወንበር እያለ መቀመጥ አልታየውም ። አባቱ ቁጭ ብለዋል ። ካንገታቸው አቀርቅረው '...ምን ይደረግ ! ቤቱ እንደሁ ባዶ ነው !... ያቺ ሴት ብትኖር እንዲህ አል ቀረብም ነበር ...' እያሉ በሐሳብ ይቆጫሉ ።



http://ethioliberty.wordpress.com/

በሩ ተከፈተ ፤ ነርሷ ብቅ አለች ።

«ግቡ !.. » እንዳለች ፣ የራሄል እናት ድንበሩን ገፍተረውት ገቡ ። ተከትለው የድንበሩ አባት ገቡ ። ራሄል ነጭ አንሶላ ላይ ተኝታለች ። የሕክምና መሣሪያዎች ከበዋታል ።

«ራሄል !... ራሄል ! የኔዋ ራሄል አለሽ ? »

«አዎ !... አለሁ እማዬ !» — በለሆሳስ ።

«እንግዲህ ምንም አያስቡ ... በርግጥ ጠጥታው የነበረው ፈሳሽ ሆዷን አውኳታል ። ማሕፀኗንም እዩ ተን ጠራርገነው ነጻ ሆኗል ... ሰሞኑን ሆስፒታል ሰት ቆይ ሙሉ ጤናማ ትሆናለች ... ትረምሳው ! » በማለት ለራሄል እናት ማጽናኛ ተናገር ፣ ቀጥሎ የድንበሩን ትከሻ መታ መታ አርጎ የወጣው ፣ የቅዳሜው ተረኛ ዶክተር ነበር ።

http://ethioliberty.wordpress.com/

# እርትእት

ጠዋት ነው ። ወደ ቢሮዬ ስገባ ለምን እንደ ገረመኝ አላውቅም ... ምስቅልቅሉ የወጣ ትዕይንት ስለሚታየኝ ይሆን ?... እናንተስ ፣ ቢሯችሁ ተለዋውጦ አስገርሟችሁ ያውቃል ?

... የሥራ ጠረጴዛዬ በመጽሔቶች ፣ በወረቀቶች ፣ በመግገቢያ ቃላት ... ከምር ተሞልቷል — በነዶ እንደ ተሞላ አውድማ ። በስተግራ ወደ ጣሪያው የሚንጠራራው የመጻሕፍት መደርደሪያ ተተራምሷል ። የሲጋራ መተር ኮሻው በመድ ብቻ ነው ። የተረከሰኩቻው ሲጋራዎች ተዳፍኖ ያደረ እንጨት መስለዋል ።

የመሥሪያ ቤታችን ቢሮዎች የሚጸዱት በምሳ ሰዓት በመሆኑ ፣ ቢሮዬ አልጸዳም ። ሆኖም ትላንት በሙሉ ስሙ ሆኜ ያላየሁትን ዛሬ ዘው ስል ፣ መልጁ አየሁት ። ቢሮዬን ታዘብኩት ።

...አንዳንዴ ራስን መልሶ ማየት ማለፊያ ሳይሆን አይቀርም !... ታዲያ ስልኩ እየረበሸኝ ...

«ሃሎ !... አቤት ...»

«ፋፋሌል ነህ ?»

«አዎ !»

«ያለፈው ወር ዕትማችሁ ላይ ... ማስታወቂያችንን በደንብ አላወጣችሁትም ። ቅር አሰኝቶናል ... ቀለሞቹ



ደብልቅልቅ ብለዋል ፣ የሥዕል ጉዳይ ስለሆነ ምንም መስሁብንት አማንበት ... ካሚ መጠየቃችን አይቀርም!»

«ከየት ነው ?... ማን ልበል ?»

«ከአርት ጋለሪ ነው ።»

«አ! ከጥበብ አለቆች ነው፣ መቼስ የአርቲስት ዐይን የቀና አይደለችም ... ለማድነቅም ሆነ ትንግት መፃፍ ለመን ቀስ አትመለስም !»

«ዝም እንል ነገር ቸገረን ! ዋሩ ካልወጣልን ብዙ ደምበኞች ማፍራት አንችልም ። ይህን መገመት አያዳግት ሆም ! »

«ይገባኛል! ዕውነት ነው ! ችግሩ የማተሚያ ቤት ሆኖ ብን ነው ... ቆይ እስቲ ... ይኸው እንዲያውም መጽሔቱ ፊት ለፊቴ አለ ... ገጽ ፃ፯ ላይ ይታየኛል ... ብዙም አያስታውቅም ... ግለቱ ... ይቅርታ ለማናቸውም — በሰው መፃ እንዳልዘባርቅ ... ይሁንና አስተያየታችሁን እቀበላለሁ ! አመሰግናለሁ ። »

«ቢሆንም አስቡበት... መጽሔታችሁ በሁሉም ረገድ ድንቅና ተነባቢ ነው ። በዚህ ብቻ አትኩራሩ ። በወዳጅ ነታችሁ ዘንድ ትንመቱና ደግ አይሆንም »

« እሺ ! አመሰግናለሁ ... ሁኔታውን ለ 'ኑሯችን' ቦርድ አቀርባለሁ»

ስልኩን ዘጋሁት ። ወ... 'ደ ታ... ድ ! ትንሽ የቀለም ነጥብ ከመስመሩ ብትወጣ ወቀሳው ይጉርፋል ! ሠማሊያን

http://ethioliberty.wordpress.com/

ድርሰውን በሚታቸው ስለ ነው ። ዐይናቸውማ ምን ይጠየቃል ?… ግን ዕውነታቸውን ነው፡፡ደህና አርገው ካላስተዋወቁ ሥዕልም ሆነ ቅርፃ ቅርፅ ማን ይገዛቸዋል ?

... አሁንስ ሲጋራዬን ጨርሻለሁ መሰለኝ ...በጠዋት ማጢጋት ... እሁሁሁ ... እሁሁሁ ...

እሺ ! ትላንት የት ነበር ያቆምኩት ?... እ .. ... እየየሞገዱ' መጣጥፍ ላይ ነው ። እሱ ደሞ ጥሎበት የብዕር ስም ይወዳል . . . እስቲ ጽሑፉን ቢያስተይበው ምን አለበት ?. . . ስንት ገጽ ነው . . . ሁለት ሦስት አራት ... ጥሩ... እም ... «እጭር መግቢያ» ይላል . . . እ . . . እም . . . አሁን እሁንማ 'ሞገዱ' ሲቃኛት ደንታቢስ ሆነ ። አይመርጥም ፣ አያማርጥም ። ደንቅር ፣ ደንቅር ፣ ንባብ ያውካል . . . የዛሬ አንባቢ እንደሁ ተሰውቢል ። ተመጥኖ የተከሸነ ፣ በተመረጠ ቃላት የታነፀ ጽሑፍ ነው የሚፈልገው—የዘመን አንባቢ ።

እኔን የሚያስቀኝ 'ሞገዱ' ከሒያ ዓመታት በፊት የተሸለመውን የሥነ ጽሑፍ ሽልማት ዐሥሬ እየጠቀሰ «. . .ያኔ ድር ፣ አለመንተሬ ብትሆን ነው ። ያኔ ነው ደንቅ የተባለውን ድርሰት የደረስኩት ፣ ምኑን እነግርሃለሁ—ታውቀዋለህ ። ማሸነፊንም አትርሳው . . . ታዲያ አሁን የምሰጥሀን ጽሑፍ ሳዘጋጅ ስንቱን ዐውደ ጥበብ መሰለህ ያገላበጥኩት—የትየለሌ ነው ። በየ'ላይብረሪው' ስዞር እግሬ ነቃ !. . » ይለኛል ።

ምን ልመልስለት ? «እሺ» ከማለት ሌላ እማራጭ የለኝም ። በግድ ወትውቶ 'አንተ በለኝ' ያለኝን አባት



ጺሒፈ ማስቀየም ይቻላል ? . . . እያልኩ ይሉኝታ ገባኝ ። የ'ሞገዱ' ሽፋንም ፣ መከራከሪያውም ያው የተንት ሥራው ነው . . . ከወቅቱ ጋር ካልተራመደ ምኑን ደራሲ ተባለ ?

የብዙዎቹ ጽሑፍ አቅራቢዎች ጉጉት ላቅ ያለ ነው ። ከሚያገኙት የድርሰት አበል ባሻገር ፣ ደንቅ ሥራዎች ካቀረቡ—ተመርጠው ወደ እንግሊዝኛና ፈረንሳይኛ ተተርጉም ፣ በመጽሔታችን ይወጣል ። ስለውጭ ገበያም ይቀርባል ። በዚህ መታወቅን ሁሉም ይፈልጋሉ ።

መጽሔታችን በውጭ ጥምር ተፈላጊነት ማግኘቱ ግድ ነው ።

. . . እሺ ! ስልኩ እንቦ የቢሮ—ለቢሮ መገናኛው (ኢንተርኮም) በርጋታ ለማሰብ ጊዜ አይሰጥም . . . ውጥረት ብቻ !

«ሩፋኤል !»

«አቤት ። »

«ብቅ በል እስቲ ፣ ደህና አደርክ !»

«ደህና ! እሺ . . .»

የአለቃ ጥሪ—የማለጋፋው ነው . . . እዚያና እዚህ በመጣከን ጊዜው ካለቀ ፣ የመጽሔቱ አርትኦት (ኤዲቲንግ) ሥራ መቼ ይሠራ ይሆን ?

አለቃዬ ቢሮ ደረስኩ ።

« ሃይ ! » አልኳት—የአለቃዬን ጺሐፊ ።

«ግድ ሩፍ !»

«ደህና ነኝ !»

«እለሁልህ ! ደህና ነህ ወይ ?»

«ደህና»

«ጠጅህ ከሲጋራ ቃጠሎ አምልጧልና ! ምናለ ሲጋራውን እርግፍ አርገህ ብትተወው ! ‘ሲጋራ ማጨስ ያጨሳል !’ እያልክ ግን ትጽፋለህ »

«እንቺ ደግሞ ከኔ ጤና ምን አለሽ ? . . . ዘለሽ ጤናዬ ላይ መጠምጠም ነው የሚቀናሽ ! ስለሲጋራም መተቸት ጀመርሽ ! እም . . . አሊቃሽ ፈልገውኝ »

«ምን ጥርጥር አለው ። ሰው ዐይኑን ካልፈለገ ማንን ይፈልጋል ! . . . ግን ፥ የምልህ መቼ ነው ጤናህን የም ትሳጨው ?»

«እንቺ ጽጉሯ ወርዶ ! ወርዶ ! . . . ስትሆኚ ነዋ !» አለኳት ። ከርዳዳው ጸጉሯ ከእፍሮ ሌላ እንደማይሆን ዐውቃለሁ ። በሽቀች ።

«እንዴ ! ይጠብቁህ የለ ! እግርህን ይዤአለሁ— አትገባም !!» አለች ከንፈሯን ጥፋ ።

እንኳኩቼ ገባሁ ።

«ሩፋኤል ! ግባ ። ብዙም አላቆይህም ። ለባሬ የሚ ደርስ ጽሑፍ እንድታዘጋጅልኝ ነው የፈለኩህ ። እያስ ቸገርሁም—አንድ ገጽ ነው ። ሆኖም የተጨመቀ ፍሬ ነገር ያስፈልገዋል» በማለት አሊቃዬ ፥ ከተቀረቀሩበት



http://ethioliberty.wordpress.com/

ቀና ብለው የወፈረ ሰውነታቸውን በደርባቸው በኩል ጣሉት ፥ ግሽከርካሪው ወንበር ላይ ።

ደህ ! ጸጉራቸውን በቀኝ እጃቸው እያሻሹ ፥

«ቁጭ በል !» አሉኝ ።

«የለም ፥ ግዴለም ! . . . ርዕሱ» ብዬ ከደረት ኪሴ የማይለየኝን ማስታወሻ ደብተር ከእርሳስ ጋር አወጣሁ።

«ልነግርህ እይደል ! የኢትዮጵያ ሥነ ጽሑፍ በጃኔ ኛው ምዕተ ዓመት የሚል ነው ። ለምሥራቅ አፍሪካ የሥነ ጽሑፍ ሊከስተርቶች ነው— የሚቀርበው . . . ነገ ወደ አሩሻ እበራለሁ . . . አንድ ገጽ ብቻ . . .»

«ባንድ ቀን ? ለዛውም ለክፍለ— አህጉር ሊከስተር ቶች የሚቀርብ ? . . . የትና እንዴት ? ብዬ ። ጥሬት የሚኖረው አይመስለኝም ። በሌላ በኩል የዚህን ወር ዕትም ረቂቅ አጠናቅቄ ፥ ማተሚያ ቤት ማድረስ አለ ብኝ ! ገና ጽሑፎችና ዘገባዎች እጠብቃለሁ . . . የመጽ ሔቱን የጎትመት ጥራት ደግሞ ደምበኞቻችን ቅር እያ ሰኙ ነው . . . ቀድመው ቢነግሩኝ ኖሮ »

«ሩፋኤል ! ለነገሩማ ልክ ነህ ፥ መልዕክቱ ለእኔም የደረሰኝ ከትናንት ወዲያ በመሆኑ ነው ። መንኛ ሐሳብ የሚያስጨብጥ ጽሑፍ ነውና እያዳግትህም . . . እስከ ማታም ቢሆን እድርሰው ። የውጭ ቋንቋ ተርጓሚዎች ቀድተው እንዲሠሩት ይደረጋል !»

በቆምኩበት ለደቂቃዎች አቀረቀርኩ ።

«እሺ ። እስቲ እያለሁ»—በለሆሳስ ።

http://ethioliberty.wordpress.com/

«በል ጀምረው . . . አንድ ገጽ »

በሩን ዘግቼ ስወጣ ፣ ጸሐፊዋ ስልክ ይዛ ነበር ። የተሰጠኝ ትዕዛዝ የማይታይ ሸክም ነውና አጉንብጄ ወደ ቢሮዬ ተመለስኩ ።

ያለኝ ጊዜ ውሱን ነው ። የያዝኩትን እርግፍ አርጌ አዲሱን ትዕዛዝ ስለ መፈጸም ማሰላሰል ጀመርኩ ። ለጽሑፉ ምንጭና መረጃ ያስፈልገኛል ። በስተግራዬ ያለው መጽሐፍ መደርደሪያ ስለዚህ ጉዳይ የሚያስፈልጉትን መጻሕፍት አልያዘም ።

ስልክ መታሁ ።

«ሃሎ ! . . . ሃሎ ! . . . ኦፐሬተር ! እባክሽን ማስታወሻ ያዢ . . . ወመዘክር ፣ ኬኔዲ ቤተመጻሕፍት ፣ ብሪቲሽ ካውንስል . . . ሌላ ማን አለ ? በየተራ ደውለሽ አገናኚኝ . . . የኛ ቤተ መጻሕፍት ኃላፊ . . . ማንች . . . ወይዘሮ ደስታን ጥሪልኝ . . . »

«እሺ . . . » አለች ። ቅር እንዳላት ያስታውቃል ። እኔም ፈልጌ አይደለም ፣ ጸሐፊዬ ፈቃድ ባትወጣ አላስቸግራትም ነበር ።

አንድ ወዳጄ ስለ አለቆች ብልጠት ያጫወተኝ ትውስ አለኝ ። አለቆች ምን ያደርጋሉ ? . . . ቀድመው ፣ የሚያሠሯቸውን ሠራተኞች በደንብ ያጠናሉ ። ንቁና ብሩህ የሆነውን ይለያሉ ። ከዚያ የደመወዝ ጭማሪ ያደርጉለታል ። ቆይ ! ከዚያ እያዘዙ ሲያሠሩት ፣ ሲያጣድ



ፉት ይኖራሉ አለኝ ። በኔም ላይ ይኸው 'ቲዎሪ' ሲሠራ ይሆን ? መቼ ነው የደመወዝ ጭማሪ የሰጡኝ? . . . አምስት ወር ሞላው ?

ይህን ሳውጠነጥን ነው ፣ በር የተንኳኳው ።

« እቤት . . . ይግቡ ! »

ቀይ ወጣት ነገር ፣ ሲፈራ ሲቸር ገባ !

«ምን ልርዳህ?» ጠየቅኩት ። ሳወጣ ሳወርድ የቆየሁትን ወደ ጐን አርጌ ፣ ልጁ ላይ አፈጠጥኩ ። ታዲያ የሥነ—ጽሑፍ ሙያተኛ ትኩረቱን ካንዱ ወደ ሌላው እየቀያየረ መንፈሱን ካላደሰ ፣ ሌላ ምን ከሐሳብ ጭንቀት ማምለጫ ዘዴ አለው?

« አጭር ልቦለድ ጽፌ አምጥቻለሁ ! » የልጁ አፍ ጠባብና ግንባሩ ሰፊ ነው ።

«እና ? . . . »

«አይታችሁ እንድታትሙልኝ ነው . . . ከፍያውም » የቆዳው ልስላሴ የሴቶችን ይመስላል ።

« ገባኝ ! . . . ገባኝ ! የምትለው . . . ለመሆን አጭር ልቦለድ ምንድነው ? »

«ለኔ እንደሚገባኝ ከሆነ . . . አጭር ልቦለድ ለመንፈስ ብርታት ፣ መዝናናት በሚወሰድ እንክብል የሚመስል ነው . . . አስፕሪን ፣ ቫይናክ ብቻ አይደሉም ለራስ ምታት የሚሆኑት ። መንፈስ ሲወጠር ፣ ድካም ሲያጠቃ ፣ ሐሳብ ሲበተን . . . አጭር ልቦለድ ፍቱን መድኃኒት ነው » ፊቱን ይደባብሳል ።

http://ethioliberty.wordpress.com/

«እም ! ... ከየት አገኘኸው ? ጥቅስ ነው ወይስ ... ?»

«የለም ከራሴ ገጠመኝ ያወጣሁት ነው ። ራስ ምታት ይሁን ሌላ የመንፈስ ውጣ ውረድ ሲይዘኝ ፣ ፈውስ የማገኘው ወይ የጻፍኩትን ሳነብ አለያም የተጻፈውን ስይዘው ነው ። »

«ብዙ የሠራኸው አለ ማለት ነው ?»

«ብዙም አይባልም ... ይሀ ግን የተሻለ ስለ መሰለኝ ለናንተ ማቅረቤ ነው ። መጽሐፋችሁን 'ንድፎችን' አገር ሁሉ ያደንቀዋል »

«እሺ ። በል አድራሻህን እዚሀ ቅጽ ላይ ሞላና ሒድ! ጽሑፉን ስጠኝ ! ... »

እም !... የዋዛ አይደለም። በኛ ዘንድ ወጣቶች እንዲሀ ደፍረው አይመጡም ። እስቲ ይታያል ! ምን እንደሚል ።

መሽቷል ።

ከግቢያችን ውስጥ መኪናዬን አቆምኳት ። ስወጣ የመኪናዬን በር በጣም ወረወርኩት ። 'እውንስ እርፍ ልበል እንጂ—ያለታዬን ትዕዛዝ ከፈጸምኩ ፣ ሌላው በተራው ይደርሳል !'— አልኩ ለራሴ ።

ባረማመዴ መንገዳገድ ነው የቀረኝ ። ሳምሶናይት ቦርሳዬን ይዤ ወደ በረንዳው የሚያወጣውን ደረጃ ስቆጥር ፣ የመወላለት ያህል ተሰማኝ . . . . ልብ የሚያጠፋ ድካም አድቅቆኛል ።



የሳሎኑን በር ከፍቼ ገባሁ ። እናቴ እንደ ወትሮዋ ሶፋዋ ላይ ፣ ምቾት እንዲሰጣት ጨርቅና የበቅሎ ግላስ የመሰለ ትራስ ጉዝጉዛ ፣ ተቀምጣለች ።

«ምነው አልመሸም ዛሬስ ? » አለች ፣ ዐይን ዐይኔን እያየች ። እርጅና ተጫጭኗታል ። እኔን እንደ ልጅነቴ የምትመለከተኝ ይመስለኛል ... ልጅ ያው ልጅ ነው— የሚሉት ዓይነት ።

« እንዷን አስገብተሀ ትዳር ብትይዝ እንዲሀ እንደ ልብህ ማምሸት የምትችል አይመስለህ ። ሚስቱ ፣ ልጆቹ እያልክ በጊዜ ትሰበሰብ ነበር ።»

የሳሎኑን ወፍራም ምንጣፍ ተረማምጄ ከሶፋው ላይ ተቀመጥኩ ። ሰዓቴን ስመለከታት ለአራት ዐሥር ጉዳይ ትላለች ። ' እፍ ! . . . ' ብዬ ፣ ፊቴን በጆቼ ደባበስኩና በጀርባዬ ተንጋለልኩ ።

« ወይ ልጄ ! ... ይሀ ብቸኝነት አክንፎ ጉድ እን ዳያረግህ ። በጊዜሀ ዕወቅበት ። እህቶችህን አታይም ! ... ቤት እሠራለሁ ፣ ዕቃ እደራጃለሁ ስትል ፣ ጊዜ ቀድሞሀ እየበረረ ነው . . . በጥሩንባ የሚታጀበው ሠርገኛ ሁሉ ቤት ሠርቶ የሚገባ መሰለሀ ? እናቱ ወይም አባቱ ላይ ተጻብሎ ነው!»

እናቴ በቀላሉ እንደማትለቀኝ ዐውቃለሁ ። ሰወ ትርው የኔን ትዳር መመሥረት እንሥተን ፣ አብዝተን እንነጋገርም ። ለርዕሱ መንገድ ካገኘች ግን እትመለ

http://ethioliberty.wordpress.com/

ስም … ስለዚህ የምትለውን በጥሞና ማዳመጥ እመርጣለሁ ።

«በትድሚያ መዘጋጀት አስፈላጊ መሆኑን እንኳ ታውቂዋለሽ … ደግሞ እያስቸኩልም ማለቴ ነው ።» ብዬ ከመናገሬ ቀለበችኝ፤

«እንዲህ ነው ! … ጸጉርህ እንኳ ሁለት ቀለም አውጥቷል ። ታዲያ ከዚህ በላይ ምን ትጠብቃለህ ?»

« እምልሽ፣ ዓመት ወይም ሁለት ዓመት …»

«እም! ይህንኑ ስትደጋግም ትኖራለህ፣ እኔም የማያልቅ ዓመት እቆጥራለሁ ። ሰውነትህን ታዘበው እንጂ ። ቢር … ቢር ስትል ራስህን ጥለህ ወረፍክ ! ሱሪህ እንዴት እንደ ሰፋብህ አይታወቅህም ! … 'ጉድ !' የሚያሰኝ ነው ። እሁንማ፣ ጺምህ ፊትህን ሲሸፍነው የሕፃን ማስፈራሪያ ሳትመስል አትቀርም!» ብላኝ፣ መሐረቧን አውጥታ «እሁ ! … እሁ !» እያለች፣ ሳለች ።

በርግጥ በዕድሜዬ መሳሳ ሁለተኛውን ይዤአለሁ ። ለምን ሽበት በዝቶ እንደ ወረረኝ አልገባኝም ። '… በዕድሜስ ምን ቁም ነገር ሠራሁበት !'— ጥያቄው ለራሴ ነው … ብናገር ሦስት ልበለዶቼ ናቸው ። ሌላው ትርኪ ምርኪ፣ እፍ የሚዋል አይደለም ።

« ስማኝ 'ጊዜ ሲያመልጥ— ጸጉር ሲመለጥ አይታወቅም' … ተው ! ግዴለህም !»



« እሺ » ስል መለስኩኝ ።

« ስልክ ተደውሎልህ ነበር፣»

« ከየት ?»

« ከውጭ ነው ። »

«ካዲሲባ ውጭ ?»

« አዎ !»

« መልዕክት የለም ?»

« መልሰው ይደውላሉ፤ እንደሉ ነበር ያሉት» አለችኝ ።

የጠየቁቱ ልጅ፣ «ጽሑፉን በመጽሔታችሁ አትሙልኝ…» ያለው፣ እንዲያው ነገረ ሁኔታው ሲከንክነኝ ወጋል ። የጻፈውን ለማንበብ ፋታም አላገኘሁ ። እሁንስ ባየው? …

«ስልኩ እየተጣራ ነው » አለችኝ እናቴ ። የስልኩ ድምፅ ስለሚቀንስ « ከርርር! … ከርር!» ይላል— እንደ መዚቃ ።

ተንደርድሬ እጀታውን እነሣሁት ።

'እሸሸሸ …ሸሸ …' በሚል ድምፅ መሐል «ሃሎ ! ሃሎ !» እልኩኝ ።

«እቶ ሩፋኤል ! … የፈጀም ርቀት ጥሪ ነው— ከጋምቤላ! » አለችኝ እጥፊታዬ ። '… ደግሞ እዚያ የማከነው ሪፖርተር ማንው ?'— በሐሳቤ ሳወጣ ሳወርድ መስመሩ ተገናኘ ።

http://ethioliberty.wordpress.com/

«ያሎ!… ሩፍ!… ሩፍ! ታዲያስ !» ከወዲያኛው ጫፍ ሰማሁ ።

«አቤት!… አቤት ፣ ማን ልበል ?» መለስኩኝ ሞቅ ብዬ ።

«ገረመው ነኝ ፣ ከጋምቤላ … እንደምን አለህ ?»

«አ ገረመው! እዚያ ነህ ለካ? ታዲያስ!… መቶቱ እንዴት ይዟችኋል ?» … እንዴ በተመሳሳይ ሥራ ሔጄ በመቶቱ ምክንያት የመጀመሪያውን ሌሊት መተኛት ያቃተኝ ታወሰኝ ።

« ይኸው ተያይዘነዋል … መቶቱ አይነገርም ። ዘገባውን ግን በተአምር ለዚህ ወር ዕትም ለማድረስ ተደፍተንበታል ። »

«ጥሩ! ጥሩ ነው … አሁን ምን ልርዳህ ? »

«ሩፍ!… የልማት እንቅስቃሴውን በከተማው ተዟዙረን አይተን ጨርሰናል ። ያነጋገርነውን ፎቶግራፎች ብታይ ድንቅ ናቸው ። አሁን ወደ ገጠሩ ስለምን ወጣ ባለቀለም የፎቶግራፍ ፊልም ያስፈልገናል ። ስፊልም ከምኝት ደግሞ የቪዲዮ ፊልም ማግኘት አለብን ። አራዊት በያይነቱ ይገኛሉ— ብለውናል ! በተጨማሪ ያገሬውን ኑሮ እንቀርፃለን … ይታይሃል አይደል ?»

«እም!… ገባኝ ፣ ታዲያ እኔ ምን ላድርግ ? ንብረቶችን ጠዋት ብታናግራቸው አይሻልም ?»



«ሩፍ … እያወቅከው ? ሳምንት ይተኙበታል ፣ ይሉት ነገሩን እንተው ብታስጨርስልን ?… ቢቻል በአውሮፕላን ብታስልከው— የልባችን በደረሰ !»

«እንዴ! ነገ ?… ነገ በየትኛው ጊዜዬ ነው ይህን ሁሉ ተአምር የምሠራው ገረመው ?»

«ሩፍ እንደ ምንም ብለህ አድርገው ። ምን አለ በለኝ ፣ በዚህ ወር ጋምቤላን በዘገባና በፎቶግራፍ እንሸፍናታለን ። … ጄይ ሩፍ! ደግሞ ያንተ መጽሐፍ ጉዳይ ። መጨረሻ ያሳተምከው 'ኖቬል'— 'ጉንትሽ' እን ባቢውን አተራምዷል ። ቢቻልህ ተጨማሪ ቅጂዎችን ላክ!… የያዝኩትን ሦስቱንም ወሰዱብኝ ፣ ይገርምሃል !»

«እሺ … እሞክራለሁ ።»

ስልኩን ዘግቼ ወደ ነበርኩበት ተመልሼ ተቀመጥኩ ።

«ነገ ወዴት ሔድ ነው— የሚሉህ ?… ምን ዓይነት ጣጣ ነው ?… ያ ይደንቃቸው ፣ የወይዘሮ እስከለ ልጅ ፣ ታውቀዋለህ ?… እሱ ልጆቹን ፣ ሚስቱን ይዞ ከቤቱ ንቅንቅ ብሎ አያውቅም … ከዲሳባስ መች ወጥቶ ያውቃል ? እንተስ እንደሱ አደብ ብትገዛ ምናለ ?»

«የለም!… ጋምቤላ የሚገኝ የሥራ ባልደረባችን ነው ። ለሥራ የሚያስፈልጉትን መሣሪያዎች ላኩልኝ ብሎ መጠየቁ ነው ። እኔ እንድከታተልለት ፈልጓል ።»

«አስብበት» አለችኝ ፤ «ኡሁ !… ኡሁ !» እያለች በመሔል … እና ይህ ጠዋት የመጣ ልጅ … ከሐሳቤ

http://ethioliberty.wordpress.com/

አልጠፋም ... ይሄ ሳምሶናይት ደግሞ እርጅና ጀምሮታል ለበለ ለመከፈትም አስቸገረኝ ።

«እራት ይቅረብ!... አሁን እንኳ እረፍ ብትል ... ከባኞው ውሃ ሞቆልሃል » እናቴ ነበረች ።

«እሺ እደርሳለሁ » ብዬ ፤ የተተየበውን የልጅን ጽሑፍ ፊት ለፊቴ ጠረጴዛው ላይ ወረወርኩት ።

መጽሔት አዘጋጅ ፤ የምትሠቃይ ነፍስ ነው ያለው ። ስለ መጽሔቱ ማግር ሌት ተቀን ሲጨነቅ ፤ የሚያቀርበውን ሲያሰላስል ፤ የቀረበለትን ሲያርም (አርትእት ሲያከናውን) ምን ጊዜ ለራሱ ያስባል ?... እኔስ ?

«አባት» ይላል ፤ የወጣቱ ጽሑፍ— ርዕስ ። የዚህ ዓይነት አርዕስት አወጣጥ የራሱ ድክመት አለው ። ታሪኩን አጠቃሉ ያመለክት ይሆናል ፤ ግን መስህብነት ፤ ድብቅነት ፤ አመራማሪነት ፤ ሐሳብ ተንኳሽነት እንዲኖረው ጸሐፊው መጠበብ አለበት ... ይሁን እስቲ ! ይነበብ ።

* * *

በዚያች ደማቅ ከተማ ጥቂት ቆይታ ያደረገ— ትዝታዋን አይረሳውም ። ነዋሪው ይከለባል ። አየሩ ይጋፋል ። ሞቅ ያለ እንቅስቃሴ የከተማዋ መታወቂያ ነው ። የልብ ምቷ ንግድ ነው ። ንግድ !... ንግድ !... ትንሹ ትልቁ! ዐዋቂው ልጁ ሁሉ !

ከነዋሪዎቹ መካከል ፤ መንታ ሴት ልጆች የወለዱ ፤ በዕድሜ የገፉ ጐልማሳ ይገኛሉ ። ሪዛቸው ሽበት ብቻ ነው ። ንግግራቸው ረጅምና ምሳሌ ይበዛበታል ።



ባለቤታቸው በሞት የተለዩት ፤ መንትዮቹን ተገላግለው በሳምንቱ ነበር ።

ታዲያ እነዚህ መንትዮች ፤ የናትም ያባትም ፍቅር ያገኙት ከእባውንቱ አባታቸው ነው ።

አባት ገንዘብ ይወዳሉ ። ልጆቹ ነፍስ ከማወቃቸው እንደሥቶ ሲላላኩ ፤ ጥቃቅን ሸቀጥ በገበያ ሲሸቅጡ ነው— ያደጉት ። ላባቸውን እንጠፍጥፈው ፤ ወጥተው ወርደው ፤ ገበያ መሐል ሥሽው ያገኙትን ለአባታቸው ያስረክባሉ ።

አባት በፊናቸው ገንዘብ ያበድራሉ ። ይደልላሉ ። በምላሹ ገንዘብ ይሰበስባሉ ። ይሆን ቁጥረው ፤ ዝጋግ ቢታቸውን አኘሽለዋል ። የዘወትር ሕልማቸው ግን ባቅራቢያቸው የሚመለከቷቸውን ቱጃር ነጋዴዎች መብለጥ ፤ ካልሆነም በሀብት መስተካከል ነው ።

መንትዮቹ ልጆች ፤ በትምህርት ያልገፉ ነገር ግን በባሕርይ ፍጹም ተቃራኒ ናቸው ። «ኩረሪማ» እያሉ በቅጽል ስም የሚጠሯት— ብልህ በድርጊቷ ፈጣን ነች ። ንግግሯም እንዲሁ ። አንድ ነገር ካደረገች ፤ ፍጹሚውን ለማየት ትቸኩላለች ።

መንትየዋ በጣም ትለያለች ። ጭምት ፤ ዝምተኛ ፤ በድርጊቷ ሁሉ ቀስስተኛ ነች ። አትበሳጭም ። ባንጻሩ የሚያስደስታት የለም ። ሪዥም ጊዜ አቀርቅሩ ብትቀመጥ አትሰለችም ። ገበያ ሸቀጥ አውጥታ ይሠረቅባ

ታል ፣ እንዳንዱ ቤት የምትገባው ባዶ እጆዋን ነው ።
ትፈባለች ...

አባት ደብዛ ሲፈጸም ግልፍ ይላቸዋል ። ይቆጧታል ። በስድብ ይወርፏታል ። እሷ ግን አትነዘንዝም ። አባት ፣ ወዲያው መለስ ይላሉ ። ተፈጥሮዋን እያወቁ ስለ ተናገሯት ይጸጸታሉ ። ልባቸው በሐዘን ይሞላል ፤

« ሰዎች! 'የናት ሆድ ዥንጉርጉር' የሚባለው ዕውነት አይደል! » በማለት ይተክዛሉ ።

የከተማው ሰው መንተባተቧን መለየት አይችልም ። ሲበዛ ይመሳሰልባታል ። አባት ለልጆቹ ልዩነት አላደረጉም በማለት ልብስ እንኳ ሲያሰፉላቸው ባንድ ዓይነት ቀለምና ባንድ ቅድ ነው ።

ኮረሪማን የተቀወቀ ሌላኛዋን ሲያገኙ ፣ ልቧን ሲያደርቅ ይመላል ። « ... ረሳሺኝ እንዴ ? ተቀውቀን አል ነበር ? ደህን ደህን አልገዛሁሽም ? ... » የማያልቅ ወቀሳ ይደረድራል ። ኮረሪማም በተራዋ አይቀርላትም ። «ያን ሰሞን ፈሸሽ ነበር ፣ አሁን ምን አግኝተሽ ተቅለበ ልብሽ ? ... » ሲሉ ይወርፏታል ።

አንድ ቀን ፣ አባት በወለድ ያበደሩትንና ያተረፉትን ሲያሰሉ ፣ ኮረሪማ ስትከንፍ ደረሰች ።

« እባ ... ባል አገኘሁ ! » ትንፋሿ ይቆራረጣል ።

« ምን? ... ምንድነው የምታወሪው ? » እንዳቀረቀሩ ነው ።



http://ethioliberty.wordpress.com/

« ባል አገኘሁ... ላገባነው ! » ፍንድቅድቅ እያለች ።

« ከነብያ ነው የገባሽው ?... ደግሞ አንቺን ማን ያገባልሻ » ብለው ማስላታቸውን ቀጠሉ ። ኮረሪማ ፣ ችላ ስለተባለች እየተቆናጠረች ወደ ቤት ገባች ።

ትንሽ ቆይቶ ፣ አባት በሌቱ ላይ ማተኮር አቃታቸው ። የልጃቸው ንግግር ኮረኮራቸው ። ስለ ባልና ፣ ልጆቻቸውን ስለመዳር አስበው አያውቁም ። አሁን ግን ሐሳባቸውን ጠቅ !... ጠቅ ! የሚያደርግ አዲስ ጉዳይ ገጠማቸው ።

« ኮረሪማ !... ኮረሪማ !... ነይ ልጄ! » አሉ ፣ በተዘበራረቀ መንፈስ ።

«አቤት!... አባ!» ብላ ስትመጣ ፣ ደስታ ከፊቷ ላይ ያበራል ።

«ምንድነው ነበር ያልሺኝ?»

«ባል ላገባ ነው ... በጣም ሀብታም ነጋዴ አገኘሁ ። ቤቱ ወስዶ ጋበዘኝ ። ሀብቱን ሁሉ አሳየኝ ። 'እወድሻለሁና እንጋባለን' አለኝ ፤ እኔም እሺ አልኩት ። »

« ወይ ጉድ ! ባንድ ጊዜ ነው — ደህን ሁሉ የሚቀባጥረው ? »

«አይደለም ፣ ... ለካ እኔ ሳላየው እሱ ሲከታተለኝ ቆይቷል ። ለንግድ ወዲያ ወዲህ የሚዘዋወር ነው ። 'አንቺ ብለህ ስለሆንሽ ሀብቱን ትጠብቂልኛለሽ' ብሎኛል ... አባ ታድ'ዬ ! ሀብታም ሰው ላገባ ነው ! »

« እሺ ! ... ነገ ወስደሽ ታስተዋውቂኛለሽ ፣ »

http://ethioliberty.wordpress.com/

በማግሥቱ አባት ከቁጇሩ ነጋዴ ተዋወቁ ። ሀብቱ በቁና ይታፈሳል ። ያከማቸው ጌጣጌጥና ገንዘብ መጠን የለውም ። አባት በዕውን ሳይሆን በሕልም ዓለም ይኖሩ ይመስል ማመን በቃታቸው ። ነጋዴውም በልዩ መስተንግዶ ጋበዛቸው ።

የሠርጉ ዝግጅት ተጀመረ ። የከተማው ታዋቂ ሰዎች ሳይቀሩ እንዲገኙ ተደረገ ።

አባት ከሠርጉ ዕለት በፊት ፣ «ኮረሪማ ! ዘመድ ጠያይቂሽ ተመለሽ!» ብለው ወደ ገጠር ላኳት ። በእጅ አዙር ሰው አስልከው ፣ ወር አከረሟት ። ሰበብ ሲሰጡ «እሚታልና ጠበል ያስፈልጋታል—ቢታገሥላት!» ነበር ያሉት ። ኮረሪማ ፣ «ሠርጌ !... ሠርጌ!» እንዳለች ከረመች።

መንፈሷ ደፈረሰ ።

«ሩፋኤል !... ሩፋኤል ! ምን ነካህ ? እራት እኮ ቀርበልሃል !» እናቴ ባለቀ ትዕግሥት ተናገረችኝ ። የመጣ ነን ያህል ነው—የተሰማኝ ።

«እሩ !... መሸ !... በትድሜያ ብታጠብ ይሻለኛል ፣ ኋላ እበላለሁ ። እሁን ትንሽ ነው የቀረኝ ።»

«በል እንደ ፈለክ ...»

ኮረሪማ ወሩን ጨርሳ ተመለሰች ።

«አባ !... ምን አረኩህ ? ምን በደልኩህ ? ለምን ሠርጌን አበላሸህብኝ ?... እሺ ብለህ አልነበር ሠርጌን የተቀበልከው ?» እያለች ተንሰቀሰቀች ።



«በይ ጉዳዩን [illegible] ... [illegible] አላምጪ ... ኮረሪማ ! እንቺ ንቁ ፣ ብልጥና ዘዴኛ ነሽ ። እህትሽ እንደምታውቂያት ከርፋፋ ትላለች ። ስለዚህ በጣም ታሳዝናለች ። እሷ ባል ፈልጋ ታመጣለች ማለት ዘበት ነው ... አይደል ? እስቢ ፣ እስቢ ... እንቺ ያመጣሽውን ለሷ ሰጠኋት ። እና እሷ በውዋውን እንድታገባ አደረኩኝ ። እንቺ ሌላ ብትፈልጊ አታጪም ፤ እሺ ? እየሽ !... ለእህትሽ እዘኝላት ። በውዋው ያመጣው ጥሎሽ ቀላል አይምሰልሽ !... ላንቺም ይሰጥሻል ።» ብለው... አልማዝ ፣ ዕንቁና በርካታ ገንዘብ አሳዩዋት ።

ልባቸውም የበለጠ እርካታ አገኘ ። የረኛዋም ጊዜ ምኞታቸው ዕውን መሆኑ ፣ ሞቢ አስረገጣቸው ። ቤታቸው ፣ ግቢው ... በልዩ ልዩ ቁሳቁሶች ተሟላ ።

ኮረሪማ አለቀሰች ። ለብዙ ጊዜ አለቀሰች ። ሐዘኗ ቶሎ አልወጣላትም ። በዚህ ሁኔታ ዓመት አለፈ ።

አባት ትልቅ ንግድ ለመክፈትና ለከተማው ለማሳየት ዋድፈያ ይዘዋል ።

ኮረሪማ ብርታት አገኛት ። ብልጠቷና ፋጣኝ ቀንሰ ። ተስፋ መቁረጥ አሸነፋት ። ግቢያ ዞር ፣ ዞር ስትል እንድ ቀን ፣ ትንሽ ግብግ አታለላት ... ጉድ ሆነች !

በከተማው የታወቀ ፣ የለየለት ሰካራምና ቁማርተኛ ነበር ያስረገዛት ። አከታትለውም «ሳይዋረዱ ልጅዎን ይስጡኝ !» ሲል ለአባት አማላጅ ላከ ።

አባት አላቅማሙም ። ሰማቸውን ለመጠበቅ ሲሉ ፈቀዱ ። እየቆረቆሩቸው ከገንዘባቸው ቆንጥረው ደገሱ— ለኮረሪማ ።

የኮረሪማ ባል ፣ ከሰርጉም በኋላ በጠባዩ ምንም ለውጥ አላመጣም ። ይሰክራል ፣ ይቆምራል ። ገንዘብ ያጠፋል ። በዚህ ከአባት ጋር ብዙ ተዳርሷል ። አንዳንዴ አባት ደም ብዛታቸው እየተነሣ ሌት እንቅልፍ ያጣሉ ።

አንድ ቀን ምሽት የኮረሪማ ባል ሲጠበቅ ቆየ ። መሸቶ ፣ ሌሊቱም ተጋመሰ ። « አሁንስ ለይቶለታል … እዚያው ማደሩ ነው » ብለው አባት ወደ መኝታቸው አመሩ ። ኮረሪማም ልጅዋን አስተኝታ ተኛች ።

ንጋት ላይ የዞረ ድምር ደም እያስተፋው ፣ ግራ ቀኝ እያስረገጠው ደረሰ— የኮረሪማ ባል ። አባትና ኮረሪማ ከደጃፍ ቆመው ነበር ።

«ኮረሪማ !… ኮረሪማ !… ቤቱ ፣ ይዞ ቤት … በቁማር ተበልቷል ፣» ከማለቱ ባሏ ፣ አባት እየተንገዳገዱ በረንዳው ላይ ተዘረሩ ።

ደማቸው ቀዘቀዘ … ልባቸው ሥራውን አቆሟል— አባት ።

* * *

እምም…አይበቃም ። ገና ረቂቅ ነው ቀሪም ነገሩ መግቢያ ነው ። ቅርፁ ሊስተካከል ፣ ርዕሱም ሊገኝ ይችላል ።



http://ethioliberty.wordpress.com/

«አሁንም አልጨረስከውም?» አለች እናቱ ፣ ከመኝታ ቤቷ ወደ ሳሎን ተመልሳ ። ዘርፋፋ የሌሊት ልብሷን ለብሳለች ።

«ውሃው ከምቀልህ ዘመን አልፎአል ። ይልቅ ታጠብ . . እራቱን እንደሁ— ትተኸዋል ! ወይ አበሳ !»

… ታዲያ የልጁ ጽሑፍ ፣ መታተም ይችላል !… ወይስ … ባኞ ቤት ገባሁ … ውሃው እንዴት ደስ ይላል … ውሃው ….

ጠየቃ

መኪተ በዋቂ መሆን በእጅጉ ያጓጓዋል — ከሁሉም ። ታዲያ ፎዚያ የምታመጣቸው ጥያቄዎች ብዙ ነገር እንደማያውቅ መሰከሩበት ። «እንዴት አላውቀውም ?» በሚል ግፊት ፣ ተስፋ ባለመቁረጥ መፍትሔያቸውን ፍለጋ ይፍጨረጨራል ። በሐሳብ ይወጣል ፣ ይወርዳል ።

ለፎዚያ ጥያቄዎች ምላሽ ፍለጋ ራሱን ማስጨነቁ ፣ «የለም! እንዴት?!» ስትለው መኪራኩሩ እርካታ እንደሚሰጠው የተገነዘበው ዘግይቶ ነው ።

መኪተ ፣ ያሥረኛ ክፍል ተማሪ ነው — በእንጦጦ አጠቃላይ ። ብዙ ጓደኞች የሉትም ። አይፈልጉትም ። ፎዚያ ፣ ከመርካቶ የምትመጣዋ ነች የምትቀርበው ።

«ፎዚያ! ጥያቄዎቹን ከየት ነው የምታመጪው ?» ሲል — ይጠይቃታል ። እቱ ለምዶበት እንጂ ፣ ያውቀዋል ።

«ስንቴ ነው የምነግርህ ? የሒሳብ አስተማሪያችን የሚያመጣው ጥያቄ ነዋ! ሒሳብ ያስተምረንና እሱቲ እሷም ፎችሁን አሠሩት እያለ ጥያቄዎቹን ይዘረዝራቸዋል ። »

«እ . . . ሺ ! ይሁንልሽ ! »

«ትቀልዳለህ ? . . . ሲያገባበን ፤ ምን ይላል መሰለህ ? 'ማትሪክ ለመውሰድ ምን ያህል ጊዜ ቀራችሁ ? ሁለት ዓመት ነው ፤ አይደል ? በሉ ! ... ከአድማስ ባሻገር



http://ethioliberty.wordpress.com/

ለማየት ፣ ዕውቀቱ ለመገብየት ፣ ጥያቄዎች ውሰዱ !' ይለናል ። እኔ ግን እሱ የሚያመጣቸው ጥያቄዎች ማትሪክ ላይ ወጡ ሲባል አልሰማሁም ። »

ፎዚያ ፤ ዐሥረኛ ክፍል ብትሆንም በ «ሲክሽን» ከመከተ ትበልጣለች ።

እነዚያ ከባድ ጥያቄዎች ሲነሽጡት — መኪተ — የማወቅ ጉጉት አናቱ ላይ ያናጥራል ። "ከፎዚያ ጋር እንድ 'ሲክሽን' በሆንኩ ።» ይላል — በልቡ ።

«አሁን መልሱን አትስሪልኝም ! » ትላለች ፎዚያ ።

«እንዴት ? ... እንቺ ተጠይቀሽ እኔ ምንድነኝ ? » መልሱን ለመሞከር እየተሽከረመመ ።

«ሒ ... ድ ! ለምንኝ እታብዛ ! ለነገሩማ እኔም እሥራቸለሁ . . . ግን አንተ ምን እንደተሰማህ ለማወቅ ነው ።»

« ባይሆን አንዳንድ ሐሳብ ካገኘሁ ፣ ጠያይቂም ቢሆን ልሞክርልሽ ! . . . »ይላል ፤ ሁል ጊዜ ሳትሰለች የምታስጠናውን የታላቁን ታላቅ እህቱን እያሰበ ። ባያውቀውም የእህቱ አንባቢነት ፣ ሁሉን በወቅንት መንፈሱን ተጭኖታል ።

«አስተማሪያችንም ያለው ይህንኑ ነው ! 'ከሚያውቁ ሰዎች ጋር ተማከሩችሁ ፤ መልስ አምጡ' ነው ያለው ። »

«ጥሩ . . . ይሁንልሽ ! »

አንድ ቀን ጠዋት — በዕረፍት ሰዓት ነው ። ተማሪዎች በሜዳ ላይ ይተራመሳሉ ፤ በመናፈሻ ይናፈሳሉ . . . ወዲያ ወዲህ ሲሯሯጡ ፣ ድምፃቸው ከፍ ብሎ ይሰማል ።

ፎዚያ እየሮጠች ፣ ወደ መኮተ ክፍል ቀረበች ።

« ታዲያስ ! »

« እሰየ ! ምንድነው ሩጫው ? »

«ባክህ የዛሬውን ጥያቄዎች . . . ልነግርህ ነው »

« እንዴ ? ! . . . ማቴማቲክስ መማር አቆማችሁ ማለት ነው ? »

«አቦ ! እኔ ምን ላርግ ? አስተማሪው ያበዛዋል ...»

«ይሁንልሽ ! . . . ቆይኝ ከክፍል ወረቀት ላምጣ » ብሎ ማስታወሻ ደብተሩን ይዞ ተመለሰ ።

« በል ያዝ ! . . . አንደኛ ለምን ከሁለት በላይ የጾታዎች ዓይነት አይኖሩም ? . . . ሁለተኛ— ድመት ለምን ልጆቿን ትበላለች ? . . . ሶስተኛ— ዓለም ትጠፋለች ወይ ? መቼ ? ...አራተኛ— ከሞት በኋላ ሕይወት አለ ወይ ? እንዴት ? »

«ይጄ ሁሉ ? . . . ከባድ ናቸው ?»

«በል ሊደወል ነው . . . » ብላው ፤ እየበረረች ተመለሰች ።

' . . . ለነገ ከሰዓት እምጣው ሳልለው ፤ ' አለች ፎዚያ በቅሬታ— ከዋቢ ለቀቀበ ።



http://ethioliberty.wordpress.com/

በመጨረሻ ፤ ሰዓት ደርሶ ተማሪዎች ተለቀቁ ። መኮተ ወደፎዚያ ክፍል ለመቅረጥ ዐይኑን ጣል እንደ ሚያደርገው ፤ ዛሬም ልማዱን ለማድረስ ቆም አለ ። . . . ወደሱ ስትሮጥ አያት ።

«መኮተ ! ሳልነግርህ ፣ ነገ ጧት 'ክላስ' አለመጣም ። የስፖርታል ለጥርሴ ቀጠሮ አለኝ ። ስለዚህ ከሰዓት በኋላ ታመጣልኛለህ ፤ ምክንያቱም ከነገ ወዲያ መልሱን እምጡ ብሎናል . . . »

«ለዛውም ለነገ ? . . . ጥያቄዎቹ ከባድ ! » በመደንገጥ መለሰ ፣ መኮተ ። የፎዚያ የላይኛው ከንፈር ለምን ጥርሷን መሸፈን እንዳልቻለ ምላሽ ያገኘ ይመስል ፤ አፍ አፏን ያያል ።

«አቦ ! አንተ ልጅ ! . . . በናትህ ! አያስቸግርህም »

«እሺ ! ይሁንልሽ ! »

«የት ታመጣልኛለህ ? »

«ሠፈራችን ነይና ውሰጂው— ካገኘሽኝ »

«አቦ ! ትቀልዳለህ . . . ይልቅ አራት ኪሎ ከም ትወደው ሻይ ቤት ጠብቀኝ— በዘጠኝ ሰዓት »

«እሺ ! ይሁንልሽ ! »

እየተንጋጉ በትምህርት ቤቱ ዋና በር ይወጣሉ ።

ተማሪዎቹ ይተማሉ ። ውካታው የቅቤ ገበያን ያስ ታውሳል ። ጉን ለጉን ተቀማጥለው የመንገደኛ ሰንሰለት መሥራት የሚቀናቸው አንዳንድ ሴቶች አሉ ። ለግት ይቸኩላሉ ። ግን ? ይሁን ግ ? ከተናገሬ መሳት

ነው ። የፈረንጅ ሥዕል ፣ ሙዚቀኛ ፣ ኳስ ተጨዋች ፣ የል
ብስ ሞዴል አስተዋዋቂ . . . የተለጠፈበት ደብተር
መያዣ ፣ በትከሻ የሚንገት ስልቻ መሳይ ቦርሳ . . .
ከነዚያ ሴቶች አይለይም ። የዘንቢል ቦርሳው . . .
ሹራብ ፣ የፎቶግራፍ አልበም ፣ መቀየሪያ 'ቲሸርት'
ሳይቀር ስለሚይዝ ይመርጡታል ።

. . . አለባበሳቸውን ልብ ብሎ ያጤነ ፣ ይገረማል ።
ለሌላ አይደለም ። ባሕር ማዶ ገበያ ያማበበው ፋሽን
ሳይዛነፍ በዚያ ልጆች ላይ መታየቱ ነው ።

ታዲያ ልጆቹ እንደ ሌሊ ከተንቀረበሱ ጨዋታ
መፈለጋቸው ፣ መግባት እንዳቸው ያስታውቅባቸ
ዋል ። 'ግቅ የደስታ ምንጭ ነው ' የሚል ሐሳብ ኘው
ይላቸዋል ።

. . . እንዴ ሙከ ብላ ትናገራለች . . .

«ልጆቹ ታያቸሁ ! . . . እዩት ያን ልጅ !
ሊያመልጣችሁ ነው . . . በዚያ በኩል » እጆቹን እንደ
ቀጭን ማስመሪያ ቀስራለች ።

«አያችሁት ! ! ሱሪውኮ ተቀዷል . . . »

የመኪቱ ጀር ወረፆን ቀለበው ።

«አሀሀሀ! . . . ኢሂሂሂሂ! » ያስካካሉ ።

እጠር ያለቸው ቀጠለች ።

«ጥቁር ፓንቱ'ኮ ብልጭ ብልጭ ይላል »

ሌላዋ ትቀበላለች ፤



http://ethioliberty.wordpress.com/

«መርፌ የለውም — የሚጠቀለለው . . . » ፤

«ጋጠአት አታውሩ ! . . . ላውገዴሪ እስገብቶት
ቀደውበት ይሆናል እንጂ ፣ ሌላ ምንም አላረገም ። »

«ሕካካካ ! . . . ኪ,ኪ,ኪ! . . . »

«ሁላችሁም አላወታችሁም . . . 'ዩ ኢድየትስ ! ' በሕ
ልሙ ሸርተቴ ሲጫወት የቀደደው ነው ። »

«ኢሂሂ ! . . . »

ባለተራዋ ታዳንታለች ፤

«እስቲ ይሄ ምስኪን ምን አረጋችሁ ! . . . መጀ
ለሉ ይሆናል ! »

«ለዚህ ነዋ መዘንጠን የወደድሽለት ? ለሱ ጥብ
ቅና የቆምሽለት ? » ወይናን እያሸሽ ትጠይቃለች

«ኪ, ኪ, ኪ, ! . . . ኪ, ኪ, ኪ, ! ! »

«ለዚህ ነዋ ! ሞኃ ጫማ አርገሀ ፣ ረጅም መሱቲያ ስከ
ተሀጸትርሀን ግላ ቁርጥ ተቀርጠሀ፥ ከመቀመጫሀ የተሰደሰ
ሱሪ አርገሀ ፤ ፒያሳ አውጣኝ ያልሽው።ትተደርባ ታፌዛለች።
ይሥቃሉ . . . .

«እዩልኝ በናታችሁ . . . ያቺኛዋን ! የውስጥ ልብሷ
ሪዘም ፣ ተንዘርፍፏል »

« . . . እ ? ያቺ ! ብታያትኮ '

እሷም ያለች ፋራ ! ነች ። ጠባ ! . . . ቀለም ግን
ፓ ! አስተማሪያችን ካለዷ አይጠይቅም ! »

«ገርቶሜ ሙሉ ! »

http://ethioliberty.wordpress.com/

«የእግሯ ወፍረት ! ኡ ! ደዘደዝ ነች ።»

«ደንደሳም . . . ይሄን ሲተ ትጋት ! ትጋትና . . .» ያሥቃቸዋል ።

«እሃሃሃ ! . . በሃታውን ትገለብጠዋለች በይኛ . . . ኪ ኪ ኪ ኪ ! »ይሥቃሉ ።

«ትሰሚያለሽ እነዚህን ጅሎች ! » መኪተ ወደ ፎዚያን የጉንተሽ እየተመለከተ ይነግራታል ።

«ይሚወቱዋ ! . . . ጊዜያቸው ነው » ዕኩል ፈግና እየተራመደች ፤ ትመልስለታለች ።

«እንዴት ? . . . ከተቸገረ ቤት የሚወጣ ልጅ የሚለብሰው ያጣ ይሆናል ፤ እ ? እና ልብሱ ተቦተረፈ ብሎ አታቂር ማውጣት— መሚወት ነው ? »

«ታዲያ ፣ ሌላ ምን ያውሩ ? »

«ይሁንልሽ ! . . . ግን ብዙ የሚሚወቱበት ቁም ነገር አያጠም— በደንብ ካሰቡበት ! »

«ካልፈለጉስ ! . . አንተ ምድነህ ?»

«እእ . . . እኔማ ? እም ! ምንድነኝ ? »

ፎዚያ ቀይ ፊቷን ታሻሻለች ። በጥድፊያ እልም . . . እልም የሚሉትን ተማሪዎች ባይኗ ተከትላለች ።

«ስሚ ! »

«አቦ አንተ ልጅ ! ስም አለኝ— ምን ነካህ ! »

«ፎዚያ»

«አቤት»



«ቆንጆ ሱሪ አርገሻል »

«ወደድከውን» በቢጫ ፣ ቀይ ፣ ጥቁር ፣ ወይን ጠጅ ፣ ሰማያዊ . . . ቀለሞች የተንቆጠቆጠው ሱሪ ደምቆ ይታያል ።

«ረቂቅ ሥራ መሆን አለበት !» ባድናቆት የቀለ ማቱን ኅብረት ያጠናል ።

«ምንም ጥርጥር የለውም ! ለወንድ አይሆንም እንጂ ታሪገው ነበር ። »

«እንዲያውም አስታወሽኝ የምታስጠናኝ እሁቱን ምክሬው አላታለሁ ። »

«አንተ ! አቦ አታፍርም ? . . . ትገርማለህ ! የሴ ዶሬ ሱሪ አርጊ ልትላት ! »

«ነውር አለው ? »

« እንጃ ! »

«ይልቅ ያልገባኝ እግረ ጠባብ ለምን ሆነ ? »

«አታይም ! . . . እንደልብ ያራምዳል ፤ አያደናቅፍም ፤ እንደ ቤልቦተም ነው— አሉፋንት እርስ በርሱ እየተጣፋ እግር አይጠልፍም ። »

«ይህ የምትይኝማ የሚታየኝ ነው ። ጂሬ ዱሮ . . . ለምን እንዲህ ተሰፋ ? »

«እንጃ ! »

«ጠይቂና . . . ትነግሪኛለሽ ! »

«አቦ አንተ ልጅ ! የነገን እንዳትረሳ ! »

«እሺ ! ይሁንልሽ ። »

* * *

http://ethioliberty.wordpress.com/

የመከት እያት ድምፃቸውን ከፍ አድርገው ይጣራሉ ።

«መከት ! . . . መከት ! ምንድነው የምትሠራው ? »

በረንዳ ላይ ወንበር አውጥተው ዐረፍ ብለዋል ።

«አቤት እናዬ ! . . . እዚህ ነኝ » ማሪያ ድረስ እየሮጠ ይመልሳል ።

«ተው አንተ ልጅ ! እህትህ የሌለችበት ከቤቷ አትገባ አላልኩህም . . . እህን የሰው ዕቃ መቀስቀስ— ደግ ነው ? ነውርም አይደል ! »

መከት ትልቁ እህቱ መኝታ ቤት ገብቶ ዕቃዎቿን እንዳይነካ ተነግሮታል ። ሆኖም ከባድ ጥያቄዎች ከትምህርት ቤት ይዞ ከመጣ ፣ ሐሳብ የሚሰጡትን መጻሕፍት ፍለጋ የእህቱን መስሰተኛ « ቤተ መጻሕፍት » ይጐበኛል ።

መኝታ ቤቷ በጣም አይሰፋም ። ባንዱ ግድግዳ በኩል ባለ አንድ ትራስ አልጋዋ ተዘርግቷል ። ከዚህ ትይዩ ፣ ተገጣጣሚው ባለብረት መደርደሪያ በመጻሕፍት ተጨናንቋል ። በግድግዳው ማዕዘን በኩል የተንበበሩት ካርቶኖች በመጻሕፍት ተሞልተዋል ፤ የጅምላ ሱቅ ሸቀጥ ይመስላሉ ።

«አንተ ልጅ ! አሁንም አልወጣህም ፤ የምታንከኘኩኸው ይሰማኛል ! »

መከት መስኮቱን ባለመዝጋቱ እየበሸቀ ይመልሳል ።

«እሺ . . . ልወጣ ነው ፤ ይሁንልሽ ! »

«ምን ትሠራለህ ? »



«የቤት ሥራ ተሰጥቶኝ ነው ። »

«ታዲያ ቤትህ ገብተህ አትሠራም »

«እናዬ ! አንቺ ደሞ— መጻሕፍት ፍለጋ ነው ። »

«ደሞ ከእህትህ ዕኩል መሆን አማረህ . . . በል እንዳማረብህ ውጣ» ልብስ ሲሰፉ ቆይተው ፣ የግል ክንዳቸውን ያፍታታሉ ። ብዙም ሳይበለጡበት አቋርጠው ወደ ሄርና ቢወርዱም ፣ በቀድሞው የእቴጌ መነን ልጃገረዶች ትምህርት ቤት የተማሩትን የልብስ ስፌት አለረሱትም ። ሲመቻቸው ይጠቀሙበታል ።

ዐይናቸውን ፊት ለፊት ካሉት አበቦች ላይ ጣል አርገው ፣ የባጥ የቆጡን ያስባሉ ።

መከት ለፎዚያ ጥያቄዎች መልስ ያመነጫሉ ያላቸውን መጻሕፍት ለፍና ወደ መኝታ ቤቱ ይዞ ገባ ። ወዲያው የእህቱ ቆጣ ብልጭ አለበትና መጻሕፍቱን ይዞ ተመለሰ ። ከመጻሕፍት ማቸኛው ያብተር ላይ ፣ አርዕስታቸውን መዘገበ ። . . . እህቱ ማስታወሻ ሳያሰፍር የሚነካባትን እንደማትወድ ያውቃል ።

አጠቃላይ ዕውቀት ከሚያስጨብጡት ፣ ቀልድና ቁም ነገር ከሚመሩት እንሥቶ እስከ ፍልስፍናና ኑክሊየር ፊዚክስ ድረስ መጻሕፍት በያይነቱ አሏት ። ሁሉንም ለማወቅ ታነባለች ። የምትችለውን ትገዛለች ። በየወሩ ወጪ ማድረጓን አያትየውም ቢሪዱ ፣ ታዝበዋል ።

http://ethioliberty.wordpress.com/

'ምን ነካኝ ነው ! የምትለው ? . . . በዚህ የኑሮ ውድ ነት ይሄ ሁሉ መጽሐፍ ተገዝቶ— ይቻላል ? ወይስ መጽ ሐፍ ተሰብ ይሆናል ? ወቻ ጉድ !' ይላሉ በልባቸው ።

መኪተ ያነባል ። ጠጠር ያሉ የእንግሊዝኛ ቃላት ሲያጋጥሙት ፣ መዝገበ ቃላት ያገላብጣል— የግዱን ። ግዱን ገለጥ . . . ገለጥ ሲያደርገው ከምባል የሚልበት ይመስለዋል ፣ ከብዙቱ የብረት እሱሱ ያህል ስለሚ ሰማው ። የፈደል ተራውን ለማግኘት . . . ወደፊት . . . ወደኋላ ሲገለጥ መስሎቸት ይከጅለዋል ። 'ዓንድ ቃል ምን አለፋኝ ? ' . . . የሚል ዓይነት . . . 'እንዴት ! ግወቅ አለብኝ ' . . . ማገላበጡን ይቀጥላል ።

. . . ጥቂት እንዳነበበ መሽ ።

እዘውትራ ከምሽቱ አንድ ሰዓት ላይ የምትገባው ትልቋ እህቱ ፣ ከእያታቸው ጋር ስታወራ ሰማት ።

«ደህና ዋላችሁ ? . . . እናቴ ታዲያስ ? » ነጭ መነጽሯን እያወለቀች ።

«እንደምን ዋልሽ ልጄ ?» ይላሳማሉ ።

«ምነው— ብቻሺን ? . . . መኪተ አልመጣም ?»

«ሸሬ ገብቷል ! . . . ወረቀትሽን ሲያተራምሰው ነበር ።»

«ሊያጠና . . . ነው ዓለምሽት አልገባችም ? »

«ቅድም ደውላ 'እመጣለሁ' ብላላች . . . »

«ምነው ? በደህና ? »



«ነገ ፈረንጅ ሀገር የሚሄድ ሰው አሸኛለሁ ብላ ለች . . . የቧ ዓይደኞች ሔደው እያሉቁ !»

«እ ! . . . እናቴ ! በይ ግቢ ። ብርድ እየመጣ ነው ።»

«እሺ ።» ከኋላ ለጥቀቀጥት ገቡ ። ' . . . እንዴህ ከሊታ ትሁን ?' ይላሉ ፣ ቅጥንቷን ባጤኑ ቁጥር ።

ምክ ብለው ይጣራሉ ።

«መኪተ ! . . . መኪተ !»

«አቤት እናቴ !»

«ይቻት እህትህ . . . »

«እሺ . . . ይሁንልሽ !» መኪተ እመር ብሎ ተነሣ ።

«ሃይ መኪተ !» ትልቋ እህቱ ወይኗን ስታኝሽው—ቀላ።

«ባክሽ . . . አንድ ጥያቄ አስቸግረኝ !» ተከትሏት ወደ መኝታ ቤቷ ገባ ።

«ማነው ? 'አንድ ጥያቄ አለኝ ' የሚል ዓምድ በጋ ዜጣ ያዘጋጅ የነበረ ? እሱን አትጠይቀውም ?»

«ትቀልጃለሽ »

«ኖ ! . . . ሲሪየስ » በርሳዋን ከጥናት ጠረጴዛዋ ላይ አስቀምጣ— አልጋዋ ላይ ተንጋለለች ። የሬብኳዋን መብ ራት ቀጭ ስታደርገው ፣ ይብዛዛ ብርሃን ወደ ኮርኒሱ ቷ አለ ።

«መስኮቱን ዝጋው !»

እየዘጋ ፤

«የሆኑ ጥያቄዎች ነበሩ . . . ግን ከባድ ናቸው ። ደግሞ ለኔን መድረስ አለበት ። » መስኮቱን በጀርባው ተደግፎ ወይን ወይኗን ያያል ።

http://ethioliberty.wordpress.com/

«መኪና ! ባለፈው ሰሞን የምታመጣው ዓይነት ነው ? »

«እም» ጉንበስ ብሎ «ጀንትራ» የተስተካከለውን ጸጉሩን እስከ ያደርገዋል ።

«እንዴ ! እንዴት ነው ነገሩ ? . . . ለዐሥረኛ ክፍል የመጣ 'ካሪኩለም' አለ አይደል ? በርግጥ ለተያ ቂምዩ መልሱን ብታውቅ ጥሩ ነው . . . ግን ለክፍልህ የሚመጥነው ዕውቀት ሳትይዝ ፣ እዛም እዛም ብትል ዋጋ የለውም ። »

«እም !»

«ታዲያ ይሄን ስታሳድድ ፣ ቀናውን ጥናት መቼ ልታጠናው ነው ? »

«እሱማ አጠናለሁ . . . እነዚህን ጥያቄዎች እስ ተማሪዎቹ እየሰጡን ነው ። 'ስለ አካባቢያችሁ ዕውቁ' እያሉ ነው። የፎዚያን ነገር ማንጣት አልፈለጉም ። 'ለሰው የቤት ሥራ ከምትሠራ — የራስህን አታጠናም ?' ብላ ትቆጣኛለች ሲል ገምቷል ።

«እሼ ! በኋላ እንነጋገራለን ።»

መኪና ደስ አለው . . . መልሱን ሲገነዘብ ፣ ሲገባው . . . ለፎዚያ ሲያስረዳት . . . ሲከራከሩ . . . ሲያሳምናት ምላሴ ሲደረደር ውልብ አለው ።

ወደ ንባቡ ተመለሰ ። እቀርቅር ሲቆይ ድካም ይጫጫነዋል ። እግሩን ያንባብራል ፣ ይደነዝዘዋል ።



ጠረጴዛው ላይ በክንዶቹ ይመረኮዛልና ጠንቻዎቹ ይገታተራሉ ። ከመሰልቸት መንፈሱ እየታገለ ፣ ሐሳቡን ወደ ጥያቄው ለመመለስ ይጥራል ።

ኪችን ጉድጉድ ያሉት እያት ፣ ከግሱን ይጣራሉ ። «የኛሽ ወርቅ !» የትልቅ እህቱ የቤት ስም ነው ።

'እናቱ! ለምንድነው በስሟ የማትጠሯት ? . . . ለምን የቤት ስም ትወዳለች? እኔ የለኝም ! . . . ማሙሽ ሲሉኝ ቆይተው ትተውታል !' ለራሱ ይጠይቃል ። . . ወደ ንባቡ ይመለሳል ።

«አቤት እናቴ !» ትልቅ እህቱ ።

«ተኛሽ እንዴ ? እራት ደርሷል ! . . . ታጠቢና ነይ ። እህትሽ ስትመጣ ትደርሳለች . . . ዘዋሪ !» አሉ የመጨረሻውን ቃል ሲናገሩ ድምፃቸውን ሰብረው ።

«እሺ »» ወደ ባኞ ቤት ታመራለች ።

እናትና አባታቸው አብረዋቸው አይኖሩም ። ሦስት ልጆቻቸውን ለአያትየው ሰጥተው፣ብቻቸውን መርጠዋል። በጥላቻ አይደለም ። አያትየው ብቻቸውን እንዳይሆኑ ነው—የሚያናግር እንዲያገኙ ። በዚህ ላይ የአያትየው ቤት ሰፊ በመሆኑ ፣ ልጆቹን እንዲመላቸው ይችሏቸዋል ፣ ተብሏል ።

እራት ይበላሉ . . .

«ትድም ያልጀውን ረሳኸው ፣ ጥያቄዎቹን »

«እንግዲህ ጀመርክ ! አላስቆም አላስቀምጥ ነው—እንብላበት ! »

http://ethioliberty.wordpress.com/

ካመል ቢናገሩትም ፤ እሁቱን አክብሮ ያልገባውን በመጠየቅ ቅር አልተሰኘም ።

«አይ ቀላል ጥያቄ ነው— እሷ . . . እንድታስረዳኝ ብዬ ነው ! » በለመና ድምፅት ይናገራል ።

«ቀላል ከሆነ አንተው አትመልሰውም ! ምን ልሷን ታወልቀዋለህ ? ! »

«እናቱ እንቺ ደሞ ! ትንሽ ብትረዳኝ ምናለበት ።
. . . እንዲያውም ይሁንልሽ ! »

ልቡ የቆመበት ጥያቄ ባለመመለሱ ፡ ወስፋቱ በወጉ አልተከፈተም ። ሆኖም 'እራት በቃኝ ! ' አላለም ።

«ምን ያደርጋ እናቱ ! መጠየቁ አይከፋም ! አስተማሪያቸው ጥያቄ እየወረወረ— እንዲያስቡ ሲያደርጋቸው ነው ። » እያቷን ለማግባባት ትናገራለች ።

«እኔ ምለው ! ለምን እዚያው አስተምሮ— እዚያው መልስ አይሰጣቸውም ? ... የምን ሰው ማስቸገር ነው ? »

«እንደሱማ የት ይሆናል እናቱ ? ልጆቹ እንዲይስንቱ በማሰብ ነው . . . ጥናቱ ቢይዛቸው አይኝልም ? አይመስልሽም ? »

መከተ ያዳምጣል ።

«ወይስ እንደ እትቱ አዛለች ልጆች ፡ ባቡር መንገድ ይገተር ነው— የምትይው ? »

እሁቱ ደገፋው ስትከራከር— መከተ— የልብ ልብ ተሰማው ።



«አሁን እሁንማ የሚገርመው ልጆች ሆንቀል ። ጠዋት ሰወጣ— ከዚያ ከትራ ሱቅ ተከልክለው እያቁቀለሁ . . . አሁን ስገባም እዚያው ነበሩ ። እምባ ጓሮ ፈጥረው ነው መሰለኝ ፡ ሲጫጫሁ ነበር ። »

«ያውንትሽን ነው . . . ከነሱ ቢገጥም ሰውም አይሆን ! ... ታዲያ ልጆቹም የሚያደርጉትን እጥተው ነው ።»

እየተጫወቱ ይጉርሳሉ ፤ እያትየው ወጥ ላነሰው ይጨልፋሉ ። እንጀራ ለሌለው ይተካሉ ።

«እየኝ ልጄ ! አዲሳባ አይመችም . . . በልጆቹ ለመፍረድ ያስቸግራል . . . የት ይሔዱ ? ምን ያርጉ ? እንደኛ ቢሆን ምንም ችግር አልነበረም ። ሂድና— ከተማው ቅዝ አይልሽም ? . . . ገጠሩን ትረሺዋለሽ ! እዚያ የምንሠራው እናጣም ! ልጆች ያርሳሉ ፡ ያግዳሉ ፡ እንጨት ይሰብራሉ ፤ ውሃ ይቀዳሉ ፤ ይላላካሉ . . . ምን ጊዜ እርፈት ተገኝቶ ! ! »

« ለነገሩማ— እዚህም ቢታሰብበት ብዙ መሥራት ይቻላል ? »

«ወሬውን ማን ያዳምቅላቸዋል ? » ድምፃቸው ከፍ ብሎ ይሰማል ።

«ጋሼ ማረልኝ ተኛለው ? . . . እማዬ ጠየቃቻቸው ? » እያቷን ትጠይቃለች ።

መከተ በሐሳቡ ወደ ጥያቄዎቹ ተመልሷል ። ሙም

http://ethioliberty.wordpress.com/

ሸቀጧን የኢምንዳንዱን ጥያቄ ማብራሪያ በቅጡ ለመረዳት የሚወስድበትን ጊዜ እያሰላሰለ ፣ '... ታዲያ ምን ላርግ ልሽ ? ጊዜ አልበቃኝም ... ብትፈልጊ ለነገ እምኪራለሁ— እላታለሁ ለርዚያ ! ደሞ የኔም የቤት ሥራ አለ ። ማማ !' ለብቻው ያወጣል ፣ ያወርዳል ።

ያያቱ ንግግር ቆም ማለቱን ከማየቱ ፤

«አንዱ ጥያቄ 'ኮ እያስቸገርም ። » የትልቅ እህቱን ዐይን ዐይን ያያል ።

«ምንድነው ?» ከተቀዳላት ውሃ እየጠጣች ።

«ድመት ልጆቿን ለምን ትበላለች ?»

ብርጭቆዋን አስቀመጠች ... እንደ መደንቅ ብላ ታስባለች ።

«ጂሬ ወዲያ ! ... በወቀህ ልብህ ወልቋል ። ይሄ ነው ጥያቄው ?» እያት ማልቃ ይገባሉ ።

«አይ እናቴ ! እጂ አንቺ መልሽልኝ ...»

«ወገኛ ! እኔ ስንት ድመት አሳድጌአለሁ ! ምስት የወለደች አንድ ቢወጣላት ነው ። ዕውነትም ትበላቸዋለች ። ምክንያቱም የናትየዋ ፍቅር ነው ። ድመት ልጆቿዋን በጣም ስለምትወዳቸው ፣ ትበላቸዋለች !»

«እህ ! የወለደውን የማይወድ ፍጥረት አለ ?»

«ሁሉም ይወዳል ! የማይወድ የለም ... ግን የድመቷ ይለያል ! እንስሳ አይደለች— አታስብማ ! ትበላ



ቸዋለች ። 'ለምን አታስተዋሉትም ነው ?'— አስተማሪያችሁ የሚለው ?»

«አዎ ! ምክንያቱን አስረዱ ማለቱ ነው ።»

«እንስሳ ምን ምክንያት አለው ። 'እንስሳ እንጂል የለውም !' አትለውም ?»

«ታዲያ ውሻ ለምን ልጆቿን አትበላም ?»

እህቱ የመከተን ጠየቃ ባንከር ትከታተላለች ።

የሚያነጣቸውን ሐሳቦች ትመዝናለች ። የመብሰል አዝማሚያ ታይበታለች ። ለማናቸውም ስለ ጉዳዩ ሐሳብ የምታገኝበትን መጽሐፍ ለማስታወስ ትሞክራለች ።

«እንግዲህ ነገርኩህ ! ውሻ ርኩስ ነው ! ... ለልጆቿ ደንታ የላትም ... ይቺኛዋ— ድመቷ ፣ የልጅ ፍቅር ነው እንዲህ የሚያደርጋት !»

«እጂ ይሁንልሽ እናቴ ! ልጆቿን እንዳትበላ በምን ንድነው የምታስተዋት ?»

«ምን ይሠራልሃል ?»

«አስረዳ ስባል ... እብራራለሁ !»

«ከፈለግ ንገረው ... በፈጦ ነው በለው ። ፈጦ ወቅጠን እንረጭባቸዋለን ፤ ከዚያ አትነካቸውም ።»

«እንዴት ?»

«የልጆቿ ጠረን መቀየሩን ስታሸት የማዷን ትለቃቸዋለች ... ከዛም ያድጋሉ ። ፈጦ መጥቀሙን ሳላውቅ እንደ በልታብኝ ነበር !»

«ሌላስ ?»

«በቃህ ! ይሄንን ንገረው !»

ገበታው ተነሥቶ ሠራተኛዋ ዕቃውን በተራ ወደ ኪችን ትመልሳለች ።

«ማን ዕውነት ነው ?» ትልቋ እህቱን ይጠይቃል— መከተ ።

«ልቧን ልታፈርሰው ነው ? . . . ነገርከው !»

«እስቲ ከመጽሐፍ ላይ ተጨማሪ ሐሳብ ፈልጌ አስረዳሀለሁ ።»

«ሌላም አለ »

«እሺ ።»

«የኛሻ ! አክስትሽ ጠበል ቅመሱ ብላለች» እያት የጨዋታውን ርዕስ ይቀይራሉ ።

«መቼ ?»

«ሳምንት እሑድ !»

መከተ አላስችል ብሎታል ።

«ዓለም ትጠፋለች ወይ ? ... ይሄ ሁለተኛ ጥያቄ ነው ።»

«ምጽአት ሲመጣ ትጠፋለች ... በለው !» ባለተ ትዕግሥት ፤ እያትየው መለሱለት ።

... እነ መከተ ጣቂ ። እህቱ በመከተ አለመሰልቸት ተደሰተች ።

«እናቴ ! ልጁ ዐዋቂነት ናፍቆታል . . .»

«እንዲህ አርጉም የለ ! . . . ትንሹንም ትልቁንም



http://ethioliberty.wordpress.com/

እያነሱ መወትወት ነው— ጉዳቱ ?»

«እዬ እናቴ ! ደግ አረገ በይ !»

«እንዴ 'አይዞህ!' እያልሽው ነው ? ... እንዴን እያ ነው ። ይኸው እንዴስ — ዐይንሽን እሳብሰ በሸቶማ አረ ፃሽ አይደል ? ሰው ሌትና ቀን — ወረቀት ላይ ያያፈልፈ ሰሌዳታ ድምፁት ይናገራሉ ።

«ቅዱስ ያሬድም እኮ ሳይሰለች በማጥናቱ ነው— የታወቀው !!»

እናት ይመኙሉ ፤

«አንተ ልጅ ! ደም ብለህ ብለህ ቅዱሳንን ታማለህ ?... የት ታውቀዋለህ ? ይሄ የሊቃውንት ሥራ ነው ። አንተን አይመለከትም ፤ ዐርፈህ ስለ ድመት አጥና »

መከተ ጣቅ እያለ ይመልሳል ፤

«እስቲ የቅዱስ ያሬድን ታሪክ ለናቴ ንገሪያት » እህቱን ይለምናታል ። እያቱን ግን 'እናቴ የት ታውቂ ዋለሽ' ብሎ ለመጠየቅ ፤ አፉ ላይ ደርሶ ነው— የመለሰው ።

«እናቴ ! ዕውነቱን ነው ። ያሬድ ዐዋቂ የሆነው ሳይ ታክት ዜማ በመማሩ ነው ። ይኸው ቤት ክርስቲያን የሱን ቅኝት አይደል የምትቀኙው !»

«ታሪኩን ንገሪያት በናትሽ !!»

«አንተ ንገራት !!» — ምን ያህል ሐሳብ እንደሚ ፈጥ መፈተኛ አጋጣሚ አገኘች — እህቱ ።

http://ethioliberty.wordpress.com/

«የማስታውሰውን እሺ!» — ጉሮሮውን '... እእእ!' አለና ጀመረ ።

«ያሬድ የዜማ ተማሪ ነበር ። ሲማር ፣ ሲማር ቆይቶ አንድ ጊዜ ጠፋው ። አቃተው ። መምህሩ ትጥቅጥቅ አርገው ገረፉት ። ወዲያው ሮጦ ያመልጥና ካንድ ዛፍ ሥር ይቀመጣል ። ሲያስብ ... ሲያስብ ፣ ባጋጣሚ ከቅጠሉ ሥር አንድ ትል ያያል ። ትሉ በቅጠሉ ላይ ለመውጣት ... ሳብ ... ሳብ ... ይልና ይወድቃል — ወደ መሬት! እንደገና ሳብ ሳብ ይልና ... ይወድቃል ! ... ያሬድ— ይህን ልቅም አርጎ ያስተውላል ። በመጨረሻ ፣ ትሉ ... ሳብ ሳብ ፣ ይልና ይወጣል ... ከዚህ — ያሬድ ትልቅ ትምህርት አገኘ ። ተግቶ መሥራት ፣ መጣጣር ከተፈለገው ቦታ እንደሚያደርስ ዐወቀ ! በኋላ ወደ አስተማሪው ተመለሰ ። ሲማር ይገባው ጀመር ። የተነገረውን አይረሳም ... የዜማ ሊቅ ሆነ — አሉኝ ለሁ ። »

«ውይ ውይ ! ... ዕውነትም የግዜር ሥራ ነው ! ታሪክ! ታሪክ ነው !»

«ሌላም አለ ... ከነበሩት ንጉሥ ፊት ቆሮ ዜማ ሲያዜም ፣ እግሩ ድንገት በጦር ተወግቶ ነበር ። ታዲያ ከመመሰጡ የተነሣ ሳይሰማው ቆይቶ— ዜማውን ካበቃ በኋላ ነበር — ከእግሩ ደም መፍሰሱን ያየው። ታዲያ አይገርምም !!»

«ወይ ጉድ ! እኔን ! የግዜር ሥራ ነው ... አንተ ልጅ ፣ ወሬህ አያልቅ !» ተነሥተው ወደ ኪችን ገቡ ።



«የተያቆዎቹን ...»

«ጸፍና ስጠኝ ! ... አሁን ትንሽ የማነበው አለኝ ፤ ስጨርስ አንዳንድ ሐሳብ እነግርሃለሁ ... »

«ልጆች ! አላችሁ ? ታጠቡ እጃችሁን ...»

ከእሁቱ ቀጥሎ እጁን ታጠበ ። ፒጃማውን ለበሰ ። ጋደም አለና እሁቱን ይጠብቃት ጀመር—እንድታስረዳው !

፤ በሦስተኛው ቀን ...

መኩት ትምህርት ላይ ነው ። አስተማሪው ጂኦግራፊ ያስተምራል ። በግራውም በቀኝም እጁ ቆልጭ አርጎ ይጽፋል ። ግልጽ አርጎ ስለሚያስረዳ ፣ ተማሪዎች ይወዱታል ።

መኩት ከመጨረሻው «ቢንች» ላይ ተቀምጧል ። አብሮት የሚቀመጠው ሰማ ቀሪ ሆኗል ። ከጐኑ የለም ። ድንክዬው ዓለማየሁ በደብተሩ ጀርባ ሥዕል ይሠራል። አፍንጫዋ ዘወትር የሚንፋፋንፈው ፍሬወይኒ ብጣሽ ወረቀት ላይ ጻፍ ጻፍ ... ታረግና በ « ቢንቹ » ሥር ለንደሞጀ ታቀብላለች ...

በር ሲንኳኳ ፣ አስተማሪው ይከፍታል ። እንግዳውን ወጣ አርጎ ቆየ ... ይነጋገራል ። ሲጨርስ ወደ ተማሪዎቹ መለስ ብሎ !

«መኩት ! መኩት ! ሰው ይፈልግሃል ... ብሎ እንዳትቆይ !» ወደ ማስተማሩ ተመለሰ ።

http://ethioliberty.wordpress.com/

ልቡ እየደነገጠ 'ማነው የሚፈልገኝ ?' በማለት ፣ ትንፋሹን ውጦ ከመቀመጫው ተነሣ — መኩት ። ተጣራምፔ እየተንጓመጡ ዐይናቸውን ሲያንሬጠርጡበት … ይደነግጣል ። ፊቱ ላይ ላብ ችፍ ይልበታል ። የደም ሥሮቹ — ይገታተራሉ ።

እንገቱን ሰብሮ ይወጣል …

በሩን ከመክፈቱ ፣ ፎዚያ ተገትራ አገኛት ።

«ኢህ ! … አንቺ ነሽ ! ምን መጣ ብዬ — ቀልቢ ጠፍቶ ነበር ።»

«አይዞህ !»

«ምን ትፈልጊያለሽ ? … ትላንት መልሱን ነግሬሽ የለ ! … አስተማሪንኪ አትፈሪም !»

«አቦ አንተ ልጅ — አትቻኩል !»

«ኢሺ ይሁንልሽ ! … ትምህርት አለኝ ፤ ምን እርግ ነው — የምትይኝ !»

«መች እጣሁት ትምህርት እንዳለህ !»

«እና»

«እና አሁን የምትሠራልኝ ነገር ስላለ ና እንሒድ!» ቀደም ቀደም እያለች ትመራዋለች ።

መናገር እየፈለገ ፣ ትምህርቱ እንዳያመልጠው እየተጨነቀ … ይከተላታል ። የነ መኩት ክፍል የሚገኝበት ሕንፃ— ከጣሪያው በላይ ከቤተ ክርስቲያን ይመሳሰላል። … ሌሎች ክፍሎችን አልፈው ፣ በሕንፃው ዋና በር ተከ



ታትለው ይወጡና ፊት ለፊት ካለው የትምህርት ቤቱ መናፈሻ ይገባሉ ። ዙሪያውን ያለው ባቡር መንገድ እንደቀለበት ይከበዋል — መናፈሻውን ።

«በይ ! ቶሎ ንገሪኝና ልመለስ !»

«እንካ ወረቀት ! … አስክሪብቶ ይዘሀል ?» ከድንጋይ ላይ ይቀመጣሉ ።

«አዎ !»

«በል ! ለክርክር የሚሆን ሐሳብ ነው — የምትሰጠኝ። አሁን ባማርኛ 'ፒሪየድ' የማቀርበው ነው … 'ሞት እፍፍ የደረሰን ሰው ፣ በሕክምና የማይረዳ ሲሆን ሕይወቱ እንዲያልፍ ማድረግ ተገቢ ነው ? ወይስ አይደለም?' … ምን ማለት ነው መሰለህ ? … እ … እ… 'ሜርሲ ኪሊንግ' — ይደነግፋል ወይስ አይደነግፍም ? ይሄ ነው ! እኔ 'ተገቢ ነው ' ብዬ እከራከራለሁ ።»

«አንቺ ! ጨካኝ ነሽ ለካ » አፉን ይዞ ።

«አይደለሁም ! … አስተማሪው ተከራከሩ ብሎኝ ነው ። በል ሐሳብ ስጠኝ »

መኩት ከዮት እንደሚነሣ ግራ ተጋብቷል ። ሕሊናው ሞትን በመደገፍ የመከራከሪያ ሐሳብ ለማፍለቅ ፈጣን አልሆነም ።

ፎዚያ ትናገራለች …

«በል አትፍራ ! … ይሄኮ ትምህርት ነው ። በመጨረሻዋ የሕይወት እስትንፋስ ላይ የሚገኝ ሰው— ፈቃዱ

http://ethioliberty.wordpress.com/

ተጠይቆ ፣ እሱም ተስማምቶ ፣ በምድር ላይ ፍጻሜውን ሥቃዩን ከሚቋቋር 'ይረፍ !' ብሎ መከራከር ፣ ማሽን ከባድ የመሆኑን ያህል ... ከዚህ በተቃራኒ 'መኖር አለበት !' ብዬ መከራከር የሚያቅተኝ አይመስለኝም። ምን ይሁን ምን — ሁላችንም ሕይወት እንፈልጋለንና ! »

«ይሁንልሽ ! ... ኃጢአተኛ ልታረጊኝ ነው !»

«አቦ በቃህ ! ... ይልቅ ቀልጠፍ ብለህ ሥራ!»

መኪት በረዥሙ ተነፈሰ ። አንዳንድ ነጥቦች በወረቀቱ ላይ ሊያሰፍር ተሰናዳ ...

«እንግዲህ ስትጀምሪ ... ቆይ ! ... አንድ በሽተኛ አለ ብለን እንውሰድ ። በጣም ያማጥራል ። ሥቃይ ላይ ነው ። ሐኪሞች የሚችሉትን ያህል መርምረው ፣ አከመው ሲያበቁ ... 'ተስፋ የለውም' በማለት ደምድመዋል ። በሽተኛው በፈናው 'እባካችሁ ! ስለጭንቅ ብላችሁ ! ገላግሉኝ ! ተሠቃየሁ !' ብሎ ተማፀነ ። ቤተሰቡ '... ምን ይታወቃል ፣ ከዛሬ ነገ ይሻለው ይሆናል!' በማለት ተስፋ ቢጥልም ፣ በሽተኛው ባሰበት እንጂ ፣ አልተሻለውም ካልን ... 'ሕይወቱ ትለፍ!' ሊባል ነው ። እና መከራከሪያሽ ነጥብ ፣ ገባሽ ?! ... ሕይወቱ እንድታልፍ ቢደረግ ሕመምተኛው ለረጅም ጊዜ ከመሠቃየት ቶሎ ይገላገላል ... ቤተሰቡም እየተሳቀቀ ፣ የማይድን ሰው ከሚያስታምም— እርሙን አውጥቶ 'እፎይ!' ይላል ! ለበሽተኛው የሚያወጣውን ወጪ ይቆጥባል ...



የጤና አገልግሎት ትግር ባለበት ... ለበሽተኛው የሚሰጠው መድኃኒት ፣ የሚተኛበት አልጋ ፣ የሚያስታምሙት ነርሶች ፣ የሚያክሙት ዶክተሮች ... ለሌሎች ሕመምተኞች አገልግሎት ይሰጣሉ ... አይበቃሽም !»

«ኧረ ! በኔ ወይም ባንተ ዘመዶች ላይ ቢሆንስ ... 'ይሁን !' ብለህ ትስማማለህ ?»

[illegible] ተቃዋሚ ተከራካሪዎቿ እንዴት ሐሳቧን ቀርጸው ለማረግ እንደሚዘጋጁ የምታሰላስል ትመስላለች።

የመኪት እያት ይማራሉ ...

«መኪት ! መኪት ! ... አትንጣም ! እንቅልፋም ረፍዷል ! ... ትምህርት ቤት የለህም ?»

ፍንጥር ብሎ ከአልጋው ሲወርድ ፣

'የቤት ሥራው ... ጥያቄዎቹ ...' እህቱ እንዲታመልጠው ተማጽኗል ።

የማጥኛ ጠረጴዛው ላይ ወረቀት ሲያይ ፣ ደንጋጠው መለስ አለ ።

«እናቴ ! ... ማታ አልጋው ውስጥ ያገባኝ ማን ነው ?»

«ጥያቄህ ... ተንሥ ረፍዷል !»

http://ethioliberty.wordpress.com/

# እ ቅ ሉ ቷ

የበልግ ዝናብ እንደ ዘንድሮ ሆኖ አያውቅም ። እንዴ ከጀመረ ልጓምም የለው — ያወርደዋል ...

«ሩጪ ! ... በይ እንጂ ሩጪ ! ... የምን መቆም ነው ?» አሉ አሠልጣኙ ሐናንያ ፣ በሚወርደው ዶፍ መሐል ለመደመጥ እየጮሁ ።

ረጅሙ ሰውነታቸው ተመጣጥኖ ፣ ፍርጥም ብሎ የተገነባ ነው ። ዐሥራ ሦስት ዓመት ሙሉ እንደሮጡ ነው ። ሆኖም ሰውነታቸው ፍንክች አላለም ። ስፖርት ያሳምራል ፣ ወጣት ያደርጋል ያሰኛል ። ታዲያ ፣ የሐናንያ የደስ ደስ ጉንጮቻቸው ላይ ይፈካል ።

በቸርችል ጐዳና ሐናንያ የሚመሩት የአትሌቶች ቡድን በከፍተኛ ልምምድ ላይ ነው ። አትሌቶቹ የልዩ ልዩ ርቀት ተወዳዳሪዎች ናቸው ። ጦር ፣ ዲስከስና አሎሎ ወርዋሪዎች አሉ ። የለበሱት ቱታ — ከላይ ቀይ፥ ከሥር አረንጓዴ ስለሆን ፣ የአንድ ሰው ልጆች አስመስሏቸዋል፥ በጀርባቸው «የጊዛ ጊዎች ፋብሪካ ስፖርት ክለብ»



የሚል ይነበባል ። [illegible] —
ፍርግሙ ነው ።

... ሞራል ... ስሜት ... ውስጣዊ ሲቃ፣ተደማምረው የማያወላውል ዓላማን ሲያራምዱ፣ውሕደት ፈጥረው ሲንበገቡ ፣ ዶፍ ቀርቶ የድንጋይ ናዳ ቢወርድ ልምምዱን የሚያቋርጥ አትሌት ከመሐላቸው የሚገኝ አይመስልም ...

«ሐር ! ... ሐር እንጂ ነው የምለው! ... ሩጪ! ዓቢ! ... ተለንገሽ መሐላችን ነው » አሉ ሐናንያ በድጋሚ ፣ አንገታቸውን የጓሊዮሽ አጠማዘው ወደፊት እየሮጡ ።

ሐር ፣ ለወትሮው ከሯጮች መሐል ትንፋሿን ቀጥና የምትገኝ ነበረች ። ሶጥ ሶጥ ብላ እንደ ቀጭኔ የተመዘዘ አካሏን አታደክመውም ። ዛሬ ፣ ኋላ ቀርታ ጭራ ሆናለች ። ጥርሷን ብትነክስ ነው እንጂ ፣ ለጉልበቷ ችላው አይደለም ። መንፈሷ መረበሹ ፣ ሰውነቷ ሰላም ማጣቱ ከገጿ ይነበባል ።

« . . . የጀመሩትን መጨረስ ፣ የያዙትን ከዳር ማድረስ ...» የሚል ግትር ዕምነት ነው የያዛት ። ምን ይሁን ምን ፣ ፍጻሜውን ማየት አለባት — ዕልኸኛዋ ሐር ።

አፏን ከፍታ «እፍ ... እፍፍፍ» እያለች — አለ ከለከች ። ከባዱን ቀዝቃዛ አየር ባፍንጫዋ ፣ ባፏ ስትስበው ፣ ሳንባዋ ዝሎ ፣ ተወጠረ ። «እሁ! ... እሁ!» እያሰኘ አሳላት ።

የሐር ጸጉር እፍር አይባልም — ያጥራል ። ለማስዋብ ደንታ አትሰጠውም ። አሁን እንዳልነበር ሆኖ ርቧል። ከላይዋ የሚወርደው እንጥፍጣፊ ወደ አፏ ሳይቀር ይወርዳል ። ይህን ጠራርጋ ለመመለስ ፣ አቅም ያጣች ትመስላለች ።

ገና ከመነሻው ፣ ጥሩ መንፈስ አልያዘችም ነበር— ሐር ።

. . . አትሌቶቹ ልምምዱን የጀመሩት ፣ በአዲስ አበባ ስታዲየም ነው ። ከባቡር ጣቢያ በሚነሣው ጐዳና ሽቅብ ሲመጡ ፣ ቁድርስ አደባባይ አካባቢ ሲደርሱ ውሽንፍር ያቀላቀለ ዝናብ ይወርድባቸው ጀመር ።

አሠልጣኙ ሐናንያ ፣ በዚህ ውስጥ የምንዳንዱን አትሌት እንቅስቃሴ ልቅም አርገው እያጠኑ ነው ። የተለየ ... አዲስ መሰሉ የሚታያቸውን ነገር በሐሳባቸው መዝገበው ፣ ሳያዛንፉ በአትሌቱ ማኅደር ያሰፍራሉ ። ቀድሞ ከተጠናቀረው ጋርም በማነጻጸር ይተነትኑታል ።

ሐናንያ ወደ ኋላ ተጠግተው ሐርን ቢያስተውሉ፣ ያው ነች ። እንዲህ ሆና ፣ መልስ መሮጥ የሚያቀጣ አልመስላቸውም ። ከሩጫቸው ዝግ እያሉ ... ዝግ እያሉ ... ከሐር ጋር ተስተካከሉ ።

«ሐር ምን ሆነሻል ? ... ምን ነካሽ ? ብዙ ምሳ ነው የበላሽው ? ይኼ የመጨረሻ ልምምዳችን መሆኑን ታውቂያለሽ ፣ አይደል ? ... የሻምፒዮና ውድድር ይጠብቀናል፣



http://ethioliberty.wordpress.com/

ታዲያስ ? ... ፍጥነት የታል ? ... በይ እንጂ» አሉ ፣ ሐሩት ሌሎቹን አትሌቶች ፣ ከጐን — እያጎን እየተመለከቱ ።

ሐር መልስ እንድትሰጥ ጠበቁት ። ቆዩ ። የለም ። ከስትርትር ካለው የሐር ፊት አንዳች ነገር ጠረጠሩ ። የጤና አይደለም !

«ሐር ! በዚህ ልምምድ በደንብ ካልሠራሽ ውጤትሽ መጥፎ እንደሚሆን መገመት አለብሽ ፣ ስንት የለፋሽበት መሆኑን አትርሺ . . . እንደ ምንም ትንፋሽ ያዢና ግፊ ... ሳቢ ! አፍፍ ... ደግሞ እግርሽ ፣ እግርሽ ! ... በጥፍር ነው !»

ንግግራቸው ቁርጥ ቁርጥ ያላል ። ፊታቸውን በእጃቸው ሲጠርጉት ፣ ዝናቡ ወዲያው ያከናንባቸዋል ።

ሐር ፣ «እሺ» ብላ ለመመለስ ፣ ምላሷን ያላወሰችው በሥቃይ ነበር ።

ሐናንያ አተኩረው ተመለከቷት ። የምትሞቷን ነው — የምትሮጠው ። « ጨዋማምር መናገር አለብኝ ፣ ምሬት መቀስቀስ ነው » ሲሉ አሰቡ ። ደግሞ ሐርን የሚያሰራት ትዕዛዝ ሳይሆን ፍላጐቷ ነው ። ሁል ጊዜ በልቧ የስፖርት ፍቅር ስሜት ልምምዷን እንደምትፈጽም ያውቃሉ ።

... ሐናንያ አንድ ባሕርይ አዳብረዋል ። ይኸውም በስፖርት ሥነልቡና ዕውቀት መጠቀም ነው ። ትግትም ቢሆን ፣ ከአንድ አትሌት ስሜት ጋር የሚጣጣምበትን

ስሌት ይፈልጋሉ ። ለዚህ ነው በስፖርተኞች ዘንድ ተወዳጅነትን ያተረፉት ።

በጀርመን ዲሞክራቲክ ሪፑብሊክ የአሠልጣኝነት ትምህርት ተከታትለው ከተመለሱ ስድስት ዓመት ሊሆናቸው ነው ። በዚህ ጊዜ ካንድም ስፖርተኛ የመረረ ግጭት አልፈጠሩም ። ይልቁንም የተማሩትን ፣ ያወቁትን ዘርግፈው ለማሳወቅ የማይታክቱ ሆነዋል ። «በርቱ !... በርቺ !... በርታ !... እንዲህ ቢደረግ ጥሩ» — ይቀናቸዋል ።

ሐናንያ የሐርን ነገር እያሰላሰሉ ፣ ፍጥነት በመጨመር ወደ መሪነት ቦታቸው ተመለሱ ።

ሌሎቹ ሯጮች ደህና ይዘዋል ። የሚወርደው ዝናብ ጋብ አላለም ። ሐናንያ ፣ በአትሌቶቹ ብርቱ ዲሲፕሊን የልብ ልብ ተሰምቷቸዋል ።

... ልምምዱ ሩጫ ብቻ አይደለም ። የአካል ማጎልበቻ እንቅስቃሴ ያካትታል ። «አትሌት — ባካሉ ካልጠነከረ — ሮጦ አያሸንፍም !» ይላሉ ሐናንያ ። ስለዚህ አካሉን ለማፈርጠም ፣ የደም ዝውውሩን ለማሻሻል ፣ ትንፋሹን ለማስተካከል ... ጥብቅ ልምምድ ማድረግ አለበት ... እየተሮጠ ... እጅ ወደ ጐን መዘርጋት ፣ ወደ ላይ ማውጣት ፣ በደረት ስፋት ልክ ወደፊት መዘርጋት ፣ ማውለብለብ ፣ በፈረቃ ማሽከርከር ... ይቀጥላል ... ይቀጥላል ።



http://ethioliberty.wordpress.com/

ሐናንያ የር[illegible] ሩጫውን ብቻ ነው ። «ምን ነገር ገጥሟት ይሆን?» የሚል ጥያቄ በሐሳባቸው ተንገዋለለ ።

ልምምድ እየመሩ ቢሆንም የሐርን የኋላ ታሪክ ማሰላሰል ከጀላቸው ። «የቅርብ ችግር እንዳንዱ ሥር በሰደደ መንሥኤ ከኋላ ታሪክ ጋር ይያያዛል» የሚል ግምት ወሰደዋል ።

ለዚህ ነው ፣ ለሐናንያ ፋይዳ ያለው ነገር ያንድ አትሌት ታሪክ የሆነው ። «... ይህን ሳልገነዘብ እንዴት ማሠልጠን እችላለሁ ? ... አትሌት ለመምከር ፣ የሚጎድለውን ለማሳየት ፣ ድብቅ ችሎታውን ለማስተዋል ... የግድ ማኅደሩን ደጋግሞ ማጥናት ያስፈልገኛል » እያሉ ይከራከራሉ ።

... እና የሐር ማኅደር ትውስታ ...

... ዕድሜ — ሐያ አንድ ዓመት ። ትምህርት — ዘጠነኛን ያልጨረሰች ። ሥራ — በፋብሪካው አትሌቲክስ ቡድን ውስጥ አራት ዓመት ። ትዳር — የላትም ። ኑሮ — ከእናቷ ጋር ። የምታዘወትረው ጓደኛ — ወንድ ። ጠባይ — ዕልኸኛ ፣ የወንዶችን ሥራ ወይም ወንዶችን መምሰል የምትመርጥ ። የተለየ ገጠመኝ — በልጅነቷ ጅማ አትራቢያ ፣ ሸቤ ስትኖር ፣ ለሽርሽር በመኪና ውስጥ ስትዘዋወር ከአነር አፍ በሩጫ ያመለጠች ፣ ስንቴ ነበር? በአህያ ስትጋልብ የወደቀችው ... በትምህርት ቤት አዘው

ትራ ተደባዳቢ የነበረች . . . የአትሌቲክስ ውጤት—በአዲስ አበባ ትምህርት ቤቶች ውድድር አሸናፊ ፤ በክልሎች ውድድር በአራትና ስምንት መቶ ሜትሮች 1ኛ እና 5ኛ ደረጃ የያዘች ። ጤንነት — በጣም ጥሩ ። አጠቃላይ አስተያየት — በጣም ተስፋ የሚጣልባት ...

... ሐናንያ የሐርን መዝገብ በሐሳባቸው ሲከልሱ ፎቶ ኮፒ የማንበብ ያህል ዋና ዋና ነጥቦችን አስታወሱ ።

ታዲያ ችግሯ «... ከቤቷ የመነጨ ይሆን ? ወይስ የወጣትነት ጣጣዎችን... የስሜት መሸበር ፣ ምናልባት ...» — መላምቶች ደረደሩ ።

ሐር በምታደርገው የአትሌቲክስ እንቅስቃሴ፣ ይተማመኑባታል ። «ነገር ግን እንደ ዛሬው ድንገት የመጣ ችግር ከቀጠለስ ? . . . የኢትዮጵያ ሻምፒዮና ውጤቷ ቢበላሽስ ? ...» የሚለው ሐሳብ ከነከናቸው ።

የልምምዱን ሩጫ እየመሩ ለአትሌቶች ምልክት ሰጡና ቸርችል ጐዳናን ጨርሰው ወደ ቀኝ — ወደ ፒያሳ ታጠፉ ። ሁሉም ጥሩ ይዘዋል ። እንዲያውም «በዚህ ዶፍ ይህን ያህል በመሥራታቸው ጐብዘዋል » ብለው ደመደሙ — ሐናንያ ።

ሐር ፣ እኪሷ በሙሉ ርሷል ። ጡት መያዣዋ ፣ ስስ ካናቴራዋ ፣ የውስጥ ሱሪዋ አልቀረም ። ጥርሷን ነክሳ ፍጥነት ለመጨመር ተንገታገተች ። ከሳንባዋ ሥር አንዳች ነገር እንደሚጮር እየወጋ ፣ ቀስር ያዛት ... እያለከለከች የኤሌክትሪክ ሕንፃን ከጀርባዋ በመተው ፣ ወደ ምኒልክ



http://ethioliberty.wordpress.com/

አደባባይ ቡድኑን [illegible] ። «... ወደ ቤትሽ ብረሪ ! ሒጂ ! በዚህ ዝናብ ለምን ብለሽ ?» የሚል ሐሳብ መጣባት ።

የፒያሳ መንገደኛ ዝናቡን ፈርቶ ፣ በየሱቁና በየቡና ቤቱ ውስጥ ተጠልሎ ነው እንጂ ፣ ተረቡ የሚቻል አልነበረም ።

ሐር ከዚህ ሁሉ አምልጣለች ።

«ከዚህ ጥሬ ! ጥሬ ! ... የማትችይውን !» የሚላትን ሐሳብ በግድ ለመርሳት ከአዕምሮዋ ሙግት ገጠመች ።

ሩጫዋን እንድትብሳ ቀጠለች ። ዝናቡ እርጥብ ባቀዘቀዘው ጭኖቿ መሐል ፣ ትኩስ ሙቀት ተሰማት። ውሃው ተደባልቆ ቢያቀጥነውም ፣ ደም ነበር ።

ሐናንያ ፣ አትሌቶቹን ምኒልክ አደባባይ አቆሟቸው። ሁሉም ከዝናቡ ተጠልለው መቁነጥነጥ ያዙ ። ገሚሱ ከወገቡ እንጎብሶ እየር በመሳብ ፣ ቀና በማለት ደጋግሞ በጀርባው ተለጥጦ ሰማይ እያየ «ኡሁ ! ... ኡሁሁሁ!» እያለ ትንፋሽ ያወጣል ። ከፊሉ የጭን ጡንቻዎቹን ወጥር ፣ ባለበት ዱብ ዱብ ይላል ። ሐር ተኩራምታ ተቀምጣለች ።

ሐናንያ ምክር ሲሰጡ ፣ «አትሌት ረጅም ይሆን አጭር ርቀት ሮጦ — ወዲያው መቀመጥ የለበትም ! ይህ ከሆነ ጅማቶች ባንዴ ይረግባሉ ። ይኮማተራሉ ። ጡንቻዎች ይተሳሰራሉ ። ለአካል ደግ አይደለም » ይላሉ ።

ሐናንያ ከተሰወሩበት ቆይተው ሲመለሱ ፣

«ሐር ! … ደግሞ ቁጭ አልሽ … በይ ተነሽ ! አይዞሽ ! ቀስ እያልሽ ዱብ ፣ ዱብ ! በይ .. ምንም ችግር ቢኖር ቀስ እያሉ መንቀሳቀስ ፣ ሰውነትን ማፍታታት ያስፈልጋል … በርቺ ! ጐበዝ ! አሁን እንመለሳለን ።»

ሐር አሠልጣኟን አክብራ ፣ እንዳዟት ፈጸመች ። ድካሟ ከገፅታ በላይ ሆነባት ።

ሐናንያ ፣ አትሌቶቹን አንድ ላይ ሰበሰቡና ፣

«ልጆች ! … አውቶቡሳችን አሁን ይመጣል ! … ወደ ስታዲየም እንመለሳለን ።» አሉ ፣ ቀደም ብለው በሕዝብ ቴሌፎን ቦሌ ከሚገኘው የስፖርት ክለቡ ጽሕፈት ቤት ደውለው ያገኙትን መልስ መሠረት አድርገው።

ሰውነት ዘና ሲል ፣ የልብ ምት ሲቀንስ … መረጋጋት ሲመጣ ፣ ዝናቡን እያሰቡ ጨዋታ ያዙ — አትሌቶቹ ። ፀሐይ በጨረሯ ደመናውን መሰንጠቅ ጀምራለች ። ማባራት ሲጀምር የፒያሳ መንገደኛ መተራመሱን ተያያዘው ። የሙዚቃ ቤቶች ጩኸት ሲያስተጋባ ፣ ተከልክለው የሚደንሱ የመንገድ ልጆች ተጠራሩ ።

የአትሌቶቹ አቶቡስ ከች አለ ። ቦታ ለመያዝ እኛ ቅድምድም ሆነ ። ሐናንያ ከፊት ተቀምጠው ፣ ጉዞ ጀመሩ —ወደ ስታዲየም ።

ሲደርሱ ፣ ሐር ተንደርድራ የመጸዳጃ ቤቱን በር ዘጋች ። … የወር አበባዋ ነበር …



http://ethioliberty.wordpress.com/

ወገን የጠና ሪፖርት እንድታቀርቢልኝ ። አሉ ሐናንያ ፣ አትሌቶቹን ሲያሰናብቱ — ሐርን ፈልገው ።

* * *

[illegible] ሐር ፣ ቦሌ ክለቡ ክሊኒክ ጐራ ብላ ስለቆየች ፣ ቤት [illegible] ዐሥራ ሁለት ሰዓት ገደማ ነበር ።

ዶክተሩ የሚያስፈልገውን ምርመራ አደረጉላት ። [illegible] ላይ አባታዊ እንክብካቤ በማድረግ የታወቁ ናቸው ። ሙያቸውንና ሰብእዊ ፍጡርን ይወዳሉ ። ለስፖርተኛ ሲሆን ይብሳሉ ። በውጤቱ ፣ ሐር ምንም ችግር አልተገኘ ባትም ። ለተሰማት ትኩሳት ማስታገሻ ፣ ለብርድ መቋቋሚያ የሚረዳት እንክብል ታዞላት ወሰደች ።

ምሥራቅ ገበያ አዳራሽ በስተጀርባ ከሚገኘው መኖሪያ ቤቷ ስትደርስ ፣ እናቷ ከእንግዳ ጋር ነበሩ ። የሐርን ጥላሸት የመሰለ ፊት ሲመለከቱ ፣

«አቤት ! . . . አቤት ! አበስ ገበርኩ ! ደሞ ምን ነካብኝ ? አሁን እንዲያው ላልጠፋ ሙያ እየሮጥሽ ራስሽን ማጥፋት — ምን ይባላል ! . . . በዚህስ የሚመጣ ገንዘብ የደም ገንዘብ ነው ፣ ቢቀርም አይደላ . . . የአባትሽን ነፍሱን ይማረውና — ጡረታው ይበቃን የለ ! . . . ኧረ ተይ ስሚ !» አሉ ፣ የሚያዘወትሩትን ሮሮ ።

ውጤቸው በቅርብ ይሁን በሩቅ የሚያውቋቸውን እየ ዞሩ ማስተዛዘን ስለሆነ ፣ ነጠላቸውን እንዳዘቀዘቁ ነው ።

http://ethioliberty.wordpress.com/

«እንዴ !... ምነው ! እማዬ ! ስንት ጊዜ ነው የም ነግርሽ ! ሩጫውን ብታይው ትወጂዋለሽ ፣ ደስ ይልሻል አላልኩሽም ... ከኛ ጋር ብትሮጪማ ! ... » እናትዬው አቋረጧት ። ሐር አትም እንቧትም ቀልደኛ ሆንችባቸው። እንግዳዋ ገርሟቸዋል ።

«ቀልዱን ተይው !... የሠፈሩ ማቲ ሲሮጥ የማላይ መሰለሽ ደሞ 'ብታይው !' ትለኛለች ... ይልቅ ... አት ተዋወቂም ?» አሉ — እናት ፣ ወደመጡት እንግዳ በአን ጫቸው እያመለከቱ ።

ሐር ፈገግ ለማለት ሞከረች ። አተኩራ ተመለከተ ቻቸው ። በዕድሜ ጠና ያሉ ፣ ውፍረት ያደበለበላቸው ወይዘሮ ናቸው ። ማስታወስ አልቻለችም ።

«አይ አረሳዘም ! ... ተመዛዘች አይደል ? ደግሞ ጨዋታዋ ! ይገርማል ። አባቷን ቁርጥ ነው ። የእናንጫዋ መቅጠን ፣ የቁመቷ መርዘም ፣ ጠይምነቷ ... » አሉ፣ እን ግዳዋ — ወይዘሮ ማለቺ ።

«አዎ ?.. .እሱ ለፏ ሲሮጥ ነበር ፣ የመኪና አደጋ ጉድ ያረገው ። አሁን ያ የተገለበጠበትን የናዝሬት መን ገድ ሳስበው ፣ እንዴት ይቀፈኛል !... ይኸው ጡረታው ደህና ይዞናል ። ... ይቺም ደራቁቻ ፣ ሩጫ ሙያ ነው ብላ ፣ ቆዳዋ ከአጥንቷ ተጣብቆ ፣ ጭጊዋ ሊወጣ ነው ... አት መከር !»

«በይ አትቁሚ እቴ ... የተሸከምሺውን አስቀም ጪው» አሉ ፣ ወይዘሮ ማለቺ ፣ ከተቀመጡበት እንጋጠው



ሐሮን እየተመለከቱ ። ከትንሿ ጠረጴዛ ላይ በብርጭቆ የተሞላውን ቅራሪ ሲጉነጩ ፣ በጣታቸው ጠቆር ያለ ቸቸ ቸውን ያስተካክላሉ ።

«እትዬ !... ዕውነትዎን ነው » በማለት ፣ ሐር ጓዳ ገባች ።

ከናቷ ጋር የምትተኛበት ፣ ዐይን የማይሞላው አል ጋ ናፈቃት ። መጋደም አሰኛት ። ግን ፣ እንግዳዋን ሊትዋ አሰበችና በሸቀች ።

ከአልጋው ጐን ፣ ሰንዱቅ ፣ ሌማት ፣ ባልዲ ፣ በሀቃ፣ ስፌድ ... ተንባብረዋል ። ግድግዳው ላይ ሆድ የሚያባቡ ቀቅሶች ፣ መስታወት ፣ ፍሬማቸው የተባነተ ፎቶግራፎች ተሰቅለዋል ።

ወደ ጓዳ ድንገት ዘው ያለ ሰው ፣ «መጋዘን ነው» ማለት ይቀለዋል ።

ሐር ትጥቋን አስቀምጣ ስትመለስ ፣

«በይ ሳሚያቸው !... ያኔ ሽቤ እያለን ፣ በልጅነ ትሽ ሲጠይቁን ይመጡ ነበር ። ሁል ጊዜ ወተት የሚ ያመጡልን እትዬ ማለቺ ... አታስታውሺም ?» አሉ ፣ እናቷ ።

«አዎ ! በልጅነቷ ነው ... አሁን ትረሳኛለች» ሲሉ መለሱ ፣ ወይዘሮ ማለቺ ።

«እማዬ ! ... ብዙ ሰዎች ሲጠይቁን ፣ ወተት ያመ ጡልን ነበር ፣ አይደል ?... እንተዋናቸው ! እትዬ ጊምቢ ፣

http://ethioliberty.wordpress.com/

እሆትሽ — እትዬ ዓለም ... ደግሞ» ብላ ፣ ሌላ የናቷን ጠሆቴ ማስታወስ አቃታት ።

«እኔ ስመጣ ... ሁለት ወይም ሦስት ዓመት ይሆ ናታል ልበል ? ሕፃን ነበረች ፣ ወደ አጋር ጠጋ ከማለታ ችን በፊት ...» — ወይዘሮ ማለቺ ናቸው ።

«ትንሽ ... ትንሽ ትዝ ይላል ፣ ብቻ ...» አለች ሐር ።

«ወይ ሐር ! . . .አሁንም እንደ ልጅነትሽ ኃይለኛ ነሽ !» — ሐር አፈር አለች ።

«ኋላስ ? ባሰባት እንጂ ! 'ተማሪ !' ብላት ፣ 'አኛሬ ሬኝ !' አለች ። ዘመንኛ ሳትጨርስ 'ስፖርተኛ እሆናለሁ' ብላ ፣ መበላሸት ነው የቀራት ። ነጋ ሩጫ ነው ፣ ጠባ ሩጫ ነው ። ልጅ ፣ ለፍቶ ያሳደገውን ሰው ምክር ቢሰማ ነውር ነው !»

«ምን ይደረግ ! ... የዛሬ ልጆች 'ሁሉን እናውቃ ለን !' ባዮች ናቸው ። የሚሳሳቱ አይመስላቸውም ። ዋናው ነገር ጤንነት ነው ፣ ሁሉም ይደርሳል ! ታዲያ ለጤናሽ እንዴት ነሽ ? ...,» — ሐርን ጠየቋት ።

«በጣም ደህና ነኝ» ብላ ፣ እጉዋ ከለበሰው የእንጨት ስንዴት ላይ ተቀመጠች ። እርይታ ዝግ እያለ አበሳት ።

«ሽቢ ሐዶሽ ታውቂያለሽ ? . . .አልናፈቀሽም !» ፣ እትዬ ! እንዴት ይናፍቀኛል ? መሰለምት ! ዓዶ



ሞኛ — የልጅነት ቢሆንም ፣ ዘመዶቻችን . . . ሳይመቸኝ ቀርቶ አልሔድኩም ። ግን አልቀርም ፣ አሁን መቼስ ተለ ውጧል ?»

«አዎ ። እኔ እንኳ ብቅ አላልኩም . . . ግና መንደሩ ተለውጧል — ይባላል ... በናው ያው ለጉድ ነው ፣» አሉ ወይዘሮ ማለቺ ።

ሐር ዘመኛ ዓመቷ ድረስ የኖረችበትን ሸቢ ፣ በእ ግሬ ሕሊናዋ መዳሰስ ያዘች ። በጉም እንደ ተጋረደ ፀሐይ ቅውስታዋ ብሩህ አልነበረም ... የሠፈሯ ፣ የገጠሩ ቀዬ ፣ የገደምጀ — የእጊ ፣ የሜልቱ ፣ የአልማዝና የአደም ጨዋ ታዎች ... የአባቷ እንክኮ ! ... ቁርጥ ቁርጥ እያለ ትዝ አላት ።

«ታዲያ ኑሮ ደግ ነው !» አሉ እናት ፣ ጨዋታውን ወደ ወይዘሮ ማለቺ ለማዞር ።

« ደህና ነው . . . አሁን ንግዱን ነው የያዝነው ። እጋር አቅራቢያ የነበረውን መሬት ከሰቀቅን በኋላ ጀማ ንግዱን ጀመርኩ ። ተመስገን ! ደህና ነኝ . . .»

«በሰላም ነው የመጡት ?»

«አዎ ! ... የታናሽ እሁቴ ባለቤት 'ታሟል' ብለው ለመጠየቅ ነው ። ይሄንን ቤት በስንት ጥየቃ ነው የደረ ስኩበት ።» በማለት የሐርን አባት መሥሪያ ቤት እጠያ ይቀው ሲያገኙ ፣ ሰዎች እንዴት እንዳመሏቸው ዘርዝ ረው ተረኩ ።

http://ethioliberty.wordpress.com/

የሐር አባት የጥንት መተዳደሪያ ግብርና ነበር ። ቀጥለው መንግሥት መሥሪያ ቤት ገቡ ። በጥበቃና በመ ላላክ ሥራ ለመንግሥት አገለገሉዋል ። ጮሌ ነበሩና ፈጥነው የሹፌርነት ሙያ ያዙ ። ወደ አዲስ አበባ ዞረው አምስት ዓመት ሠርተዋል ። ሕይወታቸው ያለፈው ለመ ስክ ሥራ ወደ ሐረር ለመድረስ ፣ በምሽት ሠራተኞች አሳ ፍረው ናዝሬትን አልፈው ሲበሩ ነበር ።

ታዲያ የሐር አባት ፣ ከአንድ በላይ ልጅ አለማ ግኘታቸው መልስ ያጡለት ጥያቄ ፣ ሽላ በድፍን ሆኖባ ቸው ፣ አብሯቸው ቀረ ።

«ስንት ዓመት ሆናቸው !» — ወይዘር ማለፊ ጠየቁ።

«ሰባት ሊሞላው ነው ፣ እዶ የኒዚው መፍጠን !» አሉ የሐር እናት በለሆሳስ ፣ የባለቤታቸው ትዝታ ስለ ተቀሰቀሰ ሐሳባቸው ሸፍቶ ።

በጆሮግና ሸቢ የሚያውቋቸውን እያነሡ «እከሌ ... ያቺ እከሊት ...» እየተባባሉ ፣ ትዝታ ሲያወጉ አመሹ።

ሐር በተቀመጠችበት እንቅላፏጀች ። ቀጥላ አሸለ በች ።

«ሐር ! ሐር ! ተነሽ ፣ ተነሽ ! ሰውነትሽ ወላለቋል ። እግርሽን መሰብሰብ አቅቶሻል ... ሒጂ ጋደም በይበት» አሉ እናቷ ።

«ወይ ልጀን ! ... ተኚ እቴ ! ደክሞሻል» ሲሉ ወይ ዘር ማለፊ በማስተዛዘን ነበር ።



ሐር ዐይኗን እያሸች ፣ ተንገዳገዳ አልጋው ላይ ተን ጋለለች ።

ከምሽቱ ሦስት ሰዓት ፣ ሌት ቀርቦ ነው — የተቀሰ ቀሰችው — ሐር ። ወይዘር ማለፊ ሔደዋል ።

ሐሳቧ ወደሚጠብቃት ውድድር ተመለሰ ።

★ ★ ★

ከአምስት ቀናት በኋላ ...

ከጠዋቱ ሦስት ነው ። የአትሌቲክስ ቡድኑ አባላት ልናንያ አማካይነት ቦሌ ከሚገኘው የጊማጊጠች ፋብ የስፖርት ክለብ ተገናኝተዋል ።

የመሰብሰቢያው ክፍል ወርዱ ጠቦ ፣ ቁመቱ ይረዝ ማል ። አነስተኛው ተንቀሳቃሽ ጥቁር ሠሌዳ ቆሟል ። ልናንያ ከጐኑ ሆነው መግለጫ ይሰጣሉ ።

አትሌቶቹ በሚደላው ቀይ የላስቲክ ወንበር ላይ ተቀምጠዋል ። ዐይናቸውን ሌት ስሌት ተክለዋል ። በጥ ሞና ለማዳመጥ ጆሮአቸውን አቅንተዋል ።

« . . . ያለፈውን ልምምድ እንመለከት ። እንደም ታስታውሱት አየሩ ቀዝቃዛ ፣ ዝናቡም ኃይለኛ ነበር ። ሆኖም ብዙዎቻችሁ በርትታችሁ ሠርታችኋል ፣ ይህ የሚያስመሰግናችሁ ነው . . . »

ሐር ፈጥና ለታጨበጭብ ነበር ። የልምምድ ጫሎቹ ሲታሰባት ነው የቀሰረቻቸውን እጆቿን የመለሰችው።

«ኢ . . . አትሌት በተለያየ የአየር ሁኔታ ሥር ልምምድ ካደረገ ፣ በውድድር ወቅት ያልታሰበ የአየር ለውጥ ቢመጣበትም ባዕድ አይሆንም ! ይህን እንዳትዘንጉ ። » ሐናንያ ትንተናቸውን ቀጠሉ ። ጥቁር ሠሌዳው ላይ ጫር ጫር ያደረጉና ተመልሰው እያንዳንዱን አትሌት በእንክሮ ይቃኛሉ ።

«ልጆች ! እንደምናውቀው የኢትዮጵያ ሻምፒዮና ቀርቧል ። በሀገራችን የሚገኙ ምርጥ አትሌቶች ይሳተፉበታል ተብሎ ይታሰባል ። እኛም በሩጫችን ተዘጋጅተናል — እንላለን ። በመቶ ፣ በአራት መቶና በሺህ አምስት መቶ ጥሩ ውጤት እንጠብቃለን ። ሌሎቻችሁም ምንም አታስገኙም ማለት አይደለም ። ከበረታችሁ ያልተጠበቀ ድል ታስመዘግቡ ይሆናል . . . ማን ያውቃል !»

«ሜዳው !» አለ ፣ አንዱ አትሌት በጩኸት ።

ሐናንያ ድምፁን ተከትለው ሲዞሩ ፣ ቀሲሁን ነበር።

«አ! . . . ቀሲሁን ባለስምንት መቶ ነህ ! ጥሩ መልሰሃል ። ሜዳው ይለያል ። ይሁን እንጂ ጠንክር ያልተለማመደ ፣ ሜዳ ገብቶ የሚያመጣው ተአምር ያለ አይመስለኝም ። ሌላው ነጥብ ፣ የአካል ብቃት ዝግጅት በሥነ ልቡናዊ ዝግጅት መታገዝ አለበት ። እንዳትረሱ ! አለመፍራት ፣ 'እሸነፋለሁ !' ብሎ አለመማባት ፣ በውድድር ሰዓት ጭንቀት ማስወገድ . . . ያስፈልጋል ።»



http://ethioliberty.wordpress.com/

ጉድ እንዳትሆን አደራ ! ... እየሻም . . . መደንገጥ መሸነፍ ነው ።» እያሉ ሐናንያ ከአንድ ርዕስ ወደ ሌላው እየዞሩ ፣ መግለጫቸውን አሰሙት ። ጢማቸውን ሲላጩ ሐናንያ ፣ እንዳች ነገር ከገጻቸው ላይ እንዳትገኝ አርገው ነው ። ዕድሜያቸውን ተወራርዶ የሚገምት ፣ ስድስት ወይም ስምንት ዓመት መቀነሱ አይቀርም ።

የእድሜ ነገር ተነሥቶ ከአቻዎቻቸው ጋር ሲጨቃጨቁ ፣

«አየህ ! ለምን የምላሸልሸው ይመስልሃል ? ስለሚኮሰኩሰኝ ነው ! . . . ልጅ ጉንጩን ሲስመኝ ያስብና እንደሚሸከረው ስለሚያውቅ ቶሎ ወደ ግንባሬ ያመራል ። ትንሽ ሲያቀመትም ማሳከኩ አይጣል ነው !» ይላሉ ። ጸጉራቸውን በእጥሩ ያስከረክሙታል ። ጉንጫቸው ይወጣል ። አንዳንድ አትሌቶች ይህንኑ ካርጅው' ጸጉራቸውን ሲያሳጥሩ ፣ «ሐን ስታይል »— በሐናንያ ስታይል ነው — የምትስተካከለው ? . . . እያሉ ያሾቋቸዋል ።

«ወደ አሰላለፋችሁ ከመዞሬ በፊት ፣ በሚቀረን በስድስት ቀን የምታደርጉትን ትኩረት እንግራችኋለሁ ። 'የምግብ ነገር ሆድ ይቆርጣል' ነው ? . . .»

«አይደለም ! 'የሆድ ነገር ሆድ ይቆርጣል' ነው— የሚባለው » ማለታ የገባቸው ሐር ነች ።

http://ethioliberty.wordpress.com/

ሐናንያ እየሣቁ ፣ «ሐሮ ገብቶኛል ፣ 'የሆድ ነገር ሆድ ይቆርጣል ' — ልክ ነሽ ። ስለዚህ ልጆች ! ምግብ ላይ ጥንቃቄ ውሰዱ ። የሚሰጣችሁን የኪስ ገንዘብ እያ ብቃቃችሁ ፣ ከዚህ ካፍቴሪያ ተመገቡ ። በተለይ ለና ንተ እንዲያዘጋጁ ታዟል ። ከሀገራችን የአመጋገብ ሥርዓት በመነሣት ፣ ጉልበት የሚሰጥ ምግብ ፣ ከምን ፣ ከምን እንደምታገኙ ከ'ልምምድ መመሪያ' ጥራዝ ውስ ጥ ማንበብ ትችላላችሁ ። ያን ማጥናት ነው ። ቤታ ችሁ ብታዘጋጁ ይደገፋል . . . »

. . . በምስቱ ሌት አትሌቶች ላይ ያፈጠጡት ወን ዶቹ ነበሩ ።

«እኛ ላይ ከሚያፈጡ ፣ ብናስተምራቸው አይሻ ልም ? » አለች ፣ ከሐሮ ኋላ የተቀመጠችው አትሌት ።

«ማነሽ ? ወርቂ ነሽ ? . . . ዕውነትሽን ነው ። ከፈ ለጉ አስጠኚያቸው . . . » እያይዘውም !

«ግን እንዴ በደንብ አንብበሺዋል ? » አሉ ሐና ንያ ። ወርቂ የመሰናከል ዝላይ ሯጭ ነች ። በተንጫጫ ጨች ቁጥር ቀይ ፊቷ በርበሬ ይመስላል ።

«እሺ እንቀጥል ! . . . ይህ ሲጋራ ፣ አልኮልና አደ ንዛዥ ዕፆችን በሚመለከት . . . ምንም ንግግር አያስፈ ልገንም ። ለዓመታት የተናገርኩትን አልደግመውም ። ስፖርተኛ ከነዚህ አጥፊዎች መራቅ አለበት ። ደግሞ ከመሐላችን ሱሰኛ ያለ አይመስለኝም . . . » በማለት ለጥቂት ደቂቃዎች ጸጥ አሉ ።



እኔ ሐሮ ተጠቃቅሰው ንብሩ ወዳጄነህ ወደ ተቀ መጠበት ተመለከቱ ። የስፖርት ቁታ አይበረክትለትም። ቶሎ ይቀደድበታል ። በሌላ ሳይሆን ፣ በምኙ ውፍረቱ ነው ። «ሲስስስ ወርጫሪ ካስኔ የለም ! » እያለ ይኩራራል። እሱ ያመጣው ጠባይ በድብቅ ሲጋራ ማጤስ ሆኗል ። ጭምጭምታም ተሰምቷል ። ሐናንያ እንዶተው መዘባ ረቅ አልፈለጉም ።

«ማንም ያለ አይመስለኝም ። » ብለው ዐይናቸ ውን ወደ ንብሩ ቢጥሉ አቀረቀረ ። «ማለፊያ መግቢ ያ» አሉ በልባቸው — ሐናንያ ።

« ሌላው የንጽሕና ጉዳይ ነው ። ዘወትር ከልም ምድ መልስ ሻወር መውሰድ አለባችሁ ። አሁን አየ ሩም ጥሩ ስለሆነ ፣ ሰውነታችሁን የማይከብድ ሳሳ ያለ ልብስ መልበስ ትችላላችሁ ። ገና ለገና ዱመና አይታ ችሁ ፣ ትንሽ ቁም ሳጥን ብትመስሉ ጥጋ የለውም ። የጸጉር ፣ የጥፍር መስተካከል ጉዳይ እኔ የማስታውሳ ችሁ አይደለም ። በተለይ . . . በተለይ ፣ እግራችሁን በጣም መንከባከብና ስለ ጫማችሁ ማሰብ አለባችሁ ። 'አትሌት ምን አለው ? ' ብትባሉ »

«ጫማና እግር አለው ። » — ሐሮ ከመቅጽበት ከአፋቸው ቀለበቻቸው ።

«አዎ ! የአትሌት መመኪያ እግሩና ጫማው ነው ። የአበበ ቢቂላን ታሪክ ከወሰዳችሁ ጫማም ጥጋ የለ

http://ethioliberty.wordpress.com/

ውም— ማለት ትችላላችሁ ። ለጊዜው ሁላችንም በጣም ስለምንገርጥ ፣ ያልጠበቃችሁን ፣ የማያስጨንቃችሁን መጣ ማት አለባችሁ ። የካልሲ ነገር ፣ እንዳያስተዛዝበን እንጂ ! ... ለመሆኑ ካልሲውን በየቀኑ የማይቀይር አለ ? » — በዘዴ አለባቸውን አዩት ። ሌሎች አትሌቶች እንዲሁ ።

የአምስት ሺህ ሜትር ሯጩ አለባቸው ፣ የሚገ ሽታ ነገር መከራው ሆኗል ። ተፈጥሮበት ፣ በማግ ቀን የሚጫማውን ሲቀይርም ሽታ ይገነፍታል ። አክ ምና ነው — ያስታግሠለት ።

በፈገግታ ፣ « ሁሉም ይቀይራል ! ብሬሽ ። የተለየ ችግር ያለበትም ይታከማል ! እሺ ! »

«እሺ ! ! » አሉ — አትሌቶቹ በጩኸት ፣ ከአለባ ቸው በስተቀር — አፍሮ ።

«አ ! ሌላው ነጥብ ... የአካል ጥንካሬ ልምምድ ጉዳይ ፣ ለአራት ቀን ያህል በዚህች ባጊጋባ ጂምናዚየማ ችን ዱብ ዱብ እንላለን ። አጭር ርቀት ሯጮች ፣ ዘላ ዮች ... በፍጥነት ለመስፈንጠር የሚረዳችሁን አጥብ ቃችሁ ትሠራላችሁ ። የረጅም ርቀት ሯጮች ፣ ትንፋ ሽና ጥንካሬ ላይ እንድታተኩሩ ይደረጋል ... መቼስ መለማመጃ መሣሪያዎች ተሟልተው ባይገኙም ፣ ባለው እንሠራለን ፣ አይደል ?»

«እንሠራለን ! ! » ብለው አትሌቶቹ ሲመሁ ፣ ሐና ንያ ፈነደቁ ።



ሰበብ እየፈጠረ ከድርጊት ገሸሽ ከሚል ሰው ፣ ዓለው ለመንቀሳቀስ የሚሽቀዳደም — ሐናንያ ትዴስ ነው ። እንደ «ስሜት ልጓም » በምድር ላይ የሚጠሉት ነገር የላቸውም ። « አላሠራ የሚልህን የስሜት ልጓም በየሰህ ካልጣልክ ፣ መስማማት አንችልም » ይላሉ አዘ ውትረው ።

«የተቀረውን ትልቅ ጉዳይ ላንግጣው ። ወንዶቹ — ልጃገረድ የምታሽኮረምሙትን ፣ ሴቶችም — ጉብል የም ታማልሉትን ይመለከታል ... አትፍሩ ! ነውር ነው— ለማለት አይደለም ። አልወጣኝም ። ሁላችሁም ለአካለ መጠን ደርሳችኋልና አትከለከሉም ! ለምን ? አትበሉኝ ...ልንገራችሁ የምፈልገው ፣ የወሲብ ግንኙነት ድግግ ሞሽ በማብዛት የሰውነታችሁን አቅም እንዳታከስ ምኑ፣ እንድትጠነቀቁ ነው ። ከዚህ በላይ ልጨምር ? ... አልጨምርም ! » ።

ሴቶቹ በፍረው አጐንበሱ ። ወንዶቹ ተሟሟቁ ። ከፊት የተቀመጠው ዓለሙ እንዶ እግሩን እየበረገደ ፣ ቀጥሎ እያንባበረ ይንከተከት ነበር ።

«እና ... አሁን ዕረፍት ነው ... ከዐሥራ አም ስት ደቂቃ በኋላ እንገናኛለን ። »

ስብሰባው ተበተነ ።

ሐናንያ ወደ ካፌቴሪያ አምርተው ፣ ቡና አዘዙ ። ዕድሜያቸው እየገፋ ሲሔድ ለመንቃንቃት ያላቸው እግ

http://ethioliberty.wordpress.com/

ፊጭ ይኸው ሆኖ አገኙት ። ሒሳብና ማተከር ሲያበዙ እንጂ ፣ ቀኑን ሙሉ ቡና ሲያማስሉ አይውሉም ።

ሐር ፣ የማንጐ ጭማቂ ይዛ ፣ ከንዱ ወንበር ላይ ዐረፍ አለች ። ወርቁ ፣ ገብሩ . . . ሌሎችም ተከተሏት ።

« አሳይሻለሁ ! » አለ ገብሩ — ዐይኑን ጕልጕሎ ጥርሱን እያፋጨ — ወደ ወርቁ በመመልከት ።

« ምን ትሆን ? ታውቆብሃል ! »

«እንቺ ነሽ የነገርሻቸው ፣ »

« አይ ! . . . ዕውነት አውቀውብሃል ። » ሐር ማለት ገባች ።

« ይቺ መልቲ ነች ያሳበቀችው ፣ ሌላ ማን ይናገራል ! » ብሎ ገብሩ ፣ ከጠረጴዛው ሥር እጁን ለቡጢ ወጥሮ ፣ ወርቁ ጭን ላይ አሳረፈው ።

«ሺሬ በናትህ ! . . . ሐር ! ገደለኝኮ ። እኔ መች ነው — የተናገርኩት ? . . . ወይኔ እግሬ አለተረፈም . . » እያለች ፣ ፊቷን ኩሶ አስመስላ ጭኗን ታሻሻለች ። ቀጥላ ፣ « ሒድ ፋብህን ፈልግ ፣ ልትሰብረኝ ነው ! » አለች ወርቁ ።

« በቃ ተይው ! . . . ዘንድሮ የሚሰክስ ሬኮርድ ለመ ሰበር እየተለማመደብሽ ነው ! ምንቺ እግር ለሱ ግር መሆኑን አጣሽው ! » አለች ፣ ሐር በቀልድ ።

«ብሬሽ ! ሐር . . . ታያለሽ ፊቷን ? ለድመታችን የምንገዛውን ሳንባ — ቁርጥ ነው ! » ሲል ገብሩ — ሁሉም



ተሣሣቁ ። ቀጥለው . . . እንዲ ስለ ልዑል ፋሲሊ ፣ ሐዲሱ ስለ ውድድሩ . . . አወሩ ። ሰዓት ሲደርስ ወደ መሰብ ሰቢያው ክፍል ተመለሱ ።

«እሺ . . . ሁላችሁም መጥታችኋል ? የቀረ አለ ? » ጠየቁ ፣ ገለጥ ብለው ክፍሉን ቃኙት — ሐናንያ ። ከቦርሳቸው ልዩ ልዩ ማስታወሻዎች አውጡና ከጠረጴዛው ላይ አኖሩት ። ገለጥ ፣ ገለጥ አድርገው ቀና አሉ ።

«ጥሩ . . . አሁን ስለ አሰላለፍ እንቀጥላለን ። ምድቡን ያዘጋጀሁት ፣ ከወር በፊት ባደረግነው የዝግጅት ውድድር ላይ በመመሥረት ነው ውጤታችሁን ታስታውሳላችሁ ። ሆኖም ከዚያ በመንደርደር አንዳንድ ለውጦች አድርጌአለሁ . . . ተቃውሞ በመጨረሻ ! » ሐናንያ ፈገግ ሲሉ ፣ አትሌቶቹ ተሣሣቁ ።

«ወንዶች — መቶ ሜትር — ወዲሳ ከማ ! » — ከተቀመጠበት ተነሣ ።

« እሺ . . . ቁጭ በል ። ድክመትና ጥንካሬያች ሁን በግልጽ እንነጋገራለን ። እኛ ባንድ ክለብ ጥላ ሥር ነን ! አትዘንጉ ። ድክመት ማውጣት ማለት ‘ታረሙ!’ ማለት ነው ። ከዚህ ውጭ እርስ በርስ መተራረብ ፋይዳ የለውም . . . ተግባባን ? »

«ተግባባን !» ሲሉ ፣ በጩኸት መለሱ ።

http://ethioliberty.wordpress.com/

«ወዩሳ ! አትቸኩል ! እርግጥ ነው መቶ ሜትር አጭር ስለሆነች ፣ ቶሎ ለመጨረስ ታጓጓለች ። ሆኖም ጅማሬህ ላይ ቸኩለህ ፣ ሳይፈቀድ መስመሩን ካለፍክ ፣ መቶ ሜትር ለመሮጥ የታጨኸው ጭራሽን እንደ ሜትር ሳትሮጥ ትባረራለህ ...»

... ግቅ ... በግቅ ... ወዩሳ በተዋና ያለም ግል ።

« ስለዚህ ... ተዘጋጅ — በቦታህ — ተኩስ ... እስከትሰማ ድረስ ስሜትህን መቆጣ ነው ... ከዚያ ጥቅልል እርገው ። ጥናው ፣ ስሜትህን ተቆጣጥረህ በም ታደርገው ድርጊት ላይ ማተኩር ነው ...» እያሉ ሲያ ስረዱት ፣ በሙሉ የሰውነት ንቅናቄ እያሳዩት ነበር ።

ሐናንያ በቅደም ተከተል ዕጩ ተሰላፊዎችን እየ ጠሩ ፣ ጉድለታቸውን እንዲያርሙ አሳሰቧቸው ።

ሐር ፣ በስምንት መቶ ሜትር ላይ ብትጠብቅ እል ተጠራችም ። በ፬ ምቅክ ምስተኛዋ አትሌት ጽዮን መታፈሪያ ነች የተመደበችው ። ሐር ፣ በዚያ የመጨረሻ ልምምድ መድከሟን አስባ '...ከውድድሩ ሊሠርዙኝ ይሆን ? ... ለፍቶ መና ?'— የሚል ጥያቄ መጣባት ።

ሐናንያ ፣ ውሳኔ ላይ ጥብቅ ናቸው ። መስሎ ካለ ታያቸው መወላወል አያውቁም ። ሐር «ጉድ ሊሠሩኝ ነው ! » ስትል — ልቧ ይያልቃል ... ሲከንድ ...



ደቂቃ ... ሐናንያ ሯጮችን ዘርዝረው ጨረሱ ። ወደ ዘላዮች ሊያመሩ ሆነ ።

«ቆይ እስቲ ! ...» ብለው ፣ ማስታወሻቸውን ወደ ኋላ አገላበጡት ።

«ቆይ ቆይ ! ... የአሰላለፍ ለውጥ ስለ ተደረገ ነው ፣ ከወዲሁ ያሠፈርኩት ። ሴቶች — ሺህ አምስት መቶ ሜትር — ሐር ጀቢር ። »

ሐር በመጠራቷ ደስ አላት ። አዲስ ምድብ ስለተ ሰጣት ደግሞ ግር ተሰኘች ። ከስምንት መቶ ሜትር በላይ ተወዳድራ አታውቅም ።

«አዎ ! ... በሺህ አምስት መቶ እንድትሳተፊ ተደርጓል ። ይህ መካከለኛ ርቀት ስለሆነ መዝለቅ የም ትችይ ይመስለኛል ። ተምዘግዛጊ እግርሽን ታውቂዋ ለሽ ። አሁን መጨመር የሚያስፈልግሽ — ትንፋሽ ነው ። በተረፈ በሩጫ የመቆየት ችሎታሽ የሚናቅ አይ ደለም ። አይዞሽ ! አትደንግጪ ! እኔም በወሰን ብዙ አስቢበታለሁ ...»

አበረታቷት ።

መልሳ መጠየቅ ፈለገች « የማልችለው ውስጥ ከመግባት ! » — በሚል መንፈስ ። የሆነ ነገር ያዛት ፣ ቢሆንስ ምናለበት ፣ እሰለፋለሁ !» — በሚል ... አት ግግች ።

ሐናንያ ወደ ዘላዮች ተመለሱ ። ዲስከስ ወርዋ ሪው ንብሩም ተወርጇል ።

http://ethioliberty.wordpress.com/

«ተቃውሞ አለ ? » ሲሉ ጠየቁ— ሐናንያ በመጨረሻ ።

ወርቂ የሚከነክናትን ጉዳይ ለመጠየቅ ፣ ጨልሌ ያየ ዶሮ ይመስል በዐይኗ ተቅለበለበች ። « ሴቶች ከወንዶች እኩል የሩጫ ጥንካሬ የላቸውም ። » የሚለው የታላቅ ወንድሟ አስተያየት ስለሚረብሻት ፣ መልስ ፈልጋ ነበር ።

«ምንም የተለየ ሐሳብ ከሌለ ይሆንኑ አብላለሁ ። ለማጠቃለያው ከነገ ወዲያ እንመለከተዋለን » በማለት ሐናንያ ወደ ስብሰባው መዝጊያ ተቃረቡ ። አትሌቶቹን ከማሰናበታቸው በፊት ፣

«ማሸነፍ የማነው ? » ሲሉ ጮክ ብለው ጠየቁ ፤

« የኛ!

የኛ!

የኛ ! ... » በማለት በጩኸት መለሱ ። የያንዳንዱ ፊት ያበራል ። ወርቂም «ቆይ እጠይቃለሁ ... እይቀር ! » አለች በልቧ ... ኸር ጉድ የተባለለት ውድድር ደረሰ ...

★ ★ ★

የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ሻምፒዮና ፍጻሜ የዋለው እሁድ ቀን ነበር ። አራት ሰዓት ላይ ፍንትው ብሎ የወጣችው ፀሐይ ፣ ለበዓሉ የተፈጥሮ ድምቀት ሆና ተቃለታለች ።



የማጣሪያ ውድድሮች ለአንድ ሳምንት ተከናውነዋል ። ለፍጻሜው ያለፉት አትሌቶች በቀለማት ያሸበረቁ ካናቴራና ቁምጣ ታጥቀው ውር ውር ሲሉ ፣ በመስከረም ፀሐይ መስክ ላይ የሚፈነድቁ ቢራቢሮዎች ይመስላሉ ።

የአትሌቲክስ ውድድር ፣ ዓይነቱ ብዙ ነው ። ሩጫ ፣ የከፍታና የምርኩዝ ዝላይ ፣ አሎሎ ፣ ዲስከስና ጦር ውርወራን በማካተት ሌሎችንም ይጨምራል ። የኒህ ተወዳዳሪዎች ፤ ብሩህ ተስፋ ይዘው ሰውነታቸውን ለማሟሟቅ ሮጥ ሮጥ ፣ ዘለል ዘለል ፣ ቁጭ ብድግ ፣ ሔድ መለስ ... ሲሉ ያስቀናሉ ። የማሸነፍ ስሜት በሕሊናቸው ያቃጭላል ። የውድድር 'ፍትወት' ያንጠራራቸዋል ።

የአዲስ አበባ ስታዲየም በተመልካች ተጣበበ ። ካታንጋ ፣ ምስማር ተራ ፣ ጥላ ፎቅ ... ጠጠር ቢወረወር መውደቂያ የለውም ... ነጭ ከፊያ ፣ ሰማያዊ ሸሚዝ ፣ ቡና ጃኬት ፣ «ጂንስ» ሱሪ ፣ ዥንጉርጉር ልብስ ... ድንቅ ቅብር ሠርተው አያሰለቹም ።

በሜዳው የሚተመው ባንድ የሚያሰማው ማርሽ ፣ ልብ ይነካል ። ተመልካቹ የውድድሩን መጀመር ከቶ ናፍቋል ። የባንዱ መሪ ዱላውን (ኩማውን) በደረሰበት ቅስር ! ነቅነቅ ! ሽከርከር ! ቅብልብል ! ውርውር ! ለቀም ! ሲያረገው ፣ ደማቅ ጭብጨባ ይዘንብለታል ።

ቀጥሎ «አትሌቲክስ» በሚል ርዕስ ስለ ሐተታ በድምፅ ማጉያ ተነበበ ። መግለጫው ፣ የአትሌቲክስን

http://ethioliberty.wordpress.com/

ጥንታዊነትና የሰው የዕለት ተዕለት ተግባርነት ይዘረ ዝራል ። ኢትሌቲክስ ከክርስቶስ ልደት በፊት በ፯፻፸፯ ዓመት መታወቁን ጠቁሞ ፣ ከሰው ልጅ ሥልጣኔ ጐን ለጐን ዳብሮ መምጣቱን ያመለክታል ።

ከሲታዲየሙ እንደ ገደል ማሚቶ የሚያስተጋባው ድምፅ ፣ ባካባቢው ጭምር ይሰማል ።

ሐር ዓይኗን መሰላት ። በማጣሪያው ውድድር ሁለተኛ የወጣችበትን 79 ቁጥር ከናቴራ አጥልቃለች ። መደቡ ሰማያዊ ሆኖ ፣ ቁጥሩን ያዘለው ነጭ ጨርቅ ፣ የብሔራዊ ሎተሪን ዓርማ ይዟል ።

ጠዋት ከቤት ስትወጣ ፣ ከናቷ ጋር አንድ ፣ አንድ ተባብለዋል ።

እናቷ ሁለት ሰዓት ላይ ከቤተ ክርስቲያን ሲመለሱ ፣

«ደሞ ወዴት ነው ? ... በሰንበት ?»

«ምነው ! እማዬ ! ነግሬሽ ! ዛሬ የሻምፒዮና ውድድር ነው ።»

«እንዲያው የማያልቅ ሻምፒዮና ! በዚህ ሰሞንማ እቤት የማያስቀምጥ ቀምበሻል መሰለኝ—መዞር ነው ! »

«እማዬ ! በይ እንሒድ? ዛሬ የግድ መገኘት አለብሽ! »

«ተይኝ ወዲያ ! ... እንዲያው ዝም ብለሽ ፣ ልጆች ለማየት ተከተይኝ ትይኛለሽ»



«ዕውነት ... ዕውነት ! እማዬ—ዛሬ የመጨረሻችን ነው ። መሔድ አለብሽ ። ዐሥሬ ከምትወቅሺኝ ፣ ዛሬ አብረን እንሒድና ምን እንደምሠራ ተመልከቺ ! »

«ምን አይሻለሁ ! ... አሁን እዚህ ታች ለቅሶ አለብኝ... መሔዴ ነው » ብለው እናት ጥቁር ጥለት ያለው ነጠላ ፍለጋ ወደ ጓዳ ገቡ ።

ሐር እመር ብላ ተከተለቻቸው !

«እማዬ የዛሬን ብቻ? በወለዱሽ ! ሁለተኛ አላስቸግርሽም ፣ የዛሬን ብቻ ? እይው ! ሌሎቹ ዘመዶቻቸውን ፣ ጓደኞቻቸውን ይዘው ይሔዳሉ ፣ እኔስ ? ... እማዬ ! አንቺ ካለሽ ግን ደስ አይለኝም ?» ድንገተኛ ሲቃ ሲተናንቃት ፣ ዐይኖቿ ረጠቡ ።

እናት ፣ የማይጋፉት ስሜት መታቸው ።

ለደቂቃዎች ዐይኗን አይተው ሲያበቁ ፣

« ይሁን እስቲ ! ... እሺ !» ብለው ፣ ጃንጥላቸውን ይዘው አብረው ወጡ ። ስታዲየም ሲደርሱ ፣ ሐር ወደ ሜዳ ከማምራቷ በፊት እናቷን አንደኛ ማዕረግ አስቀመጠቻቸው— በተሰጣት የጥሪ ወረቀት ።

ከድምፅ ማጉያው የሚወጣው መዚቃ ጋብ አለ ። «በዘመናችን ፣ ኢትዮጵያ ለአትሌቲክስ ፣ አትሌቲክስም ለኢትዮጵያ መሆኑን አረጋግጧል ...» ሲል አንቀጹን የከፈተው ሐተታ ፣ ስለ ኢትዮጵያ አትሌቲክስ ሲዘግብ ነበር ።

http://ethioliberty.wordpress.com/

«... ከ፲፱፻ እስከ ፲፱፻፰ ባለው ጊዜ ዘመናዊ አት ሌቲክስ ሀገራችን ገብቷል ። እልፍ እልፍ በአንዳንድ ትምህርት ቤቶች ተዘውትሯል ... » እያለ ጥንቱ አመ... ጡን ዘረዘረ ።

«... ኢትዮጵያ ለመጀመሪያ ጊዜ ሜልቦርን ... በ፲፱፻፵፰ ኦሊምፒክ ስትካፈል አትሌቶች አሠልፋለች ። በማያያዝ «የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ወርቃማ ዘመን በአበበ ቢቂላ ተከፈተ . . . » በማለት በ፲፱፻፶... የሮም ኦሎምፒክ ፣ በማራቶን አበበ የፈጸመውን ገድል አተተ ። ይኸው በቶኪዮ ተደገሞ ማሸብረቁን አስ... ወሰ ። በሜክሲኮም ማሞ ወልዴ ድል በማግኘቱ ፣ ኢት... ዮጵያ ለሦስት ተከታታይ ጊዜያት የኦሎምፒክ ማራቶን አሸናፊ ብቸኛ ሀገር መሆኗን ገለጠ ።

የሉተታው ጽሑፋዊ ቅንብር ብቻ ሳይሆን ፣ በ... ምፅ የሚያነበው ተመስጦ በመሆኑ ለጆሮ አይሰለችም... ድምፁን ከፍ ... ዝቅ ... ፈጠን ... ዝግ— ባለሩ በዜማ ቅላጼ ሲያንቆረቁረው ፣ ስሜት ይኮረኩራል ። መንፈ... ይማርካል ።

አንጋፋ አትሌቶችን አስታውሶ ፣ ከነጠመዋቸው... እየቀነጠበ ዘረዘራቸው ። ባንዲራም ያንጋፋዎቹን ፋ... ተከትለው ኢትዮጵያን ለመዳል ያበቁ ዐዋቂና ወጣት አትሌቶችን በየተራ አነሣቸው ። ያለም ጋዜጦች ቢ... ግራቸው « የደጋ በራሪዎች . . . የአትሌት ኮማንዶች ... አረንጓዴው ጎርፍ» እያሉ ኢትዮጵያውያን አትሌቶች...



እንደሚጠሩ ጠቅሷል . . . በማጠቃለያው ፣ «ከዚህስ በላይ እንግን ይወጡ ይሆን? የከዋክብት አትሌቶች ምንጭ ከሆነችው ሀገራችን ?!» ሲል ጠይቋል ።

ውድድሮች በየፈርጁ ቀጠሉ ። የመቶ ሜትር ፣ የሺሩት መቶ ሜትር ፣ የዱላ ቅብብል ሩጫ . . . ሜዳው መሐል የአሎሎ ፣ የዲስከስ ... ውርወራዎች ይታያሉ ። በጥምና ይዘነብ ጠርዝ ፣ የአግድሞሽና የከፍታ ዝላይ ይካሄዳል ።

ሐር ለውድድሩ ሲያሻች ድጋፍ ስትሰጥ ፣ ወዲያ ወዲህ እያለች ስትጮህ ፣ የራሷን ውድድር የረሳች ትመስል ለች ።

ቀድቶ ድምፅ ማጉያው ፣

«. . . የ፲ሺ አምስት መቶ ሜትር ሴቶች ተወዳዳሪ ዎች ! ... ቦታችሁን ያዙ ! » ብሎ ለፈፈ ።

ሐር ሆዷዋ ተንቦጫቦጨ ። ልቧም ደነገጠ ። ሰው ነቷ ቀለላት ። እንደ ምንም ትኩረቷን ወደ ውድድሩ ሰበሰበች ። እኪ.ያን በፍጥነት እንቀሳቅሳ ሙቀት አገኘች ። ድንጋጤዋ ቀስ እያለ ተነነ ።

«ሐር !... ሐር ! ያው ነው ! ተአምር ማሳየት አለ ብሽ ... ሐር ብሬቭ ! » እያለ ገብሩ ሲጮህ ፣ እነ አለባ ቸው ፣ ወርቁ ... ድምፃቸውን ከፍ አርገው አጀቡት ።

«ሐር ! ... ሐር !... » በጩኸት ።

እናቷ የልጆቻቸው ስም ሲጠራ ፣ እንጀታቸው አለ ቅጥ አለ ። ባር ባር አላቸው ። ሩት ብትሆንም ፣ በቁምጣ

ሱሪዋ ሲያዩዋት እንደ ማሽላ አገዳ የምትሰበር መ
ላቸው ፡ ባሉበት ተቁነጠነጡ ።

ሐሮ ፡ ውድድር መጀመሪያው ስፍራ ቀረበች ።
ብቻ አንድ የሆነ ነገር ቅር አላት ። መንፈሷ አመነታ ፡
እንዲያው ... ቅር ... ቅር ... ልታስላስለው ስትል ፡

«መስመር ያዙ ! ... ተዘጋጁ !... በቦታችሁ !...»
እያለ የሚያጋፍረው ፡ የቀናው ዳኛ ረዳት ፡ ውትወታ
አቋረጣት ... ስትለማመድ ይሁን ስትወዳደር የማይ
ርቃት ፡ የሐናንያ ድምፅ ነበር ቅር ፡ ቅር ያላት ።
ተኩስ!

የመጀመሪያ ዙር ነው ። ከስምንቱ ተወዳዳሪዎች
ጋር ተደባልቃ ከመሐል ሆነች ። ትንፋሽዋን ዋጥ አር
ጋለች ። እየሩም ቀላል ነበር— አላስቸገራትም ... ብቻ
ቅር ቅር ያላት ከነከናት ... ሁሉም ይሮጣሉ ።

ሁለተኛው ዙር ሲጀመር ወደ ኋላ ቀረች ። ሌሎ
ቀደሙ ። ፍጥነት የጨመሩ ይመስላል ። እጅብ ብለው
ሲከታተሉ አንዱ ሌላውን አለመጥለፉ ያስገርማል ፡
«ሐሮ! ሩጪ !... ተእምር ... » እየተቆራረጠ ይሰ
ማታል— የገብሩ ድምፅ ።

ሦስተኛው ዙር ላይ ወደ መሐል ሆነች ። ቀደ
መው ቁስ ቁስ ያሉት ከኋላዋ ቀሩ ። ሐሮ ትንፋሿን
ቆጥባለችና ፡ « አሁን በትንፋሽ መጠቀሚያ ጊዜ ነው»
የሚል ሐሳብ መጣባት ። ሰውነቷ ደህና ይታዘዝላታል ...



http://ethioliberty.wordpress.com/

... አትሌቶቹ ሲጀምሩ በነበሩበት አይደሉም ፡
ሩቅ ሩቅ ብለው ይከታተላሉ ። ፊታቸው ተኮሳትሯል ።
የተገተሩ ደም ሥሮች ወርደውበታል ።

... ሐሮ ፡ ያ ቅር ያላት ነገር ... ይረብሻታል ።

ውድድሩን በመምራት ላይ ያለችው አትሌት አራ
ተኛውን ዙር ስትጀምር ደወል ተደወለ ። አጠር ቢልም
የመጨረሻው ዙር መሆኑ ነው ። ደወሉ— ሦስት መቶ
ሜትር ይቀራል— የሚል ማስጠንቀቂያ ነው ።

የሐሮ ቦታ ተለወጠ ። ሁለት አትሌቶች ብቻ
ናቸው ከኋላዋ የቀሩት ። ሌሎቹ እየተፈተለኩ ቀደሟት...

«ሐሮ!..., ሐሮ !... በይ ፡ በይ ሩጪ! ሳቢ! በመ
ጨረሻ ኃይል ግፊ!.. ሐሮ ወደፊት! »

ሐሮ በጣም ፡ በጣም የምታውቀው !:ድምፅ ሆነባት ።
እየተርገበገበ በጆሮዋ ሲገባ ፡ በሰውነቷ ውስጥ ይህ
ነው— የማትለው ጉልበት ፈጠረባት ። ያላሰበችው ኃይል
ቅልጥሟን እያነሣ ያፈናጥረው ጀመር ! ጨፍጋጎት የነ
በረው መንፈስ ተገፈፈ ፡ ቅር ቅር ያላት ስሜት ምት
ሀት የሰለበው ይመስል ጠፋ ... ከፊቷ የነበሩትን
ቀደመቻቸው ።

ለውድድሩ ፍጻሜ መቶ ሜትር ሲቀራት ፡ መም
ራት ያዘች ። ያ በጣም የምታውቀው ድምፅ አልጠፋ
ባትም ።

«ሐሮ ! ሰዓት ... ለሰዓት ነው ! ሐጂ ሰዓት ! »
ድምፁ ይከተላታል ።

እነ ወርቁ ፣ ንብሩ ፣ አሰፋቸው … ይጠሟሉ ! እትሰማቸውም ። ብቻ ያ ሞራሏን የሚያደንድን ፣ ብርታት የሚለግስ ድምፅ ጉልበት ሆኗት ተምዘገዘገች ።

«ወይኔ ልጄን አሁን እንዲህ ሮጣ ትተርፋለች ፣ ምንስ ሰው ትሆናለች? … ወይኔ ልጄን ! አምላኬ! አደራህን!» እናቷ ብቻቸውን ያማትባሉ ።

ሐር ትሮጣለች … ትሮጣለች … ወዲያው ያ የሚያበረታታት ድምፅ «ተአምር ! ተአምር ነው !» አለ ፣ በለሆሳስ ።

ሐር የፍጻሜውን ገመድ በጥስ እንደ ገባች ፣ ተተመልምላ ተዘረረች ። እናቷ «ወይኔ ልጄን ! ጉድ አረገሽኝ ! ባደባባይ ጉድ አረገሽኝ ! » ደረታቸውን ይደቃሉ ። ከተቀመጡበት ተነሥተዋል ። ከተመልካቹ እየተጋፉ ደረጃውን መውረድ ያዙ ። ቆም እያሉ የሐርን ሁኔታ ተንጠራርተው ይመለከታሉ ። ግምት የሰጣቸው የለም ። ሁሉም በቆመበት አንገቱን አዞር የሚመለከተው ፣ የወደቀችውን አትሌት ነው ።

… ሐናንያ ተንደርድረው ሐር ላይ ወደቁበት ። ደንግጠዋል ። ልባቸው ይመታል ። ትንፋሽ አጥሯቸዋል ። መንፈሳቸው ተሠውሯል …

እንዷት ። ሐር ተዝለፍልፋ ቆመች ። ውጤት ወደሚመዘገብበት ሰዓት ከሚያዘው ዳኛ ጋር ሲሔዱ ፣ ሐናንያና ሐር ተቃቅፈዋል ። የሁለቱም ፊት በዕንባ ርሷል … የሚያንፍቅ ሲቃ ከውስጣቸው ይፈነዳል …



http://ethioliberty.wordpress.com/

«ተመስገን!… [illegible] አለ [illegible] በነጠላቸው ጫፍ ዐይናቸውን እያበሱ ።

ሐር በ 4 ደቂቃ 07.31 ሴኮንድ የኢትዮጵያን ክብረወሰን በሴቶች መያዟን ያወቀው ሰዓት ቆጣሪው ነበር … ከሁለት ዓመት በኋላ በዓለም አትሌቲክስ ሻምፒዮና አንደኛ መውጣቷን ያለመ ግን አልነበረም . . .

አትሌቷ . . .

# እምርት

«ኧረ እንዴት ነው ? ምንድነው ነገሩ ? . . . የሚቀመስም የለ ?» አሉ ጡረተኛው ደግፌ ፣ እፍንጫ በር ከሚገኘው ቤታቸው ሲገቡ ።

«ምን ጠፍቶ . . . በጡረታ ገንዘብ ቸልቷል !» — እፋቸውን ጠመም አርገው ባለቤታቸው መለሱ ። አንዴ የሚፈትሉትን ባዘቶ ጥጥ ፣ ቀጥለው ደግፌን ይመለከታሉ ።

«ቆርጥማት ተንጣብኝ መሰለኝ ! ይጎተጉተኛል !»

«ከወዴት ነው ? . . . ከሥራ ? » — በፈዝ ።

«እንቺ ደሞ ! ማሽሟጠጥ ብቻ ነው የምታውቂው . . . እስቲ የሚላስ የሚቀመሰውን ወዲህ በይ !»

ባለቤታቸው የያዙትን እንዝርት ፣ ሊቃቂት ከሞላው አገልግል ውስጥ አስቀምጠው ፣ ወደ ማድቤት ወጡ ። ሲራመዱ የአበሻ ልብሳቸው ተንዘረፈፈ ።

«እስቲ እሳት ካለ ? . . . በሥራ ላይ ለዋለ ሰው መቼስ ምግብ ያስፈልገዋል!» አሉ ፣ ደፋን ተረማምደው ።



http://ethioliberty.wordpress.com/

ደግፌ — ጀማሪ ጡረተኛ ናቸው ። ባለቤታቸው ግን በዚህ ሁኔታ አልተስማሙም ። በነገር መሻል ጣል እያረጉ « ሥራ ፈልገው ወጣ ፣ ወጣ ይበሉ 'ይ » በማለት ይናገሯቸዋል ። በቀልደም ወጋ ያረጓቸዋል — ደግፌን ።

ደግፌ በፊናቸው ፣ « ቀ መከንንት ! . . . ከዚህ ሌላ የሰው ልጅ ጠላት — ምን አለ ? » እያሉ ፣ የልጅ ዕድል በምን ምክንያት እንዳጡ ለማወቅ ያሰላስላሉ ።

ሲመልሱ ባለቤታቸው !

«እሱን ይተዉት ! . . . አሁን እንደነ አቶ ከብረት ፣ እያ ተርፈሳ . . . በየመንገዱ ተጣትረው ወሬ እያወሩ ፣ ከቆሎ ኛጭ እየተጫወቱ ፣ ከዕብዱ እየተላከፉ መዋል ያስባሉ ? እሊያስ ፣ በየሆቴሉ ደጃፍ ጫማ እያስጠረጉ ወዲ ወሬጀን በመቀላወጥ ሊዘልቁት ነው ? . . . ወንድ አንድ ነገር ይጨብጣል 'ይ ! . . . ወዲያልኝ ፣ ወዲያ !» ይላሉ ።

'ዉትጫቂ !' በልባቸው ።

«ከሰሉም ተወደደ አሁንስ ! . . . የጡረታ ገንዘብ የሚችለው አይመስልም ! . . . » ባለቤታቸው ፣ ከማድ ቤት ሲመለሱ ፣ ማንደጃውን እያቀረቡ ተናገሩ ።

« እንግዲህ ጀመርሽ ! . . . ይልቅ የሚበላውን ወዲህ በይ ! . . . ቆይ አሳይሻለሁ ፣ እኔ ደግፌ እይደለሁም !»

http://ethioliberty.wordpress.com/

«እይ ‘ጉድ! . . . ተከራ ብቻ ! »

ባለቤትየዋ ከሰሱን እያይዘው ወረሱ ። አንድ ሬስ ቨንኩርት ከትፈው ፣ በብረት ድስቱ ዘይት ጣብ አር ገው — ማቁላላት ያዙ ። ኸር ያፈላሉ ። ማገፈግ ቅመም መጥነው ይጨምራሉ ።

. . . ያቺን ጠባብ ክፍል እጅ የሚያስቆረጥም ኸር መጥ አወዳት . . . ደግፌ ገርሚቸው ‘ይቺ ቤት! መቼ ይሆን ሙያው የሚጠፋት ?’— አሉ በልባቸው ። መል ሰው ጉሮሯቸውን በምራቃቸው ያርሳሉ ።

«አልደረሰም እንዴ ? . . . እዚህ ቤት የተራበን ሰው የሚያውቅ የለም ማለት ነው ? . . . ሰንቱም በሥራ አንድ ሊሆን ነው . . . »

«ደርሷል ! . . . እስከዚያ ጋደም ይበሉ ‘ይ ! »

«የለም ! ወስፋቴ ተላወሰኮ ብለው ፣ ምራቃቸ ውን ሲውጡ ፣ ጨኸቱ ይሰማል ። «እንኳን ዘንቦብኝ ፣ እንዲሁም . . . » እንዲሉ ፣ ራብ ተጨምሮ ፣ የደግፌ አምሮት ከቶኖ ተቀሰቀሰ ። የስሜት ሕዋሳቶቻቸው ቅጽ በታዊ ግሬቶችን ወደ ሰውነታቸው ውስጥ አስተላለፉ ።

ደግፌ አንዳንዴ ስሜታቸውን መቆጣጠር አይችሉም . . . ራብ ጀምሯቸው ምግብ ካዩ ፣ አፋቸው ደርቆ ቢኖ ይሁን ቤራ ውልብ ካላቸው ፣ አለና ቢሉ የምግብ ሽታ ከተሰማቸው . . . ስሜቱ እንጉላቸው ላይ ይወጣል ። መንፈሳቸው ይረበሻል ። ትኩረታቸው ይበ ተናል ።



«መጣሁ ! ይንተከተክ . . . ቃሪያ ላምጣ » ብለው ፣ ባለቤታቸው ወደ ጓድ ቤት አመሩ ።

ደግፌ ጠበቁ ። ታግሡ . . . ሲቆይ ሆዳቸው ተገ ለበጠ የሚወጣ መሰላቸው ። ጊዜው ሲንተድ ስሜታ ቸው አሸንፋቸው . . .

«ወይል ደግፌ ! . . . መካንንት . . . የሰው ልጅ ለላ ምን ጠላት አለው ? » በማለት አጉረመረሙ ።

አላስችል አላቸው ። ተንሥተው ፣ ከተዘረጋው የበ ግ ለሊጋ ጉን እተተከፈሰው ሌማት እጃቸውን ዘው አደር ገው ፣ እንጀራ ይዘው ወጡ ። ያልፈላውን ኸር በጭ ልፋ እየጨለፉ ፣ በእንጀራው እየጠቀሱ በሉ . . . የተ ራበ ጀውላ ይመስላሉ ።

እምስቴና ሰድስቱ እንደጉረሱ ፣ «ተመስገን ! . . . አሁን ይሻለኛል » አሉ ።

ባለቤታቸው ተመለሱ ።

«ቃሪያ ጠፍቶ ፣ ጉረቤት ፍለጋ ሔጄኮ ነው . . . ቆየሁ ? »

«እም ፣ . . . ቆየሽ ! »

«ምን ‘ድነው ? ይሄ የተድፋፋ ነገር ? ጭልፋው ወድቋል ! . . . ማን ከፈተው ከላኑን ? . . . ድመቷ ስታ በላሽው ፣ ዝም ብለው ያያሉ ? . . . »

አሊጋው ላይ ቁብ ያሉትው ጥቁርና ነጭ ድመት ፣ «ሚያው ! . . . ሚያው ! . . . » እያለች ፣ በሬት መላሷ ዣንበሯን ታሻሻለች ።

http://ethioliberty.wordpress.com/

«የለም ! . . . እንዳይገነፍል ብዬ ነው የከፈትኩት ፣ — አሉ ደግፌ — የምንተፍረታቸውን ። ሆዳቸውን በማስብ ብረት ድስቱን ባለመክደናቸው ተቆጡ ።

«መች ታጣቀለች ! . . . ደኅና በውቃለች !» ሲል ልባቸው ተከራከረ ።

«እሄ ! . . . ገባኝ ! የጡረታ ገንዘብ ዝም ተብሎ አይደል የሚዛቀው ?» ገበታው ቀረበ ።

. . . አብረው ቀረቡ . . . «ተመስገን !» እያሉ ገበታው ተነሣ . . . ጨዋታ ቀጠለ . . . መሸቷል . . . ነጋ።

«እንዲያው ሌሊቱን አላስተኛ ብሎኝ !»

«እ . . . እመላለሰው ፣ አይደል ?»

«ይገርምሻል ፣ ምን እንዳገኘኝ ፣ ሲያመላልሰኝ ቆይቶ አስቀመጠኝ . . .»

«እኔም ጠርጥሬ አለሁ ! . . .»

«ምኑን ? እንዴ ደሞ . . .»

«ያለ ሒሳብ የጡረታ ገንዘብ መዛቁን — ለዚህ ውም ሳይበስል ! . . . ማብሰያውማ ሥራ ነበር !» — ተናግረው ሳይጨርሱ

'አሸመረኛ' አሉ ፣ በልባቸው — ደግፌ ።

«እንዴ ደግሞ . . . ወሬኛ ሥራ ! ሥራ ! ነው ፣ እስቲ ገና በማለዳ ደጅ ሁሉ ነገር . . . ቆይ አሳይሻለሁ !»

«እናያለን . . . ቶሎሩ ብቻ !»

* * *



ከሳይንስ ፋኩልቲ ፊት ለፊት የምግብ ሸቀጦች የሚቸረችረው መደብር ከግመቱ ሁሉ ከባድ ሥራ ያለበት ይመስላል ። ደጃፉን የሚረግጡት ደምበኞች ብዛት ቢዘረዘር ፣ የወጪና የገቢ ደብዳቤ መዝገብ አይበቃውም ።

የመደብሩ ሠራተኞች እንደንግዝርት እየሾሩ ፣ ከዘቆ ቀን እጥፍ ጉልበታቸውን ያፈሳሉ ።

ጡረተኛው አቶ ደግፌ በዚህ መደብር ከተቀጠሩ ፣ እንዴ ደመወዝ በልተዋል ። ሥራቸው የተወሰነ አይደለም ። ወሮበሎች ሥርቆት እንዳይፈጽሙ መጠበቅ ፣ ደምበኞች ያለ ችግር ገብይተው እንዲወጡ ማገዝ ፣ ለሽያጭ የሚቀርብ ሸቀጥ ወደ መደብሩ ማስገባት ፣ መሳላክ . . . ሌላም ነው ። ሁሉንም ባንዴ የሚሠሩበት ጊዜ አለ ፣ ደኅና ይጣደፋሉ ። በዝግታ ሲሆን አካባቢውን ከብዙ በማያንስ ዐይናቸው ይቃኙታል ፣ ቆም ሲሉ ደግሞ በሒሳብ ይነጉዳሉ ።

የገና ጭዚማ ፋታ አልሰጣቸውም ። ከማለዳ እንሥተው ሲንደፋደፉ ነው — የዋሉት ። ካንዴም ሁለቴ ለስላሳ መጠጥ ተሸክመው ሲያስገቡ ፣ ጐንበስ ማለት ፈስተው በመሰላል ካልሆነ ከማይደረስበት ጉበን ተጋ ጭተዋል ።

ከቀትር በኋላ የቢሮ ሠራተኞች መውጫ ሰዓት ሲሆን ፣ ያራት ኪሎ መንገድ ሁሉ ተጣበበ ። ወደ ላይ የሚወጣውን ያህል ይወርዳል ። ዐሊይዎ ሰያፍ እቅ

http://ethioliberty.wordpress.com/

ማሜ ይዛ — ትዋጋለች ። ልጅ ፣ ተማሪ ፣ ጉልማሳ ፣ የቢሮ ሠራተኛ ፣ የቤት እመቤት ፣ ሸበቶ ሽማግሌ ፣ ለማኝ ፣ ዘበናይ ወጣት ፣ ሊስትሮ . . . ወዘተ . . . ሁሉም ተወክለው ይገኛሉ ። ባንድ ቀለም ሳይሆን ከያይነቱ ነው ፤ ነጭ ነጠላ ፣ ጥቁር ኩታ ፣ ሰማያዊ ሱሪ ፣ የተቀደደ ቁምጣ፣«ባኒ»፣«ጂንስ»፣ሽንሽን ቀሚስ፣የታይዋን ጃኬት...

የመኪኖች ተካልቦ መተላለፍ ፣ የሞተሮች ማጓራት ፣ አካባቢውን በጥቀርር ጢስ ያፍነው እንጂ ፣ በሙቀት ላይ ሙቀት ይጨምርበት እንጂ ፣ ልብ ብሎ የሚያስተውል አይታይም . . . ያመት ባል ስሜት ነግሷል።

ይሄኔ በቀይ ቀለም « አዲስ ቢራ » የሚል ጽሑፍ ፣ ቢጫ መደብ ላይ የተጻፈበት ትሬንታ መኪና ፣ ከመደብሩ ተፋጦ ተገተረ ።

አቶ ደግፌ አላስተዋሉትም ፣ ግን አይተውታል ። የገናን በዓል እንዴት እንደሚያከብሩ ሲያሰላስሉ ፣ ወዲያው ደግሞ ከባለቤታቸው ጋር ከምሽቱ አንድ ሰዓት እንደ ተቃጠሩ ፣ ዋጋው አልቀመስ ቢልም ዶሮ እንደሚያንደፋድፉ ሲያወጡ ፣ ሲያወርዱ ነበር ።

አንድ ሁለቴ የመደብሩ የሽያጭ ኃላፊ ቢጣራ አላዳመጡትም ። « ምነው ? አቶ ደግፌ ! . . . መኪናው'ኮ ቆሟል ! » አለ ፣ በቁጣ ሳይሆን በጩኸት ።

«ዕውነት ! ... ዕውነት ! ... ቀልቤን ምን ወሰደው» አሉ ፣ ፈጥነው 'ካሴት ቢራ' (ማሞን ቢራ) ከመኪናው



እያወረዱ ። ቀለለው ከደረደሩ በኋላ በተራ ማስከነቱን ተያያዙት ።

«ካሴቱ» እየተናጠ ቢራው አረፋ ሲደፍቅ ፣ አፋቸው ይረጥብ ፣ ምራቃቸው ጢም ይል ጀመር — ደግፌ ። [illegible] አምሮታቸው ተቀሰቀሰ ፣ ልባቸው የፋብሪካ [illegible] ።

[illegible] « ካሴቶቹን » ቢደረድሩም ፣ ትሬንታው [illegible] ላታቸው እያጉረመረመ ቢሔድም ፣ የአፋቸው [illegible] ቀጥሏል ። ሰውም ሲያዩ ፣ ሊስትሮ የሚያባርራ ትን ውሻ ሲያዩ ፣ ትክክኛ ለትክክኛ ተቃቅፈው የሚነጉዱ ኮረዳ ጉብል ሲያዩ ፣ እርሳሱ የጠፋበት ተማሪ እዩዩ ውን ሲለቀው ሲያዩ ... በፃምጥ እንደሚሳብ የበረሃ ውሃ ምራቃቸው ይመነጫል ።

አምሮታቸው መሐል እናታቸው ሲወጣ «እባክህ አጄ ! ... አንዱ ከቢራው አስጎንጨኝ ወደ ባዳ ዞር አበል ?» ብለው ሊጠይቀው አሉ ፣ የሽያጭ ኃላፊውን በማሰብ ። «ለገንዘቡ እንደሁ ችግር የለም ፣ ሳምንት ከምትሰጠኝ ደሞዝ አምስት ቀን ሒሳብ ቆንጥርለት ማለት ነው !»

«ቢሆንስ ፣ እጉል በመል አድርጎ ቢያመናጭቀኝስ ፣ አጥርጾ ቢገምተኝስ » — የሚል ተቃራኒ ሐሳብ መጣባቸው ። «ሆሆን ጠጥተው ፣ ሙቀቱ ተጨምሮ ፣ ጋል ሲሉስ ! . . . ደምበኛ ሊያስቀይሙ አይደል ? » በሚል

http://ethioliberty.wordpress.com/

መልስ ፣ ራሴው በቆሰቆሰኩት ሲወርድብኝስ « ምን እላለሁ ?...» በዚህ ሐሳብ ተሸንፎ ።

«አቶ ደግፌ !... አቶ ደግፌ !... ወዲህ !» አለ የሽያጭ ኃላፊው — ሁለት ቀን ሲያድር ነጭ ጅማት የሚያወጣውን እስክሪብቶ ጆሮው ላይ ሰክቶ ። ወዲያ ወዲህ ሲል ፣ እጆቹን በቆሸሸው ነጭ ‘ጋውን’ ኪሶች ውስጥ ይደብቃቸዋል ።

«አቤት !... አቤት !» ብለው መጡ ። ምራቃቸው ወደ ውጪ ይፈናጠራል ።

«ይህን ዕቃ ... ለሴትዮዋ አድርሱላት !» ብሎ በጣቱ እያመለከተ አዘዛቸው ።

የተጠቀለለ ሥጋ ፣ የታሸገ ፓስታ ፣ የቆርቆሮ አትክልት ፣ በላስቲክ የታሸገ ድንች ጥብስ ፣ ብራንዲ ጠርሙስ ... በካርቶን ውስጥ አሉ ። ከጉሎት ካቤት ቢራ እንዲሁ ።

ያቶ ደግፌ ዐይን ቢራው ላይ ተተከለ ። ቢራው የደፈቀው አረፋ ፣ ባለሙያ ልብስ አጣቢ የመታቸው እየ ይመስላል ። ምራቃቸው እንደገና እየጨመረ ... እየጨመረ ... እንደ ሰሐጭ ተዘለገለገ ።

«እንዴ ! አቶ ደግፌ ! ራትዎን ይጥረጉት እንጂ !» ቆጣ የተቀላቀለበት ንግግሩን ሲለቀው ፣ ዐይኑ እሳቸው አፍ ላይ አነጣጥሮ ነበር ።

አቶ ደግፌ ፣ በደመነፍስ አፋቸውን አባበሱና ዕቃ ምኑን ተሸክመው ወደ ሴትዮዋ መኪና አደረሱ ።



ሲጨርሱ ፣ ተመልሰው ከቦታቸው ቆሙ ። የገናን ቀዚቃ ትዕይንት ያስታውሳሉ ። ሰዎች ይሔዳሉ ። ከቅጽበት የሚሻሙ ፣ አሰቡበት ለመድረስ የሚሮጡ ናቸው ። በታክሲና አቶቡስ ከሆነ ፣ ትዝ አይበላቸው እንጂ ፣ ከሌባ ተሸሽተው የሚሳፈሩ ... ብዙ ናቸው ።

ጊዜው ይሔዳል ... ጀንበር አቅጣጫዋን በምዕራብ አድርጋ ፣ ለመጥለቅ ጐምግማለች ። ያቶ ደግፌን አፍ ግን የመድረቅ ነገር ንክች አላረገውም ።

ዐሥራ ሁለት ተኩል ሆነ ። ዓመት በዓሉን አስታከው ከመደበኛው ጊዜ ግማሽ ሰዓት ቀድመው ወጡ ። ባራት ኪሎ ፖስታ ቤት አድርገው ፣ የብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት አልፈው ቀጥታ የፒያሳን መንገድ ሲይዙ ፣ ወደ ኪስ ሚዲ የሚገሠግሥ ከሚመስለው መንገደኛ እየተጋፉ ቢተላለፉም ፣ አልታወቃቸውም ። ዐሥሬ ምራቃቸውን እየዋጡ ወደ ፊታቸው ተራመዱ ።

እንዲያ ሲጓዙ ፣ ሁለት የሚያውቋቸው ሰዎች «ሰላም !» ብለዋቸው ነበር ። በሦስተኛው ነው «ዘሐርም ስጌን ! ደህና !» ብለው ፣ ላብ ያንቀበውን ቆብ ላመል ያነሡት ።

እጂፕ ማደያ አካባቢ ሲደርሱ ፣ ወደ እንጂት ቡና ቤት ጐንበስ ብለው ጐራ አሉ ። ጠበብ ያለ ክፍል አላት ። ባውሬ መንገዱ ከሚዘለው መኪና ሌላ የሰው ውካታ አይሰማባትም ።

http://ethioliberty.wordpress.com/

በመጠጥ መደርደሪያው የተሰቀሉት በጣት የሚቆጠሩ ጠርሙሶች ፣ ባዶ መሆናቸው ያስታውቃል ። አረቄ ፣ ሐይግ ፣ ጂን ፣ ኮኛክ ፣ ቢኖ ፣ ጉደር ፣ ብራንዲ . . .

አቶ ደግፌ ቆመው አጨበጨቡ ። አጠር ያለች ፣ ጸጉ ቀሚሷ ላይ ነጠላ የደረበች ሴት ፣ ከርቲስ የምትጠግን ይመስል ፣ እንጋጣ ፣ «ምን ልታዘዝ ?» አለቻቸው ።

«አንድ ቢራ ወዲህ በይ ! ... ፍጠኝ !» አሉና ግድግዳውን ከተጠጋው ኩርሲ ላይ ዐረፍ ሲሉ ፣ ሱሪያቸውን ሰብሰብ አረጉት ። በግራ እጃቸው በላስቲክ የተለበደውን ጠረጴዛ ተደገፉት ።

«እሺ !» ብላ ከሔደች — ሩብ ሰዓት አለፈ ። የቢቱን ጸጥታ በመረለግ መልክ ፣ ድካማቸውን ያሳምጣሉ— አቶ ደግፌ ። ገበር የሚል ሰው የለም ። ሰውም አይገባም ፣ ልጅቷም ገባ የምትሠራው አይታወቅም ።

እሁንም ምራቃቸውን ይውጣሉ ። አምሮታቸውን ለመወጣት አሰፍስፈዋል ። ደጋግመው አጨበጨቡ ።

ስትርገጥ መጣችና «ውይ ! አባባ ... ቆየሁ ፣ አይደል !» አለች ።

«አይርገሽ እንጂ . . . ጥም ያቃጠለው ጉሮሮ አለ ውቷም » ሲሉ ፣ ምራቃቸው ይዝረከረካል ።

«እሚቱን እንስሰላ ሳምቱ ጥ ነው » ብላ ፣ ቢራውን ጠረጴዛው ላይ አስቀመጠችው ። የቢጋራ መተርኮሻውን እንሥታ ወደ ባንኮኒ ስትመለስ ፣ አቶ ደግፌ ቢራ



ውን በመገረም ተመለከቱት ። «ለዚህ ነው ፣ እንዲህ ልቢ የተሰቀለው » በሚል ስሜት ።

ዐይናቸው ከፍት ብሎ ሲቁለጨለጭ ፣ ኬክ አስቀምጠው «አትንካኝ !» የተባለ ሕፃን መሰሉ ።

«ከፈቺው እንጂ ! ፣» አሉ ። ትዕግሥታቸው አለቀ ። እጃቸውን ሲያመናጭቁ ፣ ቃሪያ ጥፊ ሊያልፏት ነበር ።

«በማርያም ! ዛሬስ ምን ነካኝ ?!» ብላ ፣ ተመልሳ መክፈቻ ያዘች ።

ይኸኔ የሰው ጩኸት ተሰማ — ከውጭ ። «የግጭት ፤ ያዚ ሊሆን ይችላል» — ስትል አሰበች ፤ ከመደንገጧ ልጅቷ — የምታውቀው ድምፅ ሆነባት ።

ባንዴ ብር ብላ ወጻውራ ጉዳናው ስትወጣ ነው ፣ የደረበችው ነጠላ ቢራውን እንሽራቶ ከወለሉ የከሰከ ሰው ። አቶ ደግፌ — ዐይናቸውን ወለሉ ላይ ከመወርወ ራቸው ፣ ወደ ቢታቸው አፍንጮ በር — አቀኑ ።

# ዋዜማ

የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ካሉት ተቋማት መካከል ፣ የሳይንስ ፋኩልቲ አንጋፋ ነው ። በተፈጥሮ ላይ ጥናት የደገነ ፣ ፍተሻ የመራ ፣ ምርምር ያራመደ ... ምሁራንን የሰበሰበ የትምህርት ማዕከል ነው ።

የኬሚስትሪ ዲፓርትመንት በተፈጥሮ ምንነትና ማንነት ላይ ከሚጠበቡት አንዱ ነው ። በአዲሱ ሕንፃ ውስጥ ጽሕፈት ቤቱንና ቤተ መኩረቱን ( ላቦራቷር ) አደራጅቶ ይገኛል ።

በዚያ ፣ በርዝመት በተንጣለለ 'ኮሪዶር' ላይ ተንቀሳቃሹ ጥቂት አይደለም ። ተማሪዎች ፣ መምህራን ፣ የጽዳት ሠራተኞች ፣ ቴክኒሺያኖች ይገኛሉ ።

«ፕሮፌሰር ዶክተር አሸብር ከንቱ» የሚል ጽሑፍ ፣ በቢጫ ቀለም በቀጭኑ የተጻፈበት በር ፣ ቅቤ የተለቀለቀ ይመስላል ። ግጥም ያለ ነው — የሚያብረቀርቅ ፣ አሁን ፣ ተሰምቶ የማይታወቅ ትኩረት ስቧል ።

የሳይንስ ፋኩልቲ የማስተማርና የመመራመር ተግባሩን ቀጥሏል ። ሁሉም በየፈናው ድርሻውን ለማ



http://ethioliberty.wordpress.com/

በርከት የሚራወጥ ይመስላል ። ቢሆንም ፣ በኬሚስትሪ ዲፓርትመንት የሚፈጠረውን ማናቸውንም ነገር ለማወቅ ይጓጓል ።

በንጋት የተፈጠረው የሐሳብ ሞገድ በዲፓርትመንቱ ዙሪያ ይንገዳል ። አንዳንዱ የሚያዘግም ይሆንና ድንገት ፍጥነት በመጨመር ይናወጣል ።

... የፋኩልቲው ኅብረተሰብ እጅግ ከሚያከብራቸው ምሁራን ፣ ዝነኛው— ፕሮፌሰር አሸብር ከንቱ ናቸው ። የግቢው ኅብረተሰብ እሳቸው ስለሚያከናውኑት ምርምር እያነሣ ይወያያል ። መልካም ምኞቱን ይገልጻል ።

በፕሮፌሰሩ ቢሮ በኩል የሚያልፍ ሰው ፣ ለደቂቃዎች ቆም ብሎ «. . . የት ደርሰው ይሆን ? . . . ምን አገኙ ? . . . በተሳካላቸው !» እያለ ለራሱ ይጠይቃል ፤ ለራሱ ይመልሳል ፤ ይገምታል ።

ኬሚስትሪ ሳይንስ ነው ። የቁስ አካልን ስሪትና መዋቅር ያጠናል ። በዚህም የሚታየውን ለውጥ ከነስበብ አስባቡ ይተነትናል ። የመስኩ ሥነ ዘዴ መኩረትና አስተውሎት ነው ። በሌላ በኩል ፣ ኬሚስትሪ በራሱ ለብቻው የሚጠበብ አይደለም ። በሌሎች ሳይንሶች ይደገፋል ። በውጤቶቻቸውም ይጠቀማል ። የምርምር አድማሱን እያሰፋ ፣ እያሰፋ አያሌ ጉዳዮችን ይነካካል ።

ምግብ እንዲጣፍጥ ፣ የእርሻ ላይ ተባይ እንዲጠፋ ፣ አፈር እንዲለማ ፣ የእህል ዘር እንዲያፈራ ፣ ተስማሚ

http://ethioliberty.wordpress.com/

ልብስ እንዲመረት ፣ መድኃኒት እንዲፈበረክ ፣ ቀለማ ቀለማት እንዲቀየጥ ፣ የኃይል ምንጭ እንዲስፋፋ. . . ኬሚስትሪ ዋንኛ ነው ።

የፐሮፌሰር አሸብር ቢሮ ተንኳኳ ።

ነጭ 'ጋውን' ከለሲው ድረስ የለበሰው ፣ ዶክተር ከታቡ እንግቴን ሠገግ አርጎ አስገባ ።

ፕሮፌሰሩ አቀርቅረው ይሠራሉ ። ሐያ አራት ሰዓት ከመንበራቸው ሳይነሡ አንድ ጉዳይ ላይ አተኩረው ማጥናት እንደሚችሉ ብዙ ሰዎች ይናገራሉ ። መሰልቸትን አያውቁትም ። የጀመሩትን መጨረስ ባሕርይ አላቸው — ልማዳቸው . . .

በመሃሉ የፐሮፌሰር በሩ ላይ ፣ « በሥራ ላይ ነኝ... በሥራ!» የሚል ጽሑፍ የተጻፈበት መሠለው— ዶክተር ከታቡን ። እንደ አገባቡ ተመለሰ ። ተመስጠው ሲሠሩ የሚያቋርጣቸውን ከልብ እንደማይቀበሉ ያውቃል ።

ፕሮፌሰር የጀመሩትን ጉዳይ በርጋታ ማከናወን ይቀናቸዋል ። የተካለበ ነገር አይሆንላቸውም ። ሲያስ ምሩ ለነገ አይሉም— አይሰለቹም ።

ማስተማር የሚጀምሩት ፣ ሁል ጊዜ ከክፍለ— ጊዜው ቀድመው ነው ። ይህን ፣ 'ፍሬሽማን' ተማሪዎች ፋከልቲውን በረገጡ በሦስተኛው ቀን ይሰሙታል ።

ፕሮፌሰር አስተምረው የሚያበቁት ከተሰመደ ጊዜ አሳልፈው ነው ። በተለይ ፣ በጠዋቱ የመጨረ



ክፍለ— ጊዜ የሚማሩት የፐሮፌሰሩ ተማሪዎች ፣ ምግብ ቤት የሚደርሱት ፣ ምግብ ሲያልቅ ሲል ነው ። «የአሸብር ልጆች መጡ . . . መጡ!» ፣ እየተባለ በምግብ ቤቱ ይወራል ፣ ተማሪዎቹ ደብተራቸውን ይዘው ፣ እጃቸውን እየወረወሩ ሠንጥቀው ሲያልፉ ።

ይህን በተረዱ ጊዜ ፕሮፌሰር ፣ ከልባቸው አዘኑ ። ትልቅነት በመመኘት ተማሪ ማሳጣት ፈልገው አልነበረም ! ትልቅ የዕውቀት ጉተራ በያንዳንዱ ተማሪ አዕምሮ ለማዘጋጀት እንጂ ። «ዳግም አላረገውም !» ብለው ዘለል ይገባሉ ። ዕውቀት ያማለላቸው ፣ ምርምር ናፋቂ ዐይኖች ቀልጭ ፣ ቀልጭ ሲሉባቸው— « ዳግም አላደረገውም !» ያሉትን ረስተው ፣ በኬሚስትሪ ሳይንስ ተመስጠው ያስተምራሉ ። ወደ ተፈጥሮ ምስጢር ይዘልቃሉ ። ተማሪዎቹ ይከተሏቸዋል ... የምሳ ሰዓት ያልፋል ።

የፐሮፌሰሩ ትክኛ እንደ ሰንጋ ኛኛ ያበጠ ነው ። ጠረጴዛው ላይ ያለው ስልክ « ጢርር! . . . ጢርር ! ጢርርር!...» አለ ። የስልክ መነጋገሪያውን እጃቸው አንሡና በጀርባቸው ተንጋለሉ ። ለብቻው የሚንጐማለለው ትክኛ ፣ በርሚም ወይዘር ያሰንቃል ።

«ሃሎ! . . . አቤት !» አሉ ፣ በረጋ ድምፅ ።

«ምንው? . . . ይሄን ያህል ሲደወል? ... ለምን ስልኩን አታነሡም !» ከወዲያኛው ጫፍ ሽቦውን ሰንጥቆ የሚከንፈው የሴት ድምፅ ነው ።

http://ethioliberty.wordpress.com/

«ኢ... ኢ... እንቺው ነሽ? ... ምን አዲስ ነገር መጣ ?»

«ምንም ! . . . ግን ስልኩ ለምን ቶሎ አልተነሳም ?»

«አያውቅሽ? ... የፕሮጀክቱን ሥራ በማጠናቀቅ ላይ ነን ፤ 'ፋይናል' ሙከራውን ለማድረግ መሰናዶ ይዘናል ፣ 'ሥራ በዝቷል' ማለቴ ነው . . . በዚህ ላይ ስልክ ሲጨመርበት ይታሰብሽ ! ... አሁን ምን ልታዘዝ ?»

«ያው መከረኛ ኤድስ ነው ! አይደል ? . . . ምናደክመህ ? መድኃኒቱ 'ኮ ተገኝቷል ! እንዲያውም ሰንብቷል ! ከናንተ ቅመማ ሳያምጣ ይቀራል ብለህ ነው ?»

« ንገረኛ ! . . . እኛም ፕሮጀክቱን እንሠርዘው ፤ ከድካም የሚያድን ከተገኘ ማን ይጠላል ?» በማፌያ እየማቁ ።

«አንተስ መቼ አማኸው ! . . . በርበሬ ነዋ ! የኤድስ መቅሠፍት መሆኑን አገር እያወራው አይደል ?»

«ኢ. . . ሺ ! ይኸው ነው ያንቺ ምርምር ?»

«ቆይ እንጂ ልንገርህ ! . . . እኛን እንደሁ እርግፍ አርገህ ረስተኸናል ። ዛሬ የቢጤዎን ልደት እንዳት ረሳው ፤ እደራህን ማታ ቶሎ እንድትመጣ . . . አባዬ ! . . .

አባዬ ! . . . ትላለች ። ፕሮጀክት እያልክ በ'ላብራቶሪ' ከሆነ እዳርህ—ቢያንስ እንግዶቹን አስብ . . . ማታ በአንድ ሰዓት ነው ።»



«ታዲያ ጠዋት ተነጋግረን አልነበር ? . . . ለሚናዋ ውም አልረሳም ።»

«ቢሆንም ካልደጋገመልህ ልብህ አይዘውም ብዬ ነዋ ! . . . ይኼ ኤድስ እያለ ምን ጤና አለ ?»

«አሁን ገና ዕውነት ብለሻል ... ምንም ጤና የለም !»

«የሚጠጣ ቢጤም ፈልገህ ብታመጣ ጥሩ ነው ! ለእንግዶቹ . . . ወይን ከግሮሰሪ አታጣም !»

«ገባኝ . . . ቻው !»

«ወይ ጥድፊያ ! . . . 'ላብራቶሪ' ውስጥ የሚደከው ሊገኝል ነው መሰለኝ !» እንደ መሣቅ በሚል ድምፅ ።

«በይ . . . ቢቃሽ ! ቡና መሰለሽ ? » ብለው ፣ ስልኩን ዘጉት — ፕሮፌሰር አሸብር ከንቲ ።

እይ 'ስሎሜ !' አሉ በልባቸው ፤ ውሃ የመሰለውን መነጽር አውልቀው ፣ በፊደልና በቁጥር እደማው ወረቀት ላይ እያኖሩ ።

'ስሎሜ . . . መሞገስና በሰው አፍ በየምክንያቱ ካልተነሣች ላይሆንላት ነው ? . . . ለልጅ ልደት የዐቀቂዎች መንጋጋት ምን ይሉታል ? . . . . ከባለቤቱ ጋር ተዋውቂልኝ ! የመጀመሪያው ኢትዮጵያዊ የኬሚስትሪ ፕሮፌሰር ! . . . ብላ ራሷን ለማስተዋወቅ እንጂ !' እያሉ ሲያስቡ ፣ የስድስት ዓመቱ የትዳር ጉዞ እንደ ትናንት ትውስታ ፣ ተንቀሳቃሽ ሥዕል መስሎ በአሲናቸው ታያቸው ።

http://ethioliberty.wordpress.com/

'አሁን ደግሞ የሠርጋችንን ልደት ላከብር ብትልስ! ሰዓት . . . ስምንት . . ዘጠኝ . . . እያልኩ በያመቱ ልቆጥር?— ስሎሚ መዝገቡ ! . . . '

በጀርባቸው እንደ ተንጋለሉ በይናቸውን ሲያፍኩቁ። ተንጦተው ፣ በመስኮቱ አሻግረው ወደታች ተመለከቱ።

የግቢው ተማሪ ተኮልኩሏል ። ለብቻው ፣ በቡድን ይታያል ። የእረፍት ሰዓት ፀሐይ የማይከመኩም የለማ !

የተማሪነት ትዝታቸው ተቀሰቀሰ . . .ድሮ የዩኒቨርሲቲ ኮሌጅ ብርቅ ከሚባሉት ተማሪዎች አንዱ ነበሩ . . . ሐያ ዓመት መሆኑ ነው— በአሜሪካ ሚቺጋን ዩኒቨርስቲ የኬሚስትሪ ከፍተኛ ትምህርታቸውንና ጥናታቸውን በማስታወስ ፣ ሐሳባቸው እየሞላ እየሞላ በልዩ መንኩራኩር መጠቀ ።

የፕሮፌሰር አሸብር በር እንደገና ተንኳኳ ።

ፊታቸውን ከመስኮቱ መልሰው «የስ! . . . » ሲሉ ፣ ሜማው ድረስ በተንዠረገገ 'ጋውን' ውስጥ የተከተተው ሰው ብቅ አለ ።

«ታዲያስ ምን 'ዲቨሎፕመንት' አለ ?» ብለው ጠየቁት ። ከአቻዎቻቸው ጋር ሲነጋገሩ ጉራማይሌ ነው ።

«ሁሉም 'ኖርማሊ' እየሔደ ነው . . . ብቻ ያለንን ኬሚካል 'ኢንቴንሲቭሊይ' ከተጠቀምን እጥረት እንዳይገጥመን ነው— የፈራሁት . . . » እያለ ሲናገር ፣



እጁን ያወዛውዘዋል ። ምናልባት የፈለገውን ሐሳብ በእጁ ንቅናቄ ጭምር መግለጽ ፈልጎ ይሆናል— ዶክተር ከታቦ ።

የኬሚስትሪን ዲፓርትመንት ዘመናዊ ቤተ ሙከራት (ላቦራቶር) የቀረቀረ ነው ፣ ዘወትር ተፍ ተፍ የሚለው ለቤተ ሙከራቱ ነው ። ኪሱን እያራቀቀ ቁሳቁሶች ለቤተ ሙከራቱ መግዛቱን የተመለከቱ— ትንሽ ያበዛ ቀል ይላሉ— ባልደረቦቹ ። « . . . ጥቁር ሰሌዳ ላይ የኬሚካል ውሁድ እየቀየጡ 'ሰልሽን' (ብጥብጥ) መፍጠር ቅዠት ነው ። ኬሚስትሪ ያለ ቤተ ሙከራት ፣ ፋይዳው ውሱን ነው! »እያለ በያጋጣሚ ይከራከራል — ይሟገታል ። «ተማሪ በ'ቲዎሪ' ብቻ አይሠለጥንም ፣ መያውን አይሰንም ፣ ከሥራ የተፋታ ትምህርት ባፍንጫዬ ይውጣ! ተማሪው በቤተ ሙከራት ሙከራ እያካሔደ መማር አለበት . . . » ይላል ።

«ይሄኛው . . . እንደምታውቀው ወሳኝ ነው ፣ የመኖር አለመኖር ነው !. . . ለኢድስ በር ፍለጋ መጨረሻው ድረስ መሥራት አለብን ! . . . 'ፋይናል' ሙከራ ላይ ደርሰን ማፈግፈግ ያምስት ዓመት ሥራችንን ሜዳ ላይ መበተን ነው . . . ዘርና ቀለም ለማይለይ በሽታ እስከ መጨረሻው የኬሚካል ጠብታ ድረስ መጠቀም ነውን 'ጂ ! . . . » ብለው ፣ ፕሮፌሰር አሸብር ንግግራቸውን ሳያቋጡ ፣

«ሊሱማ ይገባኛል! . . . ሌሎች ፕሮጀክቶች እንዳይታጐሉ ማለቴ ነው . . . ነገሩማ ልክ ነው፣ ደግሞ ዩኒቨርሲቲውን የሚያስጠሩና የሚያኮሩ አይደሉ . . . »

«ብቻ ጥንቃቄ የሚያስፈልገው» አሉ ፕሮፌሰሩ፣ «እያንዳንዷን የኬሚካል ጠብታ ‘ኢፊክቲቭሊይ’ የመጠቀሙ ጉዳይ ነው። ብዙ ካባከንን የምንሠራው ትንሽ ነው። ‘እኬ!’ . . . ትንሽ ቆይቼ እመጣለሁ፣ ‘ዜን አይ ዊል ሲ’ . . .» ብለው፣ ተሽከርካሪው ወንበር ላይ ሲቀመጡ፣ ባለፈው ሴሚስተር ያስተማሩባቸውን ወረቀቶችና ከተማሪዎች የሰበሰቧቸውን ጽሑፎች ተመለከቱ።

ዶክተር ከታቡ በሩን ዘግቶ ይወጣ ነበር . . .

★ ★ ★

«በጀመሩት ምርምር፣ ለአዲስ መከላከያ ይገኛል ብለው ያስባሉ ነ» ይሄኔ፣ በመምህራኑ ክበብ ውስጥ የሚመገቡ፣ የሚዝናኑ ሰዎች ጥያቄው ወደ ተወረወረበት አቅጣጫ ዞሩ። እንደ ጥቅምት ወርቹ ተንሾካሾኩ። እንዲያውም አንዷዋ ሴት፣ የያዘችውን ሻይ ደረትዋ ላይ ልትደፋው ነበር።

‘ለዚያውም በምሳ ላይ እንዲህ ዐይነት ጥያቄ! . . .’ —የሚል ስሜት ይነበብባቸዋል።

ፕሮፌሰር አሸብር ምሳ የሚሉትን እቤታቸው ከሥርተዋል።



http://ethioliberty.wordpress.com/

ምስት የሳሳ ሳንድዊቾች ከእምቦ ወተ ጋር፣ ረባዳው ጠረጴዛ ላይ ይታያል . . . ጠያቂያቸውን ትኩር ብለው ተመለከቱት . . . ታደሰ ቀቅጅራ ነው። «ሳይንስ በኢትዮጵያ» የተባለ ወርኃዊ መጽሔት ያዘጋጃል። ያቀጣጠለውን «ቂንስተን» ሲጋራ ሲምግ፣ እንደ ተነፈሰ ፊኛ ጉንጩ ይሥረጉዳል። እንደ በረሃ ቁጥቋጦ ማል፣ ማል ያለው ጺሙ . . . ተበታትኖአል።

«ጥያቄው በእጅጉ ከባድ ነው . . . መልሱም ከውስብስብ ምርምር በኋላ የሚገኝ ይመስለኛል። በኛ ጥናት ውጤት ማግኘት አለማግኘታችን ገሃድ ወጥቶ የሚመለከረው ፍጻሜው ላይ ነው፣ ቀድሞ እርግጠኛ ያልሆነ ተስፋ መናገት ያስገምተናል . . .» ብለው፣ ሳንድዊቻቸውን ሲያላምጡ፣ በለበሱት ነጭ ‘ጋውን’ ላይ የተንጠባጠበውን ፍርፋሪ ያራግፉ ነበር።

ይህን ሲያዳምጥ— ታደሰ፣ የሚንቀሳቀሰው ዐይኑ ብቻ ነው። ሌላ ነገር የተፈጠረበት አይመስልም። ‘ጋዜጠኛና ዐይን’ አሉ በልባቸው— ፕሮፌሰር አሸብር።

«የኢትዮጵያን የኬሚስትሪ ግሥጋሴ እንዴት ይመለከቱታል?»

«በዚህ የሚያስፈልገውን ያህል አልተራመድንም። ‘ነገር ግን እያንቀላፋን ነው’ ማለቴም አይደለም። ድክመታችን ግልጽ ነው . . . ዕድሜት፣ የባሕር ሀብት ባህሉው አለን። በሁሉም አልተመራመርንም፣ አልመረመ .

http://ethioliberty.wordpress.com/

ርገም ! 'ፈትሸን ፣ አጥንተን ለልማት አልተጠቀምንም ። ብዙ ግኝት ለማስመዝገብ— ጥልቅ ምርምር ያስፈልጋል . . . ለአንዳንድ ጅማሬዎች ደግሞ ዐይን መጨፈን አንችልም ፣ 'ኢንከሬጅ' ማድረግ አለብን ። የምሩ ካሔደው ፕሮጀክት ፣ ሳገር ባህል መድኃኒት የሰጠነው ትኩረት አይናቅም ። በሙያ (ፕሮፌሽን) ተሰባስበን ያቋቋምነው ማኅበርም አንድ ምሳሌ ነው ። የአፍሪካን ስብሰባዎች ማስተናገድ ከጀመርን ቆይተናል ። ባጠቃላይ ለተተኪዎችም ትኩረት መስጠት አለብን ፣ በተለይ ከትምህርት ቤት በመጀመር ለሙያው የሚያድሩትን 'በርቱ!' ማለት አለብን ፣ ታዲያ ቤተ ሙከራ ማበብ አለበት . . .» በማለት ማብራሪያቸውን በስፋት ሲይዙት ፣ በሐሳባቸው ዶክተር ከታቡ ለቅጽበት ብቅ አለ— ከቤተሙከራት መሣሪያዎች መሐል ፣ እጁን እያወዛወዘ . . .

ታደሰ ቀትጆሩ ፍጥጥ ብሎ ሲመለከት የሰው ዐይን ይወጋል ። በያዘው ቀጭን እርሳስ ፣ ማስታወሻ ሲያስፍር— የበሬ ግንባር በምታህል ደብተር ላይ ይጽፋል ። ሁለት ሦስት ቃል ነው— የሚከትበው ፤ 'ቀሪውን ሐሳብ ባይኑ እየተየበ ወደ አንጎሉ ሳያስተላልፍ አይቀርም' ብለው አሰቡ— ፕሮፌሰር ።

ሁለቱም እንዲህ ተፋጠው እያሉ በመምህራን ክበብ ያለው ለስለስ ያለ ሙዚቃ ፣ ጉራማይሌ ንግግር ...



እንግሊዝኛ— ፈረንሳይኛ— ጀርመንኛ ... ያለም ቋንቋ ... ሐሳባቸውን ወስዶ አላምታታቸውም ።

«በጀመሩት የኤድስ ፕሮጀክት ውጤት ቢያስገኙም ይሰማዎታል?»

ፕሮፌሰር አሸብር ለጥያቄው ፈጥነው መልስ መስጠት አልወደዱም ።

'የማይጠየቅ ጥያቄ !' ብሉ ፣ ልባቸው ተቆጣ ።

ወደ ምሳ ከመምጣታቸው በፊት ፣ ከዶክተር ከታቡ ጋር የቤተሙከራቱን ዝግጅት ተመልክተዋል ። የኤድስ ቫይረሶችን ለማጥፋት ተስፋ የተጣለባቸው ውሁዶች ከልዩ ልዩ ተክሎች ተመዝግዘው ፣ ነጥረው ወጥተዋል ። እርግጠኛነታቸውን መሰከር በቫይረሶቹ ላይ መሞከር ነው— የሚቀረው ።

በሌሎች ሀገሮች ዩኒቨርሲቲዎች ፣ የምርምር ቤቶች የተከናወኑ ፍተሻዎች ብዙ ረድተዋል ። የተከማቹት ውጤቶች ቢሰባጠሩ የዩኒቨርሲቲውን እጥር ያሰብሳሉ ። በፈረንሳይ አንድ የፓስተር ኢንስቲትዩት ጠቢብ ወዳጃቸው ፣ «ግን ቀድሞ መከላከያ መድኅን ያገኘ ይሆን ?» ሲል በደብዳቤ ያነጣው መጠይቅ ፣ ትዝ አላቸው— ፕሮፌሰርን ።

«እንዲገኝ ጥረት የምናደርገው ውሁድ ... ፈውስ— ኤድስ ... ማለት የኤድስ 'ቫክሲን' ሆ ኖ እንዲዘጋጅ ነው ። ሙሉ በሙሉ ቫይረሶቹን የሚያጠፋ እንዲሆን ፣ በኤድስ አደጋ ላይ ለሚገኝ የሰው ዘር ፍቱን መድኃኒት ሆኖ መገኘት አለበት ። ይበልጥ የሚያስጨንቀኝ

የሚያሳስበን የምንቀምመው ውሁድ— ቫይረስ ለማጥፋት ወደ ሰውነት ሲገባ፣ ሌላ በሽታ እንዳይጠነስስ፣ እንዳይቀሰቅስ 'ሳይድ ኢፌክት' እንዳያመጣ ነው! . . . ጥልቅ ፍተሻ ይፈልጋል!»

«ምን ይሰማዎታል?» ሲል፣ ድምፁ እየሩን ወ ጠቀው— ከዚያ ቀጭን ገመድ ከሚመስል ጉሮሮ ይወ ጣል ተብሎ አይገመትም።

«ምን ይሰማኛል? . . . የሰው ዘር ፈውስ አገኘ፣ በምርምሩ የተካፈልነውም የላቀ ውጤት ላይ ደረስን፣ ተግባሩም ሌሎች ፍተሻዎችን ከፍ ባለ ጥራት መያያዝ ነው . . . ወይም ሌላው ዓለም ቀድሞ ያገኘ ይሆናል፣ ማን ያውቃል ?. . . ለማናቸውም የምርምር ጥማታችንን ማርካት አለብን— በመልካም የሳይንስ 'ኤቲክስ'... ሥነ ምግባር» ሲሉ— ፕሮፌሰር ድምፃቸው ከረር ብሏል።

ዘለግ ባሉት ጣቶቻቸው በራቸውን አሻሽተው ቀና ሲሉ፣ ታደሰ እርሳስና ማስታወሻውን ደረት ኪሱ ያስገባ ነበር። ከገጽታው የሚነበብ ነገር የለም።

«የተቃና ውጤት ከልቤ እመኝልዎታለሁ! ውድ ፕሮፌሰር . . .» ብሎ ሲሰናበት!

እሳቸው ወደ ኋላ ልጥጥ ብለው፣ እግራቸውን አ ባብረው የሕሊና ጉዞ ጀመሩ... ዶክተር ከታቦ ሙን ከር ቤተ ሙከራቱ በር ላይ ተቀበላቸው...

* * *



http://ethioliberty.wordpress.com/

ማምሻውን ፣ ፕሮፌሰር አሸብር በኬሚስትሪ ዲፓርትመንት ቤተሙከራት ውስጥ በባልደረቦቻቸው ታጅበዋል ...

ጤና በሚያስለቅሰው ነጭ መብራት ሥር፣ በነጭ 'ጋውን' ወዲያ ወዲህ ሲሉ— ጠቢባኑ— ላይን ያጥበረ ብራሉ።

ፕሮፌሰር «ድማቢ ያማረላት ...» ሆነዋል።

በቤተ ሙከራቱ ውስጥ የሚሰማው ድምፅ፣ «ጂ . . . ጂ! . . . ጂ! . . . ጂእ! ጂ . . . ጂ! . . . ፉር . . . ኩርር!...» ይላል።

መግለጫ ቁሳቁሶች ልዩ ልዩ ናቸው። ማማሰያ የመሰለ ብልቃጥ፣ የብርሌ ድስት፣ እንደ መቃ የቀጠነ የኬሚካል ማንጠሪያ፣ ጭማቂ ዓይነት ማስተላለፊያ፣ ሽክና የሚያክል ብርጭቆ፣ ማይክሮስኮፕ፣ ቴርሞ ሜትር ... ብዙዎቹ ከመስታዎት የተሠሩ በመሆናቸው፣ እየተፍለቀለቁ የሚዘዋወሩትን ውሁዶች ቁልጭ አርገው ያሳያሉ።

ከፕሮፌሰር የሚደበቅ አዲስ ነገር የለም። እያንዳንዱ የቤተሙከራቱ ደቂቅ መዝሙር፣ ላመል ለወጥ ብሎ የታየውን፣ አዲስ ያስተዋለውን ይዞ ይሮጣል—ሊያሳያቸው፣ ወይም ይማራል—ሊነግራቸው ...

እንዲ፣ ጀማሪ የቤተ ሙከራቱ መያተኛ ነው። በጣም ተመስጦ እየሠራ፣ እጁን ለረዥም ጊዜ ቆጥ

http://ethioliberty.wordpress.com/

ከሚደርስው መጣሪያ ላይ ስቅሎት አቆየው። የደም ሥር
ተቆጥተው ግትርትር አሉ ። ይህም በኬሚካሎች መ
ናጠር የተከሰተ መሰሎት ፤

«ፕሮፌሰር !... ፕሮፌሰር! ይምጡ! ይመልከቱ
ብሎ— ሲጣራ ፤ መጣቂያ ሆኖ ነበር ። በኋላ የሥነልቡ
ውጥረት መሆኑን ሁሉም ተረድተዋል ።

ፕሮፌሰር እሸብር ገር ባሉበት ፤ ተጠባበቂዎች እ
ረው ይሾራሉ ፤ ንብ አውራውን እንደሚያማክለው
ነት ... ፕያቂ ፤ ክርክር— ይህ ቢሆን ያ ይታያል
ጉራማይሌ ንግግር በየማሊቃው ይሰማል ።

«እንዴት ነው? ትላለህ ... ክታቡ!» አሉ ፤ ፕሮ
ሰሩ ፤ ባንደኛው ጥግ እንደ ባንኮኒ ወንበር በረዘመ
መቀመጫ ላይ ቂቢብ ብለው ።

እለፍ እለፍ ብለው የተጣዱት ውሁዶች ፤ በ
ተኛ ሙቀት እንዲብላሉ ፤ እንዲንተከተኩ—ምድጃዎ
ተለኩሰዋል ። የተንቦገቦገ እሳት በመልቀቅ በቤተ ሙ
ረቱ ወበቅ ቢፈጥቁም ፤ የተሰማው የለም ።

«እ... እ... ከመረጥናቸው ዕፀዋት የተመዘመዘ
'ኢክስትራክት' የተደረጉት ውሁዶች ፤ የኤድስን ቫይ
ሶች በማያዳግም ሁኔታ ለማጥፋት ተስፋ አላቸው ። የ
ኛው የውሁድ ጥንቅር ፤ ቫይረሶች ላይ ሲያርፍ የማ
ፋት አቅሙ የሚያንስ ቢሆን የውሁዱን መዋቅራ
ቅንብር መቀየር ይቻላል ... እንግዲህ ፋይዳ ያለ
ዋል የምንለው ፤ መጥነን የቀመርነው ውሁድ መ



ብው እካል ሕዋሳት የማያጠቃ ከሆነ ነው ... ስለ
ዚህ የበኩልዎን ግጢታለያ ሙከራ መቀጠል ይችላሉ ፤
'ፊስንትሊይ' የተመዘገቡትን 'ፋክትስ' በተጨማሪ እዘ
ጋጅቼአለሁ ፤» ብሎ ወደ ቤተ ሙከራቱ ሠራዊት ተመ
ለሰ—ዶክተር ክታቡ ።

ፕሮፌሰር ፤ በዚያ ውቃ በመሰለው መነጽራቸው ፤
የተንዘረፈፈውን የዶክተር ክታቡን ነጭ 'ጋውን' ተመ
ለከተው ... የመመራመርን ፤ የተሸሸገ የማወቅን ፤
የተቀበረ የማውጣትን ፤ የተሸፈነ የመግለጥን ... ሕይወት
ሙሉ የተቀበሉ ፤ ለዚህ የማይበርድ ፍቅር የነበራቸውን
ሊቃውንት አስታወሱ ።

... ኒውተንን ፤ ዳርዊን ፤ ኤድሰን ፤ ፓቭሎቭ ፤ አይን
ስታይን... ወደ ምርምሩ ሲያተኩሩ ፤ የፕሮፌሰሩ ልብ
እየፎከረ ... እየዘፈነ ... እየሸለለ ተንጣጣ ። ከአናታቸው
ላይ ችፍ ችፍ ያለ ላብ ሸፈናቸው ። በውስጣዊ ጉጉት ፤
ሲቃ ተገፍቶ የሚፈናጠር ይመስላል ።

የንጥረ ነገሮችን ምንነት ፤ የውሁዶችን መዋቅር
ቀንቀኖ ፤ ፈጣን የማመሳከሪያ ምላሽ በሚሰጠው ልዩ
መጣሪያ ፤ የቀረበውን ውሁድ—ፕሮፌሰር ተመለከቱት ።
ደውንታ በመስጠት ፤ የተገኘውን የውሁድ መዋቅራዊ
ቅንብር አጸደቁት ።

ዶክተር ክታቡ እንደገና ወደ ፕሮፌሰሩ ተመለሰ ፤
«በያንዳንዱ ንጥረነገር እንዲሁም ውሁድ ላይ
የተከናወነው የመዋቅር ጥናት ሪፖርት ይገኛል ። ከዶ

ክተር አቡበከር የተላከው የቫይረስ ስብስብ ተዘጋጅ
ቷል . . . 'ቴክኒካሊ' የጐደለ ነገር የለም . . . ከፈለጋች
ቢሮዬ ነኝ » ሲል ዶክተር ከታቡ ሁለት ሰዓ
ሊሆን ተቃርቦ ነበር ።

የቤተ ሙከራቱ ሙያተኞች የየድርሻቸውን አጠ
ቀው ተራ በተራ ወጡ ።

ፕሮፌሰሩ የቀረበውን የቫይረስ ስብስብ በማ
ያመች መግሪያ ውስጥ አኑረው ተዘጋጁ ። የሥን ሕይወ
ጠበብቱ ዶክተር አቡበከር በኤድስ ከተለከፉ ሕሙ
ተኞች ለሙከራት (ኢክስፐሪመንት) የሰበሰበውን የኤድ
ቫይረስ ናሙና ፣ ፕሮፌሰር አሸብር ፍተሻ እንዲያ
ርጉበት ልከላቸዋል ። ይህ ስብስብ በውጭ ሀገር ዩኒቨር
ቲዎች ተመርምሮ ፣ ለሙከራ አመቺነቱ ይሁንታ አ
ኝቷል ። በዚህ ላይ ስኬት መቀዳጀት ማለት ፣ ዓለም አቀ
ተቀባይነት ያለው ገድል በሳይንስ አውድማ ማስገኘ
ማለት ነው ።

ፕሮፌሰር ፣ ስለ ውሁዶች መዋቅራዊ ይዘት የ
ቡትን ዘገባዎች በድጋሚ ከለሱ ። ማጠቃለያ (መመ
ነጥቦችን መሠረት አድርገው የየደረጃውን ለውጥ አመ
ከቱ ።

የኤድስ ፀር የሆነውን ውሁድ ይዘታ ደጋግመ
በማጤን ፣ ቫይረስ የማጥቃት ኃይል በማያዳግም ሁኔ
እንዲያገኝ ፣ አንዳንድ ለውጥ በመዋቅሩ ውስጥ አደረገ
በማያያዝም የሰውን አካል የመከላከል አቅም (ኢም



http://ethioliberty.wordpress.com/

ሲስተም) እንዲያገናኝ ድጋፍ የሚሰጠውን ንጥረ ነገር አያ
ልብተዋል ።

ዳግም ያዘጋጁትን ውሁድ በልዩ መግሪያ አረጋ
ግጠው ፣ በቫይረሶቹ ላይ ሞከሩት ። በየደረጃው የሚሆ
ነውን ፣ ተያይዞ የሚከሰተውን መመዝገብ ጀመሩ —
በማይክሮስኮፕ እየታገዙ ።

ሁለት ሰዓት ተኩል አለፈ ።

ማስታወሻ በመውሰድ ይወራሚሉ ። ኬሚካል የያዙ
ብልቃጦችንና ጠርሙሶችን እያነሡ በመከራው ላይ ማስ
ተከከያ ያደርጋሉ ። በልዩ መግሪያው እያመሳከሩ ፣ ግድ
ፈት ያርማሉ ። በመሐሉ ከወደቀግ ከተቀመጡት ፣ ሦስት
ይሁን አራት ብልቃጦች ተደፋፍተው ወደቁ —መሬቱ
ላይ ተከሰከሱ ። የፕሮፌሰሩ ሐሳብ እንዳለ በምርምሩ
ተውጧል ። ስለዚህ ፣ የወደቁትን አላስተዋሉም . . .
ውጤት ! . . 'ውጤት ! ይጠብቃሉ ።

የመከራውን ውጤት በማይክሮስኮፕ አትኩሮት
ሲመለከቱ ወደ ሞት የቀረቡ ባይረሶች ጥቂት ነበሩ ።
«ዕውነትም ፈውሱ ሊያስተማምን ነው !» ብለው ገመቱ ።
የቫይረሶቹ ሞት የመከራውን ስኬት ማረጋገጥ ጀምሯል ።

. . . በቅጽበት ፕሮፌሰር ማተኮር አቃታቸው ፣ ያል
ታሰበ ማቅና ደስታ ዋጣቸው . . . ፍንድቅድቅ . . . ፍንድ
ቅድቅ ።

http://ethioliberty.wordpress.com/

በሕይወታቸው ፍርስ እስኪሉ ድረስ እንዳያ የሣቁበት ፣ የተደሰቱበት ጊዜ—ትዝ አይላቸውም ። በምርምራቸውም ትልቁን ውጤት ስላገኙ ይሆን? ፈውስ—አድስን ፤

«ቃቃቃ!...ካካካካ!...ቂቂቂ!» ሣቅ በሣቅ—ቀጠሉ...

ስሎሜ መዝገቡ እሳት ለብሳ እሳት ጉርሳ ቢጢን እስከትላ ቤተ ሙከራቱን በርግዳ ገባች ። የቢጢ ልደት እንዳሰበችው ባለመከበሩ ቅር ተሰኝታ ፣ ቁጣዋን ለመግለጥ ተቻኩላለች ።

ወዲያው ፕሮፌሰርን እያየች አብራ መሣቅ ያዘች— ቁጣው ቀርቶ ። ቢጢም ተፍነከነከች ።

...ሰስቱም እየተያዩ ይስቃሉ—ፍርስ እስኪሉ ድረስ «ቂ ቂ ቂ ቂ!..ካ ካ ካ!...»

ቆይቶ ፣ ዶክተር ከታቡ መንክር ፤ « ምነው ፕሮፌሰር ዝም አሉ ?...የት ደርሰው ይሆን ?...» በሚል ስሜት ሲመለስ ፤ አብሮ ሣቅ በሣቅ ሆነ ።

...ከብዙ ሰዓት በኋላ ነው ፣ «ናይትሮጂን እና ኦክሲጅን» (ናይትሮ ሰክሳይድ) የተቀላቀሉበት ፣ የሚያሥቅ ውሁድ ከተሰበሩት ብልቃጦች በአንዱ ውስጥ መኖሩን የተረዳው— ዶክተር ከታቡ መንክር ።



# ሽ ባ ዋ

ደብዳቤውን አንዴ ካነበበ በኋላ ቀና አለ ። በግንባሩ ላይ የሚወርደው ትልቁ የደም ሥር ፣ እንደ ወፍራም ቱቦ አብጧል ። ትንፋሹ ቁርጥ ቁርጥ ይላል ። ልቡ ከቀኝ ይመታል ። ብው !..ያለ ቃጠሎ ፣ የሥራ አካላቱን አልብሶታል ።

ዓመል ያህል በክፍሉ ውስጥ ባለው አንሰተኛ መስኮት ፣ ወደ ውጪ ተመለከተ ። ሆኖም አያስተውልም ። ዐይን ብቻውን መች ያስተውላል ! ልብ ሲሸፍት ፣ ምድር አቋርጦ ፣ ባሕር ውቅያኖስ ተሻግሮ ወደ መጣበት ሲመለስ ።

...ለዚያውም በንዲህ ዓይነቱ የሕይወት መርዶ ሲሸበር ።

ከዚያ ፣ ሞስኮ መንግሥታዊ ዩኒቨርሲቲ ማደሪያ ክፍሉ (ዶርሚተሪ) ውስጥ ብቻውን ቆሟል ።

ውጪው በበረዶ ተሸፍኗል ። ንጣቱ ነጭ ወረቀት ይመስላል ። ወቅቱን « ዚማ » ይሉታል— አገሬዎቹ ።

http://ethioliberty.wordpress.com/

የዘንድሮው ግን ኃይለኛ ነው ። በወርኃ ጥር ከዜሮ በታች ሐያ አምስት ዲግሪ ሴንቲግሬድ ቀዝቅዞ እግንት ይወጋል ። ብትን ጥጥ መስሉ የሚወርደው በረዶ የቀኑን ብርሃን ደንገዝገዝ አርጎታል ። ከተማውንና ሰማዩን አጋጥሞታል ።

ያ ብቻውን በክፍሉ ውስጥ የቆመው ጉብል ደርሶበት በሚያውቀው ቁጭትና ንዴት ነዶአል ። ከረጅም የሐሳብ መንገዱ ሲነቃ ፣ ታላቁን የሌኒን ስታዲየም ፣ የበረዶው ብናኝ ሲከልለውም ፣ አቀራርጦ ተመለከተው . . . ወደ ሰማይ የቀረቡ ፣ በበረዶ የተከለሉትን ፎቆች ለደቂቃ ካገሩ ደሳሳ ጐጆ ጋር እንደ ማነጻጸር አረገው ።

. . . ሰባት ዓመት በቆየበት ከተማ የማያውቀው አዲስ ትዕይንት ከፊቱ የተደቀነ መሰለው ። ይህን ለማውጠንጠን ፋታ አግኝቶ ሳይሆን ፣ በደብዳቤው ስለ ተረዳው አስደንጋጭ ጉዳይ የሚያደርገው ባለመኖሩ ነው ።

. . . ከርቀት በሚታዩ የእግረኛ መንገዶች ፣ አደባባዮች . . . አገሬዎቹ በርኃታ ይራመዳሉ ። ሕፃናት ይጫወታሉ ። ጉዳይ ኖሮት ከሚጣደፈው በስተቀር ። ግግር በረዶው ላይ መርገጥ ፣ መንከባለል— ልምድ አድርገውታል— አፍኝ በረዶ እያነሱ ሲወራወሩ ፣ ካንዱ ካፖርት ላይ ተፈረካክሶ ሲበተን ፣ እንደ ፈንዲሻ ይፈነድቃል ። በዚህ ይጫወታሉ ፣ ይደሰታሉ ።



ይህ ሁሉ ያለ ሙቀት ልብስ የሚቻል አይደለም ። ነጠላ ወይም ጥንድ ካልሲ ፣ በላዩ ላይ «ቡትስ» ወይም ቁርጭምጭሚት የሚሸፍን ሙቀት ፈጣሪ የበረዶ ጫማ ይጠለቃል ። ሱሪ ይለበሳል ። ለቀሚስ ሲሆን እንደሱሪ የሚሆን ወፍራም የእግር ሹራብ ወገብ ድረስ ይደረጋል ። ካናቴራ ይኖራል ። ሸሚዝና ሹራብ ይጨመርጋል ። ከከረባት ሌላ ፣ ዘና ያለ ኮት ይለበሳል ። ወፍራም ካፖርት ከላይ ይደረባል ። በአንገት ከጥጥ ወይም ከእንስሳት ፀጉር የሚሠራ «ሻርፕ» ይጠቀለላል ። ለበረዶ የተዘጋጀው ኮፍያ ፣ የጳጳስ ቆብ የመሰለው «ሻብካ» የሚሉትን መድፋት— ግዴታ ነው ።

ለሁለተኛ ጊዜ ፣ የተጣጠፈውን ደብዳቤ ገለጠው— ደንበል መኮንን ።

ይህን ደብዳቤ ያመጣለት ማስረሻ ነበር ። ሦስተኛ ዓመቱን ያጋመሰ ፣ የፖለቲካል ኢኮኖሚ ተማሪ ነው ።

ማስረሻ ለደንበል የመጨረሻ ወዳጅ ፣ የቅርብ አጫዋች ነው ። አይለያዩም ። ስለ የሐሳብ ልውውጥ ያደርጋሉ ። ልብ ለልብ ይተዋወቃሉ ። «ፓርቲው በታ አብረን እንሔዳለን . . . ይህን ከፖስታ ቤት ነው ያገኘሁት ... ብዙም አልቆይም— እመለሳለሁ ... 'ፓንያትኖ' ግባህ !» ብሎታል— ማስረሻ ደበበ ቅድም ደብዳቤውን ይዞ ሲመጣ ።

http://ethioliberty.wordpress.com/

በዩኒቨርስቲው ውስጥ የሚገኘው ፖስታ ቤት ፣ ተማሪዎቹ የተጻፉ ደብዳቤዎችን በሀገር ፣ በውጭ ሀገር ለይቶ ያሠራጫል ። ተቀብለው ለተጻፈላቸው የሚያደርሱት ከየሀገሩ ተማሪዎች ተመርጠው— የፖስታ ወኪል የሆኑ ናቸው ... እያንዳንዱ ተማሪ በፖስታቤቱ በኩል ሲያልፍ አንዳች ስሜት ፊቱ ላይ ይነበባል ። ይህ ግልምጫ ፣ ስውርም ይሆናል . . . ብቻ ያስታውቃል ። ሁሉም በጉራ የሚታዩቸው አለ ። ሀገራቸው ፣ የትውልድ በታቸው ፣ ቤተሰብና ቤተዘመዶቻቸው ፣ ፍቅረኞቻቸውና ጓደኞቻቸው... የፖስታ ቤቱም መስኮት ወደዚያ የሚወስድ ይመስላቸዋል ።

ዩኒቨርሲቲውንና ትምህርታቸውን ያልጨረሱት ተማሪዎች በመተባበር የመሸኛ ፓርቲ አዘጋጅተዋል— ጥናታቸውን አጠናቀው ለሚመለሱት ። የጋና ፣ የቪዬትናም ፣ የአፍጋኒስታን ፣ የኮንጎ ፣ የኢትዮጵያ ፣ የሴኔጋል ፣ የኮሎምቢያ ፣ የጃማይካ . . . የሌሎች ሀገሮች ተማሪዎችም ይገኛሉ ። ዕለቱ እሁድ ስለሆነ ፣ ከሉሙምባ ዩኒቨርሲቲና ከሌሎች ተቋሞች የሚመጡ የውጭ ሀገር ተማሪዎች ይጠበቃሉ ። ፓርቲው የጦፈ ይሆናል ተብሎ ታስቧል ።

. . . ማስረሻ ከልቡ አዝኗል ። ደንበል ወደ ሀገሩ በመመለሱ ተከዟል ። ተቆጪው ነው ! መከራው ነው ! ማስረሻ ፣ ትዝታና ናፍቆት ሲያጠቃው ፣ የሀገር ቤት ሕይወት ውል ሲልበት ፣ ፈጥኖ የሚጫወተው ከደንበል ጋር ነው ።



ይሄኔ የልጅነት ትዝታዎቹን ፣ የቤተሰቦቹን ፣ የጓደኞችን የፍቅር ጀብዱ ፣ የወደፊት ምኞታቸውን ... እየደጋገሙ ያወጋሉ ። አንዱ ሲተርክ ሌላው ያዳምጣል እግረ መንገዱን ትውስታ የፈጠረበትን ጫፍ ይዞ ይናገራል ። በማላገጥም ፣ ተቃልደው ፣ ተማምቀው ይለያያሉ ።

ማስረሻ ፣ «ይሄ ደንበል ሀገር ቤት ሲመለስ እንዳይረሳኝ ፣ አንድ ነገር ማድረግ አለብኝ ! . . .» እያለ ሲፎክር ቆይቶ የደንበል መመለሻ ደረሰ ።

በዓለም አቀፍ ሕግ ጥናት ፣ ከፍተኛ ትምህርቱን ዳር አድርሷል— ደንበል መኮንን ።

ደብዳቤውን ዳግም ማንበብ ጀመረ ።

የተጻፈበት ቀን ፣ ከወር በፊት ነው ። «እስቲ ... ደብዳቤው አንድ ቀን ቢያደርገኝ . . . እዚሁ ቀረ ነበርኩ ይገርማል ! . . .» እያለ ንባቡን ቀጠለ ።

ይድረስ ለደንበል !

ላንተ ያለኝ ፍቅርና አክብሮት ለመቼውም ቢሆን የሚታጠፍ አይደለም ። በቅርቡ ትምህርትህን ጨርሰህ እንደምትመለስ ሳስብ ፣ እንደምንገናኝ ሳልም — ደስታ በደም ሥሮቼ ይሠርጻል ። የልቤ ምት ይጨምራል ፣ ሐሳቤ በጥልቀት ይመሰጣል ።

የኔ ጌታ — ለፍቅርና ለመውደድ በምድር ላይ ያለኸኝ አንተ ብቻ ነህ ። ስንት መቶና መቶ ጊዜ ነው—

ይህን የምናገረው ! ስደጋግመው ብኖር አይሰለቸኝም ። በሕሊናዬ ባሰብሁህ ቁጥር ፣ በወደፊት ኑሯችን ጥሩ ዕድል እንደሚገጥመን እመኛለሁ ።

መንፈስህ ሁል ጊዜ ይከተለኛል ፣ ይሰማኛል። እስ ዛሬ የላካቸውን ደብዳቤዎች ፣ ፎቶግራፎች ፣ ስጦታዎች... በጥንቃቄ ነው — ያስቀመጥኳቸው ። ሐሳብ ፣ ናፍቆት ሲበናብኝ እነሱን ማገላበጥ ፣ ፎቶግራፍህን መሳም ትዝታዬን ይከፍልልኛል ። ጉዱ ሆነህ ፣ ረዥሙ ጸጉሬን እያሸህ 'እወድሻለሁ' የሚል ዓይነት . . . እግዚኦ !

ይህን ያህል ዓመት በቁርጠኝነት ታግሼ እንተን መጠበቄ ፣ ያኮራሃል — ብዬ እምናለሁ ! ግን ችሮታ ይህን ውለታ አልጠይቅበትም ። ዓላማ ኖሮት የቆረጠ ሰው በምድር ላይ የሚሻውን ለማግኘት የማይችልበት ምክንያት የለም ።

'ጣሩ ታገኛላችሁ ፣ ታገሉ ይሳካላችኋል' — ቢሆን አትቀበልም — አባባሉን !

የጀመርኩትን የሥራ ልምምድ እያገባደድኩ ነው ። ቀጥሎም በሒሳብ ሥራ ያሰማሩኛል ብዬ እስባለሁ ፣ ቤተሰቦቼ እየረዱኝ ነው ።

ብቻ የነሱ ነገር ከተነሣ ፣ እንተን የሚያስከፉ ጉዳይ ለመፈጸም እየተራወጡ ነው ። ንዴቴን መቆጣጠር አቃተኝ ፣ ሥራዬ በንባ መታጠብ ሆኗል ።



http://ethioliberty.wordpress.com/

ምን መሰለህ ? እንዳርገኝ ነው — የሚሉት ። አንድ በሆን ሰውዬ ነው ፤ ቤትም መኪናም አለው ። ሥራው ንግድ ነገር ይመስላል ።

ካንተ ጋር እንደሆንኩ ሳስረዳቸው ብሞክር ፣ ላግባባቸው ብፈልግ ፣ 'የምጠብቀው ሰው አለ' ብልም — ሊቀበሉኝ አልቻሉም ። እስካሁን ዝም ያልኩት እንዳትደናገጥ በማሰብ ነበር ። አሁን ግን ገፍተው ሲመጡ ፣ የግድ ላንተ መግለጽ አለብኝ ።

በሽማግሌም ተነጋግረዋል ፣ ሌላውም ዝግጅት ስለ ተጋመሰ ፣ ይህ ደብዳቤ እስኪደርስህ ሁሉም ይፈጸም ይሆናል ።

የኔ ጌታ

ለዘለዓለሙ ግን ያንተው ነኝ !

አፍቃሪህ

ሰብለ ሕይወት ካሴ

የተቀየበ ነው — ሰብለ ሕይወት አልፎ አልፎ የምታደርገው ።

«ወይ ነዶ !...» ሲል ደንበል ፣ የደም ሥሮቹ ግትርትር አሉ . . . እልህ ፣ ብሽቀት ፣ ምሬት አካላቱን ተገትቶት ። ተዘውረው ቀጠቀጡት ። ቆሽቱ ድብን አለ ... በቀልና ተስፋ መቁረጥ እየተፈራረቁ አንጎሉን በጠበ

http://ethioliberty.wordpress.com/

ጡት ። እጇ ሲንቀጠቀጥ ፣ እግሮቹ መብረክረክ አዛቁ ሙም ። ከድጋሚ ንባቡ በኋላ ጭራሽ አንገሸገሸበት !

«ሰብሲቲ ... ሰብለ ... ሰብለ ሕይወት ... በሰው ሀገር ፣ ትምህርት ፍለጋ ስንገላታ ፣ ስወድቅ ስነሣ ፣ እንቺን እንዲን ... የውበት ፣ የድምቀት ... የሕይወት ተስፋዬን ሲቀሙኝ ? ... እናት ... አባት ... ዘመንና ሰው ከ ብሎ በሕሊናው ጮኸ ።

ሆዱን እያከከ ኖር ፣ ቦርጭ ቢጤ ማል ባለበት ሰውነቱ የለበሰውን ሸሚዝ ቁልፍ ሲፈታ ፣ ነጭ ክናቴራ ታየ ። በሰማያዊ ላይ ነጭ ማል ፣ ማል ያለበት ክራቫቱ፣ ተጠምልሏል ።

ለደንበል ፣ ሆድን እያከኩ ክራባት መጠምለል ፣ ለፍሥሐ ይሁን ፣ ለመሬር ብስጭት አንድ ናቸው — እያለ ወጤ ። ከጓደኞቹ ጋር በቀልድ ሲወራረፍ እንኳ ፣ ከፊል በራው ላይ የተተከሉ የሚመስሉ ዐይኖቹን ፏ እርጉ ሆዱን ማከክ ይጀምራል ፤ «ደንበል የእንጉሱን መዘወር መጠምዘዝ ጀመረ — ማሰቡን» ይሉታል ።

እዚያው እንደተገተረ ግማሽ ሰዓት ቢያልፍም ፣ አምስት ደቂቃ የቆመ አልመሰለውም ። ማበረኛ አለተ መሰሰም ።

«መሆን ወይም አለመሆን !» አለ ፣ ታዋቂውን የሼክሴት አባባል በሕሊናው እንደ ገደል ማሚቶ እያስተጋባ፣

«ምናባቱ ! በመሰከት ወርጄ ወዲያ ብንሳንለው፣ ይሻለኛል !» የሚል ሐሳብ ከች አለበት ። በርግጥ ጀግና



ፎቅ ላይ ነው — ያለው ። «በቃ አለቀ ፣ ደቀቀ ! ... እሷ በሌለችበት እንዴት ! እንዴት ! እኖራለሁ ? ምን ሕይወት ነው ? ... የሰባት ዓመቱ መሊያየት ፣ የሰቆቃው ናፍቆት እንስ አሁን እስከነጭራሹ ልገላገል ? ... ዐይኔ እያየ ! ... ጭለማ ! . . .»

በዚህ ሐሳብ ናላው ጭው ብሎ ሲዞርበት ፣ ለወንዙ ራቅ ከሆነ ድልድይ ላይ ወደታች የሚመለከት ሰው ሲሚት ተፈጠረበት ። ሰውነቱ ዛለ ። ከኋላው ወዳለው ፎቁ ወንበር ራመድ ሲል ፣ 'ወፈ ቆመች' እንደሚል ልባ ልጅ ተብረከረከ እየተንገዳገደ አለፍ ብሎ ፣ ዘፍ አለ ። ፊት ለፊት ባለው አልጋ ላይ መንጋለል ፈልጎ ነበር ።

ጥናት ከሚያጠናበት ጠረጴዛ ላይ ፣ ትልቁን ባለቀለም የሰብለ ሕይወት ፎቶግራፍ ተመለከተው ። ወርውሮ የአመድ ብናኝ ሊያረገው ፈለገ — « እንቺ እምቢ ብትይ ፣ መች ይህ ጉድ ይመጣ ነበር !» በሚል ስሜት። ... ትንጣት አቅም አጣ . . . እሷ ግን ዐይን ፣ ዐይኑን ታየቃለች ።

«እንግዲህ ምን ይደረጋ ? ... ዛሬ አሞኛል ብዬ ሪፖርት ማድረግ ፣ የነገውን በረራ ማሰለወጥ ፣ በመሐል መላ መፈለግ . . .» ሲል አሰበ ። ጉዳዩን ለዩኒቨርሲቲው ኃላፊዎች እንዴት እንደሚያስረዳ ማውጠንጠን ጀመረ ።

http://ethioliberty.wordpress.com/

በጣም በዝግታ መንፈሱ ተመሰሰ . . . እንደ ቆሰለ አባብ አንገቱን ደፋ ። ደብዳቤውን አጣጥፎ ፖስታው ውስጥ ከተተው ። አጣበቀው ።

የሰብለ ሕይወት ይሁን የሱ አድራሻ በትክክል ተጽፎአል ። ያገር ቤት ነው— ኢትዮጵያ— ይላል . . . ግን የተደረገው ማኅተም ከቴምብሩ አልፎ ፖስታው ላይ አልዘለቀም ። . . . ካገር ቤት አልተላከም ።

«ማስረሻ ደበበ ? ! . . . » እያለ በ'ኮሪዶሩ' ሲሮጥ— ደንበል ፣ ለዓመታት ወዳጁ የነበረውን— ሲርጌይ ዲምትሪዮብ— ቃል ሳይተነፍስ አለፈው ።

« . . . ሽባዋ . . . ማስረሻ . . . ሽባዋ ። »



# ወይኔ ልጅነት !

እንዲህ ጊዜው ቢያልፍም ፣ ያለፈውን መልሰው ሊያወሱት ቀላል አይሆንም — የሚያስደስት . . . የሚያስከፋ . . . የሚያስቆጭ . . . የሚያስቅ . . . የሚያቆስል . . . ምን ዓይነት ልብሰው ? . . . እንዲያው ቃላት ተሳክተው ፣ ዐረፍተ ነገሮች ተኮልኩለው የማይገልጹት ፣ ልውጥውጥ ስሜት ያጭርብኛል ። ከሕዋሳት— ስሜቴ የሚገነፍሉ ትኩስ የስሜት ዘለላዎች ፣ ከትዝታ ቀር እየተንጠባጠቡ መንፈሴን ያምሱታል ። እንዱን— ማንሣት ፣ ሌላውን— መጣል . . . በሐሳብ መብከንከን ነው— ድርሻዬ የሆነው ።

ልንገራችሁ ። ላዋያችሁ ። ሲወጣልኝ ይቀለኛል እንደሁ ።

በጠባብ ጭንቅላቴ ፣ ባልፋፋው እስተሳሰቤ ሕይወትን ተርጉሜ ለመተቸት ፣ ለመፈላሰፍ ይቃጣኛል። ሲለው ፣ ተመራማሪ ይለኛል ። ዕውቀት በወጉ ያልቀመሰው አንጐሌ ከመጫጫቱ የተነሣ እምቡር ... እምቡር ይላና

የትም ሳያደርሰኝ ራስ ምታት ይለቅብኛል ። ይሄኔ . . . «ምናባቴ ! የምን እበሳ ነው ?» ብዬ እርግፍ አርጌ እተወዋለሁ ። ታዲያ እንዳመረቀዘ ቁስል ጊዜ እየጠበቀ የሕሊናዬን ሥርን ይዞ እንደምላችሁ ያናግረኛል ።

ልንገራችሁ ። ይወጣልኝ ።

እንደኔ ከሆነ ፣ ልጅነት በጨቅላና በጉልምስና አስተሳሰብ መካከል የሚደርቁበት ዘመን ነው— የሚፈነድቁበት ። ለነዚያ የጨቅላ ዓለም ድርጊቶች ደግ ይሁን ክፉ ይቅርታ አደርጋለሁ ። ያኔ ፣ ንጹሕ ልብ ... ፍቅር . . . ወዳጅነት . . . በላዩ ነግሠው ነበር ።

በወጣትነት የፈጸምኳቸው ግድፈቶች ግን ፣ ጠባሳ ጥለውብኝ አልፈዋል ። እነሆም ፣ ከዓመት ዓመት እንዳልተዘጋ ሒሳብ ተንከባለው ለሥቃይ ረመጥ ዳርገውኛልና መዘንጋት ያዳግተኛል ።

ያለፈውን አስቀያሚ ክስተት ፣ ተራ ብሽቀት ይመስል ወደ ጐን ማድረግ አልተቻለኝም ። ስለዚህ ፣ ቁጭ ቁን ዘንግቼ ፣ እርድ ብዬ እንዳልቀመጥ በኃይሉ ተፈንቅሎ እየወጣ ፣ ከቁጥጥሬ እያመለጠ መንፈሴን ጠቅጥቆ ያሳሳቀዋል ። እንደኛውን ወደ ፍምነት ተለውጦ — እያጥሉ አልጨረሰኝ ፤ አሊያም ረመጡ ጠፍቶ— ሰላም አልሰጠኝ ... ብቻ ንቁ እሳት ገሞራ ሆኖ ያናውጠኛል ።

ይህም አላርፍ ብሎ ሲነሽጠኝ ነው— ባለፈው ውስጥ መኖርን ፣ መመላለስን የምመርጠው ።



http://ethioliberty.wordpress.com/

. . . በትዝታ ዓለም . . . በሕልም ዓለም . . .

እግረ ሕሊናዬ የተመለሰውን ያህል ወደ ልጅነቴ ፣ ወደ ወጣትነቴ ፣ ወደ እማዬ እቅፍ መልሶ እንዲያደርሰኝ እማፀናለሁ ። ይህ ስሜት ሲያሸንፈኝ ፣ የኔ ነገር የማይሆንላት እማዬ «እሽሩሩ ... ሩ! ... እሽሩሩ ! ... ሄዴ ጮርቃዬ» የምትለኝ ፣ ተገልጦ ይከሰትልኛል ። « ይቺ ዓለምስ ... ለምን እንደ እማዬ አትሆንም ? ለምን በእቅፏ ይዛኝ አታባብለኝም ? ለምን 'የኔ ልጅ' አትለኝም ? ለምን ታቁርጸኛለች ? ... » እንዲህ እያልኩ በሐሳቤ ስማስን ፣ ለወደፊቱ እንዳች ብርታት እንደኛለሁ ባልልም ፣ መንፈሳዊ እርካታ ይጠጋኛል ። «የሆነው ሆኗል ! ... ያልሆነው አልሆነም ! ... ይኸው ነው ! ... በቃ! » ይለኛል ግምቴ ።

ልንገራችሁ ።

ትዝታዬን እንደ ብረት የሚያጠነክሩ ፣ አንዳንድ ቁሳቁሶች እጠገቤ ሲኖሩ ልቤ ይቆማል ። ትዝታዬም ቀንድ ያወጣል ። አልፎም ህልውናዬን ያስክደኛል ።

ፎቶ ግራፎች አሉኝ ። እንደ ነገሩ በአልበም አርጌአቸዋለሁ ። የጓደኞቼ ፣ የዘመዶቼ ስጦታዎች አብረውኝ ናቸው ። እንዳይለዩኝ የምፈልጋቸው የሙዚቃ ካሴቶች ጠፍተው ፣ ጉትጉትና ሠቀቀን እንዳይገለኝ አሳሳለሁ ። ይሁንና ፣ ከሆይነቱ ዕቃዎች ተፈትለከው ያጣኋቸው ፣ ሰዎች አውጁን ብለው ቀልጠው የቀሩብኝ በቁጥር አይደሉም ።

http://ethioliberty.wordpress.com/

የሚነገርመኝ ፣ ለምን እንደ ሰበሰብኳቸው አይገባኝም ... በሔድኩበት ተከትለው መንፈሴን እንደ ላስቲክ ይወጥሩታል ። እንደ ፊለጉት ሐሳቤን አመሳቅለው ሰላም ይነሡኛል ። ልሸኛቸው እስብና ከየሥርቻው ፈላልጌ ፣ አወጥቼ ለወረውራቸው እዘጋጃለሁ ። እነሱን በማጥፋት የመንፈስ ነጻነት የምቀዳጅ ፣ የትዝታን ባርነት የማሽቀንጥርና በእርንት የምተካ ይመስለኛል ። ወዲያው ሌላ ጥገደኛ ሐሳብ ይወረወርና «... ለምን ? ለምን ! ... እንቺ ቀልበ ቢስ !» እያለ ይኮረኩመኛል ።

አሁን አቅም የለኝም ። ተሳክሜአለሁ ። ከመንፈሴ ተምዘግዝጐ ይወጣ የነበረው ጥንካሬ ከድቶኛል ።

... ኤጭ ! ይህ ከምላስ የቀጠነ ፍራሽ ደግሞ ... ወለል ላይ ሊያነጥፉትማ አይመችም ። ቀረቀረኝ ... ቆይ ትራሱን ከሥሬ ላርገው ፣ አሁን ይሻለኛል... እርይ !

እናም እኒያ በመንፈሴ የሚጫወቱትን ቁሳቁሶች ፊት ለፊቴ ደረደርኳቸው ... ምን ላድርግ ?

ልንገራችሁ ። ይወጣልኝ ። እስከ መቼ አፍኘው እኖራለሁ ?

★ ★ ★

... ይሄ የስድስት ዓመት ፎቶግራፌ ነው ። አጭር ፣ ወፍራም ነኝ ። እንገሬ የደጋን ቅርፅ ነበረው ። አይ ዐይ ንና አፍንጫ ! ... እርስ በርሱ ተንባብሮ በየት በኩል



ይለያል ? ተድቦልቡያለሁ ። አይ ጊዜ ! ... እንደልብ የሚዘለልበት ነበር — የየዕለቱ እንጂ የጓሲዮሽ ይሁን የወደፊት ምናም የሌለበት ። በራስ ውስጥ ደስታ መፍጠር ፣ ጥባቢ ደስታ መፍጠር ... እንደዋዛ ሁሉም ደስታ ይሆናል ... ደርሶ ፍንድቅድቅ ማለት ። ልጅነት ።

መጅጆተ — መውደቅ ... ማልቀስ ... እባብሉኝ ማለት ... መምለቀቅ — እንደኛው ገጽ ነው ። ወዲያው ደግሞ ፣ ጠብ ያለች ምራቅ ሳትደርቅ ... መደባደብ ... መዛት .. ማኩረፍ ... መጠፋጠፍ — ሌላው ገጽ ይገለጣል ። በዚህ ብቻ መች ያበቃና ። የነበረው እንዳልነበረ ይሆናል ። ሽኩቻውን ወደ ጐን እርግፍ አርጐ — መታረቅ ! እጅና ጓንት ይመስል — መተቃቀፍ ... እንከኩ በሉኝ ! — ሁሉም ተረስቶ ይመጣል ።

'ልጅነቴ ! ... ልጅነቴ ! — ማርና ወተቴ ...' ይዘመራል ።

አይ ፆ ድንቅ ዘመን ! ምናለ ሁሌ እንደዚያ ሆኜ ብኖር !

አ ! ይሄኛው ደግሞ ሚኒስትሪ ልንፈተን ስንል የተነሣነው ነው ። አቤት ... ምንኛ ደስ ይላል !

ሰላማዊት ፣ እልፌ ፣ ሰሚራ ፣ ከፈለኝ ፣ ምሥራቅ ... ስውነት ይሆን ያሀል ደስ እንላለን ? ... አይ ! የውሪ ዓለም ምኑ ያስደስታል ? ... እም ! የትምህርት ቤታችንም አጥር አብሮ ይታያል ። ዘበኛው ጋሼ ይላለኝ በሬ

ፈደብን ቁጥር እዚህ ነበር የሚያንበረክኩን ። እይ ዲዲ ... ልጆቻቸውንም እንዲያ ይገርፉ ይሆን ? ታዲያ ከዚ ታቸው በላም አልነበራቸውም ። «ከሚስታቸው መንታ ረክ በዝቆባቸው ፣ ግሞቱ ሲካረር ተሰያዩ» — ተባለ ። «አህያውን ፈርቶ ዳውላውን» እንዲሉ ፣ በሚስታቸው የቋጠሩትን ንዴት እኛው ላይ ነበር የሚለቁት — ጋሽ ደሳለኝ ። ጠብጥበው ጨረሱን ... እግዚኦ ! እትምህርት ቤት በየክረምቱ ከሚተከለው ዛፍ ልምጭ እቆርጣለሁ ሲሉ ፣ መዓት ጊዜ ከዳይሬክተሩ ተጋጭተዋል ። እስቲ በገዛ ልጃቸው ! ... ልጆች በመደብደብ እልህ መወጫ ያገኙ ይመስል ፣ ያን ሁሉ ጥፋት መፈጸም ነበረባቸው ?

ውይ እልፌ ! . . ምን ትመስላለች ? ... ኮሳሳ ! እን ዲያው የፊት ቅላት ብቻ ነው — ያላት ፣ ይታወሰኛል ፣ «ሐይ ስኩል» ስትገባ ፣ ባልትና መርጣ ማጥናት ያዘች። የሚገርመው ፣ የባልትና ተማሪዎች እፍኝ በማይሞሉበት ወቅት ደፍራ መግባቷ ነው ። ሌሎቹ ተማሪዎች ፣ የባል ትና ተማሪዎችን ሲወርፉ ፣ «... ወጡ ጣፈጠ ? ቅመም አነሰው ? እንዴ ! ... ጨው በርከት አርጉበት ፣ አልጫ አልጫ እንዳይል ... » እያሉ ሲያፌዙባቸው ፣ ፍንክች የማትለው ዕልፌ ነበረች ። ውስጣዊ የመንፈስ ጥንካሬ ያረገዘችው ያኔ ሳይሆን ይቀራል ? ... ቆይቶ ፣ የሆቴሉ ቺና ቱሪዝም ኮርስ አዲስ አበባ ተከታተለች ። በኋላ «በሆራ ራስ ሆቴል— ደብረ ዘይት ሥራ ያዘች» አሉ ፣



http://ethioliberty.wordpress.com/

ወይ እልፌ ፣ ያኔም « ኢሉመንተሪ » አብረን እያለን ጨዋታ ልታ» ጨዋታ የሚችላት ማንም አልነበረም። ጨዋ ታውንም የተወቸው ልጃገረድ ከሆነች በኋላ ነበር . . . እንዴ የሆንቸውን ግን አልረሳውም ። ማን ነበሩ? ቲቸር አስደስቷፈትና ሰጡን ። ስንሠራ ፣ «ከኛት ደብተራችሁ ትኮርጃላችሁ» ብለው ሁለት ልጆች ከክፍል አባረሩ ። ተናደው እልፌ ላይ እንዳፈጠጡ ቆዩ ። እረፍት ካለው 'ዴስክ' ስለምትቀመጥ ፣ መንቀጥቀጧን ብዙዎቻችን ፣ አይተናል ። ከዚያ እየተጠጋት ... እየተጠጋት ቀርበው ወደኗ ላይ ተደቀኑ ። እጃቸውን 'ዴስኩ' ውስጥ ሰደዱት። ወሬያው በጣታቸው ቦርሳዋን ሲበረብሩ ... ቀርኪ ፣ እኛ ንባቢት ፣ ቅጠላ ቅጠል ፣ የተጠበሰ ጨርቅ ፣ የከረሜላ ልጣጭ ፣ የሲጋራ ፓኮ የ« ቃ' ቃ » መጫወቻዋን ፣ እንድም ሳይቀር አወጡት ።

«ቲቸር ! ... ካቫንጉሊቷ ኮርጃ ይሆናል ! » ሲል እቶ በጩኸት ፣ ክፍሉ ሣቅ በሣቅ ሆነ ። ቲቸር አስረስ እፍረው ቆጡት እንጂ ፣ በልባቸው መንከትከታቸው ያስ ታውቃል ። ዐይናቸው ፈጠ ፣ ተደፈርኩ በሚል መንፈስ ከፈሰኝን በእልህ እንበረከኩት ። ወይ እልፌ ! . . ያ ሁሉ ዝላይ ፣ ጨዋታ ተረስቶ ዛሬ ቁም ነገር ብቻ ሆነ። ልጆች ወልዳ ከብዳ — ቤተሰብ ይዛለች ። ምን ይታሰባት ይሆን፣ ይኛ ሁሉ ትዝ ሲላት ?

እ ሰላም ! ... ሰላምጣ ገና ያኔ ምንንም ሳታውቀው፣ እኛም ምንንም ሳንለይ «ሳይሞቅ ፈላ» ነበረች። እቤት

የፋሺን ነገር ! ፋሺንና ሰላም ስምና ጨርቅ ነበሩ። አነጋገር — ከቧ ፣ አለባበስ — ከቧ ... የሊፕስቲኩ ፣ የጸጉሩ አሠራር አይነገር ! ምን ታርጋ ? እቧ ፣ እህቷ ነች እስታጣቃ የምትልክብን ። እኛም ወይናችንን እያቀለጨለጭን እንቀበላታለን ። በልጅነት ሕሊናችን ፣ የምታሳየንን እናደንቅላታለን ። የምታወራልንን ፣ 'አሜን' ብለን እንቀበላታለን ።

እንዲያው ያኔ «ጂሊ» ለመሆን ለሚፈልግ ፣ የቅርብ መካሪ ነበረች ።

እቦ ዘስንቱን ወንድ ነው — ያደባደበችው ... አካካ ! ... ማን እማኘቷት ! ... ብቻ «ደርስ የኔ ነች ! ብነች !» ባዩ በዛ እንጂ ። ግን ከሁሉም የሚያሥቀኝ 'ሚተራችን' ነው ። ሰውነቱ ግዙፍ ነው ። ዕድሜውም ትልቅ መሆኑ ያስታውቃል ። ወንዶቹ የሱን ግብዳነት እያፍራቻ እንዳያደረባቸው ተረድቶ ፣ «ሰላም የኔ ነች !» እያለ ሲፎልል ፣ መልስ የሚታወመው የለም ። ሰላም እሱቷ በበኩሏ ሌሎች እንዳያስቸግሯት ፣ እይዞህ ትለዋለች ፣ ታዲያ 'ኮ ሽንት ቤት ድረስ ሳይቀር እስከትላው ፣ ይዘተሯን እስይዛው ጉዳይዋን ፈጽማ ትመጣ ነበር። ምስኪን ሁሉን ! ... ጅሉ ! ... የሚያናድደው ለወንዶቹ የሚዘከዘከላቸው ውሸት ነው ። «... ሰላምን እስከ ቤቷ ሸኘኋት ፣ ከዚያ ሻይ ተጋበዝን ፣ አውርተን ሥቀን ተጫዋወትን ። አቤት እናቷ ሲወዱኝ !» ይላቸዋል ። ወገኛ !



http://ethioliberty.wordpress.com/

ሰማና አቶሩን ሳይጠጋ ውኛ እለቅበታለሁ » ነበር— የምትለው ፣ ሰላም ። ያደረገችውን ሁሉ ለኛ ስትነግረን፣ ፍርፍር ብለን እንሥቃለን ... ምስኪን ሁሉን ! አሁን የት ደርስ ይሆን ? ... እንደ ዘመዶቹ ንግዱን ያጧጡፍ ይሆናል ።

ሰላማዊት ባገር ብዙም አልቆየች ። «ሐይ ስኩል» ሳትጨርስ ነው — ዘመዶቿ ወደ አሜሪካ የወሰዷት ። ወደ ትማራለች — ሁኔታው ከፈቀደላት ፣ ወደ በኑሮዋ ትመለሳለች — ሥርቿ ከወደቁት ።

መሚራ ከሁሉም እምርባታል ። እርጋታና ሥርዓት ፊቷ ላይ መፍረጥዋል ። የዋዛ አይደለችም ። እንደቀቅ የንቃች ፣ እንደ ኢሊ የሬጋች ቅመስለኛለች ። ትምህርቱን ስትሸመድድ ፣ እንደ ልማዱ እንደኛ ስትወጣ ፣ «... እኛ ይቅርብን ! እንቺ ብቻ ተማሪ ! ያውልሽ ! ...» ብለን ሳና ስብ እንቀራለን ! — ይገርመኛል ። ለዚህም ነው « ቀለሜዋ» እያልን የምንጠራት ... እንዴ ... የሳይንስ 'ቴስት' ስንወስድ «አላስኮረጅሺኝም» ብሎ ፣ እሸቴ ደም በደም እርጓ የደበደባትን ዛሬም አልረሳውም ። እሸቴ ለራሱ የለየለት ወርበላ ። ብይና ጠጠር ማን ሊያሳድድለት ዋጅል ! ዋርና ቀስት ተጫውቶ የበላውን ብይ በትርፍ ሊቸረችር ፣ ከሒሳቡ ሳንቲም የማያሳልፈው ፣ ከፍል ውስጥ የሒሳብ መልመጃ መመስስ እቅቶት ሲደናበር ፣ ፀይኑ እንደ ብይ ይሽከረከር ነበር ። ምን ያረጋል ? ሰው

ቀትንም ሆነ ጥበብን በዱላ ወይም በጉልበት ሊያስጣው አልቻለም ። ሠሚራን በሥራ ቢያስለፈልፈትም ፣ ጉዳዝናዋን አልወረሰም ።

የሠሚራ ትምህርት በላይ በላዩ ቀጥሎ ፣ ዛሬ ትልቅ ደረጃ ደርሷል ነው — የሚሉት ። ለዛውም ሴት እምብዛም ባልደፈረው በኤሌክትሪክ ምህንድስና መስክ ነው— የገሠገሠችው ። አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ገብታ ስታጠና ብቸኛዋ ሴት ነበረች ። ብርቅም ፣ ጌጥም መስላ ስለታየች፣ ሁሉም ይንከባከቧት ነበር ። ይሀም በትምህርቷ እንድትገፋ አግዟታል ። በሥራ ዓለም ተሠማርታ ረጅም ጊዜ ሳትቆይ የውጭ ትምህርት ዕድል አገኘች ። በዚህ ወደ ስዊድን በመሔድ የዶክትሬት ዲግሪ ተቀበለች . . . ወይ ሠሚራና ዕድሏ ! ሌላ ምን ልበል ? ለመሆኑ ዕድል ይናርበት ይሆን ? አሁን ፣ እንደሷ የተማረ ፣ የተመራመረ አገብታ ትኖራለች ። አቤት ስታስቀና !

እንዲያው ያ ከፈለኝ የት ደርሶ ይሆን ? ... ሰራሱ አፈማጠሩ የሚገርም ነው ። ሥራውም ሒሳቡም ከወንዶች የራቀ ነበር ። በተዉጣጣረ ተዉቀኞችና ከሰው ቀረቤ «ሶሽየብል» የሚባል ዓይነት ነው ። በዚህ ላይ የሴት መዖ ሲበዛ ይቀናኛል . . . እስቲ ከዋት አመጣው ይለኛል ? መቼ ነው ? . . . እንደ የወሏጆች ቀን ተከበረ ፣ የልጅ ሥራ አስተማሪያችን 'ጉበዝ' በማለት ፣ ያመሳውን ተቀብለው ፣ በኤግዚብሽኑ እንዲታይ አደረጉለት ፣ በተከታተ ዓመት ትምህርት ስንጀምር ፣ በትድመሯ በወ



ንዶች ተማሪዎች የተወረፈው ከፈለኝ ነበር ። «እንት አለሽ ! ... ሴት አረክን አይደል ! አሁን ከኛ ጋር እዚህ ምን ትሠራለህ ? ሒድ እናትህ ጓዳ ፣ እዚያ ጥጥ ፍተል !» እያሉ መድረሻ አሳጡት ... አይ ከፈ መያተኛው ! ... የት ነው ያለኸው ?

የምሥራት መድረሻ ብቻ አልገባኝም . . . ነፍስ ያላት ተጫዋች ነበረች ። መጣቅ ሥራዋ ነው ። ሰውነት አትምትቅ ሁሉም ደስ ብሏት ይሆን ? ሲያበሽቋትም ትሥቃለች ። ምን ዓይነት ስጦታ ነው ? አስተማሪ አጠፋሽ ብሎ ሲገርፋት ፣ ከዛም አቀርቅራ በማልቀስ ሲጠባት፣ ሁሉም ትረሳለች ። እንደዚና ማቂታ ፣ ፍልቅልቅ ትሆናለች ። የምትገርም ፍጥረት ! ከሚኒስትሪ ፈተና በኋላ የጠፋ ሽታ ሆነች ። ስለሷ ምንም ፣ ምንም ወሬ አጣሁ !

እኔማ እኔው ነኝ ። ሠርክ ዓለም ። የናትና ያባቷ ልጅ ። ያ ዕሥራ አምስት ዓመት ያለፈኝ ሰሞን ይለማኝ የነበረው ስሜት አሁን ድረስ ይታወሰኛል ። ሰውነቱ ከጫሊት በሽታ የያዘው ይመስል ፣ እብጥብጥ አለብኝ ። ታዲያ ቤት ውስጥ ይልቀኝ ፣ አማርርሙ በልቼ አይደለም ። ዝም ብሎ ነው ። ብቻ ሰውነቴ ሲራሲ ደስ ፣ ደስ እያለ ሲያስኮመኩመኝ ፣ መቁንጥንጥ ... መንቀሳቀስ ... ሰውነት መስበቅ — ዘረብኝ ።

የጠፋ ነገር ይገርመኛል ። «ወይፈት !» እንደ ተባለ ላገኝ የወደረ ወታደር ቅስር ማለቱ ፣ ለኔም በታወቀኝ ጊዜ ያሳፍረኝ ነበር ። ዓመት እንደ የሚገባልኝ ቢሆንም ፣

የሌብሴ ነገር ነፍሴ ነው ። ታዲያ እማዬ ፅተይ ልጇ... በልክ አርጊው ፤ ሰው ዐይን መግባት ደግ አይደለም ፣ እያለች የጭንቀቷን ትመክረኝ ነበር ። ሆኖም ለምክሯ ደንታም አልሰጠሁትም ። ያኛኝን መርጬ ፤ ከሰውነቴ የተጣበቀ እንዲመስል በማድረግ እሰፋቸዋለሁ ። ... ሰውነቴን አስብቃለሁ ...

በያጋጣሚው የማገኛቸው ወጣቶች ባዩኝ ቁጥር ያልተለመደ ነገር ከፊታቸው ላይ አሳዩኝ ። መጀመሪያ መጀመሪያ ፤ 'በኔ ላይ ጥላቻ አድሮባቸው ይሆን ?' ... ስል ገመትኩ ። ሲቆይ ግን ፤ የሚዘፍነውን ሰውነቴን በተመለከቱ ቁጥር መቆጣጠር የማይችሉት ስሜት ከውስጥ እየገነፈለባቸው መሆኑን ተረዳሁ ። ወይ ወንዶች ! በቃ እንኳ አይመርጡም ... ወይናቸው ቅብዝብዝ ፤ ቅልብ ልብ ፤ ቁና ቁና ትንፋስ ፤ ምራቅ ጭጥ ፤ ጭጥ ፤ ከንፈር ልምጥ ... ዶስ የሚል ትርዒት ነው ። ያኔ ? እም ! ... አሁን ግን ሳስበው አልፈርድባቸውም ፤ እዝንላቸዋለሁ ።

ሰበብ አግኝቶ ሰውነቴን መጉንተል የሚፈልግ ወንድ በዛብኝ ። በሆን ምክንያት ብሽቅ ብዬ ፤ ወይ ስሜቴ ጨዋታ አልፈቅድ ብሉ ጭምድድ ሲልብኝ ... እንተል ሲደባብሱኝ ፤ እጁን በጨኽት እያበላልቀቸዋለሁ ።

ሆኖም ጥቅሻው ፤ ጥሪው በረከተ ። ምክንያት ሰጥቶ ... 'ልክተልሽ ?' ... 'ቢመችሽ በዚህ ቀን እዚህ ቦታ ልጠብቅሽ ?' ... እያሉ ቁጠር የሚያስመዘግቡኝ ጥቂት አልነበሩም ።



http://ethioliberty.wordpress.com/

ሰውነቴ ይሆን ያህል ወንዶች እርበድባጅ መሆኑ ሲገባኝ ፤ ምራሌ ጠንከረ ። ኃያልነቴን ተገንዘብኩት ። የተለማኝ ፤ የማይደረስብኝ ፤ የማልቀመስ ፤ ሁሉም የሚያመልከኝ ... እየመሰለኝ ፤ ተኩራራሁ ። ብዙም ሳልቆይ የኔቴ ጆሮ እንደነገሩ ሆነ ። ወይኔ እማዬ ! እንዲህ ወድቄ የደሞ የወሬ ወሬ ስምተሽ ከሆነ ፤ ምን ትይኛለሽ ? ... ውቧቴን እኮ ? ... እማዬን ባገኛት ፤ ያኔ ከሐረር ስወጣ የለበስኩኝ መርጦ ታወሰኝ ። በሰማያዊና በወይን ጠጅ ደርብ ቀለም የተሸለመ ነው ። ይኸው ዐሥራ አንድ ዓመት ሙሉ አብሮኝ ይንከራተታል ። ቆይ እንዲያውም፣ ከሰንዱቁ አውጥቼ ልልበሰው !

ቢቃ ... አርይ ! በላዬ ሳጠልቀው እማዬን ያገኘሁ ያህል ይሰማኛል !

የት'ጋ ነበርኩ ? ... እፍ ቀልቤ ጠፋ ! እዎ የእማዬ ነር ። እባታችን ከእናጢንት ሙያ ከሚያገኘው ብዙም ስለማይረዳት ፤ ሁሉም በእ ላይ ወደቀ ። በኋላ የተወለደውን ግማሹን እንኳ በወጉ አልያዘችም ። ተርበል ፤ ታርበል ።

እማዬ ሸዋ በር ገበያ ፤ ሸቀጥ ይዛ ወጣች ። ትርፏም ደካም ሆነባት ። የናቴ ታላቅ እህት ፤ ሐረር የወረዶች ገዘ ደጃንት በውል ተረዳችው ። እያደላም እኔን እዲሳብ ወስዳ ልታስተምረኝ ፈቃዷን ሰጠች ። እኔም ከቤቱ ትል ቁና ነፍስ ያወቁች ተብዬ ተመረጥኩ ።

በደንብ ይታወሰኛል፤ ገና ዐሥራ ዘጠኝ ዓመት ቢሆነኝ ነው ።

http://ethioliberty.wordpress.com/

እማዬ ኑሮ ተፈታትኗት እኔን ለመስጠት ብትገደድም ፤ የናትነት እንጀቷ ፍጹም እንዳልፈቀደ ከገጿ ይነበብ ነበር ።

አዲስ አበባ . . . አክስቴ ዘንድ ገባሁ ።

የገባሁበትን ቤተሰብ ፤ ሰፈር እንዲሁም ውቢት አዲሳባን እስክላመድ አንጎቴ በምን እንዳቀረቀረ አላውቅም። ብቻ ጸጥ ፤ ሰጥ ብዬ አሳለፍኩት ።

ቆየት ብዬ እንደ ልማዱ እግር አበዛሁ ። ወንዶች ተዋወቁኝ ። ማራኪ ቃላት ... ግብዣዎች ... ስጦታዎች— በያይነቱ ደረሱኝ ። ለሙያ ትምህርት የማታው ይሻለኛል — ስል አክስቴን ወተወትኳት ። እሷም ተስማምታ የማታ ትምህርቴን ተያያዝኩት . . . ቀን ቀን ምን ሠራሁ ? ዙረት ይቀናኝ ነበር ። ይኼው ነው — የሚታወሰኝ ። በትምህርቴ ስወድቅ ስነሣ ፤ ፈቀቅ አላልኩትም። በሥራ ሁለተኛ ክፍል ገብቼ አንድ ወር ያህል የተመላለስኩት የመጨረሻ ሆኖ ይታወሰኛል ።

አሁን ላለሁበት ያበቃኝ በዚያ ወቅት የፈጸምኩት ስሕተት ለመሆኑ እንዳች ጥርጥር የለኝም ።

ቅስሜ ተሰበረ ። የሕይወቴ ዘለበት ላላ ። ከሰጠጋ ችኝ አክስቴና ቤተሰቧ እሳትና ጭድ ሆኝ ፤ ጭራሽን ተለያየሁ ። ደፋ ቀና ብላ ያሳደገችኝ እናቴ ፤ እንባቷን ሳወጣ ለማየት እንዳልጓጓች ሁሉ በኔው ድርጊት ምኞቷ ትቢያ ሆነ ... የቀን ብርሃኔ መጨለም ጀመረ . . .



ማነው ሰው ?... እም! ሀብቴ ነው ። ሰሙን ቴስ ይተራውና ፤ በቀን ጉደሉ እንጐዳድሉኝ ሔደ ። ሰው ሰሙን ቢሆን ምንኛ ደግ ነበር ። ለምን በዕኩይ ጠባይ የተሞላ ሰው ፤ ጀጋና ቸር ገላጭ ስም ይሰጠዋል?... አይገባኝም !

ሀብቴ ፤ ለኔ ምንም ሀብት አልሆነኝም ። ውድቀ ቶኛ ድህነት ነው— የሰደደብኝ ። ወይ ሀብቴ! ... ያባቴን ስም እንኳ ጠይቄ አልያዝኩም ። ያኔ ፤ የኔስ ልብ የጠፋ አልነበር ? ለዚያውስ ሰው በዕውነት ሀብቴ ቢሆን ነው’ ኮ ! ... አጠራጠራለሁ ። ያሬዳ ልጅ— ጨለሌ ፤ መቼ ስምና አድራሻውን ይሰጣል ?

ከሀብቴ ጋር የተዋወቅኩት ፤ ፒያሳ አካባቢ ከሴጆች ጋር ወዲያ ወዲህ ስል ነበር ። ሁለቴ ያህል በመኪና «ሊፍት» ሲሰጠኝ ፤ የትውውቅ ጨዋታ አደረግን ።

ሬጋ ያለ መንፈስ ይታይበታል ። ፊቱን ይደብታል። እንዳች ስሜት በውስጤ እየተገላበጠ ሀብቴን ቀርቤ እንዳውቀው ፤ ይኼው ድብቅነቱ ገፋፋኝ ። ሰሥር ወንድ ሥር ከመለጠፍ ፤ በሀብትም ቢሆን ከፍ ያለውን ጠበቅ አርጎ መያዝ የተሻለ መሰለኝ ።

መቀራረብ ስንጀምር ፤ ሠፈራችን—ሜክሲኮ አደባባይ ድረስ ለመምጣት ቀጠሮ ሰጠኝ ። ቀቢ ሸበሌ ሆቴል ሥር ካለው « ጋርደን ካፌ » አብረን ታየን ። ሀብቴ ሦስት የወርቅ ጥርሶቹን ብልጭ እያረገ ፤ በቅጥብ ንግግሩ አሜወተኝ ።

በእንዲህ እንዳለን ፡ ሳምንታት አለፉ ።

«ለምን በሻይና ቡና ግብዣ ብቻ እንለያያለን ከ
አለኝ ፡ አንዲን ቀን ማምሻውን— እዚያው «ጋርደን
ካፌ» እንደ ተቀመጥን ።

«አንተ ደግሞ ... መተሳሰብና ጨዋታው ነው
እንጂ ፡ ባፋችን የሚገባው ይሆን ያህል ያንገበግበናል
ማለትህ ነው?» ብዬ መለስኩለት ።

«ቢሆንም !... ተዝናንተን ለመጫወት ሰፋ ያለ ጊዜ
እንዲኖረን ፡ ቦታም ፡ የግብዣ ደረጃም መለወጥ አለብን»

«ሻይና ቡና ስለማይደጋገም ወደ ቢራው ግዙን
በልህ ነው ... አይደል»

«ለከበሬታው በማሰብ ነው ፡ 'እትሊስት' ሳንሺ
ምን እንደሚሰማኝ ፡ ያለኝን የአክብሮት ግምት ለማሳ
የት አንድ ነገር ማድረግ አለብኝ ።»

«እስካሁን አላሳየህም ማለት ነው?»

«እንደሱ ማለቴ አይደለም! ደጋግሜ ታማኝነቴን
አረጋግጫለሁ ። እንቺም ታውቂዋለሽ ... እቤት ክርክር
ስት ወጂ !» አለና እንደ ሳፋ ወደ ጉን የሰፋውን ጭንን
በማቶሻ መታ መታ አድርጎ ፡ ጥርሱን እንደ ወርቅ
ሻምላ አብለጨለጨብኝ ።

«እኬ!... ወርብ ኢትዮጵያ ሆቴል— ተጋብዘሻል ...
ታዲያ ዝግጅቱ ብሉ መገኘት ነው!» አለኝ ፡ አንገቱ



http://ethioliberty.wordpress.com/

ሥር ያለውን ከራባት ተወረግርጐ በማስተካከል ፡ ትከ
ሻውን እየሰበቀ ።

«እሺ ... » አልኩት— እየቀረቀርኩ ። ከዚህ ወጣ
የማለለው ... የሆነ ነገር መንፈሴን ሲወጥረው ፡ አካላቴ
ተሸማቀቀ ።

በቀጠሮው ዕለት ዘጠኝ ተኩል ሲሆን ተገናኘን ።
ሆቴሉ መኪና ውስጥ ስገባ !

«እንዲህ ነው እንጂ ! እንዳሁኑ ... የተደበቀ ውበት
ሊገለጥ ፡ ውበትም ወደ ባለቤቷ በደስታ ስትመለስ !»
አለ ባድናቆት ።

ሆቴሉ ከተቀመጠበት የዳንስ ያህል ተወዛወዘ ።
ቀጥሎ ግንባሬን ሳመኝ ። መልሶ ከንፈሬን ።

«ታቲያለሽ? 'ያልታደለ ከንፈር ሳይሳም ያረጀል'
ተብሎ የተተረተው ፡ መቼ ነበር ? ... ያንቺ ከንፈር ግን
ታድሏል!»

«ዕውነት ከልብህ ነው ?» ኮስተር ብዬ ።

«ዕውነት ፡ ዕውነት እልሻለሁ ... ልቢ ሥር ከምት
ገኘው ፡ የመጨረሻዋ ደቃቅ ሕዋስ አንሥቶ ነው— እን
ዲህ ስለ ውበትሽ የምናገረው» ከማለቱ ፡ መኪናውን
አስፈተለከት ።

ዕውነቱን ነው— ሆቴሉ ። በተቻለኝ ሁሉ አጊጫለሁ ።
ሊፐስቲክ ፡ የጸጉር ጌጦች ፡ የጥፍር ቀለም ... የወትሮ
ልምዱ ቢሆንም ፡ ፍጹም አድምቄአቸዋለሁ ። የጨመር

ኩት የወርቅ ጉትቻና ሐብል ፣ 'ቡትስ' ጫማና ከፖርት አብሮት ከሚሔደው የተንቆጠቆጠ ቦርሳ ጋር ነበር ። እነሆን ብርቅዬ ጌጦች ከአክስቴ ልጆች የተዋስኩ መሆኑን ሀብቴ ቢሰማ ፣ ምን ይል ይሆን? ስል በልቤ አሰብኩ ።

ኢትዮጵያ ሆቴል ስንደርስ ፣ በክብር ቅድሚያ ገባሁ ። ሀብቴ ፈጠን ፣ ፈጠን ብሎ ቀድሞኝ በማለፍ ወደ ግራ ካሉት ፎቴዎች መራኝ ። ነጹ አካባቢ ነበር ።

አይሞቅም ፣ አይቀዘቅዝም ። ለስለስ ያለ ተስማሚ አየር አለው ። ቶሎ የሚግርክ ፣ ዘና የሚያደርግ ድባብ ተስማኝ— የሚመስጥ ዓይነት ነው ። ወደድኩት ። የሰፋው ምቾት ይደላል ።

ከሀብቴ ጋር ተጠጋግተን እንደ ተቀመጥን ፣ ሙሉ ጥቁር በጥቁር ልብስ ከ«ቦተር ፍላይ» ከራባት ጋር ያደረጉ ትልቅ ሰው— አስተናጋጅ ሆነው ፣

«ምን ላቅርብላችሁ ?» አሉን ፣ ቀድመው ወደ ሀብቴ ፣ ቀጥለው ወደኔ እየተመለከቱ ።

«ሁለት ውስኪ !... ከበረዶ ጋር» አለ ሀብቴ ። ዝግ ብሎ ፣ በጣቶቹ ጭኔን ጫን ፣ ጫን ... አየት ... አረገኝ ።

ባንዴ ከውስኪው ጋር መጋተር ቀፈፈኝ ። ግን ስለ ታዘዘና ለመምረጥ ዕድል ስላልተሰጠኝ ፣ ምንም ማድረግ አልቻልኩም ።



http://ethioliberty.wordpress.com/

ራቅ ያለ ይመስለኛል ፣ በሙዚቃ መሣሪያዎች የተቀነባበረ ሙዚቃ በለሆሳስ ይወጣል ... ቀስ እያለ ተመጥኖ በጆሮችን ተንቆረቆረ ... የቀጭን ምንጭ መንጎርጎር ይመስላል ።

ሀብቴ የወደፊት ምኞቴን አስመልክቶ ጥያቄ አነሣብኝ ፤

«ምን መሰለህ ... ትምህርቴ እሺ ቢለኝ እንደ ሌሎቹ ሴቶች ጥሩ ሙያ ኖሮኝ ሥራ እንድይዝ እፈልጋለሁ ። ከዚያ የሚያስከብረኝ ባለቤት ኖሮኝ ፣ ቤተሰብ መሥርቼ ፣ ወልጄ ከብጄ መኖር ነው የምኘው ... ግን ይህ ሐሳብ አልጨበጥልኝ ብሎኛል» ከማለቴ መለኪያውን አቀበለኝ— ሀብቴ ።

«አይዞሽ ... በትምህርቱ እንድትበረቺ እኔም አግዝሻለሁ ፣ ታዲያ ብርቱ ሰው መሆን አለብሽ» አለኝ ፣ ፊት ለፊት ካለው ታሪካዊ ሥዕል ላይ ዐይኑን ተክሎ በረዥሙ በማሰብ ። «እሺ... እየጠጣሽ እንጂ!»

በዚያ ሶፋ ላይ ወደ ኋላዬ ለጥጥ ስልበት ፣ ሐሳብ ወሰደኝ ። ሀብቴም በልዩ ጥንቃቄ ፣ እጆቼን ፣ ጭኖቼን ፣ ጀርባዬን ... እያሻሸ ደባበሰኝ ። ደስታ ... መዝናናት ... ተደብቀውኝ የቆዩ ይመስል ፣ ከየሥርቻው ተወርውረው ተጠመጠሙብኝ ። የራሴ የሆን ዓለም ተቀበለኝ ። እኔም ቀኘሁበት ። አቀበትና ቁልቁለት የለበትም ፣ እንግዳ ሆንኩበት ።

በኋላ ፣ በኋላ ... ጊዜ ካለፈ በኋላ... ነቃሁ ። ያን ለበኝም መሰለኝ ። የተሰማኝ ግን ፣ ከኃይለኛ እንቅልፍ እንደ ተነቃ ሰው ስሜት ነው ። ሰራሴ ፣ ሁኔታው ባዕድ ሆነብኝ ።

ሰዓቴን ብመለከት እጄ ላይ የለም ። ደንገጥኩ ጆሮ ብል ሀብቴ የለም ። የተጐነጨሁት ውስኪ የጐደለ መሰለኝ ፣ የሀብቴ ንክችም አልተደረገም ፣ እንደ ተሞላ ነው ። ዘና በማለት ራሴን ለማረጋጋት ብሞክርም አቃተኝ ። ተአምር የመታኝ ይመስል ፣ ትንፋሼ ተቆራረጠ ።

ተውሼ ያደረኩትን ጉትቻ ከጆሮዬ አጣሁት ። የእጅ አምባሬ የለም ። ውድ የሆነው ካምርት አይታየኝም ... በዚያች ቅጽበት ላየኝ ላባዋ የተነጨ ዶሮ ላልመሰል እቀራለሁ?

ሰውም ባካባቢዬ አጣሁ ።

ወይኔ ልጅት !... እሹሩሩታውን ለለቀው ነበር ። በደ መንፍስ ዋጥኩት ።

ተንደርድሬ በመውጣት ፣ የሀብቴን መኪና ፈለኩ ፣ የለችም ። ጊዜው ደንገዝገዝ ብሏል ። ተመልሼ ሁኔታውን ለአስተናጋጆች ብነግራቸው ፣ የሚያውቁት እንደ ሌለ መለሱልኝ ።

...ወይኔ ልጅት! ... ጉድ ሆንኩ!

... ተቃጠልኩ!... ንዴት በሥራ አካላቴ ሠረፀ ፣ ሆዴ ተንበጫበጨ ። እርር ! ድብን! አልኩ ። ደም ማነስ



http://ethioliberty.wordpress.com/

ይመስል ጭው !... ጭውውው ! አለብኝ ። ልቤ እየደቃ ፣ ሰምባዬ እየተነፋ ፣ ደሜ እየተጋፋ . . . ስተነፍስ ፣ ትንሽ መንፈሴ መለስ ይላል ። ስመራመድ ጉልበቴ ቢጤ እንቻለሁ ። እዚያና እዚህ ሀብቴን ፍለጋ ስቅበዘበዝ ፣ ከልፍልፍ ያበደ ውሻ ይመስል— ሰዎች ታዝበውኝ ይሆናል ።

ምን ላርግ... የት ልሂድ? ንገሩኝ!! የታሣባቴ ልድረስ ?... ኡፍ! እፎይ ... አክስቴ 'ጋ ? ምን ብዬ እወራለሁ ? ምን ብዬ እገባለሁ ? እንዴት የልጆቿን ዐይን አያለሁ ?

ተስፋ ቆረጥኩ ።

ቀልቤ አልሰበሰብ አለኝ ። ማድረግ ያለብኝን ሆነ መራት የሚገባኝን መለየት— አዕምሮዬ ማሰብ አቃተው ።

ያክስቴ ዘመዶች ለኔ ሥጋ ቢሆኑም ፣ እንዴትና በየት ብዬ እንደምደርስባቸው— በረጋ ሕሊና ማገናዘብ አልቻልኩም ። እንዲያው ብቻ— ዓለም ተገልብጦ 'ዐይንሽን ላፈር ! እርኩስ ! ቀላል ! አሰዳቢ ! ...' የሰድብ ናዳ የሚያወርድብኝ መሰለኝ ።

... የነር ሥቃይ አካሌን ያጠወለጋት እናቴ ፣ ላዩታ ትውስ ስትለኝ ፣ 'አልቀኝ ! ወየው ! እርም አውጪ ! ኡኡ በይ!' አለችኝ ፣ አንሰፈሰፈኝ ።

ወይኔ ልጅት ! ከልቤ አይደለ የምነግራችሁ— ይወጣልኝ!!

http://ethioliberty.wordpress.com/

... በኔ ቤት— ብሌጥ ነኝ ። በኔ ቤት— አልታለልም ፣ በኔ ቤት ቂልነት ሜፈን አይነካውም ። በኔ ቤት— የሌላ መጨረሻ ከኔ ወዲያ ላግር ነው ።

ዙሪያው ባሕር ሆነብኝ ...

የሕይወት ፣ የመኖር ምስጢር ማን ይገርማል ። ምን ይሁን ምን ፣ ማን ይሰንከል ማን ይበድ ፣ ማን ይጣ ማን ይዋረድ ... ሕይወት ታሳሳለችና ዘለበቷ ሲላላ— ለማጥበቅ ሲባል ፣ ለመቀጠል ሲባል ... የማይጣስ ጉድባ ፣ የማይፈንቀል ድንጋይ ፣ የማይፈለጥ ግንድ ... የለም ።

አቅል ያጣው ሕሊናዬ መለስ ሲል ፣ ለውሳኔ አላመንታሁም ። ለድርጊት ፣ ለሕይወቴ ወደ ኋላ አላልኩም ።

ቀላል ነው ። ድቅን ያለብኝን ወሰንኩ ። እንዴ በማታ ትምህርት አብሬኝ ከተማረች ጓደኛዬ ቤት በመሔድ ለመጠጋት ቆረጥኩ ... የሆቴሉ አሳላፊዎች ዞር ሲሉልኝ ፣ የምንተፍረቴን በርሬ ወጣሁ ። አልተገላመጥኩም ። አላመንታሁም ። አቅጣጫዬ ወደ ነፍስ ስልክ ነበር ...

ጓደኛዬ እንደማታሳፍረኝ ተስፋ በማድረግም ፣ በልቤ በመማፀንም ነው— ራሴን ያጽናናሁት ። ለወትሮው ፍልቅልቅነቷ የሚታወሰኝ በዚያ ወቅት ውልብ ባይለኝም ፣ ሰብእዊነቷ በደመነፍስ ይታወቀኛል ። በስዋ ላይ የጣልኩት ዕምነት በሬናው— እቢን እንዳስብ ሳያስገድደኝ አልቀረም ። በጨዋታ ጊዜ— ስለምታውቃቸው ሰዎች የምትዘረዝረው ፣ ዕቃ በማሻሻጥ የምታሳየው



ብልጠት ፣ የተጣላ ለማፋቀር የምትመዘው ሰበብ ... በስ ፊል ሽው ሲሉኝ ፣ ብስጭቴን እያመነመነ እርዳታ ያጋራኝ ጀመር ።

... ዕድሜ ይስጣት! አላሳጣችኝም ። ሳምንት እቶይታ ወደ ሞጆ ላከችኝ ። በምልከት ከነገርኳት አክስቴ ቤት ሔዳ ፣ ተመላልሳ ፣ ደጅ ጠንታ ፣ ዕቃዎቼን በከረጢት አጭቃ ላከችልኝ ። በና ቤት ሥራ ተገኝቶ ነው— የወጣሁት ። ገንዘብ ቋጥሬ ወደናቴ መመለሴን ተስፋ በማድረግ — ስንባበትኩ ። የቤተኛ አዳሪነት ኑሮን ካንገት በላይ እንጂ ፣ ከልቤ አልተቀበልኩትም ። ታግሼ ቆየሁ ። ገንዘቡ ጠብ አላለም . . . መቅኖ ማጣት የናቴ ትዝታ ፣ በአክስቴ ላይ ያደረስኩት በደል... ቅጣት ሆነኝ ።

ሞጆን ባየው— የተስፋ ጭላንጭል የሚታይበት አልሆነም ። «ያልተገላበጠ ያራል!» ብዬ ፣ ወደ ሻሸመኔ ወረድኩ ... ምንም የለም !

ዛሬ ፣ እዚህ ደቡብ ኢትዮጵያ— ሞያሌ— በቤተኛ አዳሪነቴ እዘልቅበታለሁ ብዬ— ያኔ ወደ ጓደኛዬ ቤት ነፍስ ስልክ ስገዝ ፣ አልጠረጠርኩም ነበር ።

«ተገላብጨ አረርኩ!» በራሴው ሌተርት እንጂ!!
እስቲ ... «የዋንቱ ትዝ አለኝ» ዘፈን ያባብለኝ !
«ያ ሁሉ ጨዋታ ... የዋንቱ ትዝ አለኝ
ባሳብ በቅዝዜ ... እያመላለሰኝ»
ወይኔ! ያ ሁሉ ጨዋታ... ወይኔ ልጅነት!

# ም ኞ ት

እመንገዱ ላይ ብልጭ ባለው የመስከረም ፀሐይ የሚፍነከነከው ሾምቤ ፣ ቆም ብሎ ሰዓቱን ተመለከታት ። ሦስት ከአምስት ትላለች ። ሩብ ሰዓት ብትዘገይም ፣ እቶ ጨዋን እንድትነግረው አያስገድዳትም ። እንዲያው ሲወራጭ ፣ ከሰው ጋር ቀጠሮ ይዞ ትዕግሥቱ ያለቀበት ይመስላል ።

ሾምቤ ፍጥነቱን ጨምሮ እየተራመደ ፣ ቁርስት ሆቴል ገባ ።

ሆቴሉ የወትሮ እንግልግሎቱን በመስጠት ላይ ነው ። እሑድ ጠዋት ቢሆንም ፣ ተስተናጋጆች ምኞት በሚ ሰጠው ሶፋ ላይ ተበታትነው ተቀምጠዋል ። ሾምቤም ጥግ ካለው ጥቁር የላስቲክ ሶፋ ላይ ተቀመጠ ። ከላይ የሚያስለየውን ጥቁር «ሌዘር» ኮት አውልቆ ፣ ጉልበቱ ላይ አጋደመው ። የነጭ ሸሚዙን እጅጌ ሰብሰብ ዘና እንዲል ማለት ... አሰኘው ።

ወጣት ነው ። ሲመለከቱት ፣ ተገልብጦ የወጣው ዐይኑ ጅላጅል ያስመስለዋል ። ሰውነቱ ድብልብል ቢጤ



http://ethioliberty.wordpress.com/

ሥጋም በወፍረት አብቧል ። ... ደመውን ሁሉ ሲመለከት ፣ የቅርብ ዕውቂያ ያለው ይመስላል ። በየጣልቃው ፈገግ እያለ ሣቅ ቢጤ ሲሸፍነው ፣ «እነዚህ እሚያውቃቸው ሰዎች ላይ ምን አይቶ ብቻው ይሆን?» ያሰኛል ።

አንድ አጭር ወጣት ዘው ብሎ የሚፈልገውን ሰው ቃኘት ፣ ቃኘት ሲያደርግ ፣ ሾምቤ የሚያውቀው ልጅ በማግኘቱ እጁን በማውለብለብ ሰላምታ ሰጠው ። ጥቁር ግንባሩ በጉልህ የሚያብረቀርቀው ወጣት ፣ አጸፋውን ካንገቱ አጐንብሶ ሰላምታ በመስጠት መለሰለት ። የመቸኮል ምልክት እያሳየ ፣ በመጣበት አኳኋን ተመለሰ ።

ሾምቤ ፣ ወጣቱን የሚያውቀው ከአራት ዓመት በፊት ነበር ።

ሾምቤ ዐሥራ ሁለተኛ ክፍል ደግሞ ለመማር በማታ ትምህርት ሲመዘገብ ፣ ወጣቱ ከሥራው በተጨማሪ የማታ ትምህርቱን እየተከታተለ ዐሥራ ሁለተኛ ደርሶ ነበር ። ለአንድ ዓመት ሲማሩ አንድ ጠረጴዛ ተጋርተዋል ። ጐን ለጐን ተቀምጠው ተጫውተዋል ።

«ታዲያስ!»

«ታዲያስ !» ይባባላሉ ።

«የዚህ ክፍል ሽቶ ደግሞ ... ገና ተማሪው ላይ ገባ ያውላል !» በማለት ፣ ይጀምራል— ሾምቤ ።

«ተቸግቸው !... ይልቅ የቤት ሥራውን ሠራህ ?»

http://ethioliberty.wordpress.com/

«ምን እተዋቸዋለሁ … ያቺ ከኋላ የምትቀመጠው ንች ‘ኮ በሽቶ ታጥባ የምትመጣው ። ማታ ማታ የሚ ወስዳትን መኪና አይተሃል ፣ አይደል ?… ደግሞ በሚ ዜው ነው የምትቀያይረው ! … ወይኔ ! እኔም እንደ ምንም መኪና ብይዝ እሳያት ነበር …»

«አንተ ! ትቀልዳለህ ?… ምኞት እንዳይገልህ ፣ ይት ርብህ !… የቤት ሥራውስ ? …»

«አንተ እለህ ብዬ ተውኩታ !.. »

«አስተማሪው መጣ ! … » ናትናኤል ያቋርጠዋል ፣ እየሣቀ ።

… አስተማሪው ትምህርት መስጠት ያዘ … ‘እስቲ እንዲህ ቢሆን … ብለን እናስብና ቀጥሎ የሚመጡትን ሁኔታዎች እንረዳ …’— እያለ ፣ ያስረዳል ።

«ታያለህ በ‘አስምሽን’ መናገር እንዴት ደስ እንደ ሚል?» ይንሾካሾካል ፣ ሾምቢ ።

«ዝም ብለህ አዳምጥ !»

«ቆይ! እኔ አስተማሪውን— ብሆን … እንደሱ ኮሌ ታው የተቀደደ ኮት አላደርግም ነበር . . . ምን እንደ ምለብስ ታውቃለህ? ሽክ ያለ ሱፍ በክራባት ፣ ደግሞ መነጽር አረጋለሁ … »

«አንተ ልጅ! …» - ያቋርጠዋል ።

«ቆይ ልጨርስልህ … »

«እረ ተው ይቅርብህ … ምኞት ይጐዳሃል !… »

ይህ ዓይነቱ ምልልስ ፣ ቢያሠልስም አይቀርም ።



ናትናኤል ዓመቱን ሙሉ ፣ እንደ በሾምቢ ንግግ ሮ ልብብ ሲበሳጭ ፣ መልስ የሾምቢን ልጅነት እያሰበ ሊያዝንለት ቆየ ። ከዛ ወዲህ ድንገት እንዲ ሾምቢን ሲያገኘው ፣ በእጭር ሰላምታ ይለየዋል ። «የቀን ሕልም ማየለው !….» ይላል በልቡ ።

ሾምቢ የናትናኤልን ዩኒቨርሲቲ መግባትና መቀጠል ሲሰማ «ታዲያ ቢሆንስ ?…እኔም እደርስበታለሁ! እኔ ደግሞ የምገባው ቀን እንጂ ፣ እንደሱ ማታ አይደለም . . . ቀድሜው እጨርሳለሁ … » በማለት ነበር የፎከረው ።

በአረንጓዴ ኮትና በና ቀሚስ የተዋበችው ቤቷ አስተናጋጅ ።

«ምን ልታዘዝዎት?» አለችው—ፊቷን ቅጭም አርጋ ።

ሾምቢ ተሟዴ ዐይኑን ተክሎባት ቆይቶ ፣

«ሻይ ይሁንልኝ!» አላት ።

ሻዩን ይዛ ስትመለስና ስታቀርብለት ልብ አላላትም ።

… እየጀመረው ሆነ— ሐሳቡ ። የማይለየው የሐሳብ ጉዞ ፣ የመንፈስ ምናኔ ፣ ዛሬም ቱሪስት ሆቴል ተከትሎት ገብቷል ።

አሁን እማዬ ቢታሰምግረኝ ምን አለበት ?. . እኔ ለራሴ በውቄ አደርገው የለ ! ‘ተማር ! ለራስህ እስብ ! በኋላ መውደቂያህን እወቅበት ! …’ የማያልቅ ንትርክ

… እንዴት ይሰለቻል ? ኡፍ !… ግን እማዬ ምን ታርግ ! ያቺ ሙጢ ነች እማዬ እየተበሳጨች እንድትናገር የምታረጋት ። ይህች መናጢ ፤ ገና ለገና የኔ ታናሽ ሆና ጥቁር አንበሳ— ሚዲካል ኮሌጅ መግባቷ ይሆን ያህል በኔ ላይ ያንጠባርሬታል ? ይቺ ጉዶ ! እኔ ነኝ የማላያት ። ቆይ ! … እኔ አይደለሁም ፤ እሷ ከምታገኘው ገንዘብ የበለጠ ባገኝ !

እኔ 'አልማርም !' መች አለኩ ። አሁን ተምሬ ሥራ ከምዝኩ በኋላ ፤ ተአምር ሳመጣ እማዬን ይገርማት የለ ! ምን እሷን ብቻ !… የሠፈሩን ሰው ጭምር ነው— ጉድ የማሰኘው ።

… ግን ምን ብሆን ይሻለኛል ? … ምን ብሠራ ? … ጥሩ ሥራ ወይም «ቢዝነስ» ከያዝኩ ጥጋ የለውም ። ደግሞ ታይተኛል ። «አቤት ! አቤት ! እንዴት ታድሏል … » የሚያሰኝ ሥራ ነው— የምይዘው ።

ቆይ … የፓይለትነት ማስታወቂያ ወጥቶ የለ ? ትንሽ ጊዜ ቢቆይ የማትረሳ ውጤት አቅርቤ እመዘገብ ነበር ። ከዚያ የጐረቤት ሰዎች ሁሉ እማዬን ለመጠየቅ ሲመጡ ፤ 'ወይዘሮ አጋመቤት ደህና ሰንብተዋል ? እን ደምን አሉ ? ቤተሰቡስ ? ያ ልጅዎ … ይኼ በራሪው ! … ቀይሉቱ ? … እም ! … ደህና ነው'ም ይሏታል ። እኔ ደግሞ ከደብረ ዘይት ለማዬ ስልክ እደውልላትና «እማዬ … አሁን አየር ላይ ልወጣ ነው ፤ በአዲስ አበባ በኩል አልፋለሁ ፤ ተመልከቺኝ ! » እላታለሁ ። ወዲያው …



http://ethioliberty.wordpress.com/

ከደብረ ዘይት አየር ማረፊያ ጀቱን ይዤ እንደረረርና በግ ፍን ለሁለት እየሰነጠቅኩ መብረር ነው … «ኡ ሸ ሸ ሸው … በሰማይ መሔድ አቤት ደስ ሲል ! ሆኖም ብርዱ ያስፈራል ። ታዲያ የሚሰጠን ልብስ ፤ ሙቀት የሚፈ ጥር ስለሆን አያስቸግርም ። እማዬ ወደ ሰማይ ታንጋ ጥጥና እየተንጫጩ ለሚከቧት የሠፈር ልጆች «እዩት !… እዩት ! ልጄን ! እርብባትን ሲያበረው … እግዚኦ ! ጭራሽ ወደ ሰማይ ሲገባ አይደል ? … በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ … ጌታዬ አደራህን ጠብቀው ፤ ሲቀ መጣኩ በከንፍህ ሸፍነው … ሌዴ ! … ሌዴ !» ስትል ፍው ፤ ልጆቹ ደግሞ «በራሪ !» እያሉ ይጮኻሉ ።

ቅዳሜ በሰሪፍት ቀን እማዬን ለመጠየቅ ወደ ቤት ጉራ ስል «ወይኔ በምትኩትት! እሬር በሆን ፤ ደህና ነህ ? ልጄ … ሥራው እንዴት ነው ? … እንዲያው በዚህ በሰ ማይ እንደ እሞራ ስትከንፍ አትፈራም ወይ ትለኛለች ።

«እያስፈራም …, አይዞሽ ! መያዣውን በደንብ እጥ ንቄቃለሁ ። ምንም አያስቸግርም » እላታለሁ— ኩራ ብዬ ። … ታዲያ ያቺን ሙጢ እዚያው ባገኘት በጥሬ ማጠናፈር ነበር ! ወይኔ — ማስታወቂያው የሚቆይ ቢሆን … እንዴት ዓይነት ሀሩፍ ዕድል ነበር ! ታድዬ … ኡፍፍ ! …

ግን ከዚያ በፊት ፤ እማዬ ዕቁብ ሲወጣላት ታክሲ ብት ገዛልኝ ?—ጥሩ አይሆንም ?… ይሆናል ! ተበድራም ቢሆን

ማሟላት ትችላለች ። አዎ ፣ ገንዘቡንም ብዙ አላቆይባትም ፣ በየቀኑ ከማገኘው ግማሹን እንኳ ባጠራቅም ቶሎ ልመልስላት እችላለሁ ። እንዲያውም በኋላ ከማገኘው ትርፍ፣ ለሷም እተርፋለሁ ። ግን መንጃ ፈቃድ ለማውጣት ቀድሜ መማር አለብኝ . . . አዎ ! የግድ መማር አለብኝ ። ዐሥራ አምስት ቀን ወይም ቢበዛ ሐያ ቀን ቢፈጅብኝ ነው ። ጉረቤታችን ሉሉ ከሥራው ሲመለስ ትንሽ ትንሽ ካስተማረኝማ ፣ ይህን ያህል ጊዜ አይወስድብኝም ። ከሁሉም ከሁሉም የሚያብሩት ግን አላፊና የሚሉ ሴቶች ናቸው ። አፈላማንበት ውስጥን ማሊታቸው አይቀርም ። በነጻ ሆኖ ፣ እንዲገና ሌላ ሰው እንዳይሳፈር ገበያ ዘግተው «ብቻዬን አድርሰኝ» ሲሉ ያናድዳሉ ። እነሱ ባሉበት ታዲያ ምን ታክሲ ይነዳል! ምንስ ትርፍ ይገኛል !

ይልቅ የሚያዋጣኝ «ቢዝነስ» ጸጉር ማስተካከል ነው ። እንደሱ የሚቀል ምን ሥራ አለ?... የሚገኘው ገን ዘብ ደግሞ ጠቀም ያለ ነው ። ጸጉር ማስተካከል ለመማር ደቂቃም አይፈጅብኝ!ማናቸው?... ጋሼ አምቢበል ጋ ሔጄ «አሳዩኝ ! » ብላቸው ፣ ባንዴ እቀስመዋለሁ ። «ለምን አብረን እንሠራም ? እርስዎ በ እንድ ክፍል ለብቻዎ ከሚ ይዙ አብረን ብንሠራ ብዙ እናገኛለን ! ትርፉም የጋራ ይሆናል ...» ብዬ አግባባቸዋለሁ ። በየቀኑ ደንበኞቻቸ እስኪሰለቹ ሠላሳ ሰው ባስተካክል ፣ በሦስት ብር ሒሳብ—



http://ethioliberty.wordpress.com/

ብዙ አገኝበታለሁ ። ይሄ ደግሞ በወር ሲታሰብ የትየለሌ ነው ።

ኡዋ!...ስኮላርሺፕ መፈለግ ጥሩ ዘዴ ነው—ከሁሉም! ሌላው ቢቀር ሲቪል ኢንጂነሪንግ ለማጥናት ዕድል ይሆነኛል ። እንደ— ሦስት « ኤ » በማትሪክ ባመጣ እንዳገለ ነበር ። አውሮፓ እሔዳለሁ ። ስድስት ዓመት ምን አላት?... ቅንጽ ናት ። ታዲያ ቶሎ ተመልሼ የቤት ገላን አውጪ ነው— የምሆነው ... እና እዚያ ሀገር በትምህርት ላይ ስሆን ፣ እስ አይደል! ደብተ! እርጌ ትምህርቱን አጠናቅ ለሁ ። ክፍል ውስጥ ለክቸሬሮቹን «ቻሌንጅ» ሳረጋቸው ፣ ያሬው ሴቶች ያው ለመተዋወቅ ተቀናጥጠው ይቀር ቡኛል ። እኔም ደረቴን ነፋ አርጌ ፣ « እሾ ! ‘ጥቁር እን ዲሀ ነው!’ ንገሽኖ» ብዬ ፣ ለያንዳንዷ እሳያታለሁ ። ወይኔ ... ቢታ ለ «ስኮላርሺፕ» ማመልከት ነው— የሚሻለኝ?... ውው !

ቆይ ... ቆይ ! ከዚህ ሁሉ በፊት እንደንትፈለስ የቱ ሪስት «ጋይድ» ብሆን ያዋጣኝ የለ! በርግጥ ቋንቋ ማጥ ናት ያስፈልገኛል ። እንግሊዝኛ እከልላለሁ ። ጀርመን ኛና ፈረንሳይኛ ቋንቋዎች ብጨምርበት ይበቃኛል ... በደ ንብ ይበቃኛል ። ስንት ጊዜ ይፈጅብኛል?... እራት ብበዛ ስድስት ወር ቢሆን ነው ። ታዲያ ቱሪስቶችን ከተማ ለማሳየት « ጋይድ » እሆናለሁ ፣ ብዙ ገንዘብ መሰብሰብ እችላለሁ ። ያኔ መኖሚ ሳትቀበ «ኛይ መጠሜ ስጠኝ!»

እያለች ስትቅለሰለሰብኝ ፣ « ምን ? … ምን ፈለግሽ ? » እላታለሁ — በኩራት ። ብሡ ካስለፈለፍኳት በኋላ ብር እወ ረውርላታለሁ ። እግዜ ደግሞ «ተይ ! እንጂ … ልጄን አታ ስቸግሪው ፣ ስንት ለፍቶ ነው ያመጣው … ልጄ ሆዬ ብለህ ገንዘብ አትርጭ … ትንሽ ብትቆጥር ይሻልሃል !» ትላለች ።

ያቺ መጢም ፣ ቀንዷን እንደተመታች እጋዘን ከምግቧ ትላለች ። እሾህ እፏን እንዳሸገች ፣ ከጠገቢ ትጠፋታለች !

ያም ያም ሆኖ የሚያልቅ ውጣ ውረድ ውስጥ ከም ገባ ፣ ሎተሪ ቢወጣልኝ ዓለም ነው ። ምንድነው የማደር ገው ? ሦስት ሎተሪ ሻጮች አንድ ላይ እጠራለሁ ። ከዚያ በሚቀናኝ «ማጂክ» ቁጥር ፣ የሎተሪ ቲኬት እቆርጣ ለሁ ። ያቺ «ማጂክ» ቁጥር ደግሞ አንድ ነች ። መጀመ ሪያ ፣ መሐልና መጨረሻ ። ግን ነበር ? እሱ ! … ሰሚን በእንግሊዝኛ ከዚፊ በኋላ «ካንሰል» እያደረገ ፣ የዕድል ቁጥሬን የነገረኝ እም ! እሌክስ ነበር … እሡን ነትያ ለሁ ፣ ከሁሉም የሚበልጠው ሎተሪው ነው ። እንዴ ገን ዘብ ፣ በገንዘብ ከሆንኩኝ ፣ ጣጣም የለብኝ … ይኼው ነው — የሚያቆጣኝ ።

ሾምቢ ከሐሳቡ ባነነ ። በሱሩ ኪሶቹ አካባቢ ለሙ ቀን ሲነካካ ፣ ምናምን እንደ ወረረው ሰው የሚያክ ይመስ ላል ።



ፊቱ ፣ ቁልል ተራራ ለመውጣት እንደሚጣደፍ መን ገደኛ በላብ ታጥቧል ። ዐይኖቹ ከመጠን በላይ በስፈ ጠጡ ፣ የአዲስ መኪና የፊት መብራት ይመስላሉ ።

በቀረበለት ሲኒ ውስጥ የነበረው ትኩስ ወተት ቀዝ ቅዟል ። ክታብ መሳይ ፣ በስስ ወረቀት የታሸገው « አዲስ ሻይ ቅጠል » ፣ ሲኒ ማስቀመጫው ላይ ተቀምጧል ። ሲኒ ሩም ፈንጠር ብሏል ።

ሾምቢ በድማሚት እንደ ፈነዳ ድንጋይ ፣ ተወርውሮ ወጣ ። እስተናጋጇቱ በግርታ ደረሰች ። ስለ ሒሳቡ እየተ ጨነቀች ፣ ያቀረበችውን ተመለከተችው ። ምንም እልተ ነካም ። እንደቆየ ሾምቢ ይመስላል ብላ ተስፋ አደረገች ።

ሾምቢ ባራት ኪሎ መንገዶች እየተቅበዘበዘ ወዲያ ወዲህ ይላል ። ሎተሪ ሻጮች ፍለጋ ይባዝናል ።

ሾምቢ ተጫነ … « ምኞት !! » እያለ በሕሊናው ሲጮህ — በመንገዱ ላይ ያስቆመው የለም ።

ግን ማለፍ ያቃተውን ያሥራ ሁለተኛ ክፍል ትምህ ርት በማጠናከሪያ ፕሮግራም መከታተል እንዳለበት ትዝ ያለው — አንድ የክፍል ተማሪው አደባባዩን ሲሻገር ተመ ልክቶ ነው ።

http://ethioliberty.wordpress.com/

# ሸ በ ጥ

«በቃኝ! ... በቃኝ! ነው የምልህ ። ከዚህ ወዲያ አል ችልም ። እስቲ እራስህ አስበው ? እስካሁን ኪራዩን አልከፈልከኝም ፤ ድፍን አራት ወር ሙሉ ። ንቀት አይ ደል ? ለንፍሌ ባስጠጋሁህ ፣ በቻልኩህ ! 'የት ትደርሳለች ?' ብለህ ቀለድክብኝ! ቆይ ግዴለም !»

«እረ እንደሱ አይደለም! ወይዘሮ አንቺዬ ... እንዲህ አልጠጣኝም ። 'ትንሽ ፋታ ይስጡኝ' አልኩ እንጂ ፤ መች 'አሻፈረኝ !' ወጣኝ ?... ዕብለት የለብኝም 'ኮ !»

«ነው እንጂ !... 'ሴት ነች፣ ብቻዋን ነች !' ብለህ ነው ሁሉንም እየንተህ አይደል ይህን ያህል ጊዜ የምታሾፍ ብኝ?... ቆይ እንዲያውም ለደረስዬ አሁኑኑ ነግሬ ፣ ይህን ቅራቅንቦ ዕቃህን ጠራርጎ ያወጣልኛል ... ኃይል ነው ! አይደል— የምትፈልገው !... ወዲያ መጣጣል ይሻለኛል ! ዶሞ በና ለማቃጠጣ ኪራይ አበላ ማየቴ ፣ መጠበሌ !.. ቆይ ግዴለም እንተያያለን!... አንቺዬ አይደለሁም !»



አዲስ አበባ ...

አራ በከንቱን አልፎ ወደ ታች ላሽቆለቆለ ፣ ተዳፋቱ ይንጣል ። ውሃ ቢንንድበት ፣ ፈረሰኛ ሆኖ ያገኘውን ሁሉ ይጠራርጋል ። ራቅ ሳይል የቄራ ድልድይ ይገኛል ።

አርበ ጠባብ ነው — የቄራ ድልድይ ። ከአንድ መኪና በላይ ከያዘ ይጣበባል ። በስተቀኝ ከረኮንቹን ይዞ ለዘዴ፣ የተቆመቆሙ ቤቶች ያያል ።

ንጋት ሆኖ ሰው ገና ውር ውር ቢልም ፣ የከረኮንቹ ግራና ቀኝ ጉልት ነው ። አርጊቶች ፣ ሕፃናት ፈረታ እየ ገቡ እንዲት ዘለላ ቃሪያ እንኳ ቢሆን ይዘው ይወጣሉ— ጉልት ። የቄራ ድልድይ ድምቀትም ይኸው ነው ።

የድልድዩ ጉረቤቶች ጭሰማን ተገን አርገው ፣ ምሽትን ተማምነው አመድ ፣ ገራባ ፣ እግቢ ፣ የማድቤት ጥራጊ ፣ የአሻሮ ንፋሽ ... ቢደፉበትም ፤ ከረፈደ እንጦቀ ሲሙሁ ፣ ሲስቁ የሚውሉት የጉልት ቸርቻሪዎች ፣ በመ ናፈቅ 'አግሬኛ ይሁን መኪና እናሳልፍም' — የሚሉ ሕፃናትን በማስብ ሁሉን ችሎ ያድራል ።

ሰሞኑን « ሆያ ሆዬ ... ሆ ! » — የሚሉትን ልጆች እላስጨፍር ያለው ዝናብ ፣ ሌሊቱን ሲረግጠው ነው — ያደረው ። ቆርቆሮው የተሸንቆረ ፣ ግድግዳው የተቦደሰ ቤት ፣ ብርድና ቅዝቃዜውን ሳይከላከል ፣ እንዲሁ ያስገ ባዋል ። በንዲህ ዓይነቱ ቤት የሚያድረው ሰው ፣ ከረም ቱን ይረግማል ። የቄራ ድልድይ — የቆሸሸ ግንቡ ፣

http://ethioliberty.wordpress.com/

የከረቱ ሥርቻው በዚያ አህያ በማይችለው ዝናብ ታጥቦ ፣ ተጠራርጐ ሲነጋ ፣ እርይ ይላል ።

በዚህ ንጋት የቤት ቆርቆሮ ከዳን እንጥፍጣፊ ላይደርቅ ፣ በቦይ «ጡር ... ጡርርር» የሚለው ወራጅ ውሃ ላይ ጠራ ፣ በወይዘሮ እንቺዬ ቤት ከረር ላይ ምልልስ ተሰምቷል ።

የእንቺዬ ወሰን ሰገድ ቤት ከእጉራብቶቹ ሲነጻጸር ሰይን ይሞላል ። አጥሩ በቆርቆሮ ተለብጧል ። እንቺዬ መኪና ባይኖራቸውም ፣ ግቢው የመኪና በር አለው ። እተካሪው ተጥዷል ።

« እንግዲህ ከዚህ በላይ መናገር አልችልም ... ሥርቼ እከፍላለሁ ! ... የምናገረው እግርኛ ነው ። የቶ ለየ ሊመና እላውቅም ።» ብለው ሮሙ — አብዬ በርባሶ ። የእጥሩን በር ከፍተው እንደ ፈንጣ ተፈናጥረው ወጡ ።

« እንዴ ! እንዲህ ነው ! አንቶ ምናምንቴ ! ... እእ ላይ ነው — በር ዘግተህብኝ የምትወጣው ? ... ወይእ እንቺዬ ! ... እማን ቤት በኖርከው ! አሁን ከተንሀ ቃጣኸው የለ ? ... የዛሬን ለሊት ብታድር እእ እይደለሁም ! እመ ብርሃን ትፍረድብኝ ... አሁን ይረበሽን እጠራው የለ ! ቤትህን ሊያሽጉው ፣ የት እንደምትገባ እናያለን ... እንዲህ እርን ይቀልድብኝ ! » አሉ ፣ እንቺዬ በቁጭት ።

እቶ ገሪማ ገብሬ ወልድ መታየቸው ሽበታ መሥራት ሆነና ቅጽል ስም አግኝተዋል — « አብዬ በርባሶ »



የሚል ። ሕፃናት ይሁን መንደረተኛው የሚጠሯቸው በዚሁ ነው ።

በዚያ ኮረኮንች ለዘለቀ ፣ የተቆፈሩ ቤቶች ያገኛል ። ሰዎች የማለዳውን ብርድ «እትትትት ! ...» እያሉ የማ ዳቸውን ይቀበሉታል ።

የመንደሩ ነዋሪ እቶ ከፍሌ ፣ ከእጃቸው የማይለየውን ከዘራ ከጭታቸው መሐል ላይናቸው በሚታይ ድንጋይ ላይ እየተመረኮዙ ፣ በዝግታ ወደ ድልድዩ ያዘግማሉ ። ወይዘሮ እንቺዬ አጥር ሲያርሱ ሲሉ ነው ፣ አብዬ በርባሶን የተመለከቱት ።

እቶ ከፍሌ ለወሬ ያለ ነገር የተገነዘቡ ይመስል ፣

« ምነው እያ ገሪማ ! ... በማለዳው ምን መጣ ? » አሉ ፣ ሮጥ ብለው ። ካፋቸው የሚወጣው እየር ፣ እንደ ግድ ቤት ጢስ ይጤሳል ። ገሪማ ገብሬ ወልድ የሚለው ስም ጠፍቷቸው « አብዬ በርባሶ ! » ሲሉ ምንም አል ቀሩቸውም ነበር ። በሥራቸው ያለፈች የጉረቤት ልጅ ፣

« ይሄማ እይደሉ ! ... ጋሼ ከፍሌ ! » ብትልም ፣ ሽበት ጣል ጣል ያለበት ቅንድባቸውን ወደ ላይ ወጥረው ፣ አብዬ በርባሶ ላይ እፍጠው ፣ መልስ እልሰጡትም ።

አብዬ በርባሶ ፣ ዓይን ወደ ድልድዩ ለመሔድ ያሰቡትን ያህ እርገው ፣ ከወደ ኋላ ያዳመጡትን ድምፅ ተከትለው ዞሩ ።

« እንዴ ? . . . አቶ ከፍሌ ! . . . ሰሞኑን አልተ ናኘንም 'ኮ ፣ እንዴት ሰንበቱ ? . . . ደህና አደሩ ! »

« ደህና ፣ ደህና . . . ይመስገን ! አለው ። እኛማ ወደ ናዝሬት ወርጄ ነበር ። እግረ መንገዴን ፣ ለቀ ደረስኩ ። የኛን የጡረተኞች ነገር መች አጣኸው ? . . . አደባባይ መውጣት ነው ። ፀሐይ መሞቅ ነው ። ከዚያማ ወግ አውግቶ ፣ ተጨዋውቶ ወደ ቤት መመለስ ነው ። ዘመድ ለመጠየቅ ወዲያ ወዲህ ማለት ፣ ሐዘን ቤት ጉራ ማለት ፣ በሽተኛውንም ከሆስፒታል መጠየቅ የት ይቀራል ? » ሳመል ያህል ፣ « እህ ! . . . እህ ! » እያሉ ሳሉ ።

« ደግ . . . ደግ ! ለማናቸውም ጤንነት ይቀድ ማል ። አሁን ለጤናም እንዴት ነዎት ? » አሉ ፣ አብዬ በርባሶ ። ልቡ እስኪጠፋ ከለፋ ቆዳ የሠሩትን ባርኔጣ ዞር ዞር አድርገው አስተካከሉት ። ስልቻ ማሠሪያ በሚ መስል ቀጭን የሌጦ ገመድ ተብትበው አጊጠውታል ።

በል ሲላቸው አብዬ በርባሶን ፣ ከሸበቶ ሌላ እን ዳንድ ነገሮችን ይሠራሉ ። ቀበቶ ፣ ቦርሳ ፣ ባርኔጣ ፣ የግ ድግዳ ጌጣጌጥ . . . ሆኖም ፣ ሁሉንም የሚሠሩት ከቆዳ ነው ።

« ደግ ነኝ ! እንተስ ደህና አይደለህም እንዴ ? . . . በማለዳ ወዲያ ወዲህ ሚያደርግ ምን ጉዳይ ገጠመህ ? » አሉ ፣ ከጆንበሬታቸው ሥር በቀጭኑ የተመዘዘ አንገቻ ውን እሽት ፣ እሽት እያደረጉ ።



http://ethioliberty.wordpress.com/

« እረ ምንም አይደል ! . . . እንዲያው አንቺዬ ተነሡብኝ እንጂ ፣ 'ቤቱን ልቀቅ ፣ ደባልነታችን ቢቃ' ብለው ። ወፍ መንጫጫት ሳይጀምር ነቅተው ይነትር ኩኛል ። ሲሉ ፣ እጃቸውን ጉራዳ ካፖርታቸው ኪስ ውስጥ አግብተው ወደፊት ወጠሩት ። ወፍራምና አጭር ጣታቸው ፣ ፍርጥም ብሎ ቅርፁ ይታያል ። ካፖርቱ ጥቁር ቡኒዬ ቀለሙን ፣ በአመድማነት እየተቀየረው ነው ።

« ታዲያ ዝም ይባላል እንዴ ? . . . መስማማት አይ ሻልም ? . . . እረ ደግ አይደለም — ነገር ሲከረር ይበ ጠሳል ! . . . »

«ጨዋነት እንጂ መች ሰው ያናግራሉ ። አንቺዬ የሰው ነገር ሊገባቸው ?. . .እይ ! እርግማን ። የድህነት እርግማን ይኸው ያባስናል ። 'ሠርቼ እከፍላለሁ— ኪራዩን' ብል ፣ አልሰማ አሉ ። ተለማምጬው አልኖር !—እኔ ደግሞ ። ሰሞኑን ዐረፍ ብዬ ነበር ። ዛሬ ምን ከቶ ሕልም እንዳዩ አላውቅም ፣ ተነሡብኝ ። እንዴ ነገር ከያዙ ደግሞ ምንቸኩ ነው— የሚሉት ። እስቲ እግዜር ያሳዩዎ ! » አሉ አብዬ በርባሶ ፣ አጭሩ ቁመታቸው ይመዘዝ ይመስል ፣ ባውራ ጣታቸው እየተንጠራሩ . . . ወደ ላይ . . . ወደ ላይ . . .

* * *

ገሬማ ገብረ ወልድ ፣ ከልጅነት ዕውቀት ድረስ ሥራ አልተለያቸውም . . . ሥራ ሰው አርጎቸው ፣ በመንፈስ ጠንክረዋል ። ቁመናቸው ከዕድሜያቸው አንድ ዐሥር

ዓመቱን ይደብቅላቸዋል ። 'የሚሠራ እያረጀም'፣ የሚያስኝ ሐሳብ የሚፈጥር ዓይነት ።

በዚች ምድር ምን ያህል ዓመት እንደኖሩ ማንም መገመት አይችልም ። እሳቸውም ፣ ዕድሜውን አያውቁትም ፤

«ማሲያን በ፲፱፻፴፫ ወደ መጣበት ሲመለስ ፣ ሐረር ከተማ ቄስ ትምህርት ቤት እመላለስ ነበር» ይላሉ ። አባታቸውን ለይተው አያውቋቸውም ። ነፍስ ሲያውቁ የተረዱት ቢኖር ፣ አባታቸው ከማሲያን ፍልሚያ ጊዜ በዚያው ማለፋቸውን ነው ። እናትየውንም ወዲያው በሽታ ቀሠፋቸው ።

በናትና አባት ፍቅር ፋንታ የተተካው ሥራ ፣ ከዚያ ጀምሮ ለምጦ ፣ እቅንቶ ቀርፆአቸዋል ። በራስ መኖርን ፣ ራስ መቻልን አሳይቷቸዋል ። ሥራ— እምዬ ፣ ሥራ —አባቴ ፣ ሕይወት ራሷ ሥራ ሆነች ።

ጉስቁልናቸውን የተረዱ የግሪክ ነጋዴዎች አስጠጓቸው ። እየተላላኩ ፣ ሸቀጥ እየተሸከሙ ፣ መደብር እየጠረጉ አደጉ ። የዕለት ጉርሳቸውንና ያመት ልብሳቸውን አገኙ ።

እያቋረጡ ፣ እየጀመሩ በትምህርታቸው መድረሻ ዓለም ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ደርሰው ነበር ። ትምህርቱም ቀንቷቸው ፣ መምህራንም በውቀቶቸው—አስበጿቸው ። ሆኖም ከሕንዶቹ ጋር ግጥም መሆን አልቻሉም ፤ ጉሮሮ ለጉሮሮ መተናነቅ ነበር— የሚቀራቸው ፤ ሲከራከሩ ፣ ሲከራከሩ ... የእንግሊዝኛን ቋንቋ ስለሚያ

ቀራቀሩት ፣ ሐሳባቸውን እንደፈለጉት ስለሚገልጹ ... ተናግረው ይወጣላቸዋል ። ታሪክን እንደነበር አርገው ይሸመድዱታል ። ታዲያ ሳይገስ ይጠምባቸዋል ። ያ ጠምባዛ ደሳብ አለምጀቸውን ይቆጣጠረዋል —አይሆናቸውም ።

ደገፉ አልነበራቸውምና ሙሉ ጊዜያቸውን ለትምህርት ማዋል አልቻሉም ። ኑሮ ኑሮ ማለታቸውን የተገነዘቡት ነጋዴዎችም ፣ መጠጊያ ሊከለከሏቸው ሆነ ።

ወዲያ ወዲህ ሲሉ ፣ ብልጠታቸውን ያጠና ማሲያን ፣ በቢንቢን ማደያው በገንዘብ ተቀባይነት ቀጠራቸው ።

«ይህን ጭንቅላትህን ሥራበት ። አለዚያ ሸረሪት አድርቶብት ይሸማቃል ። እንዴት ሰው እንደምትሆን ልምከርህ ። አላምዋ ! . . . ማሲያንኛ ቋንቋ አጥና ። ታሪክ ይቀናህ የለ ! . . . የማሲያንን ታሪክ ለብልበው ! ከዚያ በኋላ እንድትግባር ዘዴ እፈልግልሃለሁ ። ሮማ ሔደህ ትማራለህ . . . . . . ጥሩ አርጌ ስላንተ ለዘመዶቼ እነግራቸዋለሁ . . . ገባህ ! ሰው ሁን ! ምን ትፈዛለህ ! ማማሚያ !» ይላቸዋል ፤ረጅም ሰውነት ያለው አጀፍልፕ ማሲያን ።

«ግን ! ግን ! ትልቅ ቁም ነገር ዘንግተሃል ፤ ሲኖር ! የሰው አገር ታሪክ ለማጥናት ከማንጓበል በፊት ፣ ያገሬን ማጥናት ያስብኛ ይመስለኛል ። አንተ 'ያገርህን ትተህ የኢትዮጵያን አጥና !' ቢሉህ ፣ 'እሺ !' ትላለህ ? . . . አየህ አቢሲኒያ ገና የሚመረመር ታሪክ ፣ የሚወሳ ገድል አላት ። መጽሐፍ ቅዱስ አላገላበጥከም ! የሳባን ፣ የጠቢቡን ሰሎሞን ድንቅ ሥራ አታውቅም ማለት ነው !



http://ethioliberty.wordpress.com/

http://ethioliberty.wordpress.com/

. . . የአቢሲኒያ ታሪክ እንዲያ ረዥም ነው ። የጥንቱ የጠዋቱ የአክሱም ምጡቅ ሥልጣኔ ደማቅ እንደነበር አስብ !አውሮፓ የት ነበር ? ያኔ ፣ የት ነበር ? ደም ማሊያንኛ ሆን ተወኝ ። እኔ አይሆንኝም ! 'እሺ !' አይለኝም » እያሉ ይከራከሩታል ።

አብረው ለብዙ ጊዜ ሠሩ ። ተከራከሩ . . .

የኋላ ኋላ የጣሊያኑ ጤና ታወከ ። ዕድሜ ተጫጫነው ። በጣሩ ሌላውን ተክቶ ወደ ሀገሩ ተመለሰ ። አብዬ በርባሶ አዲስ ከመጣው ጋር አልተጣጣሙም ። 'ሐሳብ ጉደለ ፤ እያያዙ የተዘረከረከ ነው' — በሚል ሽፋን ፣ ወደ ጋራዥ ዝቅ አረጓቸው ።

ይሄኔ ፣ አንዱ ጣሊያን መለስተኛ ጫማ ቤት ሲከፍት ተከትለውት በመውጣት ፣ አብረው ለአሥራ ስድስት ዓመታት ያህል ሠሩ ። ይህኛውም በለውጡ ወቅት ተደናግጦ ሲወጣ ፣ የቀራቸው ሙያው ብቻ ነበር ። ጊዜው በሩጫ ሲያልፍ ፣ ሕይወትም ፋታ አልሰጥ ስትል ፣ ትዳርን በቁም ነገር አልጨበጡትም ። ይልቁንም ከመጽሐፍ ተጣብቀው ተገኙ ። ዕረፍት ሲያገኙ ማንበብን ፣ ዓለምን መመርመርን መረጡ ።

«መምህርነት ከተገኘ የእንግሊዝኛ ቋንቋ ላስተምር !» ብለው ፣ ቢተልሔም ትምህርት ቤት ድንግላውያኑ ዘንድ ተቀጠሩ ። እዚያም ለተወሰኑ ዓመታት አዩትና ወደ አዲስ አበባ ገቡ ።



«ካንዱ ቤት ወደ ሌላው» እያሉ መጠጊያ ፍለጋ መባከን፣ እንገሸገሻቸው። አሁን መተዳደሪያ የሆናቸውን የሸበጥ ሥራ ሙያ ፣ የት ቁጭ ብለው እንደሚሠሩት ጨነቃቸው ። መጨረሻ ላይ ነው— ከወይዘሮ እንቺዬ ወሰንሰገድ ጋር የተዋወቁት ። ለዚህም የበቁት በእያሌ ውጣ ውረድ ፣ በደላላ ልምምጥ ነበር ።

እንቺዬም ፣ «እጅ አለው ፣ አይደል? ቆየት ብዬ ማን ብለውም— ይችለዋል !» ሳይሉ አልቀሩም ።

በእንዲህ እንዳሉ ፣ አንድ ቀን አብዬ በርባሶ ያመረቱትን ሸበጥ ተሸክመው ፣ ከሚሸጡ እየከፈሉት ወደሚሸጥላቸው ሱቅ ይዘው ሲሔዱ ፣ እንቺዬ ከበር ቆመው ፣

« እያ ገሪማ ! . . . ጊዜው'ኮ እንደምታየው ነው ። ነጋዴው ዋጋውን አልሰብር አለ ። እኔም ሰማይ ሲደፋብኝ ሆነ— ብያዩን ። አቅሙ የለም ። ከሌሉው ፣ የቤት ሠራተኛው በትንሹ አይደለለም ። ታዲያ የቤቱን ጉዳይ ሳስበው ፣ ለሌላ ቢከራይ የበለጠ እጥፍና እጥፍ የሚገኝበት ይመስለኛል ። ሆኖም ፣ ያንተን ጠባይ አይቼ ፣ ድምፅህ የማይሰማ ፣ ሥራህን አሳቢ በመሆንህ አይደል ያስጠጋሁህ ፣ በል ከዚህ ወር በኋላ ዐሥር ብር ተጨምሮብህ ፣ የየወሩን ትሰጠኛለህ » አሏቸው ።

አብዬ በርባሶ በፈናቸው ፣

«እሺ ይተውኝ እንቺዬ ! ልሥራበት ፣ 'መድረሻ የለውም !' ብለው ሲወጣ ፣ ሰንባ ኪራዩን እየቆጠሩ ተራሩ

http://ethioliberty.wordpress.com/

እያሳከሉት ! እንዲያው ስለ ሲቀመላኩ ብለው ኃጢያቱ አይታይዎትም?» ብለው ይረግሙኛል። መልሰው ደግሞ «ጠቅ ልለው ያስወጡኝ እንደሁ የት እገባለሁ ?» በሚል ሥጋት ፤ ከተጠየቁት ግማሹን ይሁን ብለው ቃል ሰጡ ።

★ ★ ★

አሁን ፤ 'እሻፈረኝ !' በማለት በሩን ዘግተው ወጥተዋል ።

« አሁን እሱ ታዲያ ? . . . ወይዘሮ እንቺቱ ?» ይጠይቃሉ አቶ ክፍሌ ደሱ ።

«መናገርማ እሱ . . . እንዲያው እንደ ጧት ጸሎት እኔን ካልለከፉ አልሆን አላቸው እንጂ !»

«ቆይ እስቲ ። ተጐራብተን እያለ ፣ ዝም ብሎ ማየት ይገባ አይመስለኝም ። . . . ላናግራቸው ?»

« የለም ! የለም ! . . . አቶ ክፍሌ ፣ ለምን ብለው ? እንቺቱ እንደሁ አይሰሙም ። እያዳምጡም እያልኩ ! ይልቅ ወዴት ነው ፤ የሚሔዱት ? ይቀጥሉ አብረን እናዝግም ። እንቺቱ የሚያደርጉትን እያለሁ ፣ መታገሥ የፈሪነት ምልክት ከሆነ እንሒድ ፤ አሁን ሌላ ጉዳይ አለኝ » አሉ ፤ ባውራ ጣታቸው እየተንጠራሩ ።

«ቢሆንም ! እናግራቸዋለሁ ። እንዲያው ሁሉም ነገር በዕልህ አይሆን ! » ሲሉ አቶ ክፍሌ ፣ ቀይ መስመሮች ሸንተር ያወጡለትን ጥቁር ክራባት ፣ ሁለት እፍኝ በሚዘጋው እጃቸው አስተካከሉት ።



ፊታቸውን ወደ ግቢው በር አዙረው ፣ እንዳሉ ።

«ቤቶች ! . . . ጃረ ቤቶች ! የማለዳ እንግዳ አትቀበሉም ! » እያሉ ፣ ገብተው እንዳይመታቸው ጕንበስ ብለው ወደ ውስጥ ዘለቁ ።

አብዩ በርባሶ በባዶ ስሜት እጃቸውን ከካፖርታቸው ኪስ እንዳደረጉ ፣ የግዳቸውን ተከተሏቸው ።

«ቤቶች! ወይዘሮ እንቺቱ ! ወዴት ነዎት ! ሰውም የለ ?» ይላሉ ።

አንዲት ልጅ እግር የሳሎኑን በር ከፈተች ። ከቤት ውጭ የሚቀፈፈውን አየር ያልተለማመደው ሳንባዋ እየገፋት ፣ ከአፍንጫዋ ቡልቅ ፣ ካፏ ብትን የሚለው አየር ያልተቀጣጠለ እርጥብ እንጨት ጢስ ይመስላል ።

ወይዘሮ እንቺቱ ብቅ እንዳሉ ፣ አቶ ክፍሌ ሰላምታ ለማድረስ ከዶረታቸው ገቅ አሉ ። በሩ ሥር እንደሆኑ አብዩ በርባሶ ፣ ካንገታቸው አቀረቀሩ ።

«ውይ ! ውይ ! አቶ ክፍሌ ! ከወዴት ተገኘህ ? ደህና ሰነበትክ ? . . . እህ! አያ ገራማም አለ ለካ ፣ አልሔደምና ። በር ዘግቶብኝ አልወጣ መሰለህ ? ለካ አንተ ዘንድ ሰሞታ ሊያሰማ መርጦ ኖሯል ? . . . ግባኝ ! »

«ደህና አደሩ ወይዘሮ እንቺቱ ! ጃረ በፍጹም ስለ ሞታ አልመጣም ፣ ወዲህ ከኮረኮንቹ ተገናኘተን ነው ። እኔስ ምንድን ነኝና ሰሞታ አሰማለሁ ? እንዲያው ሁኖቴውን አይቼ ነው ፤ 'ምንውን' ብዬ፤ አያ ገራማን የጠየቅኩት ።

http://ethioliberty.wordpress.com/

እኔው ነኝ ካልገባሁ ያልኩት ። እግሬ መንገዱንም ለሲ ምታ ነው ... ብርቱ ነዎት ?»

«ምን ብርታት አለ ?— በብቸኝነት ። ወይ ያቺ ልጅ እዚሁ መጥታ ፤ ቤተሰብ ይዛ— እይዞሽ ! ብትለኝ ፤ ይሻለኝ ነበር ። አሁን ደግሞ ወደ መተከል ሔዳለች ። የቢ መሔጃ ፤ መቼም ማለቂያ የለውም . . . ታዲያ ግባ ’ንጂ ወደ ቤት ?»

«የለም ! እሔዳለሁ ፤ . . . እያ ገሪማ በሰጡት ቤል ፤ ተጕራብተን እያለ እንደ’ት የጕሪጥ ተያይተን እንተላለ ፋለን ?... ብዬ ነው ፤ » ሲሉ አቶ ክፍሌ ፤ በቀማቸው እግራቸውን አጠላልፈው ፤ ባንድ ጕናቸው ከዘራቸውን ተደግፈዋል ።

«እዬ ! ... እያ ገሪማ የመጣ ሰሞን የሰው መጨረሻ መስሎኝ ነበር ። ዛሬማ ተቀይሯል ። እንደ ድሮው ፤ የሚሉ ትን አይሰማም ። ኑሮዬን ፤ ብቸኛነቴን እያወቀ ገፍትሮኝ ያልፋል ። ይኸው አራት ወር ሙሉ ኪራዬ አልከፈለኝም። ምን ልቅመስ ? ደግሞ ለነፍሴ ብዬ ነበር— ያስጠጋሁት ። እዬ ጽድቅ !... ዘመኑ ነው ! . . . ቅድም ‘እንተያያለን !’ እያለ ሲፎክር ነበር ። ግዴለም ፤ ዛሬውኑ ባዘን ጠቅልሎ ይወጣታል ! »

« እዬ ! ወይዘሮ እንቺዬ ! ይህን ያህል ዓመት አብ ራችሁ ኖራችሁ ፤ ተቻችላችሁ ፤ አሁን ማኪረር ምን ይበ ጃል ! .. ታዲያ ሁናቴው እየታየ አስተያየት ማድረግ ነው— የሚገባው ። ሁሉ አይቀሬም !... ይጕድላል ! እርስዎስ እስ



ተቀይ እያደሉ ?» አሉ ፤ አቶ ክፍሌ ሾጠጥ ያለውን አገጫ ቸውን እያሻሹ ።

«አሁንስ ብንከባበር ይሻላል ፤ ወይዘሮ እንቺዬ ! ቸዬ ይኸው እዚህ ከገባሁ ጀምሮ እንደ ፈለጉት ሲሆኑ ፤ ቸዬ ቆይቻለሁ ። መደዳኛ የጫማ ምስማር ተንተርሼ ለማደ ርበት ክፍል የእጥፍ ፤ እጥፍ ማስከፈልዎ እንሰዎት ፤ ማስ ፈራራትዎ ምን ይባላል ? ይደንቃል !... ይልቅስ ቅንሽ ይቃማሁኝ » አሉ ፤ አብዬ በርባሶ። እጃቸውን ከካፖርታ ቸው ኪስ አውጥተው ሲያወራጩት ፤ ቆፈን ከአጥንታ ቸው ዘልቆ ሲነካቸው ፤ ተሰማቸው ።

«መከባበር ?! ... ይኸው ነው—የቀረህ ። ቤቱ የማን እንደሆነም ዘንጋኸው ? ማን የጠፈጠፈው ጭቃ መሰለህ ? ... ደንቄም መከባበር ። ሰው ለነፍስ ሲያስጠጉት እያ ወቅም !... እንዲያውም የልጄ መመለሻዋ ደርሷል ። ማረፊያዋ የላት ። መልቀቅ አለብህ ። ዕቃህን ሰብስበህ ተከብረህ ሒድ ! ‘እይ!’ ካልክ ፤ ደረስ አሁን ይመጣልሃል ! ደውቁልታለሁ ። ቅርኪምርኪህን ጠራርጎ ሲጥለው ፤ በሩን ሲቆልፈው— ቀጋህን ታገኛለህ ። ካንተ ገንዘብ ፤ የልጄ እብሬኝ መኖር ይበልጥብኛል !»

«ወይዘሮ እንቺዬ ፤ ለቤት መፈለጊያ ጊዜ መስጠት እንዳለብዎ አይዘንጉት ፤ በውላችን ላይ የሠፈረ ነው ። ኪራዬን እንደ ምንም ብጨርስም ፤ ሌላ ቤት መፈለጊያ ጊዜ መስ ጠት ግዴታዎ ነው ። »

http://ethioliberty.wordpress.com/

«ኧረ ወዲያ ተወኝ .... የምን ውል ነው ? የሚያወራብኝ ? ... አላቅልህም ተናግሬአለሁ ! »

አንቺዬ ሸብረክ ሸብረክ ብለው፣በረንዳው ላይ ካሉት ምሰሶዎች ወደ አንዱ ተጠጉ ። የለበሱት የሀገር ልብስ፣ ጀፖኒ ነው ። ክንዳቸውን አጥፈው ፣ በክርናቸው ሜዳ ምሰሶውን ተደገፉት ። ፍርጥም ያለው የክንዳቸው ቀይ ጡንቻ ፣ እንዲያ በግዳድ ሲያዩት የደረሰች ልጃገረድ ጭን ይመስላል ።

«ይሁን ያህል መከረርም አያሻም ። ወይዘሮ አንቺዬ!... በተከበሩበት መንደር ወደዚህ ጭቅጭቅ ማምራት አይገባዎትም ። የእያ ገረማን አቅም መድከም አይተው ወዲህ መያውን ወዶ ፣ ደፋ ቀና ማለቱን ተገንዝበው አስተያየት ያድርጉለት ... እሱም ልፋቱን መክፈል አለበት ... ከዚያ በሰላም መኖር ነው »» በማለት ማሊቂ የገቡት አቶ ክፍሌ ነበሩ ።

* * *

ደረሰ አጉናፍር ፣ በወይዘሮ አንቺዬ ባለቤት ክርስትና ተነሥቷል ።

«አምላኬ በልጅ አላደለኝ ፣ ሠናይትን ሠጥቶ አለ ደግሞ አለኝ ። አሁን አንተው ነህ ያለኸኝ ! ማን አለኝ? ደረሰዬ ! ብቸኝነቴን ብታየውኮ እንዴት ታዝንልኝ ነበር ። ይሁን ፣ አምላክን አላማርረውም ፣ ብቻ አንተ



ኑርልኝ ! ... » ይሉታል ዘወትር— በስለኩም ፣ በማንባር ሊጠይቃቸውም ሲመጣ ። ቤቱ መኪና በሱ ስም ፣ ወፍጮ ቤት በልጁ ፣ ደግሞ ሚስቱ ቅልጥ ያለ ቡና ቤት ይዛለች ።

የወይዘሮ አንቺዬን 'አቡነ ዘበሰማያት' ቢሉት ስለሚወጣው ፣ የሚሉትን ጨርሰው ከንፈራቸውን ሲገጥሙ ፣ የሃምሳ ይሁን መቶ ብር ኖት መዞ በመዳፋቸው ውስጥ ያስጨብጣቸዋል ።

ከልጅነቱ 'እንቱ' ማለትን ስላስማሩት ፣

«ካለን መረዳዳት ይቀድማል ። ኋላ መንጫጫት ምን ዋጋ አለው ? ብቸኝነትሽ ዕውነት ሥቃይ ነው ። ይሉት ያሻን ሠናይት 'እዚህ ተቀመጭ ፣ አትያትም ? ደሞ እቢን ብሎ ሀገር አቅኝ ከ» ይላል ደረሰ አጉናፍር ።

«ዕውነት ነው ... ዕውነትህን ነው » ይሉታል— አንቺዬ ወሰንሰገድ የተቀበሉትን ብር እያሻሹ ።

* * *

«እኔማ በሰው ቤት፣ ዝም ብዬ ልኖር ፣ ልዘናዘና አላልኩም ... ለጊዜው ያለችኝን እሟጥጠው ቆዳ ገዛሁበት ፣ ቢሆንም እከፍላለሁ ። ደግሞ ቆዳውን ተሸክሜ ስገባ አይቀጥል ። በዚህም ሥርቼ ከማገኘው መክፈሉ አይቀርም ። አቅምና ሙያዬ እያለ ፣ ብድርና ልመና ልሔድ ? አልሔድም ። ምስጋና ይግባው ለእጄ ! ...

እዚህ አድርሶኛል ... እርስዎስ በኔ እጅ የተሠራውን ሸበጥ አይደል የሚያደርጉት !» አሉ ፤ አብዬ በርባሶ ።

አቶ ክፍሌ ዐይኖቻቸውን ጉልጉለው ፤ የቡና መቀጫ ከሚያስንቀው የወይዘሮ እንቺቱ ባት ሥር ፤ እግራቸው የተጫማውን ሸበጥ ተመለከቱት። የሥረኛው እንደ ምላስ የሳሳ ነው ። ዳር ዳሩ በጥንቃቄ ተቀምቅሟል ። ቁርጭምጭሚታቸውን በከፊል ሸፍኖ የሚነካው ቀጭን የቆዳ ጥብጣብ ፤ ወደ መሐል ከሥረኛው ቆዳ ጋር ይጣበቃል ። ተመልሶ እንደ ሐረግ በመጠምለል ፤ አውራ ጣታቸው ላይ እንደዋዛ ተጠቅልሏል ። ፊት ለፊት የሚታየው ጌጥ ፤ ጥብጣብ የፈሰሰበት ፤ ወይን ካገኘ የማይለቅ ነው ፤

«እሺ !... እንግዲ በመጣ ቁጥር ፤ 'አባክህ እንድ ሸበጥ ቆንጆ አርገህ ፤ አሳምረህ ሥራልኝ !' እያሉ አለ ጠየቁኝም? ሌት እንቅልፍ እያጣሁ ነበር የምሠራው ፤ ለስንት እንግዳ ሰጥተውት ይሆን ! ለመሆኑ ያውቁ ታል !... ሙያ ያስከብራል ፤ ባያስከብር መች ሥራ ይሉኝ ነበር !... እኔ በጄ ነው— የቀምኩት ። የማገኘው እጅና ችሮታ አላይም ። ሸበጥ ሕይወቴ ነው ። ሬጆም መንገድ ይወስደኛል ። ጉልቤ ነው ... እንዲያው እስቲ ያስተውሉ ፤ በዚህ እንጀት በሚያቆስል ክረምት ሕፃናት ባዶ እግራቸውን ከሚሔዱ የእኔን ሸበጥ እያደ ረጉ ቢያደርጉ ፤ ምን ነውር አለበት !... ይህስ ፤ 'እዚህ ቤት ነው — የሚሠራው' ቢባል ፤ ያደርቀል !» ብለው ፤ ወደ አቶ ክፍሌ ዞሩ ።



http://ethioliberty.wordpress.com/

«እያ ገሪማ !.. ዛሬ ሙያን ማን ይንቀዋል ? ማን ይንቃል ! ሌሙና ነው— የሚያስንቅ ፤ የሚያዋርድ ፤ ከሰው በታች የሚያደርግ... የኔን ልጆች የያዘልኝ ማን መሰለህ ናሯል ! ምክባሊያን ፤ ከፈረንሳይ የሚያመጡት ሜማ መሰለህ ? ምንተው ሸበጥ ነው ... ለማናቸውም ልዩ ሆን ከፈል ። ወይዘሮ እንቺቱ! ይህን ያህል ጊዜ እንደ ኖራችሁ ሁሉ ፤ አሁንም ልድሚያችሁን እያሰባችሁ መኖር ነው» ሲሉ አቶ ክፍሌ ፤ ከዘራቸውን አዙረው በሌላ ጉናቸው ተደገፉት ።

«ንበረ ! በዕድሜ መከባበር ... እያ ገሪማ መቼ እን ዲህ ሆንና? ሰው ሲባል ሙሉታ ቢስ ነው ። ለንፍሌ ብዙ ያስጠጋሁት ሰሞን ሲቅለሰለስ ቆይቶ ፤ አሁን ጭራሽ ልዘዘ ባይ ሆንኩ!»

«የለም!... መቅለስለስ ማንም አላስተማረኝም ። አላውቅበትም ። የሚያቅለሰልስ ሲኖር ነው— መቅለስ ለስ የሚያሰኘው ... ሕይወት እግር እላይታኛለች ፤ መለማመጥ አላስጠናችኝም ። ከልጅነቴ እንዲሁ ወግ ሬኛለች ... እኔ እዚህም ስመጣ አሁንም ያው ነኝ» አሉ ፤ አብዬ በርባሶ ፍርጥም ብለው ። ባዶ እንጀራቸው «ጮር ... ጮርር» እያለ ሲጮህ ይሰማል ።

«ለማናቸውም ይረስ አሁን ይመጣል ። 'ሰውን ማመን ቀብሮ ነው' አሉ!... ወዲያ ከታንኩትህን ይወረውሪ

http://ethioliberty.wordpress.com/

ውና ታርፈዋለህ » ይላሉ እንቺዬ ፣ የተደነቁትን ምስ ለቀው ፣ በእጃቸው ነጠላቸውን እያጣፉ በመከናነብ ። ቁፈት የተሰማቸው ይመስላሉ ።

«መቼስ መወታቀስ ያለ ነው ። ያጠፋ እንዲያርም ፣ የበደለ እንዲክስ ። በየቤቱ የምናየውን የሚያሳየን ሁኔታ ፣ እዚህ መልሶ ማየት አያስፈልገንም ። ስለዚህ ይታገሡት ፣ ትንሽ ይመልከቱት» አሉ አቶ ከፍሌ ወደ ወይዘሮ እንቺዬ እየተመለከቱ ።

«አንተም ፈጥነህ ስዳህን መክፈልና ዐርፈህ መቀመጥ ነው » ወደ አብዬ በርባሶ እፍጠው— አቶ ከፍሌ ።

«በል ሒድ!... ደህና ዋል ። ደረስ ሲመጣ እኛው እንነጋገርበታለን ። » ወይዘሮ እንቺዬ ፣ ለአቶ ከፍሌ ነበር— የሚናገሩት ።

«ታዲያ እሱም ቢመጣ ፣ አብረን እንማከራለና !... ምን መሔድ ያስፈልጋል!» ከማለታቸው አቶ ከፍሌ — የመኪና ጥሩምባ ሲመህ ተሰማ ።

«መጣ መሰለኝ ! » እንቺዬ ፣ የቤት ውስጥ መጥረጊያውን ፣ ከበረንዳው ግድግዳ ላይ በመጫን እንዉረዉሩት ።

የቅድሚ ልጅ አግር ፣ « አቤት!» በሚል መልስ መጣች ።

«እስቲ ወጣ ብለሽ ተመልከቺ !... ደረሰዬ መጣ መሰለኝ!» እንቺዬ ፣ በር በሩን እየተመለከቱ ተናገሩት ።



አቶ ከፍሌ የሚሆነውን ለማየት ጓጉተዋል ። ሥራ ተኛዋ የሰከቸውን ሽበተ ባይናቸው ተከተሉት ። ጭቃ ለከፍ አደርጎታል ። እንደ አቅሙ የተዋበ ነው ። 'እንዲያው ምናለ ለሚሠራ ብናግዝ ? እዬየሁ በርታ ፣ ሥራ ብገል ? ታዲያ እንዴት ያልፍልናል ? እንዴት ከችግር እንላቀቃለን ? መኖር ፣ መዉታዉት ፣ ከጉንሆም አቅቶር መምዘዝ ... የት ያደርሰናል ? የት ? ...' የሚል ሐሳብ መጣባቸው ።

ደረስ የመኪናውን ቁልፎች እርስ በርሳቸው እያጋጨ ፣ ጭቃ ጭቃውን ለይቶ እያለፈ ገባ ።

«ደረሰዬ መጣህ ? ... ያላንተ ማን አለኝ ? የኔ ፈጥኖ ደራሽ ! ... ግባ ፣ እለፍ ወዲዚህ ! ... ደረሰክልኝ ! በል ይህን ሰው አባርልኝ!... ለዚህ ነው በጠዋት ያገኘሁት ሁሉ ... አባርልኝ ! ...»

«ደህና አደራችሁ ? ... ምን ነው ? ምን መጣ በጠዋት ነው» ብሎ ወደ እንቺዬ ሲያመራ ፣ አብዬ በርባሶን እንደ ነገሩ 'ሰላም!' አላቸው ። ለአቶ ከፍሌ እጅ ግም ነበር ።

«ኖ !... ኖግባ! ብርዳም አያስቀምም ። ሰው ሁሉ ተነሥቶብኛል ፣ ምን ላርግ ? ወዲህ ደግሞ ብቸኝነቱ ... ግባ ! ... ታዲያ ይህን ሰው አባርልኝ . . . ቀይቶ ሊያጠፋኝ ይቀራል» ብለው ፣ ተከትለውት ገቡ ።

አብዬ በርባሶ ፣ አሁን ገና ቁፈት ተብሶት እርጎ የጠቀጠቃቸው ይመስል ፣

http://ethioliberty.wordpress.com/

«እተተተ !... አይ እርግማን !» ይላሉ ፣ ባሙሩ ማታቸው ፣ ወደ ላይ ... ወደላይ እየተንጠራሩ ።

አቶ ከፍሌ ከዘራቸውን ወደ ሌላ ጐናቸው ሲያዞሩ በደመነፍስ ነበር ። የሰውን ባሕርይና ምንነት አን ጠርጥረው ለማውጣት ወደ ፍልስፍናው ነጐዱ ...

«ምንው መተሳሰብ እንዲህ ይጥፋ? ተንኮል ፣ ጥላቻ ወሬያውም የራስ ጥቅም ብቻ ! ታዲያ በምን ተአምር ችግራችን በኛ ይጠፋል ! 'ሥራ ! በርታ !' ይባላል እንጂ ፣ ሰበብ እየሰነጠሩ አብራሪ ፣ ተባራሪ መሆን! ... ሰው አጥፊ ፣ አልሚ ...» — ተቋረጠባቸው ።

«በል ደህና ዋል !... በሌሊት አለፋሁህ ፣ ማን አለኝ ብለህ ነው ?» አንዷይዬ ንግግራቸውን ሳይጨርሱ ፣ ደረሰ እየፈጠነ መጣ ።

«አቶ ከፍሌ !... በዚህ ቀፈን ተጠበሰክ አይደል! ደህና ዋል ፣ ተሰማምተናል ፤ 'እሱቲ አንድ ዕድል እን ሰጠው' ብለናል» ሲሉ ፣ በእጃቸው የሚያሻሹት የብር ኖት ታየ ። እየፈነደቁ ወደ ሳሎን ገቡ ።

አብዬ በርባሰና አቶ ከፍሌ ተያዩ ። ተያይዘው ከግ ቢው ወጡ ።

ወደ ድልድዩ አቅንተው ሦስት ፣ አራት እርምጃ ዎች እንደ ተራመዱ ፣ በደረሰ አጕናፍር መኪና ውስጥ የተወጠሩ ሁለት ወጠምሻ ጉረምሶች ገላመጧቸው ።

ከእንገታቸው ሲያቀረቅሩ ፣ መንደረተኛው የተጫ ማው ሸበቶ ነበር . . . ሸበቶ . . .



# ፈጣን!

በሰኔ ያስገመገመው ደመና ፣ የክረምቱን ኃያል ነት አብሥሯል ። ቁልቁሎቹ ጠቁረው ፣ ተንጠልጥለው ... እያለቁ እያለቁ በሰማዩ ላይ ይታያሉ ። የሚሆንበው ዝናብ አዲሳባን አርጥቧል ።

በከተማዋ መንገዶች ሰዎች ችምችም ይላሉ—የችብ አስር ይመስላ ። ከዚያ አንድ ወይም ሁለቱ ተነጥለው ሲወጡ መጠነኛ መተራመስ ይታያል ። እንዳልነበረ ሆኖ የተሰበሰበው የሚበተነው ፣ ከመሐል የሚገኘው ያፈተ ለክ እንደሆን ነው— ንግሥቱን እንዳጣ ንብ ኸረው ይላል ። ይህ የመንገድ ላይ ትርዒት ፣ «... ምን መጣ?... ምን መጣ?» እያሰኘ አጠያየቀ— ያልሰማውን ።

«ፈጣን !... ፈጣን! አዲሱ ፈጣን ሎተሪ ነው የመ ጣው ። ታዲያስ ! ... እርስዎስ ተጋፍተው አይሞክሩም?» መልሱ ማግባቢያ ሆነ ።

«... ይሞክሩ ፈጣን ሎተሪ
ችግር አባራሪ !...»— ተብሎ ተገጠመ ።

የመንገድ ላይ ትርዒቶች መመልከት ሲበዛ ያስደስተኛል . . . የሚሰማኝን መናገሬ ወሬኛ ያሰኘኝ ይሆን ፣ ቢሆንም አንዳንድ ለአደጋ የሚሰጡ አጋጣሚዎች አይታጡም— ዝርፊያ ፣ ድብድብ . . .ሌሎችም ። እነዚህንና ሌሎች ትርኢቶን በሩቅ ማየት ነው ፣ ባይ ነኝ ።

ቆየት ቢሆንም ፣ አንድ አዛውንት ያጫወቱኝ ትዝ አለኝ . . .

አቡነ ጴጥሮስ ሐውልት ወረድ ብሎ አንድ ቡና ቤት በረንዳ ላይ ቡና አዝዤ ቁጭ እንዳልኩ ነው— ሰውየው መጥተው እኔ የምጠቀምበትን ጠረጴዛ የተጋሩት ። ፊት ለፊታችን ወጭ ወራጁን እናስተውላለን። ከወደ ላይ በኩል ልጆች ቀድመው ፣ ዐዋቂዎች ለጥቀው ከመንገዳቸው እየወጡ ሰብሰብ አሉ ። ከበው የሚመለከቱት ፣ የሆነ ነገር ያለ ይመስላል ።

«አይ የዛሬ ሰው !» ሲሉ ንግግራቸውን ጀመሩ ፣ ሰውየው 'ይቀጥሉ . . .' በሚል ስሜት ፣ ወደ ጐን አየኋቸው ።

«ይኸውልህ ...አንድ ጊዜ በራስ መኮንን ድልድይ በኩል ሳዘግም አሁን እዚህ እንደምታየው ፣ ድልድዩን አጣበው ቁልቁል ወራጅ ወንዙን ይመለከታሉ ። እኔም ምን ተፈጠረ ብዬ ፣ ለማየት በፍጥነት ገሠገሥኩ ። ሰዎቹ ተንሰፍስፈው ሲመለከቱ ፣ ከበድ አደጋ መሰለኝ ። 'ወይ መኪና ተገል



ብጦ ፣ ወይም ሰው ወድቆ ... ይሆናል ' እያልኩ ድልድዩ ስደርስ መፈናፈኛም የለም ። የሚተላለፈው መኪና ጥሩንባውን ይለቀዋል ። መንገደኛው ይጋፋል ። እንደ ምንም ተጋፍቼ ቁልቁል ብመለከት ፣ ለካ አንዲት ትንሽ ውሻ ገብታ ነው — ያ ሁሉ ሰው የተሰበሰበው ። ነደደኝ ። አሁንም እዚህ የተሰበሰበው ቁም ነገር ፍለጋ አይምሰልህ . . . » በማለት ፣ ባለፈው የተቆጩትን መልሰው በስሜታቸው ረጩት ።

'እውነትም ያናድዳል !' ብዬ በሐሳቤ— የሰውየውን ቁጭት በመደገፍ አንገቴን ነቀነቅኩ ።

የሌሊቱን ባቡር የሚሳፈሩ ፣ ቀድመው ለመገኘት ልባቸው እንደቆመ በችኩላ ሲራመዱ ፣ ፈጣን ሎተሪ በአዲስ መጥንቱ የፈጠረውን የመንገድ ላይ ትርዒት እያሰላሰልኩ ለገሐርን አልፌ አዘገምኩ ። ዐረፍ የምልበት ቡና ቤት ፈልጌአለሁ . . .

. . . በአውቶቡስና ታክሲ ውስጥ ፣ በቢሮዎች ፣ በሆስፒታሎች፣ በቀበሌ ሕዝብ ሱቆች ፣ በትምህርት ቤቶች . . . ወሬው ይኸው ፈጣን ሎተሪ ! መሆን አለበት ። በሦስትና አምስት ሰኮንድ አንድን ነገር ማወቅ አለማወቅ በራሱ ታላቅ ጉጉት ይፈጥራል ። ሰው ደግሞ በተፈጥሮው ጉጉ ነው ። እና «ፈጣን ሎተሪ ያጓጓል ! . . .» እያልኩ ሳወጣ ሳወርድ ፣ ብዙ እንግዶች የሌሉበት ቡና ቤት በጨረፍታ አይቼ ገባ አልኩ ።



http://ethioliberty.wordpress.com/

http://ethioliberty.wordpress.com/

ታውቃላችሁ፤ ሰዎች የሚሰበሰቡባቸው መዝናኛዎች የለየላቸው የንግድ መናኸሪያዎች ናቸው። ከሜዳ አሳማ ሬው ሲሰትር እንሥቶ፤ ጋቢ ወይም ውድ ጌጣጌጦች ሻጩ ድረስ... ሁሉም ነጋዴዎች ናቸው ። ካንዱ ሌላው በማባበያ ብልጠቱ ይለያያል። ሬት የሰጡት የእግር ሹሩብ እሷሬ 'ካልገዙኝ!' የሚለውን ያህል ፣ በቁጣ ብርር የሚል የእቸሎቷ ቸርቻሪ አለ ።

ሰዎች በቡና ቤቱ ሲጨመሩ፤ ጫጫታው በረከተ ።

የሚካሰበው አስተናጋጅ ወደኔ ቀርቦ፤

«እሺ ሀስ!...» አለኝ ። በጠፈ ንግድ መሓል፤ 'ፍትንት' ታግስ የመጠበቅን ቦታ እንደሚወርስ ተገንዝቤ፤

«ቡና እንደ ወረደ ...ያለ ስኳር!» በማለት አዘዝኩት ።

ወዲያው የደረት ኪሴን ደባብሼ የሲጋራ ፓኮ አወጣሁ ። ከብሬት ይዤ ለመለኮስ ስዘጋጅ፤ ሬዘም ያለ፤ ልጅ ነት ያለው፤ ጥቁር መነጽር ያረገ ሰው ሲገባ እንደቆባ ቀልቤን ወሰደው ።

ሕፃን ቤት ልጅ እሬት እሬቱ እያለች፤ እጁን ይዛ ትመራቸለች። ፈጥና ወንበር ሰባ፤ ወጣቱን አስቀመጠችው። እሷም ከሌላ ወንበር ላይ በሬቧ ተንጠራርታ ተቀመጠች ። እግርጿ ተንጠልጥለዋል። ስታወዛውዛቸው ትሥቃለች። ንፍጧ ሲያስቸግራት ደግሞ በሰማያዊ ሽሚዟ ትጠርገዋለች ።

ሲጋራዬን ማግ፤ ማግ አርጌ ጢሱን ባፍና ባፍንጫዬ ከለቀው ሁለቴ፤ ሁለቴ እያለ ወጣ ።



ወጣቱ—ዐይነ ሥውር ነው ። በእተግመጡ፤ ከወንበር ጀምር ቀና ይላል ። ወደ የትኛውም የብርሃን ጭላንጭል ሬቱን እያዞረም ። ቀስ እያለ መነጽሩን ወደ ላይ ገፋ፤ ገፋ ያደርገዋል፤ እንዳይወልቅ መመለሱ ነው ።

«ይኸው...» አለኝ፤ ያዘዝኩትን ቡና ከጠረጴዛ ላይ ያኖረው አስተናጋጅ ።

ቡናውን ፉት ብዬ ወጣቱን ዐይነ ሥውር አስተዋል ኩት ። እጁን ያፍተለትላል ። ትንሿ ልጅ በበኩሏ፤ በማቶቿ ያዘ...ጭምቅ...ለቀቅ ታረገዋለች ።

በእርግጥ ሁለቱም የሚመሳሰሉ ናቸው ... እህቱ ትሆ ናለች ። ወይም ወጣቱ እንጦጦ ሲሆን ይችላል ። የሱ ልጅ ብትሆንስ...መላ ምት ደረደርኩ ።

ከወጣቱ ገጽታ ብልጠት ይነበባል ። ጉንበስ ብሎ ልጅ ቷን ሲያናግራት ትሥቃለች... መልሰው አብረው ይሣ ሣቃሉ ።

« ትምህርትሽን ታጠኚያለሽ ወይ ! »

«እም !»

«ግን ደብተርሽን በደንብ አትይዢም ይባላል !»

«ውሸት ነው፤ ውሸት ! ቀልድ ነው ። እኔ ባንድ ደብተር ሁሉንም ትምህርት ስለምጽፍ ነው !»

«ይኸማ ስንፍና ነው ። ለምን ለየትምህርቱ ደብተር

http://ethioliberty.wordpress.com/

አትይገርም ! »

«ለኔ የሚቀለኝ ባንድ ደብተር ሲሆን ነዋ !»

«በኋላ ፣ ፈተና ሲመጣ እንዴት ማጥናት ትችያለሽ !»

«እ. . . እችላለሁ ፤ አሁን ጊዜዬንን ፣ የኛ ክፍል ተማሪ ብታየው ፣ ጭን ላይ በስክሪብቶ ይጽፍና እቤት እገለብጠዋለሁ ይላል ።»

«እሱም ሰነፍ ተማሪ ነዋ ! እብራችሁ ነው—የምትቀመጡት!». . .ወጣቱ ይሥቃል ።

የልጅቷ ዐይን ቅብዝብዝ ይላል ። በሌላ ጠረጴዛ ላይ የቀረበውን. . .ኬክ ፣ ለስላሳ ፣ ሻይ. . .ስትመለከት ምራቋ ተፈትልኮ ይወጣል—የልጅ ነገር!. . .በዚህ ሁኔታ ባይኗ ዙሪያዋን ትዞርና እኔ'ጋ ስትደርስ ቆም . . . ፈገግ ትላለች ። ይሆንኑ ይጋገመችው . . . ምናልባት ዓይኔን ስለተከልኩ ባት ይሆን ?. . . ወይም ትልቅ ኩይላ የሚያክለው ሰውነቴ አስገርሟት ይሆናል ።

. . .ዐይነ ሥውር መሆን ከዓለም መራቅ አይደለም። ስንት አለ አይደል! ዐይናማ ግን ልቡ የታወረ ፣ እያየ የማያስተውል ፣ እየሰማ የማይገነዘብ . . . ዐይነ ሥውር ያይኑን ብሌን እማ እንጂ ፣ የመናር ፣ የመፍጠር ፣ የመጠበብ ብሉኑን አላጣም ። ልዩ ሥልጠና ፣ ክብካቤና ማበረታታት . . . ቢያስፈልገው ነው . . .



ይህንን በሕሊናዬ ሳውጠነጥን ዐይኔ ቀዘዘ ። ቡናው ሊቀዘቅዝ ሆነና ቶት አልኩት ። ሲጋራዬን ለመጨረሻ ጊዜ ሳብኩና ተረኮስኩት . . . መልሼ ቡናውን ቶት ፣ ቶት ብዬ ጨለጥኩት ።

ወጣቱ ያዘዘውን ዳቦና ወተት የጨረሰው እያጣጣመ ነበር ። እጁን ወደ ኪሱ ከቶ እንዲት አራት ማዕዘን የሆነች ወረቀት አወጣ። ለልጅቷ'እጅዋን በዳበሳ ፈልጎ ሰጣት። በደንብ ይታየኛል—መለየት አላቃተኝም . . . ፈጣን ሎተሪ ነው ።

ለምን እንደሆ አላውቅም ፤ ብቻ ገረመኝ ።

ምናልባት ባልነቃው ያይምሮዬ ክፍል የተቀበረው የተሳሳተ ዕምነት ብልጭ ብሎብኝ ይሆን?—'ዐይነ ሥውር ባይን ታይቶ የሚያደርገውን ነገር ሊመኝ አይችልም' የሚል ጊዜ የሻረው ግምት!—ራሴን ታዘብኩት ።

ልጅቷ ሞሌ ነገር ነች ፤

«ፈጣን !. . .ፈጣን !» እያለች በጩኸት ፣ አካባቢዋን ታንቀች ። ወዲያው በዐሥር ሳንቲም ሜፍ ትኬቱን መፋቅ ያዘች . . . ትሥቃለች . . ወጣቱ በርጋታ ይጠይቃታል። ትመልሳለች ።

ሌሎች ሰዎች ፣ ከልጅቷ ጩኸት ገልመጥ ፣ ገልመጥ አሉ ።

http://ethioliberty.wordpress.com/

አራት ሆነው በርቀት ያለውን ጠረጴዛ የከበቡት፣ ልጅቷ ላይ ዐይናቸውን ጥለዋል ... ትንሽ ተንጋግረው፣ ወጪ ገቢውን ይመለከታሉ ... ይጨዋወቱና ዝም ሲሉ፣ ጊዜ ለማሳለፍ የተቀመጡ ይመስላሉ ።

ልጅቷ የትኬቱን አንድ መሥመር ስትጨርስ፣

«መሰ ቦርቅ ! . . . መሰቦርቅ ! » አለች ።

‘ ትልቁ አሸናፊ የሚገኘው በመሰቦርቅ መሆን ማወቅ አለባት’—የሚል ሐሳብ መጣብኝ ።

እንደገና «መሰቦርቅ . . .» አለች ።

‘ትሚወታለች !’ እልኩ ባለማመን . . . ሆኖም ልቤ መደንገጡ አልቀረም ።

የቀራትን ፍታ ስትጨርስ፣

«መሰቦርቅ !. . . መሰቦርቅ ! » ብላ፣ ፍቅራቲውን «ኢፍ ! . . . ኢፍ ! » እያለች ጠራረገችው ።

‘ . . . ሦስት መሰቦርቆች ? የማይሆነውን ? እንዴ ያየችውን ስትደጋግም ይሆናል . . . ’ ብዬ ፣ ዐይኔን ወደ በሩ ብወረውር የሠፈር ሽርኬ ይመኑ ውልብ አለኝ . . . ለምን ጉዳይ ነበር ስፈልገው የከረምኩት ? . . ከፋቱ ጉዳዩ ጠፋብኝ ። ደግሞ ብቻዬን ከምሆን ፣ ተከትየው ዞር ዞር ብልስ ? . . . መጀመሪያ ፣ መጣራቱ —ይኸው እዚሁ እደከመኝና ተውኩት ።



« ጋሼ !... ሦስት መሰቦርቆች » ስትለው ለመጣቱ ከሐሳቤ ነቃሁ ። እንደ ልማዱ ዙሪያውን ተመለከከታ እኔ ጋ ስትደርስ . . . ፈገግ—ልጅቷ ።

መጣቱ ደንገጥ ያለ ይመስላል ።

«እስቲ ! . . . እስቲ ! » አላትና ትኬቱን ዳበሰው—መነጽሩን ወደ ግንባሩ እየገፋ ።

« ጋሼ ! . . . በቃ አሸነፍኩ » አለችው ። ቀጥቀ ንቀ አልኩ ። ዘልዬ ነጥቄያት መመልከትም ከጀለኝ ።

ዐይኔ እባበላት መሰለኝ፣ ፍንጥር ብላ ወደኔ መጣች —ልጅቷ ። የሱ-ተረፈውን ትኬት አየሁት ። ሦስት መሰቦርቆች ተዘባርቀው ይገኙበታል ። በጣቴ አሸት ፣ አሸት አረኩት ። ያው ነው ። ዐይኔን ማመን አቃተኝ . . . ከው አልኩ ። ልቤ እየዘለለ ፣ እየዘለለ ሰውነቴን ወዘወዘው ። ትኬቱን ስመልሰላት ፣ እጄ እንዳይንቀጠቀጥ ብጠነቀቅም አልቻልኩም ።

ወደ መጣቱ ተመለሰች ።

«ጋሼ ! . . . በቃ ገንዘብ ታገኛለህ » አለችው ።

«ተይ ዕውነት ተናገሪ ! »አላት ፣ ከፊል መጓጓት ወዲህ ያለማመን ጥርጣሬ ተደባልቀውበት ።

« ዕውነት ! . . . ዕውነት ! ሦስት ነው ፣ ለሰው አሳይቻለሁ »

ከወዲያ አራት ሆነው ከተቀመጡት መካከል ፣ ዝል ዝል ያለ ኮት የለበሰው ቀጭን ሰው ፣

«አንቺ ! አንቺ ልጅ ! . . . ነይ ! እስቲ እምጪው ! » አላት ።

ልጅቷም አላመነታችም ። ዐይን ዐይኑን እያየች ሰጠችው ። ተመለከተው ። ቀጥሎ ለጓደኞቹ አሳየቻቸው ። እንዱ ራሱን ይይዛል ። ሌላው «ኡኡ !» ለማለት የተዘጋጀ ይመስላል . . . በደፈናው አድናቆት ረብሿቸዋል . . .

« ፍሬቴ ! . . . . ፍሬቴ ! » በማለት ዐይኑ ሥጡሩ ሲጣራ ፣ ልጅቷ መለስ ብላ እናገረችው ።

የልጅቷን ስም ያዘከረት ።

ፍሬቴ ፣ ብዙም ሳትቆይ ትኬቷን ከቀጭኑ ሰው ተቀ ብላ ወደ መቀመጫዋ ስትመለስ ፣ እንዓብጣ አየችው ።

« ጋሼ ! . . . መሰቦርቆቼ ሁለት ሆነዋል ። »

« ቅድምስ ፣ መች በደንብ አየኸው ? »

«አይቼው ነበር ፣ አይቼው ነበር ፣ አይቼዋለሁ ! ሦስት ነበር ፣ አሁን ሁለት ብቻ ! . . . »

« ዕውነት ተናገሬ አላልኩሽም ? . . . በይ ተነሽ እን ሒድ ! » —በቁጣ ።

« ዕውነቴን ነው ፣ እብቴ ይሙት ! »



http://ethioliberty.wordpress.com/

« በደንብ አላየኸውማ . . . እንሒድ ! » ብሎ ጠረ ጴዛውን ገፋ ፣ ገፋ አደረገው ።

ፍሬቴ በስጭት ብላ ከንፈሯን ጣለች . . . ዐይኗን ራት ለራት ካለው ግድግዳ ላይ ወርውራ ተተከለች . . .

. . . . . እንዳች ነገር ራሷን መታኝ ። ልቀበለው የማልችል ግጭብርብር ዐይኔ ሥር ሲፈጸም ማየት ፣ ለሕ ሊናዬ እምቢ አለኝ ። ‘በምን ተአምር ትኬቱ ላይ የነበረው ይለወጣል ?’ — ድፍን ያለማያቄ ሆነብኝ ። የሆን ስሜት ከውስጤ ገንፍሎ ይንዘረኝ ጀመር . . .

« ፍሬቴ ነይ ! ዝጨኸቱ አልታወቀኝም ።

ወጣቱ ዐይኑ ሥጡር ከመቀመጫው እየተንቀሳቀሰ በዳበሳ ሲያዛት ሲል ፣ . . . በራ ወደኔ መጣች— ፍሬቴ ።

« ምን ሆንሽ ? » አልኳት ፣ ጉንበስ ብዬ ።

« አንዴ መሰቦርቅ ጠፋች . . . ቅድም አይተኸው አልነበር ? . . . አንዴ የለችም ! » ስትል ፣ ዕንባዋ ዱብ ዱብ ይላል ።

« ሦስት ያለው አይደል የሚያሸንፈው ? . . . አሁን በቃ ! ጋሼ ተሸንፈ ! . . . አይደል ? ሲያሳዝን ! . . . »

ሳግ ይተናነቃታል ።

ቀና ስል ፣ ያ ቀጭን ሰውዬ ጓደኞቹን ለመሰና በት ቆሞ እጁን ሲዘረጋ አየሁት ። ብርክ ያዘኝ ። የደም

ዝውውሬ የተቆጠን ቢመስለኝም ፣ የመደንዘዝ ያህል እንገሬ ተሳሰረብኝ ።

« አይዞሽ ! . . . » ብዬ ፣ ከፍሬቲ የሎተረውን ትኬት ተቀበልኳት ።

«. . . ቅድም ሦስት ሆኖ ባይኔ ያየሁት ፣ አሁን በተዓምር እንዴት ሁለት ሊሆን ይችላል ? . . . »

ምንም ሳላወላውል ወደ ቀጭኑ ሰውዬ አመራሁ ። ለመውጣት አንድ ሁለት ርምጃ እንደ ተራመደ ደረስኩበት ። ተፋጠጥን ።

« የልጅቷ ትኬት ተሰውጦባታል መሰለኝ ? የቅድሙ ያሁኑ የተለያየ ነው ። » ራሴን አረጋግቼ ለጠይቅ ብልም ፣ የፈነዳብኝን ስሜታዊ ግንፍልነት መግታት አልቻልኩም ።

ሳፈጥበት ፣ ሰውዬው ቀስ እያለ ወደ ኋላው ተመለሰ ። ከነበረበት ወንበር ላይ ተቀመጠ ።

« አንተ ምንድነህ ? . . . ተቀብያት ካየሁ በኋላ መልሼላታለሁ ! » አለኝ ። ግንባሩ ላይ ያለው የደም ሥር እንደ ወሃ ቱቦ አብጧል ።

« የወንድሜ ልጅ ነች . . . ይሆን ዐይኑ ሥውር ወደ ቤቱ የምታደርሰው እሷ ነች ። ቅድም ትኬቱን ይዛ ስትጫወት ሳንተም አላይታህ ነበር ። አይቻለሁ ። ሦስት የነበረው መስበርቅ በተአምር ሁለት ሊሆን



http://ethioliberty.wordpress.com/

ይችላል ? » አሬ እንዲመጣልኝ በእልህ ተናገርኩት ።

ሰው ሁሉ ያፈጠጠበት መሰለው ። ጓደኞቼ እል

ተነፈሱም ።

ፍሬቲ ከሰሬ ቆማ ፣ እንጋጣ ታየኛለች . . . በሰ ማያዩ ሽሚዚ ትናፈጣለች ። ዐይኑ ሥውሩ ወጣት ፣

«ፍሬቲ ! . . . ፍሬቲ ! ነይ ነው — የምልሽ ! ነይ እን ሒድ አንች ዘዋሬ ! » አላት በቁጣ ። እኔ ቀጭኑ ሰውዬ ላይ እንዳፈጠጥኩበት ስለሆን ፣ እሱና ጓደኞቼ ዐይኑ ሥውሩ ወጣት የተናገረውን አልሰሙም ።

« የልጅቷ ትኬት ሦስት መስበርቆች እንዳሉት አይቶታል ፣ መጀመሪያ እኔ ነኝ ባይኔ ያየሁት . . . ምና ልባት እዚህ ተሰዋውጦባት ከሆን እንዲመልስላት ነው ! » አልኩት ። ንዴቴ እየጨመረ ሔደ ።

ሰውዬው ኪሱን ደባበሰው ።

« ቆይ እስቲ ! . . . » አለኝ ። ከፍሬቲ የተቀበልኩትን ትኬት ወሰደና አየው ። የኩትና የሰሬ ኪስ ዋን ምንም ሳያስቀር በረበራቸው ። እያረሳሳ ዐይኑን ወደ ጓደኞቼ ይወረውራል — በዘዴ ። « ምን ዝም ትላ ላችሁ ? እርዱኝ እንጂ ! . . . ከጉድ አውጡኝ ! » በሚል ስሜት መሰለኝ ። የጓደኞቼን ሐሳብ ከገጽታቸው ለማየት ዕድል አላገኘሁም ። ዐይኔ መጭጭ ያለው በ"ያው ቀጭን ሰው ላይ ነበር ።

http://ethioliberty.wordpress.com/

« ቆይ እስቲ . . . » ደገመና ፣ ኪሶቹን አራገፈ ። ከወረቀቶች መሐል የፈጣን ሎተሪ ትኬት እንዳየሁ ፣ ከመቅጽበት የመቀማት ያህል ከእጁ መንተፍኩት ።

« ተለውጦ ይሆናል » ሲል ፣ ትኬቱን እየተመለከትኩ ወደ ቤታቹ ተመለስኩ ። ፍሬቴ ተከትላኛለች . . .

መጀመሪያ ያየሁት ነው ።

«ፍሬቴ ይዘሽ ሒጂ! እንዳትጥይው! » አልኳት ።

እየፈነደቀች . . . ከወጣቱ ዐይን ሥውር ጋር ስትወጣ ፣ ያን ቀጭን ሰው በምላሷ ታሾፍበት ነበር . . . ዐይን ሥውሩ ወጣት ወደ ኋላው ገልመጥ ፣ ገልመጥ ሲል . . . እንዳች ነገር የከነከነው መሰለኝ ።

. . . አራቱም ከእኔ ተፋጠው ግማሽ ሰዓት አለ ለፈቀል . . .

http://ethioliberty.wordpress.com/

- አርትኦት
- አትሌቷ
- ዋዜማ
- ወይኔ ልጅት
- ሌሎችም ...

AMH Ber
Berehan Dana
Sabat 199
ihvu 1
03010422508001